በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሃ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድህረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አሰጣጥ ፍተሻ

በላይሁን አለባቸው

ሰኔ 1999

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሃ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድኅረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አሠጣጥ ፍተሻ

በላይሁን እውላቸው

ሰኔ 1999

# በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሃ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድኅረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አሠጣጥ ፍተሻ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም ኤ ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት።

በ

በላይሁን አውላቸው

ሰኔ 1999

# በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10 + 3 መርሀ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድኅረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አሰጣጥ ፍተሻ

በ


በላይሁን አውላቸው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY


## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አቶ ዓለም እሸቱ (ረዳት ፕሮፌሰር) አማካሪ — ፊርማ

የውጭ ፈታኝ — ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ — ፊርማ

# ምሥጋና

መምህሬና አማካሪዬ ረዳት ፕሮፌሰር ዓለም እሸቱ- እነዚያ ግልፅ፣ በሳልና ፈጣን ምግበ መረጃዎችህ ጥናታዊ ዕሁፌን በማቃናትና መልክ በማስያዝ ብቻ የተወሠኑ አይደሉም። ለወደፊቱም በህይወቴ የማልዘነጋቸውና ለመምህርነት ሙያዬ በሞዴልነት የምጠቀምባቸው ናቸው።ሥለሆነም ምሥጋናዬ ከፍተኛ ነው።

የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራንና የቋንቋ ትምህርት ክፍል የ1999 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ተማሪዎች- መረጃዎችን በመስጠት፣ በማሰባሰብና በማስተባበር ያደረጋችሁልኝ ድጋፍ ከፍተኛ ነበርና ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ። የቋንቋ ትምህርት ክፍል 3ኛ ዓመት ምድብ 1 እና 1 የቀድሞ ተማሪዎቼም ያደረጋችሁልኝ ድጋፍና ያሳያችሁኝ ፍቅር የሚረሳ አይሆንም።

የአማራ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ እና የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ-ሙሉ ወጭዬን ሥለሸፈኑልኝና ይህንን ትምህርት እንድከታተል ሥላደረጉኝ አመሠግናለሁ።

ወላጆቼ ቄስ እውላቸው ደመቀ እና ወሮ. ሙሉመቤት መንግሥቴ፣ ልፋታችሁ ብዙ ነው። ትጉታችሁና ፀሎታችሁ ሠምሮ በህይወታችሁ ይህንን ሥኬት አብረን ለማዬት በመቻላችን እንኳን ደሥ ያለን። ታናሽ እህቴ ሠብልዬ ለእኔና ለቤተሰቦቼ ምን ያላደረግሽልን ነገር አለ-መኩሪያዬና አለኝታዬ ነበርሽ፣ ነሽም።

ባለቤቴ ወሮ. ፋናዬ ተሻለ እና ልጆቼ (ብሥሩና ኦርትዬ)- የብርታቴ መሠረቶች ናችሁ። ብቸኝነትንና ናፍቆትን ችላችሁ ለሥኬት በመብቃታችሁ ኮራሁባችሁ። ብርታታችሁን እኔም ተጋርቼ ለውጤት በቅቻለሁና ምኞታችን ሁሉ በመሟላቱ እንኳን ደስ ያለን።

የሥራ ባልደረባዬ ቻላቸው እንዳርጌ- ቅንነትንና ዕውነተኛነትን በአንተ አየሁ። ያደረግህልኝን ሁሉ አልረሣውም። አቶ ጌታቸው ቸርነት፣ አቶ መሀሪ መንግሥቴ፣ አቶ እጅጉ ዓለማየሁ፣ አቶ ንጉሥ ልንገር እና ወት. ሀያት ማሩፍ ባለውለታዎቼ ናችሁ።

ሠብለ ተስማ- ሥራዎቼን ያለመሠልቸት በጥንቃቄ ሥለተየብሽልኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

## ማውጫ

| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|


ምስጋና ....................................................................................i
ማውጫ ....................................................................................ii
የሠንጠረዥ ዝርዝር ....................................................................................V
የአባሪዎች ዝርዝር ....................................................................................Vii
አጠቃሉ ....................................................................................Viii
ምዕራፍ አንድ - መግቢያ ....................................................................................1
1.1 የጥናቱ ዳራ .................................................................................... 1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ....................................................................................5
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................................................6
1.4 የጥናቱ ክልልና ገደብ ....................................................................................6
ምዕራፍ ሁለት - የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ....................................................................................8
2.1 የመምህራን ሥልጠና .................................................................................... 8
2.2 የማስተማር ልምምድ ምንነት ዓላማና ተግባር .................................................................................... 10
2.2.1 የማስተማር ልምምድ ምንነት ....................................................................................10
2.2.2 የማስተማር ልምምድ ዓላማና ተግባር .................................................................................... 11
2.3 የሱፐርቪዥን ምንነት ዓላማና ተግባር ....................................................................................14
2.3.1 የሱፐርቪዥን ምንነት ....................................................................................14
2.3.2 የሱፐርቪዥን ዓላማና ተግባር ....................................................................................16
2.4 የሱፐርቪዥን ዓይነት (አቀራረብ) ....................................................................................17
2.4.1 መራሔ (ትዕዛዛዊ) ሱፐርቪዥን ....................................................................................17
2.4.2 ኢ-መራሔ ሱፐርቪዥን ....................................................................................17
2.4.3 ትብብራዊ ሱፐርቪዥን ....................................................................................18
2.4.4 እማራጫዊ ሱፐርቪዥን ....................................................................................18
2.4.5 ራስመር ሱፐርቪዥን ....................................................................................18
2.4.6 ባልደረባዊ ሱፐርቪዥን ....................................................................................18
2.4.7 በምርምር ላይ የተመሠረተ ሱፐርቪዥን .................................................................................... 19
2.4.8 መደበኛ ያልሆነ ሱፐርቪዥን ....................................................................................19
2.4.9 ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን ....................................................................................19

2.4.9 ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን ........ 19
2.5 የሱፐርቪዥን መርሆዎች ........ 21
2.5.1 አመለካከታዊ ........ 21
2.5.2 ፈጣሪነት ያለው ........ 21
2.5.3 ትብብራዊ ........ 21
2.5.4 ንድፈ ሀሳባዊ ጥልቀት ........ 21
2.5.5 ሳይንሳዊነት ........ 21
2.5.6 ሚዛናዊነት ........ 22
2.6 ሱፐርቫይዘራዊ ክህሎቶች ........ 22
2.6.1 የማስተዋል ክህሎት ........ 22
2.6.2 ቴክኒካዊ ክህሎት ........ 22
2.6.3 የመግባባት ክህሎት ........ 23
2.7 ሱፐርቪዥንና ምልከታ ........ 23
2.8 ሱፐርቪዥንና ምግበ መረጃ ........ 25
2.8.1 የምግበ መረጃ ምንነት ........ 25
2.8.2 የምግበ መረጃ ፋይዳ ........ 26
2.8.3 የምግበ መረጃ አቀራረብ ........ 28
2.9 የመምህራን ሥልጠናን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ተለውጦች ... 30
2.9.1 የዕጩ መምህራን ምልመላና መረጣ ........ 30
2.9.2 ሥርዓተ ትምህርት ........ 31
2.9.3 የአሠልጣኞች ብቃት ........ 31
2.9.4 ምቹ ሁኔታ እና አገልግሎት ........ 32
2.10 የቀደምት ሥራዎች ቅኝት ........ 34
**ምዕራፍ ሦስት - የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ...... 38**
3.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች ........ 38
3.2 የመረጃ አሠባሠብ ዘዴ ........ 39
3.2.1 የዕጩ መምህራን ማስታዎሻ ........ 39
3.2.2 መቅረፀ ድምጽ ........ 39
3.2.3 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 40
3.2.4 የግምገማ ቅፅ ........ 40
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 41

ምዕራፍ አራት - የመረጃዎች ትንተና ....................43
4.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች ዳራ .................... 43
4.1.1 ዕጩ መምህራን ....................43
4.1.2 ሱፐርቫይዘሮች .................... 43
4.2 የማስተማር ልምምድ ተግባር ....................46
4.3 የሱፐርቪዥን ሂደትና ትግበራ ....................47
4.3.1 ቅድመ ማስተማር ልምምድ ....................47
4.3.2 የሱፐርቪዥን ትግበራ ....................50
4.3.3 የምግበ መረጃ መስተጋብር ....................58
4.3.4 የምግበ መረጃ መስተጋብሩ ትኩረት ....................69
4.4 የጥናቱ ተተኳሪዎች ምግበ መረጃ፣ ሱፐርቪዥንና የማስተማር
ልምምድን በተመለከተ ያላቸው አስተያየት ....................75
4.4.1 የዕጩ መምህራን አስተያየት .................... 76
4.4.1 ዕጩ መምህራን ሥለ ምግበ መረጃው ፋይዳ ያላቸው አስተያየት ...76
4.4.1.2 ዕጩ መምህራን ሥለ ሱፐርቫይዘሮቻቸው ያላቸው ግምትና
አስተያየት ....................77
4.4.1.3 ዕጩ መምህራን ሥለ ሥርዓተ ትምህርቱ ያላቸው አስተያየት ...78
4.4.2 የሱፐርቫይዘሮች አስተያየት .................... 80
4.4.2.1 የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አፈፃፀም
መመሪያንና ዕጩ መምህራን የተመደቡባቸውን
የአጋር ት/ቤቶች በተመለከተ ....................80
4.4.2.2 ሱፐርቫይዘሮች ሥራ ት/ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምዱ
ያላቸው ግምትና አስተያየት ....................81
4.4.2.3 ሱፐርቫይዘሮች ሱፐርቪዥንና ምግበ መረጃው
ስላሥገኘው ፋይዳ ያላቸው አስተያየት ....................83
ምዕራፍ አምስት - ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ ....................85
5.1 ማጠቃለያ ....................85
5.2 የመፍትሔ ሀሣብ ....................89
ሙዳዬ ቃላት ....................91
ዋቢ ጽሁፎች ....................92
አባሪዎች ....................99

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡- የተተኳሪ ዕጩ መምህራን ዳራ ..... 43
ሠንጠረዥ 2፡- የተተኳሪ ሱፐርቫይዘሮች ዳራዊ መግለጫ ..... 44
ሠንጠረዥ 3፡ ሱፐርቫይዘሮች ሥለ ዘመናዊ ቋንቋን የማስተማር ሥነዘዴ ያላቸው ግንዛቤ ..... 45
ሠንጠረዥ 4፡- የሱፐርቫይዘሮች የሥልጠና ፍላጎት ..... 46
ሠንጠረዥ 5፡- ዕጩ መምህራኑ ሥለማስተማር ልምምዱ ያላቸው ግንዛቤ ..... 46
ሠንጠረዥ 6፡- ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይትና የሱፐርቪዥን ዕቅድ ..... 48
ሠንጠረዥ 7፡- ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት ክንውን ..... 48
ሠንጠረዥ 8፡- የሱፐርቪዥን አተገባበር አቅጣጫ ..... 50
ሠንጠረዥ 9፡- ዕጩ መምህራኑ በመሥኩ የሠለጠነ ሱፐርቫይዘር ማግኘት ሥለመቻላቸው ..... 51
ሠንጠረዥ 10፡- የሱፐርቫይዘሮች ክትትል ..... 54
ሠንጠረዥ 11፡- ሱፐርባይዘሮች ሙሉ የክፍል ውስጥ ምልከታ ስለማካሄዳቸው ..... 55
ሠንጠረዥ 12፡- ሱፐርባይዘሮች ሙሉ የክፍል ውስጥ ምልከታ ስለማካሄዳቸው ..... 55
ሠንጠረዥ 13፡- የአጋር ትቤት ነባር መምህራን ዕገዛ ..... 57
ሠንጠረዥ 14፡- ነባር መምህራን ስለሚያደርጉት ክትትልና ዕገዛ ..... 57
ሠንጠረዥ 15፡- የኮሌጁ አሠልጣኝ መምህራንና የአጋር ትምህርት ቤቶች ነባር መምህራን ስለመመካከራቸው ..... 58
ሠንጠረዥ 16፡- የውይይቱ መንፈስ ምን ይመሥል እንደነበር ..... 59
ሠንጠረዥ 17፡- የውይይቱ መንፈስ በዕጩ መምህራኑ ሲታይ ..... 59
ሠንጠረዥ 18፡- የሱፐርቫይዘሮች የቋንቋ አጠቃቀም ..... 60
ሠንጠረዥ 19፡- ምግበ መረጃው በምልከታ ውጤቶች ላይ ስለመመሥረቱ ሱፐርቫይዘሮች የሠጡት ምላሽ ..... 61
ሠንጠረዥ 20፡- ምግበ መረጃው በምልከታ ውጤቶች ላይ የመመሥረቱ ሁኔታ ..... 62
ሠንጠረዥ 21፡- ምግበ መረጃው ቋንቋን ከማስተማር ሥነ ዘዴ ጋር ያለው ተጣጥሞ ..... 63
ሠንጠረዥ 22፡- ዕጩ መምህራኑ በምግበ መረጃ መሥተጋብር ያላቸው ሚና ..... 65

ሠንጠረዥ23፡- ውይይቱና የስትርቫይዘሮች ዳኝነት ..............................66
ሠንጠረዥ24፡- ስትርቫይዘሮች በምገበ መረጃ መስተጋብሩ ያላቸው ሚና .........67
ሠንጠረዥ25፡- የምገበ መረጃው ትኩረት..............................................70
ሠንጠረዥ26፡- ለድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሰጠው ጊዜ ...............74
ሠንጠረዥ27፡- የምገበ መረጃው ፋይዳ በዕጩ መምህራኑ አተያይ ...................76
ሠንጠረዥ28፡- ዕጩ መምህራኑ ስለስትርቫይዘሮቻቸው ያላቸው ግምት ...........77
ሠንጠረዥ29፡- ዕጩ መምህራኑ ስትርቫይዘሮቻቸው ለእነሱ ድጋፍ ሰጭና
አበረታች ስለመሆናቸው ያላቸው እስተያየት ..........................77
ሠንጠረዥ30፡- ዕጩ መምህራኑ ስትርቫይዘራቸው ስለ እነሱ
ያለውን አመለካከት በተመለከተ ያላቸው ግምት .....................78
ሠንጠረዥ31፡- ዕጩ መምህራኑ ስለሥርዓተ ትምህርቱ ያላቸው አስተያየት .......79
ሠንጠረዥ32፡- ስትርቫይዘሮች የት/ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ
መመሪያ ግልጽና ተተግባሪ ስለመሆኑ ያላቸው አስተያየት..........81
ሠንጠረዥ33፡- የማስተማር ልምምድንና ስትርቪዥንን ተተግባራዊ ለማድረግ
ምቹ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው.................................................81

# የአባሪዎች ዝርዝር


| የአባሪ ቁጥር | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| አንድ | የማስታዎሻ አያያዝ መመሪያ | 99 |
| ሁለት | የዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻ ናሙናዊ ጥንቅር | 101 |
| ሦስት | የሱፐርቫይዘሮች እና የዕጩ መምህራን ድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ቅጅ ናሙና ጥንቅር | 112 |
| አራት | የሱፐርቫይዘሮች መጠይቅ | 131 |
| አምስት | የዕጩ መምህራን መጠይቅ | 134 |
| ስድስት | የኮሌጅ የመገምገሚያ ቅጽ | 137 |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በ1999 ዓ.ም. ሁለተኛው ወሠን ትምህርት በተካሄደው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ላይ የተመሠረተ ነው። የጥናቱ አቢይ ዓላማም በድኅረ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምምድ ዕጩ መምህራኑ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ያካሄዱትን የምግበ መረጃ መስተጋብር መፈተሽ ነው።

ለጥናቱ የሚያሥፈልጉ መረጃዎች በመቅረፀ ድምፅ፣ በዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻዎች፣ በፅሁፍ መጠይቅና ኮሌጁ ለግምገማ በሚጠቀምበት ቅፅ አማካይነት ተሰብስበዋል። የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉትም በአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ልምምድ ያካሄዱት የኮሌጁ የ10+3 መርሃ ግብር ዕጩ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮቻቸው ናቸው።

የመረጃዎቹ ትንተና በኮሌጁ ያለው የሱፐርቪዥን አተገባበርና የምግበ መረጃ አሠጣጥ የተለያዩ ችግሮች ያሉበት መሆኑን ያሣያል። ሱፐርቫይዘሮቹ ሥለ ሱፐርቪዥን አተገባበርና ምግበ መረጃ አሠጣጥ ሥልጠና ያልወሠዱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ባልሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት የዕጩ መምህራኑን የማስተማር ልምምድ ይከታተላሉ (ይገመግማሉ)፣ ምግበ መረጃም ይሠጣሉ። በምግበ መረጃ መስተጋብሩ ሱፐርቫይዘሮች የሚጠቀሙት መራሔ ሱፐርቪዥን (አቀራረብ) በመሆኑ ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን ተግባር ራሳቸው ፈትሸው አማራጮችን ከመጠቀም ይልቅ ተሳትፎአቸው መመሪያና ምክር በማዳመጥና በመቀበል ላይ እንዲያተኩር ሆኗል። ከዚህም በተጨማሪ ሱፐርቪዥኑ ለግምገማና ምዘና የቅድሚያ ትኩረት በመስጠቱ በምግበ መረጃ መስተጋብሩ ወቅት እጩ መምህራኑ ውጥረትና ጭንቀት እንዲሠማቸው የሚያደርግ ዋነኛ የሥጋት ምንጭ ሊሆን ችሏል።

በሠፊው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ውስጥ ለሱፐርቪዥኑ የተሠጠው ጊዜ አጭር ከመሆኑም በተጨማሪ አንድ ሱፐርቫይዘር ለበርካታ እጩ መምህራን አጋዥነት (ገምጋሚነት) በመመደቡ የሱፐርቪዥኑን ሥራ የይድረስ ይድረስ እንደሆነና ምግበ መረጃውም ባግባቡ እንዳይሰጥ እንቅፋት ፈጥሮአል።

ዕጩ መምህራኑ ተከታታይነት ያለው ሱፐርቪዥን ባለማግኘታቸውና ከአጋር ትምህርት ቤቶች መምህራን የሚደረግላቸው እገዛም አናሳ በመሆኑ በምግበ መረጃ ተጠቃሚ መሆን እንዳልቻሉ ጥናቱ ያሳያል። በመጨረሻም የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ የተለያዩ የመፍትሔ ሃሳቦችን ለመጠቆም ተሞክሮአል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የትምህርት ተቋማት እንደሌሎቹ ማህበራዊ ተቋማት ሁሉ ሊያሳኩት የሚፈልጉት ግብ አላቸው:: Saiydain (1985) እንዳሉት የሥልጠና መሠረታዊ ዓላማ ሰውን ከሚጠበቅበት የሥራ መሥክ ጋር ማዛመድ ነው፡ ዓላማውን ግብ መቺ በማድረግ በኩል ቁልፉን ሚና የሚጫወቱት ደግሞ መምህራን ናቸው::

ትምህርትን በሥፋትና በጥራት ለማዳረሥ መምህራንን በበቂ ሁኔታና በጥራት የማፍራቱ አሥፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም:: የሠለጠኑና ብቃቱ ያላቸው መምህራን በሌሉበት ዕድገት /ለውጥ/ የሚያመጣ የትምህርት ሥርዓት የለም:: Alebachew (1996:42) እንደገለፁት "ብቃት ያላቸው መምህራን ያሏት ሀገር ብሩህ መፃኢ ህይወት ያላት ናት::" ሆኖም በመስኩ የተካሄዱ ጥናቶች እደሚያመላክቱት በመምህራን ሥልጠና ላይ የንድፈ ሀሳብ እና የተግባር አለመዋሀድ፣ ከዕውናዊው የመማር ማሥተማር ሂደት ጋር አለመጣጣም (ሥልጠናው ሌላ በዕውን የሚገጥመው ሌላ)፣ በጥቅሉም የትምህርትን ዓላማ ለማሳካት ብቃት ያላቸውን መምህራን ማፍራት አለመቻል ጎልቶ ይሥተዋልበታል (Smith 1970, Goldhammer 1980, Searason et al 1986, Leavit 1991, MOE 2002, ተክለሃይማኖት 1992፣ ሥንታየሁ 1995)::

የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ተሞክሮ እንደሚያመላክተው የመምህራን ትምህርት ሥልጠና ከመንግሥት ሥርዓት ጋር ቁርኙ ነው:: ሥርዓቱና አሥተዳደሩ ሲቀየር የአሠለጣጠን ዘዴውም ይቀየራል (Tirusew 2006):: በመሆኑም የመጀመሪያው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም በ1937 ዓ.ም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የሥልጠናው መርሀ ግብርም ሆነ የአሠለጣጠን ዘዴው በተለያየ መንገድ ሲተገበር ቆይቷል (Teshome 1979):: በሂደቱ ላይም ከፍ ሲል የተጠቀሱት ችግሮች ሲንፀባረቁበት ቆይቷል፤ አሁንም ከዚህ ችግር ገና አልተላቀቅንም (ዓለማየሁ 1997፣ ትምህርት ሚኒስቴር 1996፣ ሥንታየሁ 1995):: ሥልጠናው በንድፈ ሀሳብ ላይ ማተኮሩና ሥነዘዴው መምህር መር መሆን ከሚጠቀሡት በርካታ ችግሮች ውሥጥ አበይቶቹ ናቸው (ዓለም 1988፣ ተክለሃይማኖት 1992፣ ዓለማየሁ 1997)::

የትምህርቱ ዓላማ ወደ ተግባር ተለውጦ በተማሪዎች ላይ እንዲታይ የተፈለገው የመማር ማስተማር ውጤት እውን እንዲሆን በማድረግ በኩል ዋነኞቹ ተዋንያን መምህራን በመሆናቸው በሀገሪቱ የትምህርት ፍልሥፍና መሠረት የተቀረፀውን ግብ ከማሳካት አንፃር የላቀውን ድርሻ ይወስዳሉ::

የመምህራን ትምህርት ተቋማት አቢይ ተልዕኮም በዕውቀታቸው፣ በክህሎታቸውና በአመለካከታቸው የዳበሩ፣ በሥነ ምግባር የታነፁ ሁለንተናዊ ስብዕናቸው የተሟላ ሀገር ተረካቢና ገንቢ ዜጎችን ማዘጋጀት የሚችሉና ለደረጃው ብቁ የሆኑ መምህራንን ማፍራት ነው (ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ 1997)::

በአሁኑ ጊዜ በርካታ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በመንግሥትና በግል ተከፍተው ብዛት ያላቸው መምህራንን እያሰለጠኑ በማውጣት ላይ እንዳሉ ይታወቃል:: ተጨባጩ ዕውነት በመምህራን ቁጥር ረገድ ብዙ እንደተራመድን ቢያመላክትም የጥራቱ ጉዳይ ግን በየጊዜው እሮሮ እየተነሳበት ያለ አጅግ አሳሳቢ ችግር ሆኗል:: ዓለማየሁ (1997) እንደገለፁት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሀገርንና የአካባቢን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት አድርገው ያሥቀመጡት ርዕይና ተልዕኮ ዕውን የሚሆነው በተቋማቱ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መምህራንን በገፍ በማፍራቱ ብቻ ሣይሆን፣ የመምህራንን ትምህርት በተመለከተ ኮሌጆቹ የሚከተሉት የመማር ማስተማር ፍልሥፍና ንድፈ ሃሳብንና ተግባርን አዋህዶ ሲገኝ ነው::

ዛሬ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ቁዛምዶ የሥልጠናን ግብ ለማሳካት እንደሚያስችል ከታወቀበትና ብዙ ሀገሮችም የመምህራን ትምህርት ሥርዓታቸውን ያሻሻሉበት ወቅት ላይ እንገኛለን:: "ዕውቀትንና ተግባርን ነጣጥሎ ማየት ሥለማይቻል በመምህራን አሠለጣጠንም ይህ ዓይነቱ አመለካከት ከሌለ ተልዕኮን ማሳካት አይቻልም" (ተክለሃይማኖት 1992 "የሴንግትስን 1995"ን ሥራ በመጥቀስ ያቀረቡት):: በዚህ መሠረት ብቁ መምህራንን በማፍራት በኩል ከንድፈ ሀሳብ ጋር የተቀናጀ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማሥተማር ልምምድ ሚና አጅግ የጎላ መሆኑን በመገንዘብ በሀገራችን የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ ተካትቶ ይገኛል:: ሆኖም ጥናቶች እንደሚያመላክቱት "በሀገራችን የማስተማር ልምምድን በተመለከተ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውና ዛሬም እየተሠራበት ያለው አመለካከት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና አፈፃፀም ኋላቀርና ጥራት የለሽ ነው:: ብቃት ያላቸውን መምህራን ለመፍጠር ያደረገው አሥተዋጽኦም ዝቅተኛ መሆኑ አይካድም" (ዓለማየሁ 1977፣ ተሰጠ 1997፣ ሂሩት 1998፣ መሃመድ 1999)::

Perrot (1982) እንደገለፁት ማስተማር፣ ተፈላጊውን የትምህርት ግብ ማሳካት የሚችለው የትምህርትና ሥልጠና መገለጫ የሆኑት የንድፈ ሀሳብ ትምህርት፣ የተግባር ልምምድ፣ እንዲሁም ከልምምድ በኋላ በስፐርቫይዘሮች የሚሰጥ ምግበ መረጃ ተገቢ ትኩረት አግኝተው ሲተገበሩ ነው::

የዚህ ጥናት አቢይ ትኩረትም በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሱፐርቫይዘሮች የሚሠጧቸው ምግበ መረጃዎች የዕጩ መምህራኑን የመማር ፍላጎት

የሚቀሠቅሡ፣ ለበለጠ እና ለተሻለ ሥራና ውጤት የሚያዘጋጁ መሆናቸውን መፈተሽ ነው።

በአማራ ክልል የ10+1 (ሠርቲፊኬት) መርሃ ግብር የሀገር አቀፉን የሥልጠና አቅጣጫ የተከተለ ቢሆንም የ10+3 (ዲፕሎማ) መርሃ ግብሩ ግን ለየት ባለ መልኩ ገባ-ወጣ-ገባ (In-Out-In) የተሠኘውን ሥልት የተከተለ ነው (ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ 1997፣1)።

በዚህ መሠረት የ10+3 መርሃ ግብር እንደሌሎች ክልል ኮሌጆች በሦስት ዓመት ውስጥ የሚጠቃለል ቢሆንም አተገባበሩ ግን በተለየ መልኩ እንደሚከተለው ነው።

ሀ. በመጀመሪያው ዓመት ዕጩ መምህራኑ በኮሌጅ ሆነው ንድፈ ሀሳባዊ ትምህርት በመቅሠም የሚሠለጥኑበት፣

ለ. ሁለተኛው ዓመት ኮሌጁን ለቀው በተለያዩ ወረዳዎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በመመደብ የፕራክቲከም ተግባራትን የሚያካሂዱበት፣

ሐ. ሦስተኛው ዓመት ደግሞ ዕጩ መምህራኑ ወደ ኮሌጅ ተመልሰው ከት/ቤት ያገኙትን ተሞክሮ ከንድፈ ሀሳባዊ ትምህርት ጋር በማቀናጀት የሚሠለጥኑበት ሆኖ በመተግበር ላይ ይገኛል።

የ10+3 መርሃ ግብር የኮርስ አደረጃጀትም በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን መሠረት አድርጎ እንደ አዲስ የተዋቀረ ነው። በዚህ ኮርስ አደረጃጀት ላይ የተደረጉ ለውጦች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. የይዘት ሽግሽግ ተደርጓል።

ለ. ዕጩ መምህራኑ ከኮሌጅ ውጭ ሲሄዱ በርቀት (Distance) የሚሠጡ ኮርሶች ይዘት ተመርጠዋል።

ሐ. የፕራክቲከም ኮርሦች ለብቻ ተደራጅተዋል።

የፕራክቲከም ኮርሦች በብዙ ክልሎች እንደሚደረገው በአራት የተከፈሉና በየጎመቱ የሚሠጡ ሣይሆኑ እየተጣመሩ በሁለተኛው ዓመት በሚገኙ ሁለት ወሰነ ትምህርቶች ውሥጥ የተጠቃለሉ ናቸው። በዚህም መሠረት በፕራክቲከም I እና II የሚከናወኑ ተግባራትን በአንድ ላይ በማጠቃለል "Prac 201" በሚል ስያሜ የትምህርት ክብደቱ (Credit hours) 6(ስድስት) እንዲሆን ተደርጓል። በፕራክቲከም III እና IV

የሚከናወኑ ተግባራት ደግሞ በአንድ ላይ ተጠቃለው "Prac 202" በሚል ስያሜ የትምህርት ክብደቱ 12 (አሥራ ሁለት) እንዲሆን ተደርጓል።

በዚህ አደረጃጀት መሠረትም፡-

1. የፕራክቲከም "Prac 201" ከመስከረም እስከ ጥር ያለውን የ5 ወር ወቅት (የ1ኛውን መሀን ትምህርት ወቅት) የሚሸፍን ትምህርት (Course) ሲሆን፣ ከመስከረም እስከ ጥቅምት ወር መገባደጃ ያለው ጊዜ የትምህርት ቤት አጠቃላይ ምልከታ እና ለአጋር ት/ቤቶች መምህራን አጋዥ በመሆን የትምህርት ዕቅድና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት መለማመጃ ወቅት ይሆናል።
2. ከኅዳር እስከ ጥር መጨረሻ ያለው ጊዜ ደግሞ በነባር መምህራን ተመልካችነት የማሥተማር ሥራን ያከናውናሉ፤ በተጨማሪም አንድ የጥናት ርዕስ በመምረጥ የጥናት መሪ ጽሁፍ (Project Proposal) አዘጋጅተው በመጀመሪያው የቱቶሪያል መሥጫ ወቅት ለኮሌጅ አሠልጣኝ መምህሮቻቸው ያቀርባሉ።
3. የፕራክቲከም II (Prac 202) ደግሞ ከየካቲት እስከ ሰኔ ወር ድረስ ያለውን የሁለተኛውን ወሰነ ትምህርት ወቅት የሚሸፍን ኮርስ ሲሆን፣ ዕጩ መምህራኑ የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ ይጠበቃል፤
   - 3.1 በPrac 201 የጀመሩትን የክፍል ውስጥ ማሥተማር በተጠናከረ መልኩ ይቀጥላሉ።
   - 3.2 አሥፈላጊ ሲሆን የነባር መምህራንን ዕገዛ እያገኙ ያዘጋጁትን ጥናታዊ ፅሁፍ ለኮሌጅ አሰልጣኝ መምህሮቻቸው ያቀርባሉ።
   - 3.3 በቆይታቸው ያዘጋጁትን ዝግበ ጥናት (Portfolio) የኮሌጁ መምህራን በተገኙበት ዕብረታ (Reflection) ያካሂዳሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ኮርሦች ይህ ጥናት በተለይ Prac 202 በተሠኘው ኮርስ ላይ በማትኰር በዚህ ኮርስ ውሥጥ በተለይ በስፐርቪዥንኑ አተገባበር የምግበ መረጃ አሰጣጡን ተገቢነት ከተለያዩ ጎድፈ ሃሳባዊ ቅኝቶች አንፃር ለመፈተሽ ይሞክራል።

የዚህ ጥናት አዘጋጅ ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮለጅ መምህራን አንዱ በመሆኑ በሥልጠናው መርሃ ግብር ላይ በመሣተፍ ሂደቱን በቅርበት ለማዬት ችሏል። በሥራው ሂደት ከታዘባቸውና ትኩረቱን ከሳቡት ጉዳዮች አንዱ በመምህራን ሥልጠና ሂደት ቁልፍ ሚና የሚጫወተው ስፐርቪዥንን በዓላማው መሠረት የዕጩ

መምህራኑን ሙያዊ ብቃት የተመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብና ገንቢ ምግበ መረጃዎችን በመስጠት እየተተገበረ ይሆን? የሚለው ነው ። በተለይም በኮሌጁ የተለያዩ ርዕሠ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚካሄዱ ሰሚናሮች እና ወርክሾፖች ላይ ከአሠልጣኝ መምህራን የሚጠበቀውን የሱፐርቪዥንን አተገባበርና የምግበ መረጃ አሠጣጥ የሚመለከቱ ጉዳዮች አለመኖራቸውን በመታዘቡ ለምን ይሆን? የሚል ጥያቄ ሊያጭርበት ችሏል። በመሆኑም በኮሌጁ ምግበ መረጃ ትኩረት አግኝቶ ባግባቡ ይተገበራል? ሱፐርቫይዘሮች የሚሠጧቸው ምግበ መረጃዎች ዕጩ መምህራኑን ለተሻለ ሥራና ውጤት የሚያነሳሱ ናቸው? በምግበ መረጃ መሥተጋብሩ ይበልጥ የሚተኮርባቸው ጉዳዮች ምን ምን ይሆኑ? ዕጩ መምህራኑ ሥለ ምግበ መረጃው መስተጋብር ያላቸው አስተያየት ምን ይመስላል? የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለሥ ያደረበት ጉጉት ይህንን ጥናት ለማካሄድ አነሳስቶታል።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማሥተማር ልምምድ መርሀ ግብር ትግበራ ወቅት ዕጩ መምህራኑ በተለይ በቋንቋ ድጎሬ የማሥተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር የሚኖራቸውን መሥተጋብር መፈተሽ አቢይ ዓላማው ያደረገ ነው። በመሆኑም በሱፐርቫይዘሮቹ የሚሰጡ ምግበ መረጃዎች ለእጩ መምህራኑ የሥልጠና ንሸ ከመፍጠር አንፃር ያላቸውን እገዛ በጥናንት ይመረምራል። ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

1.2.1 ምግበ መረጃዎቹ በምልከታ በተደረሰበት ነገር ላይ የተመሰረቱ መሆን አለመሆናቸውን መለየት፤

1.2.2 በምግበ መረጃ አቀራረብ ሂደት ውስጥ የሚታየውን የሱፐርቫይዘሮች የቋንቋ አጠቃቀም መመርመር፤

1.2.3 በሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራኑ የሚካሄደውን የምግበ መረጃ መስተጋብር ሚዛናዊነት መመርመር፤

1.2.4 የሱፐርቫይዘሮቹ ምግበ መረጃ በተለይ የሚያተኩርበትን ጉዳይና የሚቀርብበትና ስልት ለይቶ መጠቆም፤

1.2.5 ዕጩ መምህራኑ ስለ ምግበ መረጃው ያላቸውን አስተያየት መፈተሽ፤

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት አበይት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፣

1.3.1 በኮሌጁ ያሉ ሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን በድኅረ የማስተማር ልምምድ ወቅት የሚያካሂዱት የምግበ መረጃ መሥተጋብር በምን በምን ላይ ማተኮርና እንዴትስ መቅረብ እንዳለበት ጠቋሚ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

1.3.2 በምግበ መረጃ መስተጋብሩ ጊዜ የሱፐርቫይዘሮች የቋንቋ አጠቃቀም በዕጩ መምህራኑ ዘንድ ማስተማርን የመማር ንሸ ከመፍጠር አንፃር ምን መልክ እንደነበረው መረጃ ይሠጣል፣ ምን መምሠል እንዳለበትም ያመላክታል፡፡

1.3.3 በሱፐርቪዥን አተገባበር ሂደት ባለው የምግበ መረጃ መስተጋብር የሱፐርቫይዘሮችና የዕጩ መምህራን ሚና ምን ምን መሆን እንዳለበት ያመላክታል፡፡

1.3.4 ዕጩ መምህራኑ በሱፐርቫይዘሮች ከሚሠጣቸው ሙያዊ እገዛ በተጨማሪ ራሳቸውን በራሳቸው የሚገመግሙበትንና ብቃታቸውን የሚያጎለብቱበትን ሥልት ይጠቁማል፡፡

1.3.5 በኮሌጁ የሚከናወነውን የሱፐርቪዥን አተገባበርና የምግበ መረጃ መሥተጋብር በተመለከተ ተጨባጭ መረጃ በማቅረብ የሚጠናከርበትንና የሚሻሻልበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡

1.3.6 ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ለሚኖራቸው ቀጣይ ጥናቶች የመነሻ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ክልል እና ገደብ

ይህ ጥናት የተመሠረተው በአማራ ብሔራዊ ክልል ከሚገኙ አራት የመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች መካከል አንዱ በሆነው በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በ1999 ዓ.ም. ሁለተኛ ወሠን ትምህርት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ላይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የዚህን መርሀ ግብር አጠቃላይ ዕንቅስቃሴ የሚያካትት አይደለም፡፡ ጥናቱ እግረ መንገዱን የሚዳስሳቸው ተያያዥነት ያላቸው የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማሥተማር ልምምድ ጉዳዮች ቢኖሩትም በተለይ በሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን በድኅረ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር የሚካሄደው የምግበ መረጃ ልውውጥ የሚያተኩርበትን ጉዳይና የሚቀርብበትን ሥልት በመፈተሽ ላይ የሚያነጣጥር ነው፡፡

ጥናቱ በትምህርት ክፍሉ የሚገኙ የ10+3 (ዲፕሎማ) መርሃ ግብር ሁለተኛ ዓመት ተማሪዎችን በዋናነት ሲያጠቃልል፣ የሱፐርቪዥኑን አገልግሎት የሚሰጡ የኮሌጁ መምህራንን የመረጃ ምንጩ አካል አድርጎ ያሳትፋል::

ይህ ጥናት በተለይ ትቤተማል II (Prac 202) በተሰኘው ኮርስ ላይ የሚያተኩር ሲሆን የዚህን ኮርስ ዓላማና ይዘት በመመርመር ወደተተኳሪው ጥናት ያመራል እንጂ በሌሎቹ ኮርሶች ይዘት ላይ ትኩረት አያደርግም::

UNIVERSITY LIBRARY

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

## 2.1 የመምህራን ሥልጠና

ሥልጠና፣ ግለሰቦች ተቋማዊውን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ተገቢ ዕውቀት እና ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያዘጋጅ ሥርዓታዊ ዘዴ ነው (Armstrong 1991:90):: ማሠልጠን ማለትም ግለሰብ ወይም ግለሰቦች አንድን ዕውቀትና ችሎታ ለመተግበር እንዲችል /እንዲችሉ/ መምራት ማለት ነው (Smith 1970:71):: ዓለም (1988፣12) የኒቲልን (1988) ሥራ በመጥቀስ እንደገለፁት የመምህራን ሥልጠና ደግሞ የሚያተኩረው ዕጩ መምህራን ማሥተማርን እንዲማሩ በሙያውም እንዲካኑ በማድረግ ላይ ነው::

የመምህራን ትምህርት የትኩረት ገፅታዎች የንድፈ ሀሳብ ትምህርትና የተግባር ትምህርት ተብለው ሊፈረጁ ይችላሉ:: እነዚህ የመምህራን ትምህርት ገጽታዎች እንደሚገኛውም ተግባር ሁሉ መሰረት የሚያደርጉት የስነ ዕውቀት ፍልስፍና አላቸው:: ፍልሥፍናውም Calderhead J (1987) እንደገለፁት በማስተማር ምንነትና በመምህር ተማሪ መስተጋብር፣ እንዲሁም በንድፈ ሃሳብና ተግባር ግንኙነት በሚኖረው አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነው::

አበይቶቹ የፍልሥፍና ዓይነቶች የአምንታዊያን አመለካከት (Positivism) እና የተግባራዊያን አመለካከት (Constructivism) ናቸው (Wallace 1991, Eruat, 1994)::

በአምንታዊያን አመለካከት በሚያስተምረው ትምህርት ላይ ዕውቀቱ ያለው ሰው ሁሉ ማስተማርን ይችላል:: አምንታዊያኑ ተፈጥሮአዊ ዕውቀት፣ ችሎታና ሌሎች ዳራዊ ባህርያት ከሥልጠና የበለጠ የማሥተማር ብቃትን ያቀዳጃሉ ብለው ያምናሉ (Wallace 1991):: በመሆኑም በዚህ ፍልሥፍና መሠረት የመምህራን ሥልጠና መርሃ ግብር መምህራኑ ወደፊት ያሥተምሩታል ተብሎ በሚጠበቀው የትምህርት ዓይነት በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማሥቻልን ዓላማው ሊያደርግ ይገባል:: በአምንታዊያኑ አመለካከት የመምህራን ትምህርት የተጠራቀመ /የተካበቱ/ ዕውቀቶችን /መረጃዎችን/ በማሥተላለፍና ያለ ንቁ ተሳትፎ በመቀበል ላይ የተመሠረተ የመማር ማስተማር አቀራረብ ያስፈልገዋል (Freire 1993):: የማስተማር ልምድም ከማሠልጠኛ ተቋማት የተካበቱ ዕውቀቶችን በማሥተላለፍ ላይ ይመሠረታል:: ኮርሶቹ በይዘት የታጨቁ ልምምዱም በመስጠትና በመቀበል እንዲከናወን ይፈለጋል (Livingstone 2001)::

ይህ አይነቱ የሥነ ዕውቀት ፍልስፍና ማስተማርን መማር ተራና ቀላል ነገር እንደሆነ አድርጎ በመመልከት ሰዎች በሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ላይ በቂ

ዕውቀት ካላቸው ለተማሪዎቻቸው የማስተላለፍ ጥበቡና ችሎታው ግን ተፈጥሮአዊ በመሆኑ የሚያውካቸው እንዳልሆነ ያስረዳል (Fish 1989)::

በተግባራዊያኑ አመለካከት ግን ማሥተማር እንደቀላል ነገር አይታይም:: ስፊ ዕውቀትን፣ ባህርያትን፣ ውሳኔ የመስጠት ችሎታን፣ የማደራጀትና የመምራት ብቃትን . . . የሚጠይቅ እጅግ ውስብስብና ሂደተ ብዙ ተግባር ነው (ዝኒ ከማሁ):: ማሥተማር የዕጩ መምህራኑን ንቁ ተሳትፎ፣ የባለሙያዎችን ድጋፍ፣ የአማካሪዎችን ክትትል የሚጠይቅ ጣይንስም ጥበብም ነው (Dove 1986)::

የተግባራዊያኑ የስነ እውቀት ፍልስፍና እንደሚያስረዳው "ዕውቀት ከባለቤቱ ውጭ ነፃ ሆኖ የሚኖር ሳይሆን አጥኚው ግለሰብ/ተማሪው/ የሚገነባው፣ ቀድሞ ከተገነዘበውና ካዘበተው ባህርይ ጋር አዛምዶ የሚፈጥረው የተስተጋብሮት ውጤት ነው (ተክለሃይማኖት (1992፣1) የዘሚሽለኪ (1996)ን ሥራ ጠቅሠው ያቀረቡት)::

በዚህ ፍልሥፍና ድጋፊዎች መሠረት ማስተማር በህግ የታጠረ ትዕዛዝ/መመሪያ/ አይደለም:: Day (1993) እንደአስረዱት ማስተማርን መማር እንደየመማሩ አውድ ተግባራዊ የሚሆንና በተግባራዊ ክንውኑም ዕውቀትን ሊያስጨብጥ የሚችል መሥተጋብር ነው:: በመሆኑም ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን ንድፈ ሀሳቦች ወይም መርሆዎች በተግባርና በዕብረታ አዳብረው ማስተማርን ሊማሩና ሙያዊ ተግባራቸውን ሊያሳድጉ ይገባል (Fletcher 2000):: እንደ ተግባራዊያኑ የሥነ ዕውቀት አመለካከት ዕድገት/ለውጥ/ በተስተላልፎ የሚገኝ ሳይሆን በግለሰቦች ተግባራዊ ዕንቅስቃሴ ውስጥ የሚገነባና የሚፈጠር ነው (Piaget 1973):: ለዚህም ይመሥላል Tabachinka and Zeicher (1991) ዕጩ መምህራን በዕውናዊ የተግባር አውዶች ላይ በመሣተፍ ከሚያገኙት ልምድ ንድፈ ሀሳብን አመንጭዎች እንዲሆኑ እንደሚጠበቁ ያስረዱት::

በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሀገሮች በሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተቀባይነትን ያገኘውና እየተሠራበት ያለው የተግባራዊያኑ የሥነ ዕውቀት ፍልሥፍና ነው (Schon 1983):: ሥለሆነም ቀደም ሲል ሲሠራበት የነበረውና መምህራንን እንደ ዕውቀት ምንጭና አሥተላለፊ፣ ተማሪን ደግሞ እንደ ዕውቀት ተቀባይ አድርጎ የሚቆጥረው የመማር ማሥተማር ሥርዓት ወደ አዲስና ዘመናዊ አሥተሣሠብ ተቀይሯል (Goble and Porter 1977:13)::

የመምህር ተግባር ምን መሆን እንዳለበት (Searason et al (1986:76) እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

> የመምህራን ተግባር የዕውቀት ምንጭ ነኝ በሚል ስሜት ያልኩትን ተቀበሉኝ መሆን የለበትም:: በአንፃሩ ሥነ ልቦናዊ ፈታሽ (Psychological diagnostician) እና ብልሀተኛ በመሆን ተማሪዎች ዕውቀትንና ተግባርን በማቀናጀት እንዲት

> መምራትና መጠቀም እንደሚችሉ የሚያሳዩና ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከቀረበው ግላጼ መረዳት እንደሚቻለው የመምህራን ተግባር የመማር ንሽ መፍጠር፣ ማበረታታትና አቅጣጫን ማመላከት . . . እንጂ የተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ ገድቦ የምለውን ስሙ /ተቀበሉ/ ሊሆን አይገባም፡፡ በሀገራችንም ይህን ዓይነቱን ትዕዛዛዊ የማስተማር ዘዴ አሳታፊ በሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ ለመቀየር ጥረት እየተደረገ መሆኑ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ (1994) ተገልጿል፡፡

በመምህራን ትምህርት ንድፈ ሃሳብ ከተግባር ጋር ተዋህዶ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ ሊከሰት የሚችለውን ችግር ዓለማየሁ (1997፤26) ቀለል ባለ መንገድ እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

> . . . ሥለ ብስክሌት አንዳድ ሌክቸር ሰጥቶ ያለ ተግባራዊ ልምምድ ግለሰቡ ብሥክሌት እንዲነዳ እንደመጠበቅ ነው፡፡ የመምህርነት ሙያ ደግሞ ውስብስብና ከፍተኛ ክህሎት የሚያሥፈልገው ነው፡፡ ንድፈ ሃሳብን ብቻ ሠብከን እንዲያሥተምር ብዙ የምንጠብቅበት መምህር ያንኑ ሥብከት ከማሥተጋባት ሌላ ፈጠራ የመጨመር ችሎታ ላይኖረው ይችላል፡፡ ብዙ ንድፈ ሀሳብ አስተምረን ውሡን ተግባራዊ ልምምድ ላይ ብቻ ብናተኩር መምህሩ በንድፈ ሃሳብ ማዕበል ይዋጥና ብዙ የንድፈ ሃሳብ ጥቂት የተግባር ሰው ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ዛሬ በኢትዮጵያችን በሁሉም መሥክ የምናሥተውለውና ችግራችንም ነው፡፡ በተለይ በመማር ማሥተማር ሂደት ውሥጥ ንድፈ ሀሳብ የገነነበት መምህር 'መሪ' ተማሪ 'ተመሪ' በሆነበትና ለተግባር አሉታዊ አመለካከት በሠፈነበት ሁኔታ የትምህርት ጥራት የሚታሠብ አይደለም፡፡

ከፍ ሲል የቀረበው ተጠቃሽ ሀሳብ እንደሚያመላክተው የመምህራን ትምህርት ግብ መቶ የሚሆነው ዕጩ መምህራኑ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የቀሰሙትን ዕውቀት በተግባር ሲፈትሹ፣ ከዕውናዊው የማሥተማር አውድ ጋር ሲተዋወቁና እንዲሁም በሥልጠናው ሂደት ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ ነው፡፡ ሥለሆነም በስልጠናው መርሃ ግብር የንድፈ ሀሳብና የተግባር ትምህርቶች ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ተዋህደው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.2 የማስተማር ልምምድ ምንነት፣ ዓላማና ተግባር

### 2.2.1 የማስተማር ልምምድ ምንነት

የማስተማር ልምምድ ዕጩ መምህራኑ በዕውናዊው የመማር ማስተማር መቼት ተግታፊ ሆነው ወደፊት ከሚሠማሩበት ሙያ ጋር በተግባር የሚተዋወቁበት ምንና እንዴት እንደሚያስተምሩ ሠፊ ተሞክሮ በመቅሠም ለሙያው ብቁ የሚያደርጋቸውን

ክህሎት የሚያዳብሩበት የመምህራን ትምህርት አንዱ አካል ነው (Srivastava and Bose (1978), Fish (1989), ዓለማየሁ (1997)።

ደረጀ ገብሬ (1997፡1) የማስተማር ልምምድን በተለይ ከቋንቋ ትምህርት አንፃር በመቃኘት እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

> . . . ይህ ወቅት የተማሪ አስተማሪዎቹ ከልዩ ልዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ተዋውቀው፤ እነሱ ላሠቡት ሁኔታ ተስማሚውን ዘዴ ቀይሰው /አልመው/ ከዕለታዊ ትምህረት ዝግጅት እንስቶ እስከ ምዘና ያለውን የማስተማር መማር ሂደት አጣጥመውና አቀናብረው የሚገኙበት ወቅት ነው። በሌላ በኩል ተዘጋጅተዋል ወይም ሊዘጋጁበት ይገባል ተብሎ የሚታሰብበት ወቅት ነው።

ከግላጼው መረዳት እንደሚቻለው የማስተማር ልምምድ ዕጩ መምህራኑ ወደፊት ያስተምሩታል ተብሎ የሚታሠበውን ትምህርት በተግባር ፈትሸው የሚረዱበትና ለተማሪዎቻቸው እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ስነዘዴያዊ ችሎታ የሚያዳብሩበት ማስተማርን የመማሪያ መንገድ ነው። Grower and Walters (1983:1) "... አንድን ቋንቋ ባግባቡ መጠቀም መቻል እንደመዋሰሉት ከሂሎች ሁሉ ማስተማርን ሳትለማመዱት (ተግባራዊ ሣታደርጉት) በወጉ ልትማሩት አትችሉም" በማለት እንደገለፁት የማስተማር ልምምድ በመምህራን ሥልጠና ሂደት ውስጥ ወሳኝና አማራጭ የለሽ ግብአት ነው።

### 2.2.2 የማስተማር ልምምድ ዓላማና ተግባር

የማስተማር ልምምድ ብቃት ያላቸውን መምህራን ለማፍራት በዕቅድ የሚከናወን ተግባር በመሆኑ የራሱ የሆኑ ዓላማዎች አሉት። በመሆኑም Grower and Walters (1983:2) የማስተማር ልምምድ በትምህርትነት ከሚሰጠው የትምህርት ዓይነት ዓላማና ትምህርቱ ከሚሰጥበት ደረጃ አንፃር ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንዱ በላይ የሆኑ ዓላማዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ ይገልፃሉ፤

ዕጩ መምህራኑ፤

ሀ. የማስተማር ቴክኒኮችን እንዲሞክሩ/በተግባር እንዲፈትሹ/ ዕድል ለመስጠት፤

ለ. ቀስ በቀስ በራስ የመተማመን ነፃነታቸው እያደገ በሚሄድበት መልክ ከቀላል ወደ ውስብስብ የማስተማር ደረጃ ለመረማመድ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር፤

ሐ. የማስተማር ዕንቅስቃሴያቸው እንዲገመገምና ገንቢ ሂስ እንዲሠጣቸው አጋጣሚዎችን ለመፍጠር፤

መ. ራሳቸውን የመገምገም ልምድ እንዲያዳብሩ ለማበረታታት፤

ሠ. የራሳቸውን የማስተማር ሥልት (Teaching style) እንዲያዳብሩ ለመርዳት፤

ረ. ከተማሪዎች፣ ከትምህርታዊ ችግሮቻቸውና በመማር ሂደት ተፅዕኖ ከሚያሳድሩባቸው ሥሜት ነክ ደንቢዎች (Affective factors) ጋር እንዲተዋወቁ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣

ሰ. በገንቢ ሙያዊ ዕገዛ እየተረዱ ከዕውናዊው የመማር ማሥተማር ክንውን ጋር እንዲተዋወቁ ዕድል ለመስጠት፣

ሸ. የሚያሥተምሩት ትምህርት ምን ያህል በተማሪዎች ዘንድ ተፈላጊነት እንዳለው ግንዛቤ እንዲኖራቸው።

ተ. ለሚያሥተምሯቸው ተማሪዎች የኃላፊነት ስሜት እንዲሠማቸው፣

ቢ. ተከታታይነት ካላቸው ደረጃዎች ጋር እንዲተዋወቁና ሥራ ላይ በሚውሉት የማሥተማሪያ ዘዴዎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት እንዲረዱ ለማድረግ ... ያሥችላቸዋል።

የማሥተማር ልምምድ በክንውኑ ለሚሳተፉ ዕጩ መምህራን ዕውነተኛ /ተጨባጭ/ ትምህርት እንዲያገኙ የሚያሥችል መሆኑን ከላይ የቀረቡት ዝርዝር ዓላማዎች ያመላክታሉ። ዕጩ መምህራኑ በተቋማቸው የሚያገኙትን ዕውቀት በተግባራዊ ልምምድ በማዳበር ለሚዘጋጁበት ደረጃ የሚመጥን የሙያ ብቃት እንዲኖራቸው ማሥቻል የማሥተማር ልምምድ አቢይ ዓላማ ነው።

የማሥተማር ልምምዱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድም የሚከተሉትን ሥድስት ደረጃዎች ማካተት ይኖርበታል፣

ሀ. በትምህርትንት የሚሰጡትን ይዘቶች ማደራጀት፣

ለ. የትምህርት ዕቅዶችን ማዘጋጀት፣

ሐ. የትምህርት ዕቅዶች አሥተያየት እንዲሰጥባቸው ለስፐርቫይዘሮች ማቅረብ፣

መ. ለክፍል ውስጥ የመማር ማሥተማር ትግበራ ዝግጅት ማድረግ፣

ሠ. ማሥተማር እና ምገበ መረጃ መሥጠት (Gowers and Walters (1983), Cohen and Manion (1983)።

ዕጩ መምህራኑ ከመደበኛው መምህር ክፍሉን በመረከብና ኃላፊነቱን በመውሠድ ማስተማርን ከመለማመዳቸው በፊት በትምህርት ቤትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምልከታ ያካሂዳሉ። በምልከታቸውም በትምህርት ቤቱ በሚታዩ ተፈጥሮአዊ እና ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎች፣ በመምህር ተማሪ መስተጋብር፣ በተማሪዎች ባህርይ (በትምህርታቸው፣ በጠባያቸው፣ በአመለካከታቸው ለየት ያለ ሁኔታ በሚያሳዩ) ላይ ትኩረት እያደረጉ ዝግበ ጥናት እንዲፅፉ ይጠበቃል (Azeb 1971፣48)።

ለክፍል ውስጥ ምልከታ መሠረት የሆኑ አራት አበይት ተተኳሪዎች አሉ (Lema and Taffesse 1997)። ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፤

ሀ. የመጀመሪያው ተተኳሪ መማሪያ ክፍሉ ሲሆን ዕጩ መምህራኑ የተማሪ ክፍል እና የተማሪ መምህር ጥመርታውን፣ ንፅህናውን፣ ማራኪነቱን፣ ተፈላጊ ቁሳቁሶች (ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ጥቁር ሰሌዳ . . .) መሟላታቸውን፣ የተለያዩ የመማር ማሥተማር ሥነዘዴዎችን ለማሥተናገድ ምቹ መሆኑን . . . ይመለከታሉ።

ለ. ሁለተኛው ተተኳሪ የክፍሉ መምህር ነው። ዕጩ መምህራኑ የመደበኛውን መምህር የጥቁር ሠሌዳ አጠቃቀም፣ የትምህርት አደረጃጀት፣ የመማር ማስተማር ዘዴ፣ የሚዲያ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የክፍል ውስጥ አመራር፣... ይመለከታሉ። Evertson (1985:5) እንደገለፁትም፣ "በትምህረቱ ትግበራ የመምህሩ ማና ምን ምን እንደነበረ፣ የተማሪዎችን ቀልብ (ትኩረት) እንዴት መግዛት እንደሚቻል፣ የሥነ ሥርዓት ጉድለት የሚያሳዩ ተማሪዎችን መቆጣጠርና መመለሥ የሚቻልበትን ዘዴ ይቃኛሉ።"

ሐ. ሶስተኛው ተተኳሪ ተማሪዎች ናቸው። ተማሪዎችን በተመለከተ ዕጩ መምህራኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፤ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን መነቃቃት፣ የሚያሳዩትን ተሳትፎ (እያንዳንዳቸው የመሣተፍ ዕድል ሥለማግኘታቸው) የተለያዩ ተግባራትን ማከናወናቸውንና በትምህርቱ መርኳታቸውን ወዘተ. በንቃት መከታተልና መዘገብ ይጠበቅባቸዋል (Allwright Dick 1988)።

መ. አራተኛው ተተኳሪ ደግሞ ትምህርቱ ነው። ትምህርቱን በተመለከተ ዕጩ መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ሊከታተሏቸው የሚገቡ አበይት ጉዳዮች ተገቢነቱ፣ ግልፅነቱና አደረጃጀቱ ናቸው (ዝኒ ከማሁ)። የትምህርቱ ዓላማ ምን እንደነበረና ለተማሪዎች ሥለመገለፅ አለመገለፁ፣ የቀረበበት ቋንቋ ግልፅ ሥለመሆኑ፣ ከተማሪዎች ዳራ (ዕውቀት፣ ችሎታ፣ ዕድሜና . . .) እና ፍላጎት ጋር ስለመጣጣሙ፣ የተለያዩ ተግባራትን (Activities) ሥለማካተቱ፣ ዕውቀትንና ችሎታን በመገንባት ሥላለው ፋይዳ፣ እያንዳንዱ ተግባርና በጥቅሉም የዕለቱ ትምህርት በተመደበለት ክፍለ ጊዜ ሥለመጠናቀቁ . . . በአትኩሮት እየተከታተሉ ማስታዎሻ መያዝ ይገባል።

ከፍ ሲል በተጠቀሱት ተተኳሪዎች ላይ ምልከታ ማካሄድ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፣ ቀጣዩን ማስተማር ልምምድ የተቃናና ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ ዕውቀትና ልምድ ለማግኘት ያስችላል። የእንግዳነትና የመደንጋገር /መደናገጥ/ ስሜትን ለመቀነስ

ወይም ለማሦገድ ይረዳል፡፡ በጥቅሉ ከዕውናዊው የመማሪያ አውድ ጋር ለመተዋወቅ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ዕጩ መምህራኑ በትምህርት ቤት አውድ ውስጥ ተገኝተው በምልከታ አማካይነት ወደ ተግባር የሚያስገባቸው ግንዛቤ ከጨበጡ በኋላ በሱፐርቫይዘሮች ክትትልና እገዛ እየተደረገላቸው ማሥተማርን ይለማመዳሉ፡፡ በልምምዱ ሂደትም ትኩረት ሊቸራቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ በቋንቋ ትምህርት የሚደረግ የማስተማር ልምምድ በሚከተሉት አራት ዘርፎች ላይ ያተኩራል፤

ሀ. በመማሪያ ክፍል ለቋንቋ አጠቃቀም ችግሮች የሚሠጡ ምላሾች፤

ለ. በመማሪያ ክፍል በቋንቋ መማር ሂደት ለሚያጋጥሙ ግላዊ የመማር ችግሮች የሚሰጡ ምላሾች፤

ሐ. መሠረታዊ የመማሪያ ክፍል አመራር፤

መ. የማስተማሪያ ቴክኒኮች (Dick Allwright 1988, Gower and Walters 1983)::

## 2.3 የሱፐርቪዥን ምንነት፣ ዓላማና ተግባር

### 2.3.1 የሱፐርቪዥን ምንነት

በርካታ ፀሐፍት ሱፐርቪዥንን በተለያየ መንገድ ገልፀውታል፡፡ ሥለሆነም ዓለም (1998) ዋላስ (1991)ን በመጥቀስ እንዲገለፁት ለሱፐርቪዥን ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት ያስቸግራል፡፡ ለአብነት ያህል የአንዳንዶቹን ግላጼ ቀጥለን እንመልከት፤

ሱፐርቪዥን፣

2.3.1.1 የትምህርት ቤቶች ሥርዓት የተማሪዎችን መማር ማሳደግ በሚችልበት ሁኔታ የመቆየር /የመለወጥ/ ተግባር ነው (Goldhammer 1980:17)::

2.3.1.2 ትምህርታዊ አገልግሎቶች ውጤታማ በሚሆኑበት ጉዳይ ላይ የሚያተኩር የትምህርት ቤቶች አሥተዳደራዊ ሥርዓት አንዱ ገፅታ ነው (Eye and Netzer 1965:400)::

2.3.1.3 ከተማሪዎች ጋር አብሮ በመሥራት በትምህርት ላይ መሻሻልን ለማምጣት የሚካሄድ ጥረት ነው (Spears 1955:18)::

2.3.1.4 ዕጩ መምህራኑ በተለያዩ ግላዊና ቡድናዊ ተግባራት ላይ ሥለሚያደርጉት ተሳትፎና ሥለአፈፃፀም ብቃታቸው ሙያዊ ልምዱ ካላቸው ሰዎች ምግበ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መረጃዎችን እያገኙ የበለጠ መለወጥ/ማደግ/ እንዲችሉ የሚያግዝ ሙያ ነው (Girmay 2005:9)።

2.3.1.5 የማሥተማርን ሥራ ለማሻሻል የታቀደ መርሀ ግብር ነው (Knezevich 1969:263)።

2.3.1.6 ሠልጣኝ መምህሩ በልምምድ ወቅት የሚሠራውን ስህተት እየነቀሰ ማውጣት ማለት ነው (ሂሩት 1998፣11 የ"Abrham et al 1999"ን ጠቅሳ የገለፀችው)።

በገላጺዎቹ ውስጥ እንደየፀሐፊዎቹ አመለካከት የሱፐርቪዥንን ምንነት ይበልጥ አጉልተው የሚያሳዩን ቃላትና ሀረጎች አሉ፤ ከነዚህም ውስጥ ዕድገት/መሻሻል፣ ውጤታማነት፣ ትብብር፣ ሂደት፣ ዕርማት፣ ምገበ መረጃ መስጠት፣ ዕቅዳዊ ፕሮግራም፣ ስህተትን መንቀስ የአመራር አካል የሚሉት አበይቶቹ ናቸው።

ገላጺዎቹ ከፅንሰ ሃሳብ ይዘታቸው አንፃር ሲታዩ አንዳንዶቹ ጠባብ አንዳንዶቹ ደግሞ ሰፊ ናቸው። እንደ Abrham (1999) ሱፐርቪዥን ሥህተትን ነቅሶ አመላካች ነው። ይህ ጠበብ ያለ ፅንሰ ሀሳብን የያዘ ነው። እንደ እነ Goldhamer, Spears, Knezevich, . . . ደግሞ ሱፐርቪዥን ሂደት፣ ለውጥ፣ ጥረት ወዘተ. በመሆኑ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ መያዙን ያመላክተናል። "Eye and Netzer" ሱፐርቪዥንን ከማሥተማር ሣይሆን ከአሥተዳደራዊ ሥርዓት ጋር አያይዘው ገልፀውታል።

ሱፐርቪዥን እንደየዘመኑ የትምህርት ፍልሥፍና እንደየተግባሩ ዓይነት የተለያዩ ትርጉሞች ሲሰጡትና ለተለያየ ጠቀሜታ ሲውል ቆይቷል። በሀገራችን ቀደም ባለው ጊዜ ሱፐርቪዥን ስህተት ፈላጊ፣ የፖሊሲዎችና ደንቦች ጠበቃ ከመሆን የዘለለ ፋይዳ እንዳልነበረው መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ ሱፐርቪዥን የሚለው ሥያሜ በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚማሩ ዕጩ መምህራን በማሥተማር ልምምድ ሂደት ላይ እያሉ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን በመለየት እንዲያሻሽሉና እንዲያጠናክሩ ከተለያዩ አካላት (አሠልጣኝ መምህራንና የአጋር ት/ቤት ነባር መምህራን) የሚደረግላቸውን ሙያዊ ድጋፍ የሚመለከት ነው።

በአጠቃላይ ሱፐርቪዥን፣ ዕጩ መምህራኑ የመማር ማስተማር ሂደት የትምህርት ዓላማዎችን ከግብ ማድረሻ መሣሪያ በሚሆንበት መልኩ የመተግበር ብቃት እንዲኖራቸው ሙያዊ ዕገዛ የሚያገኙበት የሥልጠና አካል ነው ማለት ይቻላል። ዕገዛውም የመምህራን ትምህርት ገፅታዎች የሆኑት ንድፈ ሀሳብና ተግባር አንዱ ለሌላው ሥልጠት ምክንያት እየሆኑ በትምህርት አማካይነት ሊደረሥበት ወደሚፈለገው ግብ መራመድ የሚቻልበትን አቅጣጫ በማመላከት ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

### 2.3.2 የሱፐርቪዥን ዓላማና ተግባር

በሥልጠና ተግባር ውስጥ የሱፐርቪዥን አቢይ ዓላማ የዕጩ መምህራኑን ማስተማርን የመማር ችሎታ ማሻሻል ነው:: ዕጩ መምህራኑ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችንና ቴክኒኮችን በመጠቀም ማስተማርን እንዲማሩና በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር አውድ ላይ በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያዳብሩ ይረዳል (Srivastova and Bose 1978:15)::

ሱፐርቪዥን የዕጩ መምህራኑን ብቃት ከማሳደግ አንፃር ያሉትን ዓላማዎችና ተግባሮች በተመለከተ የተለያዩ ፀሀፍት እንደሚከተለው ያስረዳሉ፤

ሀ. የትምህርት ግቦችን በሚገባ በመለየት እነዚህ ግቦች ጋር ለመድረስ የትምህርት ቤት ሚና ምን ምን መሆን እንደሚገባው የጠራ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣

ለ. ዕጩ መምህራኑ የተማሪዎችን የመማር ችግር በሚገባ እንዲረዱና ችግርን የማቃለያ /የመፍቻ/ ብልሀቶችን እንዲያዳብሩ ያግዛል፣

ሐ. ዕጩ መምህራን በማሥተማር ሙያቸው ወደ ተሻለ ብቃት እንዲረማመዱ ያግዛል፣

መ. በማስተማር ተግባር ላይ ንቁ ተሳታፊ የመሆን ዕድልን ይፈጥራል:: በተጨማሪ አንድን የተወሰነ ትምህርት በዘመናዊው ትወራ ማዕቀፍ (Modern theoretical frame) መሠረት መገምገም (መተቸት) እንዲችሉ ያግዛል፣

ሠ. ዕጩ መምህራንን የራሳቸውን የመማር ማስተማር ፍልሥፍና እንዲያፈልቁና እንዲያዳብሩ፣ ይበጃሉ የሚሏቸውንና የሚያምኑባቸውን ሃሳቦች እንዲያንፀባርቁ፣ እንዲሁም ራሳቸው ለሚያነሷቸው ሀሳቦች፣ ሥለ ግለሠቦችና ማህበረ ባህላዊ ልዩነቶች ምክንያታዊና ብቁ ተከራካሪዎች እንዲሆኑ ያግዛል፣

ረ. በትምህርት ሥርዓቱ በሚከሰቱ ለውጦች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና የተለማጭነትን (Flexibility) ባህሪይ እንዲያዳብሩ ያበረታታል፣

ሰ. ሙያዊ ብቃቱ እና ልምዱ ያላቸውን ሰዎች ተሞክሮ እንዲቋደሱና ማስተማርን የበለጠ መማር እንዲችሉ በከፍተኛ ሁኔታ ያግዛል፣

ሸ. በግልፅ የመወያየት ስሜትን በማዳበር ችግሮችን የመለየት፣ የተለያዩ (መልከ ብዙ የሆኑ) በመማሪያ ክፍል ውስጥና በትምህርት ቤት የሚከሰቱ የመማር ማሥተማር ተግባሮችን ከትምህረት ግብ አንፃር በመመልከት የመግለፅ፣ እንዲሁም በሥፋት ሥለማህበረሰቡ ያላቸውን ግንዛቤ የማንፀባረቅ አቅም እንዲፈጥሩ ዕገዛ ያደርጋል፣

ቀ. ራሳቸውን የመገምገም ችሎታን እንዲያጎለብቱ ያግዛል . . . (Anberbir 1975, Grower and Walters 1983, MOE 2003)::

ከቀረቡት ግላጼዎች መረዳት እንደሚቻለው የመምህራን ሥልጠና አካዳሚያዊ ብቃት ሙያዊ ችሎታ ያላቸውን መምህራን የማፍራት አቅም እንዲኖረው ሱፐርቪዥን የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ሱፐርቪዥን፣ ዕጩ መምህራኑ ትምህርቱ በተማሪዎች ዘንድ እንዲያስገኝ የተፈለገውን የባህርይ ለውጥ ተረድተው የመማር ማስተማሩን ሂደት ይህንን ለውጥ ዕውን በሚያደርግ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡ ዕጩ መምህራኑ በማሠልጠኛ ተቋማት ያገኙትን ንድፈ ሀሳባዊ ዕውቀት በተግባር መተርጎም እንዲችሉ መርዳት የሱፐርቪዥን አቢይ ዓላማና ተግባር ነው፡፡

## 2.4 የሱፐርቪዥን ዓይነት /አቀራረብ/

የሱፐርቪዥን ዓይነትና ሱፐርቫይራዊ አቀራረብን በተመለከተ ወጥ የሆነ አመዳደብ የለም፡፡ የተለያዩ ፀሐፍት እንደየትኩረታቸውና ገጠመኞቻቸው በተለያየ መንገድ እንደፈረጁት ድርሳናት ይጠቁማሉ፡፡ የሱፐርቪዥን ዓይነት ወይም አቀራረብ መብዛትና መለያየት ሱፐርቫይዘሮች የተለያዩ አማራጮችን በማግኘት ዕጩ መምህሩ እንደሚፈልገው የእገዛ አይነት እየመረጡ እንዲጠቀሙ ሰፊ ዕድልን ይፈጥራል (Girmay 2005:9)፡፡ ከበርካታ የሰፐርቪዥን ዓይነቶች (አቀራረቦች) ውስጥ የተወሰኑትን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**2.4.1 መሪያዊ (ትዕዛዛዊ) ሱፐርቪዥን (Directive Supervision)**:- ይህ ሱፐርቪዥን ሱፐርቫይዘር መር (Trainer centred) ነው፡፡ ሱፐርቫይዘሩ በክፍል ውስጥ ከዕውናዊው የማስተማር አውድ ያገኛቸውን መረጃዎች ለዕጩ መምህሩ ይገልፃል፡፡ በቀጣይ ምን ምን ማድረግ እንዳለበትም ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ዕጩ መምህሩ የተነገረውን አዳምጦ ለትግበራው መነሳሳት ይጠበቅበታል፡፡ ሱፐርቫይዘሩም ያስተላለፈው መመሪያ (ትዕዛዝ) መፈፀሙን ይከታተላል (ይገመግማል)፡፡ በዚህ ዓይነቱ አቀራረብ ዓለም (1988፣19) እንደገለፀው የሱፐርቫይዘሩና የዕጩ መምህሩ ግንኙነት የአለቃና የምንዝር ያህል ሥለሚሆን ዕጩ መምህሩ የራሱን ግንዛቤና ችሎታ እንዳያዳብር ከመገደቡም በላይ የበታችነት ስሜት እንዲያድርበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**2.4.2 ኢመሪያዊ ሱፐርቪዥን** (non directive supervision):- በዚህ ሱፐርቪዥን ሱፐርቫይዘሩ የምልከታውን ውጤት ለዕጩ መምህሩ ይገልፅለታል፤ መሆን አለበት ያለውንም መፍትሔ ይጠቁመዋል፤ ሆኖም የራሱን አመለካከት እንዲቀበለው ምክርም ሆነ ትዕዛዝ አያቀርብም፡፡ በመሆኑም ዕጩ መምህሩ

የመቀበል ወይም ያለመቀበል ሙሉ ነፃነት አለው:: ራሱ ይበጀኛል የሚለውን የማሻሻያ /ዕርምት/ መንገድ መከተል ይችላል (ዓለም 1988)::

**2.4.3 ትብብራዊ ሱፐርቪዥን (Collaborative supervision):-** በትብብራዊ ሱፐርቪዥን ሱፐርቫይዘሩ እና ዕጩ መምህሩ የሚተያዩት እንደጓደኛ ነው፤ አብረው ይሠራሉ፤ አብረው ይወስናሉ (Wallace 1991:11):: የእጩ መምህሩ ብቃት በሚሻሻልበት /በሚያድግበት/ ሁኔታ ላይ እየተወያዩ ችግሮችን ይፈታሉ:: የተሻሉ አሠራሮችን ይቀይሳሉ (Cogan 1973)::

**2.4.4 አማራጫዊ ሱፐርቪዥን (Alternative supervision):-** ይህ ሱፐርቪዥን እንደ መራኂ ሰፐርቪዥን በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በማስመልከት ዕጩ መምህሩ ከሱፐርቫይዘሩ የሚሠጠውን መመሪያ ተቀብሎ የሚተገብርበት አይደለም:: ሊሻሻሉ/ሊታረሙ ወይም ሊጎለብቱ ለሚገባቸው የምልከታ ውጤቶች ሱፐርቫይዘሩ የተለያዩ አማራጮችን አቅርቦ ነፃ ውይይት በማካሄድ ዕጩ መምህሩ በአማራጮቹ እንዲጠቀም ዕድል የሚሰጥ ነው (Girmay 2005)::

**2.4.5 ራሥመር ሱፐርቪዥን (Self directed supervision):-** ይህ ሱፐርቪዥን ዕጩ መምህራን ለራሳቸው ሙያዊ መሻሻል የሚበጁ ነገሮችን በግላቸው እንዲሠሩ የሚያበረታታ ነው (ዝኒከማሁ):: ለምሳሌ የራሳቸውን የማሥተማር ተግባር ራሳቸው በመገምገም ካገኙት ውጤት በመነሳት ግቦችን ያመላከተ ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁና ለሱፐርቫይዘራቸው እንዲያሳዩ ሊደረግ ይችላል ሱፐርቫይዘሩም ዕቅዱ ትክክለኛና ሊደረስበት የሚችል መሆኑን ያረጋግጣል::በዓመቱ መጨረሻም ሱፐርቫይዘሩና መምህሩ በዕቅዱ መፈፀምና በዓላማው መሳካት ዙሪያ እየተወያዩ ምገበ መረጃ ይለዋወጣሉ::

**2.4.6 ባልደረባዊ ሱፐርቪዥን (Colleague Supervision):-** ይህ ሱፐርቪዥን ዕጩ መምህራን ሙያቸውን ለማሻሻል በጋራ እንዲሠሩ የሚያግዝ ነው:: Girmay (2005:15) እንደገለፁት ከሆነም "ባልደረባዊ ሱፐርቪዥን ሁለት ወይም የበለጡ መምህራንየጋራ ትብብር /ቡድን/ በመመስረት አንዱ የሌላውን የክፍል ውስጥ የማስተማር ተግባር እየተመለከተ ምገበ መረጃዎችን የሚሰጣጡበት፣ ሥለምልከታው በመወያየት ሙያዊ ተሞክሮአቸውን የሚለዋወጡበት ሱፖርቪዥን ነው::" ዕጩ መምህራኑ ራሳቸው በንዑሳን ቡድኖች (ሁለት ወይም ሶስት እየሆኑ) ሊደራጁ ይችላሉ:: ወይም ሱፐርቫይዘሩ ሊያቧድናቸው /ሊያደራጃቸው/ ይችላል:: በዚህም በሥረዓተ ትምህርቱ እና ማሥተማርን በመማሩ ተግባር ላይ ሊወያዩ፣ እርስ በርሳቸው ልምድ እየተለዋወጡ አዳዲስ



ABABA UNIVERSITY
LS LIBRARY

የማሥተማር ዘዴዎችን ሊለማመድ፣ ተግባራዊ ምርምር በማድረግ የተለያዩ ችግሮችን ሊፈቱ ይችላሉ::

2.4.7 **በምርምር ላይ የተመሠረተ ሱፐርቪዥን (Inquiry based Supervision)**:- ይህ ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ በተግባራዊ ምርምር ላይ የተመሠረተ ሆኖ ዕጩ መምህራኑ በግል ወይም በቡድን ሆነው ችግሮችን ለማቃለል የሚችሉበትን ብቃት ማግኘት ዓላማው ያደረገ ነው (Girmay 2005:17):: ተመራማሪ መምህር አትኳሪ፣ ጠያቂ፣ ተማሪ እና የበለጠ ብቃት ያለው ነው የሚል ዕሳቤን መነሻ የደርጋል:: በግል በሚሠራው ተግባራዊ ምርምር ዕጩ መምህሩ በማስተማሩ ልምምድ ያጋጠሙትን የራሱን ችግሮች በመለየት የማቃለያ ሥልቶችን እንዲቀይስ ይጠበቃል:: በቡድን በሚሠራው ተግባረዊ ምርምር ደግሞ የጋራ የሆኑ ችግሮች ላይ በማተኮር የማስተማር ልምምዳቸውን በተሻለ መንገድ መተግበር የሚችሉበትን መላ እንዲያፈላልጉ ይጠበቃል:: በዚህም ሱፐርቫይዘሩ ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን ችግሮች በግልና በቡድን የመፍታት ብቃት እምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ከሥራዎቻቸው ያገኘውን መረጃ በመያዝ ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል::

2.4.8 ሌላው (Girmay 2005:16) የጠቆሙት ሱፐርቫይዘራዊ አቀራረብ **መደበኛ ያልሆነ ሱፐርቪዥን** (Informal supervision) ነው:: ይህ ሱፐርቪዥን ሁለቱ ተሥተጋባሪዎች /ዕጩ መምህሩና ሱፐርቫይዘሩ/ የመገናኛ ቀጠሮ ሣይኖራቸው ሱፐርቫይዘሩ በመምህራን የተለያዩ ተግባረዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ድንገት እየተገኘ ምልከታ የሚያካሂድበት ነው:: ሱፐርቫይዘሩ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ተግባር ሲካሄድ፣ መምህራን በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ሥለ ሥኬቶቻቸውና ችግሮቻቸው ሲወያዩ፣ እንዲሁም ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ ተግባራትን ሲያከናውኑ በድንገት/አስቀድሞ ቀጠሮ ሣይያዝ/ እየተገኘ ምልከታ የሚያካሂድበትና ተሳታፊ የሚሆንበት አቀራረብ ነው:: ይህ ዓይነቱ ሱፐርቪዥን የሰመረ ሊሆን የሚችለው የሱፐርቪዥን ዓላማ በሚገባ ግንዛቤ ባገኘበትና አገልግሎቱ በጎለበተበት መቼት ውስጥ ነው:: ሱፐርቪዥንን እንድ አንድ የሥራ አካል ሱፐርቫይዘሩንም እንደ አጋር መመልከቱ ባልዳበረበት መቼት ውስጥ ለመተግበር መሞከር አሉታዊ ገፅታው የጎላ ይሆናል (ዝኒ ከማሁ)::

2.4.9 ዘመናዊና ውጤታማ በመባል የሚታወቀው ሌላው ሱፐርቪዥን **ክሊኒካዊ ሱፐርቪዥን** (Clinical Supervision) ነው:: አቢይ ዓላማው ዕጩ መምህራኑ በዕውናዊው የማሥተማር እውድ እና በንድፈሀሳባዊ መሠረቱ መካከል ያለውን መጣጣም በተጨባጭ እንዲገነዘቡ ማሥቻል ነው (Richards and Nunan 1990):: በዚህ ዓይነቱ ሱፐርቪዥን ሱፐርቫይዘሩ ከዕውናዊው የክፍል ውስጥ

የማሥተማር ልምምድ ሁነት ርቱዕ መረጃዎችን በማግኘትና በመተንተን መሻሻል/ለውጥ/ ለማምጣት ጥረት ይደረጋል (Goldhammer 1981፣ Cogan 1973፣ Girmay 2005)።

ክሊኒካዊ ስ·ፐርቪዥን በተግባራዊ ሂደቱ ዑደታዊ ተያያዥነት ያላቸውን አምሥት የምልከታ ደረጃዎች ያልፋል፤ እነርሡም፦ ቅድመ ምልከታ ውይይት፣ ምልከታ፣ በምልከታ የተገኘን መረጃ መተንተንና ሥትራቴጂ መቀየስ፣ የድኅረ ምልከታ ውይይት፣ እንዲሁም ድኅረ ምልከታ ትንተና ናቸው (Goldhammer 1981)።

ከፍ ሲል የቀረቡት ስ·ፐርቪዥኖች አብዛኞቹ ዕጩመምህር መር (Candidate centered) ሲሆኑ መሪ·ሄ (ትዕዛዛዊ) ስ·ፐርቪዥን ግን ስ·ፐርቫይዘር መር (Trainer centered) ነው። ስ·ፐርቪዥኖቹ ተማሪዎች እንዴት መማር እንዳለባቸው የሚነግሩ፣ የተለያዩ አማራጮችን በማቅረብ ዕጩ መምህሩ የሚሻለውን መርጦ እንዲጠቀም የሚጋብዙ፣ ዕጩ መምህራን የራሳቸውን ተግባር ራሳቸው በመገምገም መፍትሔ እንዲያፈላልጉ የሚያበረታቱ . . . ናቸው።

እዚህ ላይ የትኛውን ስ·ፐርቪዥን መከተል ያዋጣል? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ይችላል። በመስኩ ምርምር ያካሄዱ ሰዎች የተለያዩ ምላሽ አላቸው። ለምሳሌ ዓለም (1988፤13) የእነ "ጊብሀርድ 1990፤ ዛሆሪክ 1988፤ ዋላስ 1991፤ እነሁብር 1988"ን ሥራ በመጥቀስ የስ·ፐርቪዥን ሂደት ከትዕዛዛዊ አቀራረብ መላቀቅ ያለበት መሆኑን ያጠቃግላሉ። ተሰጠ (1997፤30) ይህንኑ ሀሳብ በመጥቀስ ያጠናክራል። ሂሩት (1988፤21) ግን እንደአስፈላጊነቱ አቀራረቦቹን እያቀናጁ መጠቀሙ የጎላ ፋይዳ እንዳለው ገልፃለች። በአስረጅነትም የሚከተለውን አቅርባለች፦

> ለምሳሌ አንድ የተማሪ አስተማሪ ምን ማስተማር እንዳለበት ለመወሰን ሲቸገር . . . ስ·ፐርቫይዘሩ በመሪ·ሄ ስ·ፐርቪዥን ውስጥ ይሆናል። እንዲሁም እንዴት ማስተማር እንደሚገባው ለመግለፅ ስ·ፐርቫየዘሩ አማራጫዊ አቀራረብን ሊከተል ይችላል። ወይም ደግሞ ለምን ማሥተማር እንደሚገባው ለመግለፅ በኢመሪ·ሄ አቀራረብ ሊጠቀም ይችላል። ስለዚህ በአንድ የስ·ፐርቪዥን ግንኙነት ውሥጥ የተለያዩ አቀራረቦችን አቀናጅቶ ሊጠቀም ይችላል።

Daniel (2002) እንዳስገነዘበት መማር የተግባር ልምምድ ውጤት ሆኖ የሚከሠት የዕውቀት፣ የችሎታና ያመለካከት ለውጥ ነው። ለዚህም ይመሥላል ዓለም (1998፤23) የኬኒዲ (1993)ን ሥራ ጠቅሰው የተማሪ አስተማሪዎች የራሳቸውን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ በትክክል የሚረዱበትንና ዞርብለው የሚመረምሩበትን መንገድ ስ·ፐርቫይዘሮች ሊሹ ይገባል... የተማሪ አስተማሪዎች በዚህ መንገድ የራሳቸውን ዕንቅስቃሴ በአንክሮ ማጤንና መመርመር ሲችሉ ነው የሥልጠናው ሂደት... ከሥልጠና

... ወደ ሙያዊ እድገት መሸጋገር የሚችለው፣ በማለት የገለፁት። ሥለሆነም የሥልጠና ስሌት በትዕዛዝና ያልኩህን ፈፅም በሚል አምባገነናዊ ስሜት ሳይሆን አማራጮችን በማመላከት፣ በማትጋት (ማነቃቃት)፣ የራሱን ተግባር ራሱ እንዲያይና እንዲፈትሽ በማገዝ . . . ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሠድበት ይገባል።

## 2.5 የሱፐርቪዥን መርሆች

ሱፐርቪዥን ትምህርታዊ አገልግሎቶች ውጤታማ በሚሆኑበት ጉዳይ ላይ የሚያተኩር የመማር ማስተማሩ ተግባር አጋዥ ነው። Anberbir (1975) የእነ Hailessilasie (1967), Ayer (1954)ን ሥራ ዋቢ በማድረግ እንደገለፁት ሱፐርቪዥን የሚከተሉት አበይት መርሆች አሉት፤

**2.5.1 ሱፐርቪዥን አመለካከታዊ (attitudinal) ነው**፡- ሱፐርቪዥን የታለሙ ዕቅዶች የተፈፀሙ ተግባሮችን በጥልቀት መመልከተንና በተመለከቱት ነገር ላይ ተመሠርቶ ምግበ መረጃ መስጠትን ይጠይቃል። ስለሆነም ይህ መርህ የሱፐርቪዥን ውጤታማነት በሱፐርቫይዘሩ የአመለካከት ብቃት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመላክታል።

**2.5.2 ሱፐርቪዥን ፈጣሪነት ያለው (Creative) ነው**፡- ይህ መርህ ሱፐርቪዥን የተደበቀ ተሰጥኦን እንዲወጣ በማድረግ አዲስ ልምድ እንዲገኝና የተለዩ (የተሻለ) አስተዋፅኦ ማበርከት እንዲቻል የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል።

**2.5.3 ሱፐርቪዥን ትብብር ነው**፡- በትምህረት እና በማስተማር ላይ ለውጥ/መሻሻል/ ሊመጣ የሚችለው በሂደቱ ላይ የተሠማሩ አካላት ሁሉ ተባብረው ሲሰሩና ዓላማን ለማሳካት ሲጥሩ ነው። ሱፐርቪዥን ይህ ዓይነቱ ትብብር እንዲጎለብት ያንዱ ተሞክሮ ለሌላውም እየተረፈ እንዲሄድ ሙያዊ ዕገዛ የሚሰጥበት የሥራ አካል ነው፤ ትብብር ነው መባሉም ለዚህ ነው።

**2.5.4 ሱፐርቪዥን ንድፈ ሀሳባዊ ጥልቅነት (Theoretical Sound) ሊኖረው ይገባል**፡- ሱፐርቪዥን አበይት ዕሴቶችን፣ ዓላማዎችን፣ ፖሊሲዎችን . . . ለብቃታቸው፣ ሁቅንታቸው እና ህጋቸው ሳይንሳዊ ማጣቀሻዎችን በማቅረብ ለትክክለኛነት፣ ለለውጥና ለዕድገት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን ይህ መርህ ያመላክታል።

**2.5.5 ሱፐርቪዥን ሳይንሳዊ ሊሆን ይገባል**፡- ሱፐርቪዥን በቅደም ተከተል የሚከናወንና በሥርዓት የሚመራ፣ የጥናት ውጤት የሆኑ አበይት ዘዴዎችን፣ እንዲሁም ትክክለኛና በቂ የሆኑና የበለጠ ሙያዊ ተረጋግጦ ያላቸውን መረጃዎችን የሚጠቀም ነው።

**2.5.6 ሱፐርቪዥን ሚዛናዊ ሊሆን ይገባል፡-** ይህ መርህ ደግሞ ሱፐርቪዥን ለትብብር እና ለተሟትጩ ሙሉ ነፃነትን ሰጭ መሆን እንዳለበት ያመላክታል። ሱፐርቪዥን ሥራን ማዕከል ያደረገ፣ ከአንድ ወገን ተፅዕኖ የፀዳ/የራቀ/ ና ግቡ ዕድገት /ለውጥ/ የሆነ የሥልጠና ሂደት አካል ነው።

## 2.6 ሱፐርቫይዘራዊ ክህሎት

ሱፐርቪዥን ግብ መች እንዲሆን አገልግሎቱን የሚሠጡ አካላት ሙያዊ ዕውቀቱና ችሎታው ሊኖራቸው ይገባል። የተለያዩ ፀሐፍት (Griffths, 1956; Katz, 1979) እንደገለፁት ሱፐርቫይዘሮች ሊኖሯቸው የሚገቡ አበይት ክሂሎች የማስተዋል/መገንዘብ/ ክሂል (Conceptual skill)፣ ቴክኒካዊ ክሂል (Technical skill) እና ከሰዎች ጋር የመግባባት ክሂል (Human Relation skill) ናቸው። ቀጥለን የእነዚህን ክህሎቶች ምንነት በዝርዝር እንመለከታለን።

**2.6.1 የሱፐርቫይዘር የማስተዋል ክህሎት፡-** የሚገለጠው የሱፐርቫይዘርን የተለያዩ ተግባራት ለይቶ በማወቅ፣ የትምህርት ቤቱን መርሀ ግብር /ዕቅድ/ እና በመርሀ ግብሩ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ሚና . . . በመረዳት ነው። በተቋሙ ያሉ ልዩ ልዩ ተግባራት አንዱ በሌላው ላይ የተመሠረቱ እና ርስበርሳዊ ተደጋግፎ ያላቸው፣ በአንዱ ላይ የሚደረግ ለውጥ በሌላው ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር . . . መሆናቸውን ማየትና መገንዘብ፣ ፋይዳቸው ምን እንደሆን በውል መለየት መቻልን ያመለክታል (Griffiths 1979)። ስለሆነም ሱፐርቫይዘሩ ሁኔታዎችን ከጠቅላላው የድርጅቱ ደህንነት አንፃር ቅድሚያ እየሰጠ የሱፐርቪዥን ተግባሩን መከወን ይጠበቅበታል።

**2.6.2 ቴክኒካዊ ክህሎት፡-** Harris (1963:4) "ቴክኒካዊ ክህሎት ከሶስቱ ክህሎቶች ይበልጥ አሥፈላጊውና ዋነኛው የሱፐርቪዥን ባህርይ አካል ነው" በማለት ያሥረዳሉ። ቴክኒካዊ ክህሎት በተለያዩ ዕውቀቶች (በማስተማር፣ በሙያ /Profession/፣ በትምህርታዊ አገልግሎት (Educational service)፣በአንድ የትምህርት ዓይነት ...) ይገለጣል። Haymmon T. and Reymond L (1977) እንዳስረዱት ቴክኒካዊ ክህሎት ያለው ሱፐርቫይዘር የማሥተባበር፣ የማንሳሳት፣ የማቀድ፣ አቅጣጫን የማመላከት፣ የክፍል ምልከታን በተገቢ ሁኔታ የማካሄድ፣ በትምህርት ሂደቱ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ውስብስብ አሰራሮችን የመቆጣጠር . . . ብቃት አለው። Griffiths (1956:9) ይህ ክህሎት ዕውቀትን የመተንተንና ለተለያዩ ጠቀሜታዎች የማዋል ብልሀት እንደሆን ይገልፃሉ።

**2.6.3 የመግባባት ክህሎት**:- ይህ ክህሎት ግጭቶችን ለመፍታት፣ የመማር ማሥተማርን ንሽ ለመፍጠር፣ ከሌሎች ጋር በብቃትና ተደማጭነት ባለው መንገድ ለመግባባት የሚያስችል መሠረታዊ ክህሎት ነው:: ሥራዎች ባግባቡ ሊከናወኑ የሚችሉት ሰዎች ተባብረውና ተደጋግፈው ሊሰሩ በመሆኑ ከሰዎች ጋር የመግባባት ክህሎት ማህበራዊ ዕሴቶችን በመገንዘብና በመተግበር እንዲሁም የሰዎችን ባህርይ በጥልቀት በመመርመር ብቃት ላይ ይመሰረታል (Kinard 1988:15-17):: Griffiths (1956:9) በበኩላቸው ከሰዎች ጋር የመግባባት ክህሎት በቡድኖች ውስጥ ትብብራዊ ጥረት የመገንባት ብቃት እንደሆነ በማስረዳት ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ያጠናክራሉ::

ከላይ የተዘረዘሩት አበይት ክሂሎች ያሉት ሱፐርቫይዘር የሱፐርቪዥን መርሆዎች በመከተል ዓላማን የማሳካት ብቃት ይኖረዋል:: በመማር ማስተማሩ ልምምድ ዕጩ መምህራኑ ሥለትምህረት ቤት ዕውናዊ አውድ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲጨብጡ፣ የራሳቸውን ተግባር ራሳቸው እንዲፈትሹ፣ የገጠሟቸውን ችግሮች በግልፅ አውጥተው እንዲወያዩና ተገቢ የምግበ መረጃ መሥተጋብር እንዲካሄድ፣ በጥቅሉም ዕውቀታቸውና ችሎታቸው ዳብሮ ተፈላጊ የመምህርነት ሥብዕና እንዲኖራቸው ለማገዝ የሱፐርቫይዘሮች አካዳሚያዊና ሥነልቦናዊ ዕውቀት እንዲሁም ይህን ዕውቀት ለተገቢው ግልጋሎት የማዋል ብልሀት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል::

## 2.7 ሱፐርቪዥንና ምልከታ

ምልከታ በማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር የዕጩ መምህራኑን ማስተማርን የመተግበር ሂደት በተመለከተ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ተግባር ነው:: ምልከታ እጩ መምህራኑ ቀጣዩን ሥራቸውን በተሻለ ጥራት ማካሄድ እንዲችሉ መሠረት የሚሆኗቸውን መረጃዎች እንዲያገኙ የሚያደርግ የሥልጠና አካል ነው::

የክፍል ምልከታ ሂደት ሶስት አበይት ደረጃዎች አሉት፤ እነርሱም ቅድመ ምልከታ ውይይት፣ የክፍል ምልከታ፣ ድኅረ ምልከታ ውይይት ናቸው (ፋንታና ዮሴፍ 1997፡45)::

**ቅድመ ምልከታ ውይይት**:- የክፍል ምልከታ ከመካሄዱ በፊት ሥለ ምልከታው ዓላማ፣ ሥለሚካሄድበት ጊዜ እና ሥለትኩረት ነጥቦቹ . . . ሱፐርባይዘሩና ዕጩ መምህሩ የጋራ ግንዛቤ እና ስምምነት የሚይዙበት ውይይት ነው:: በቅድመ ምልከታ ውይይት ሊተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. የምልከታውን ዕቅድ መንደፍ፣

ለ. ምልከታው የሚያተኩርባቸውን ነጥቦች መለየት፣

ሐ. መረጃዎችን ማሶሬፌያ ቅፅ ማዘጋጀት፣

መ. ሶለ ምልከታው ዓላማና ፋይዳ ለመምህሩ ማስረዳት፣

ሠ. የምልከታውን ጊዜ በጋራ መወሰን፣

ረ. የትምህረት ዕቅድን ቅጅ መያዝ፣

ሰ. ዕጩ መምህሩ ሶለምልከታ ያለውን ግንዛቤ መጠየቅ፣

ሸ. ዕጩ መምህሩ ተጨማሪ አስተያየት እንዳለው መጠየቅ . . . (http://gli/berkelay.edu/faculty/observation/doc)::

**ምልከታ**:-ቀጣዩ ተግባር የክፍል ውስጥ ምልከታ ሂደት ነው በአንድ የማስተማር መማር ተግባር ላይ የሚካሄድ ምልከታ ሱፐርቫይዘሩ የመማሪያ ክፍሉን አውዳዊ ሁኔታ፣ የማስተማሩን ሂደት፣ የተማሪዎችን ስብእዊና ትምህርታዊ ፍላጎቶች የሚታኝበትና የሚመረምርበት ሂደት ነው (Pajak 1989):: የክፍል ውስጥ ምልከታ አቢይ ዓላማ የመምህሩንን እጅግ አስፈላጊ ነገሮች በመለየት ማሻሻልና ብቃትን ማሳደግ የሚችሉበትን ቴክኒካዊ ብልሀት ማስገኘት ነው (Harris 1963:93)::

ሱፐርቫይዘሩ የክፍል ምልከታ በሚያካሂድበት ጊዜ የሚከተሉትን ተግባራት ሊፈፅም ይገባል፤

ሀ. በተዘጋጀው የመመልከቻ ቅፅ መሠረት የመማር ማስተማሩን ትግበራ በጥንቀቁ መከታተል፣

ለ. ገንቢ አስተያየቶችንና ጥየቄዎችን መመዝገብ፣

ሐ. አሶፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የመማር ማስተማሩን ሂደት በማይረብሽ መልኩ የተማሪዎችን የግል እና የቡድን ሶራ ተዘዋውሮ መመልከትና መረጃ መያዝ፣

መ. በመጨረሻም መምህሩን ማመሶገን፣

ሠ. በምልከታው ላይ የሚወያዩበትን ጊዜ/ቀጠሮ/ በጋራ መወሰን ይህም ከ48 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲፈፀም የጋራ ስምምነት መያዝ (http://gli/berkelay.edu/faculty/observation/doc)::

**ድህረ ምልከታ**:- ሶስተኛው ደረጃ ደግሞ ድኅረ ምልከታ ውይይት ነው:: ድኅረ ምልከታ ሱፐርቫይዘሩና ዕጩ መምህሩ በምልከታ በተደረሰባቸው መረጃዎች ላይ የሚወያዩበት ነው:: ውይይቱ ዕጩ መምህሩን ወደፊት ሊያደርጉት ወይም ሊያዘጋጁት በሚገባ ጉዳይ ላይ ያተኩራል::

ድህረ ምልከታ ውይይት ሲካሄድ የሚከተሉት ጉዳዮች ልብ ሊባሉ ይገባል፣

ሀ. ውይይቱን ፀጥታ በሰፈነበት ክፍል ወይም ቦታ ማካሄድ፣

ለ. ከመምህሩ የማስተማር ተግባር በፊት የተማሪዎችን ፍላጎት በተመለከተ መወያየት፣

ሐ. መምህሩ በራሥ የመተማመን ስሜት ለማሥረፅና በምግበ መረጃው መስተጋብር ንቁ ተሳታፊ ለመሆን በሥነ ልቡና ዝግጁ እስኪሆን ድረስ በቀጥታ ወደምልከታው ውጤቶች ከመግባት ይልቅ በአጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን በማንሳት በመግቢያነት መጠቀም፣

መ. ዕጩ መምህሩ የራሱን የማስተማር ተግባር በራሱ ዕይታ እንዲገልፅ የቅድሚያ ዕድሉን መስጠት፣

ሠ. በውይይቱ ወቅት ከጠንካራ ጎን መጀመር፣

ረ. ደካማ ጎኖቹ የበዙ ቢሆንም እንኳ ሁሉንም በአንድ ጊዜ አለማቅረብ /አለመዘርገፍ/

ሰ. በትህትናና በወንድማዊ /እህታዊ/ መንፈስ መቅረብ፣

ሸ. በምልከታና በድህረ ምልከታ ውይይት መካከል የረዘመ የጊዜ ክፍተት እንዳይኖር መጠንቀቅ/ወዲያውኑ መፈፀም/፣

ቀ. ዕጩ መምህሩ ራሱን በራሱ እንዲመለከት የሚጋብዙ አንዳንድ መሪ ጥያቄዎችን በሥልት መጠየቅ. . .(Gorton 1988, Gwynn 1984, MOE 2004, Ruth wajnryb 1992)::

በዚህ ንዑስ ርዕስ በአጠቃላይ ምልከታ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉትና በየደረጃዎቹ ሊከናወኑ የሚገባቸውን ሱፐርቫይዘራዊ ተግባሮች ለማሳየት ተሞክሯል:: በማሥከተል ደግሞ በድህረ ምልከታ ውይይት አቢይ ተተኳሪ የሆነውን የምግበ መረጃን ምንነት፣ ፋይዳና አቀራረብ በዝርዝር እንመለከታለን::

## 2.8 ሱፐርቪዥንና ምግበ መረጃ

### 2.8.1 የምግበ መረጃ ምንነት

በሱፐርቪዥን አተገባበር ሂደት ከሚታዩት ክስተቶች አንዱ ምግበ መረጃ ነው:: ምግበ መረጃ የዕጩ መምህራኑን የማሥተማር ብቃት በሚመለከት በሱፐር ቫይዘሮችና በዕጩ መምህራኑ የሚካሄድ የመረጃ ልውውጥ /መሥተጋብር/ ነው:: Gage (1970) እንደገለፁትም እጩ መምህራኑ ከሚፈለገው የትምህርት ግብ አንፃር ራሣቸውን እንዲያሻሽሉና እንዲለውጡ ከሚያሥፈልጉት የመምህራን ትምህርት ተግባራት አንዱ ምግበ መረጃ ነው:: የማሥተማር ልምምዱ በሱፐርቪዥን ሊታገዝ እንደሚገባው ሁሉ የሱፐርቪዥኑ ተግባርም ማሥተማርን የመማር ንሸ የሚፈጥሩ ምግበ መረጃዎችን ሊያካትት ይገባል (Srisvastava and Bose 1978)::

መሀመድ (1999፣24) የ"Ausubel and Robinson (1969)ን ሥራ በመጥቀስ የምግበ መረጃን ምንነት እንደሚከተለው ገልጸታል፣

> ለተማሪ አስተማሪዎች ሥላከናወኗቸው የማሥተማር ተግባራት ተገቢነት ማረጋገጫ የሚያገኙበት፣ ሥህተት ገድፈታቸውን ተመልክተው የሚየሥተካከሉበት፣ የተለያዩ የማሥተማር ክሂሎቶችን እንዴት መካን (Master) እንደሚችሉ ጠንቅቀው የሚረዱበት፣ በመጨረሻም

> ሥለሚያሥተምሩት ትምህርት ከፍተኛ የሆነ በራሥ መተማመን የሚጎናፀፉበት ሂደት ነው::

የቀረበው ጥቅስ በምግበ መረጃና በዕጩ መምህራኑ ብቃት መካከል ቁርኝት መኖሩን ያመላክታል:: ምግበ መረጃ ዕጩ መምህራኑ የማሥተማርን ሥራ ምን ያህል እንደተወጡት የሚየዩበት፤ ድክመት ጥንካሬያቸውን በውል ለይተው ለተሻለ ሥራና ውጤት የሚያበቁ አማራጮችን የሚያገኙበት፤ በመጨረሻም የሥኬት መንገዶችን የሚያገኙበት የስትርቪኝን አተገባበር አካል ነው:: Stones and Morries (1972:148) እንደገለፁትም ማስተማርን በመማሩ ሂደት ላይ አዎንታዊ ሚና የሚጫወት እጅግ አሥፈላጊ ጉዳይ ነው::

### 2.8.2 የምግበ መረጃ ፋይዳ

ምግበ መረጃ በቀድሞውና ተለምዷዊው የቋንቋ ማሥተማሪያ ዘዴ (Traditional language teaching) ሥህተትን እየፈለገ /እየነቀሰ/ በማሣዬት አዎንታዊና አሉታዊ አሥተያየት የሚሠጥበት ነበር:: በዘመናዊው /ተግባቦታዊ/ ቋንቋን የማሥተማሪያ ዘዴ (Communicative language teaching) ግን በተከናወነው ተግባር ላይ ተመሥርቶ ወደ ተሻለ ውጤትና ብቃት ማምራት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመላከቻ ነው (Jacobs et al 1981):: ምግበ መረጃ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች የጎላ አስተዎፅኦ አለው:: ትዕግሥት (1998፡13) የHerisL. (1997)ን ሥራ በመጥቀስ እንደገለፀችው ምግበ መረጃ መምህራን የትምህርቱ ዓላማ ምን ያህል እንደተሳካ ለመረዳት እንዲችሉ የሚያደርግ ሲሆን፤ ተማሪዎች ደግሞ ስህተቶቻቸውን ለማረምና ወደተሻለ ብቃት ለመሸጋገር የሚረዱ መረጃዎችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል::

ዓለም (1998፡25) የሰላም ዓዶች አውደጥናት (1994)ን ጠቅሰው በማስተማር ልምምድ ሂደት ውስጥ የምግበ መረጃን አሥፈላጊነት እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

> . . . እያንዳንዱ ሰው የራሱ ግላዊ ባህርይ አለው:: ለነገሮች የሚሠጠው ምላሽ ከዚሁ ከባህርዩ አኳያ በመሆኑ ለሌሎች ሰዎች ድርጊትና ሀሳብ የሚሰጠው ምላሽ ከራሱ ዳራ፤ ልምድ፤ ዝንባሌ፤ ፍላጎትና አሥተዳደግ አኳያ ሥለሚሆን ብዙ ጊዜ የሌሎችን ሀሳብ ወይም መልዕክት በትክክል ላይረዳ ወይም በተሳሳተ መንገድ ሊገነዘብ ይችላል:: በመሆኑም አድማጫችን ወይም ተመልካቻችን ካልነገረን በቀር የኛን ድርጊት አሥመልክቶ በውስጡ የተፈጠረውን ሥሜት በትክክል ለማወቅ የምንችልበት መንገድ የለም:: በእርግጥ ልንገምት እንችል ይሆናል:: ይሁን እንጂ የአድማጫችን ወይም የተመልካቻችን ስሜት በእሡነቱ ውስጥ ጠልቶ ያለ ነገር ነውና ካልገለፀልንና ካልነገረን በቀር ልንረዳው አንችልም:: ምግበ መረጃ የመሥጠትና የመቀበል ሂደት ባለበት ሁኔታ ግን ይህንን ልዩነት ማጥበብ ይቻላል::

ምግበ መረጃ የተሻለ ውጤት ማምጣት ላይ ያነጣጠረ፣ የመሥራት ፍላጎትን የሚያነሣሣ፣ ብሩህ ተሥፋን አመላካች ሊሆን ይገባል:: Owen et al (1978) እንደገለፁት ከሆነ ጥሩ መሥራት እንደሚችል የሚጠበቅ መሆኑ የተገለፀለት ተማሪ የሥራ ፍላጎቱ ይነቃቃል፣ ባለው የብቃት ደረጃ ጥሩ ስሜት ይኖረዋል፣ በተከታታይ በሚሠጡ ለጣቂ ሥራዎችም የተሻለ ብቃት እንደሚያሳይ ይጠበቃል:: በተቃራኒው በቀጣይ የተሻለ ሥራ ማቅረብ ይችላሉ ተብለው እንደማይጠበቁ የተገለፀላቸውና ገንቢ ምግበ መረጃ ያላገኙ ተማሪዎች ለሥራ አይነቃቁም፣ አይተጉም:: ይልቁንም ሥለራሳቸው ያላቸው ግምት የተዛባ፣ የዝቅተኛነትና ተሥፋ የመቁረጥ ስሜት የሚስተዋልባቸው ይሆናሉ:: በተከታታይ በሚሠጡ ሥራዎችም የበለጠ ደክመው ሊታዩ ይችላሉ:: ሥለሆነም Clifford (1981) እንዳሥገነዘቡት ለበለጠ ሥራና ውጤት በማነሳሳት ፈንታ ተሥፋ አሥቆራጭና ሞራል (ስሜት) ጎጂ የሆኑ ምግበ መረጃዎች ሠልጣኞችን የሚያሸማቅቁና የሥልጠናውን ዓላማ የሚያሠናክሉ ሊሆኑ ሥለሚችሉ ሊወገዱ ይገባል:: ስለዚህም ነው ኅለም (1988፣26) የእነ ማየር (1985)ን ሥራ በማጣቀስ የምግበ መረጃ መኖር ወይም መትረፍረፍ በራሱ ምንም አይፈይድም:: ከሚቀርበው ምግበ መረጃ ተጠቃሚ መሆን እንድንችል የግድ ይህንን ምግበ መረጃ እንዴት እንደምናቀርበውና እንደምንቀበለው ልናውቅ ይገባል በማለት የምግበ መረጃ መሥተጋብር ጥንቃቄ እንደሚያሻው ያሥገነዘቡት::

Clifford (1981) ጥሩ ምግበ መረጃ የሚከተሉት አበይት ፋይዳዎች እንዳሉት ይገልጻሉ፣

ሀ. መነቃቃትን (የመማር ጉጉትን) ይፈጥራል፣ የበለጠም ያጎለብታል::

ለ. የብቃት ደረጃ እያደር እንዲሻሻል ያደርጋል::

ሐ. ምግበ መረጃን መሥጠት አለመቻል ወይም ምግበ መረጃ መስጠትን መቀነሥ ውጤቱ በብቃት ደረጃ ውድቀት ላይ ይታያል::

መ. ምግበ መረጃ ሥለብቃት ደረጃ ብዙመረጃዎችን ሥለሚሠጥ ፈጣን መሻሻልን ለማምጣት ያስችላል::

ሠ. በወቅቱ ወዲያውኑ የሚሠጡ ምግበ መረጃዎች ከራርመው /ዘግይተው/ ከሚሠጡት ምግበ መረጃዎች የበለጠ ውጤታማ ናቸው::

Markos (2000) በበኩላቸው የበርካታ አጥኚዎችን ሥራ (Gilman 1969, Hamer (1972), Butler and Nissan (1986) . . . ) በማጣቀስ እንዳቀረቡት የተለያዩ የምግበ መረጃ ዘዴዎች እንዳሉ ጠቁመው በቀጣይ የተሻለ ውጤት ሊያሥመዘግቡ እንደሚችሉ የሚጠቁም ዝርዝር ምግበ መረጃ (ለምሳሌ ደህና፣ ከዚህ የበለጠ እንደምትሠሪም እርግጠኛ ነኝ፣ የተጠቀምኽባቸው ቃላት ትክክልና ተገቢ ናቸው፣ ነገር ግን መፃፍ

የሚገባህን ያህል አላቀረብክም ለወደፊቱ ይህን እንደምታደርግ እርግጠኛ ነኝ ወዘተ.) የተሠጣቸው ተማሪዎች ምግበ መረጃ ካላገኙት ወይም የተሠጣቸው ምግበ መረጃ አጠቃላይና ድፍን ከሆነባቸው ተማሪዎች የተሻለ ውጤት በቀጣይ ማሳየታቸውን አሥረድተዋል፡፡

ዕጩ መምህራኑ ዕውቀትንና ችሎታን የሚተገብሩትና የቋንቋን ትምህርት የተለያዩ ገፅታዎች ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ሥትራቴጂዎችን ማዳበር ወይም ማሥረፅ የሚችሉት በክፍል ውስጥ ቋንቋን በማስተማር ልምምድና በምግበ መረጃ መስተጋብር ነው (Richards and Nunan 1990:101)፡፡

ምግበ መረጃ ዕጩ መምህራኑ ቀጣዩን ሥራቸውን በተሻለ ጥራት ማካሄድ የሚችሉባቸውን አማራጮች የሚያገኙበት መሥተጋብር ነው፡፡ ብዙ የሥነ ልቦና ምሁራን (Dececco, J. 1968, Milton Ohmer, 1978, Clifford Margaret 1981 . . .) እንደገለፁት በትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚሠለጥኑ ዕጩ መምህራን በሱፐርቫይዘሮች አማካይነት የሚሠጡ ምግበ መረጃዎች እጅግ አሥፈላጊዎች ናቸው፡፡ ይህንን በመገንዘብም በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሀገሮች ያሉ የትምህርት ቤት መምህራንና የዩኒቨርሲቲ አሠልጣኞች/ምሁራን/ ለተማሪዎቻቸው ምግበ መረጃ መሥጠትን ባህላቸው እያደረጉት ይገኛሉ (Page 1964, Hammer 19"2)፡፡

### 2.8.3 የምግበ መረጃ አቀራረብ

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የምግበ መረጃ መሥተጋብር አቢይ ዓላማ የሥራ ተነሳሽነትን መፍጠርና የተሻለ ብቃትን ማሥገኘት ነው፡፡ ይህ ዓላማ ግብ መቺ የሚሆነው ደግሞ ምግበ መረጃው በምልከታ ውጤቶች ላይ የተመሠረተና በመግባባት መንፈስ የሚካሄድ ሲሆን ነው፡፡

ጎለም (1988፣27) የተለያዩ ፀሐፍት ሥራ (የሰላም ጓዶች፣ 1994) Gebhard.G. Jerry (1990), (Goil E. Myers and Michrele T.M (985), Wajnryb R. (1990) . . . በመጥቀስ ምግበ መረጃ ምን ምን ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዳለበት በዝርዝር ካስቀመጧቸው ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፤

ሀ. ምግበ መረጃ በሰዎች ባህሪያ እንጂ በሰዎች ሥብዕና ላይ ሊያተኩር አይገባም፡፡ በሰዎች ስብዕና ላይ የሚያተኩር ምግበ መረጃ በተቀባዩ ላይ ለውጥ ሊያመጣ የማይችል ከመሆኑም በላይ ሰዎችን ሊያስቆጣና ሊያበሳጭ ይችላል፡፡

ለ. ምግበ መረጃ የሚቀርበው በተመለከትነው ወይም ባስተዋልነው ነገር ላይ እንጂ በእኛ ግንዛቤና አተረጓጎም ላይ በፍፁም ሊመሠረት አይገባም፡፡

ሐ. ምግበ መረጃችን የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታ በመተንተን ወይም በማብራራት ላይ እንጂ በራሳችን ግላዊ ዳኝነት ወይም ግላዊ ፍርድ ላይ መመሥረት የለበትም፡፡ . . . የተማሪ አስተማሪዎች በተደጋጋሚ በሱፐርቫይዘራቸው አማካይነት ተግባራቸው

የሚዳኝ፣ ፍርድ የሚሰጥበት ወይም የሚተች ከሆነ ከስትርቫይዘራቸው ጋር በግልፅ ለመወያየትና ለመማማር የሚኖራቸውን ስሜት ሊያደበዝዘው ይችላል።

መ. ምግበ መረጃ በሀሳብ ወይም በመረጃ ላይ ማተኮር አለበት እንጂ፣ በምክር ልገሳ ላይ መመሥረት አይገባውም። . . . ምክር የመስጠት ሂደት አንድን ችግር የማቃለያ ደካማ መንገድ ነው . . . ምግበ መረጃ ተቀባዩን የራሱን አማራጭ እንዳይጠቀም መፈናፈኛ የሚያሳጣ ቀጥተኛ መንገድ ነው።

ሠ. በምግበ መረጃ ልውውጥ ሂደት ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀማችን ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው አቢይ ጉዳይ ነው። . . . የቋንቋ አጠቃቀሙ በተማሪ አስተማሪው ላይ ፀፀትንና ቁጭትን ከሚገልፁ ቃላትና ሀረጎች የፀዳ ሊሆን ይገባል።

ረ. ምግበ መረጃ በተቻለ መጠን ዝርዝርና ውሱን እንጂ አጠቃላይ ይዘት ኖሮት መቅረብ የለበትም። . . . አጠቃላይ በሆነ መንገድ የሚቀርብ ምግበ መረጃ ተፈላጊውን መልዕክት የማስተላለፍና የማስጨበጥ ብቃቱ ይቀንሳል።

ሰ. የቀረበውን ምግበ መረጃ ትክክለኛነት አቅራቢውና ተቀባዩ ሊያረጋግጡት የሚችሉት ቢሆን ይመረጣል። . . . ሁለቱም ወገኖች ማረጋገጫ ካላገኙለት . . . የትኛውንም ወገን ሳይጠቅምና ሳይረዳ እንዲባክን ይሆናል።

ሸ. የምግበ መረጃ ልውውጡ አንዱ ሌላውን እንዳይጫን ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

Stern (1995) በበኩላቸው የምግበ መረጃ ልውውጡ በመግባባት መንፈስ እንዲካሄድና ወደ አንድ ወገን ዳኝነት እንዳያመዝን በምልከታ ውጤት ላይ ብቻ ተመሥርቶ መቅረብ እንዳለበት በመግለፅ ከፍ ሲል የተገለፀውን ሀሳብ ያጠናክራሉ። ስትርቫይዘሩ የዕጩ መምህራኑን ሀሳብን የመግለፅ /የመሣተፍ/ ነፃነት የሚገፍና ደካማ ጎናቸውን ሁሉ በንቂስ በመዘርዘር የሚያሥጨንቃቸው መሆን የለበትም (Grower and Walters 1983)። ዕጩ መምህራን በምግበ መረጃ ልውውጥ በንቃትና በነፃነት የሚሣተፉ ሊሆኑ ይገባል። ይህ እንዲሆንም ስትርቫይዘሩ የሚጠቀምበት ቋንቋ ግልፅና ትህትናን የተላበሠ መሆን ይኖርበታል። እጩ መምህራኑ ምግበ መረጃን ከተለያዩ አካላት (አሠልጣኝ መምህራን፣ ነባር መምህራንና እንዲሁም ከብጤዎቻቸው) እንዲያገኙ ብቻ አይጠበቅም። ከዚህ የበለጠ እጅግ ጠቃሚውና አሥፈላጊው ጉዳይ የራሳቸውን ተግባር ራሳቸው የሚቃኙበትን /የሚገመግሙበትን/ ሁኔታ ማመቻቸት ነው (Hailom 1997)። በጥቅሉ ከምግበ መረጃ ተጠቃሚ ለመሆን በምንነቱ ፋይዳውና አቀራረቡ ላይ ግንዛቤ መውሰድንና በሚፈለገው መልኩ መተግበርን ይጠይቃል።

Stones and Morries (1972) እንደሚሉት ደግሞ በምግበ መረጃ ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው አቀራረቡን ከፍ ሲል በተገለፀው መንገድ በመተግበር ብቻ አይደለም። ይብልጥ አስተማማኝና ተጨባጭ እንዲሆን በመቅረፀ ድምፅ ወይም በቪዲዮ ተቀርፆ ወዲያውኑ የሚሠጥ ሊሆን ይገባል። የመማርማስተማሩን ሂደት በመቅረፀ ድምፅ ወይም በቪዲዮ መቅረፅ ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን ሥራ በተጨባጭ እንዲመለከቱት

ያደረጋል፣ በስትርቫይዘሮችና በዕጩ መምህራኑ መካከል የሚኖረውን የመተማመን ደረጃ ያጠናክራል፣ ምግበ መረጃው ትኩረት ሊሠጣቸው የሚገቡ አበይት ጉዳዮችን በቀላሉ ለመለየትና ለማቅረብ ያመቻል፡፡ የቀረበውን ምግበ መረጃ ትክክለኛነት አትራቢውና ተቀባዩ ሊያረጋግጡት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

እስከአሁን የምግበ መረጃን ምንነት ፋይዳና/አሥፈላጊነት/ አቀራረብ በተመለከተ የቀረቡት ሀተታዎች በስትርቪዥንን አተገባበር ሂደት ውስጥ ገንቢና አዎንታዊ ይዘት ያላቸውን መረጃዎች መሥጠት የዕጩ መምህራኑን ሙያዊ ብቃት ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ያሥገነዝባሉ፡፡ ምግበ መረጃ ለዕጩ መምህራኑ ማሥተማርን የመማር ንሽ በመፍጠር ለተሻለ ሥራና ውጤት የሚበቁበትን መንገድ የሚያመላክት፣ በተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ፣ ተከታታይነት ያለው፣ በግልፅ ቋንቋ መቅረብንና ጤናማ ግንኙነትን የሚሻ . . . መስተጋብራዊ ሂደት መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ሆኖም ከTekeste (1990) ጥናት መረዳት እንደሚቻለው ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ መምህራን ምግበ መረጃን በአግባቡ አይጠቀሙበትም፡፡

## 2.9 የመምህራን ሥልጠናን ሥኬታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ተላውጦዎች

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የሥልጠና መርሃ ግብር ግለሰቦች ተቋማዊውን ርዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው የሚያዘጋጅ ሥርዓታዊ ዘዴ ነው፡፡ መርሃ ግብሩ ውጤታማ እንዲሆን ከምልመላ እስከ ምረቃ ባለው ሂደት በብቃት ሊከናወኑ የሚገባቸው አበይት ጉዳዮች አሉ፤ እነዚህን አበይት ጉዳዮች ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፤

### 2.9.1 የዕጩ መምህራን ምልመላና መረጣ

የሠልጣኞች ብቃት በቅድሚያ የሚጀምረው በአመላመልና በአመራረጥ ሂደቱ ላይ ነው፡፡ የምርጫ መስፈርቱ ለመምህርነት ሙያ ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸውን ተማሪዎች ለመመልመል የሚያስችል ባህርይ ያለው ሊሆን ይገባል (Freedman et al. 1980)፡፡ ምክንያቱም Ivancevich and Glueck (1989) እንዳስገነዘቡት ውጤታማ የሥልጠና መርሃ ግብር በሠልጣኞች ፍላጎትና በተቋሙ ዓላማ ላይ ተመሥርቶ ሠልጣኞችን መምረጥ የሚችል ነው፡፡ በትምህርት ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ሀገሮች ተሞክሮ የሚያመላክተውም ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡ ለምሳሌ በካናዳ በመምህርነት ሙያ ለመሠልጠን የሚገቡ ተማሪዎችን የመመልመልና የመምረጥ ተግባር ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጠው ነው (Dennis Thiessen and Arda Cole (eds) 1993)፡፡

## 2.9.2 ሥርዓተ ትምህርት

ሁለተኛው አሥፈላጊ ግባት ሥርዓተ ትምህርቱ ነው:: የሥርዓተ ትምህርቱ ሁኔታ በሥልጠናው መርሃ ግብር ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው (ICDR 1999:27):: ሥርዓተ ትምህርቱ ዕጩ መምህራኑ ማሥተማርን ሊማሩ በሚችሉበት መንገድ መቀረፅ እንደሚኖርበት ግንዛቤ ሊወሠድ ይገባል:: ተሠጠ (1997፣9) የ"(Brown 1990)"ን ሥራ አጣቅሶ እንደገለፀው፣ "መምህራንን ለማስልጠን ተብለው የሚቀረፁ ኮርሶች ዕጩ መምህራኑ ምን፣ ለምን፣ መቼ እና እንዴት ሊያስተምሩ እንደሚገባቸው በቂ ግንዛቤ ሊያስጨብጧቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው::"

በተለይም በአሁኑ ጊዜ በበርካታ አገሮች በሚገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚሠሩበትንና አቋጭነቱ የታመነበትን የተግባራዊያንን የሥነ ዕውቀት ፍልሥፍና መሠረት ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት መኖር እጅግ አሥፈላጊ ነው "ዕውቀት የሌለው ተግባር ፋይዳ እንደማይኖረው ሁሉ ተግባራዊ የማይሆን ዕውቀትም ፍሬ የለውም" (ተክለሃይማኖት 1992፣13):: ለመምህራን ሥልጠና የሚቀየስ ሥርዓተ ትምህርት ንድፈ ሀሳብንና ተግባርን አዋህዶ ሊይዝ ይገባል:: በንድፈ ሀሳባዊ ክፍሉ ዕጩ መምህራኑ ሥለ ትምህርት መሠረተ ነገሮች፣ ወደፊት እንደሚያስተምሯቸው ሥለሚጠበቁ የትምህርት ዓይነቶች፣ ከተለያዩ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎች ጋር የሚያስተዋውቁና ሥነልቦናዊ ዕውቀት የሚያስጨብጡ የሙያ (Professional) ትምህርቶች ሥለማሠልጠኛ ተቋማት ዓላማ ፋይዳና ልዩ ልዩ ግብአቶች የሚያስገነዝቡ ተቋማዊ ጥናቶች (Institutional study) ግንዛቤ ማስጨበጥ ይጠበቅበታል:: በተግባራዊ ክፍሉ ደግሞ ዕጩ መምህራኑ በተለያዩ አጋር ትምህርትቤቶች እየተመደቡና የሱፐርቫይዘሮችን ዕገዛ እያገኙ ማሥተማርን የሚለማመዱበትና ሙያዊ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ሆኖ ሊቀየስ ይገባል (Hussien T. and Postlethy W. 1994)::

## 2.9.3 የአሠልጣኞች ብቃት

የአንድ ሀገር የሰለጠነ የሰው ኃይል መገኘት በመምህራን ብቃት ላይ ይመሠረታል:: የሥልጠናው ዓላማ ግቡን እንዲመታና ሠልጣኞች በዕውቀት፣ በክሎትና በአመለካከት ብቁ ሆነውእንዲገኙ የአሠልጣኞች አሥተዋፅኦ የጎላ ነው:: በሚገባ የሰለጠኑና ብቃቱ፣ የኃላፊነት ስሜቱ፣ ያላቸው፤ ለሀገር ዕድገት መልካም ርዕይ ያነገቡና ለተለያዩ ጠቀሜታዎች የሚውሉ ግኝቶችንና መፍትሔዎችን በምርምር የሚያወጡ ሰዎች መኖር የአንድ ሀገር የዕድገት ደረጃ በተፈለገው ፍጥነት እንዳጨምር ወሳኝ ናቸው (Teshome 2004:116):: የአሠልጣኝ መምህራን ዕውቀት፣ የማስተማር ብልሀት፣ ለማስተማር ያላቸው መነቃቃት፣ ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት፣ . . . በጥቅሉ ሥልጠናውን ግብ መቼ ለማድረግ የሚያሳዩት ጥረትና ትጋት ብቁ ተተኪ

መምህራን ለማፍራት ከፍተኛ አስተፅኦ አለው:: Okumbe (1998:235) እንደገለፁት የተለያዩ ባለሙያዎች (ሀኪሞች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ኢንጅነሮች፣ የሥራ መሪዎች . . .) በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ አዎንታዊ ሚናዎችን እንዲጫወቱ የሚያስችላቸው ብቃት ላይ መገኘታቸው ከአሠልጣኞቻቸው ብቃት ጋር የተያያዘ ነው::

አሰልጣኝ መምህራን ኃላፊነታቸውን የመወጣት አቅም እንዲኖራቸው ለሚሰጡት ሥልጠና ተመጣጣኝ የሆነ አካዳሚያዊ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል:: ባደጉት ሀገሮች ለምሳሌ በአውሥትራሊያ፣ በካናዳ . . . በየትኛውም ደረጃ ባሉ ትምህርት ቤቶች ያሉ መምህራን የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያም በላይ ያላቸው ናቸው (Murray, Harvey et al 1999, Dennis Thiessen and Arda cole 1993)

Daniel et al. (2002: 8) እንደገለፁት ጥሩ መምህር የሚባለው በውጤታማ ማስተማር ውስጥ የተካተቱ ተግባራትን መፈፀም የሚችል ነው:: ስለሆነም አሠልጣኝ መምህራን የጥሩ መምህር መገለጫ ተግባሮችን የመፈፀም ብቃት ሊኖራቸው ይገባል::

### 2.9.4 ምቹ ሁኔታ (Facility) እና አገልግሎት

የመምህራን ሥልጠና ዓላማ እንዲሳካ ለመማር ማስተማሩ አሥፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች መሟላት፣ ተገቢ አገልግሎት የሚሰጥ አካል መኖር፣ የመልካም አመራር መሥፈን ወሳኝ ነው (World Bank 1994):: በተቋሙ ያሉ የመማሪያ ክፍሎች፣ ቢሮዎች፣ የጉባኤ አዳራሾች፣ ላቦራቶሪዎች፣ መዝናኛ ቦታዎች፣ ስፖርት ሜዳዎች፣ የዕቃ ግምጃ ቤቶች ወዘተ. ለሥልጠናው ሂደት መሳለጥ የየራሳቸው ሚና አላቸው (Mbamba 1992:154)::

ምቹ ሁኔታ ሲባል አንፃራዊ ነው:: ለምሳሌ የካናዳ መምህራን በቂ የገንዘብ (በጀት) እና የማቴሪያል አቅርቦት፣ እጅግ የተመጣጠነና የተመቸ የተማረ መምህር እና የተማረ ክፍል ጥመርታ . . .ባለበት አውድ ውስጥ ያሥተምራሉ :: በታዳጊ ሀገሮች ግን እነዚህ ሁሉ እጅግ ፈታኝ ችግሮች ናቸው (Tekeste 1990):: ሆኖም ትምህርት የሁሉም ነገር መሠረት በመሆኑ በጀት፣ አሥፈላጊ የሥልጠና /መማሪያ/ ማቴሪያሎች እና ሌሎች መማርን የተሳለጠ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንዲሟሉ አቅም በፈቀደ መጠን ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው::

Reed and Bargeman (1995) በበኩላቸው የውጤታማ ሥልጠና መገለጫዎች ናቸው በማለት በተለይ በተቋማቱ ውስጣዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ ጉዳዮችን እንደሚከተለው በዝርዝር ይጠቁማሉ፤

የመምህራን ትምህርት (ሥልጠና) ግብ መቺ የሚሆነው፣

ሀ. ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወላጆች፣ አስተዳደሩ . . . የተስማሙበትና በሚገባ የሚያውቁት በግልፅ የተቀመጠ ዓላማ ሲኖር፣

ለ. ተማሪዎችና መምህራን ሲያስኩት እንደሚችሉ የጋራ ዕምነት የተያዘበት አምንታዊ መርህ ግብር ሲኖር፣

ሐ. ብቁ አሰልጣኝ መምህራን ሲኖሩ፣

መ. ትን፣ ግልፅና ብቁ አመራር ሲኖር፣

ሠ. በተማሪዎች፣ በአሰልጣኞች፣ በአስተዳደር ክፍሎች . . . መካከል ጥሩ እርስ በርሳዊ መግባባትና መተባበር ሲሰፍን፣

ረ. ተማሪዎች በማንኛውም ዕንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሲደረግ፣

ሰ. ትክክለኛና ተገቢ የሆነ ማበረታቻና ሽልማት ሲኖር . . . ነው፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሱት የሥኬት መገኛዎች እንደሚጠቁሙት የመምህራን ሥልጠና ሙያዊ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸውን መምህራን ሊያፈራ የሚችለው መድረሻ ግቡን ሲያመላክት፣ ሊፈፀም የሚችል ተገቢ መርህ ግብር ሲነድፍ፣ ብቁ መምህራንና ትን አመራር ሲኖሩት፣ በሥልጠናው ተዋንያን ዘንድ መግባባትና መተባበር ሲኖር፣ እንዲሁም ጥሩ ለሠራና ውጤታማ ለሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን ማበረታቻ የሚሰጥ ከሆነ ነው፡፡

Livingstone (2001:15-16) ደግሞ በተለይ የማስተማር ልምምድ ውጤታማ የሚሆነው የሚከተሉትን መፈፀም ሲቻል ነው ይላሉ፤

ሀ. ለእያንዳንዱ የማስተማር ልምምድ ደረጃ ግልፅ አላማ ሲኖር፣

ለ. ሰልጤ መምህራኑ እያካሄዱት ላለው የማስተማር ልምምድ መሣካት ተገቢ የሆኑ ግቦች ሲጧሉ፣

ሐ. አሥፈላጊ የሆኑ ግባቶች እያደር በመጠንና በአቅርቦት ሲሻሻሉ፣

መ. በሥልጠናው መርህ ግብር የሰልጤ መምህራኑ፣ የአሠልጣኝ ኮሌጆችና የአጋር ትምህርት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ምን ምን እንደሆነ ተለይቶ ሲቀመጥ፣

ሠ. የተግቱ መመሪያዎች ሲኖሩ እና ለእያንዳንዱ የሥልጠና ተሳታፊ አካል ሲዳረስ፣

ረ. አሰልጣኝ ኮሌጆችና አጋር ትምህርት ቤቶች ፊት ለፊት እየተገናኙ ሲወያዩ፣

ሰ. በዝርዝር የተቀመጠ የመመዘኛ መሥፈርት ሲኖርና የምዘናው ተሳታፊዎች ሚናቸውን ለይተው ሲያውቁ፣

ሸ. ሂደቱን ለመከታተልና ለመገምገም፣ የተገኙ ለውጦችን (መሻሻሎችን) በውይይት ለሁሉም የሥልጠናው ተዋንያን ለማሳወቅ የሚያስችል የድርጊት መርህ ግብር ሲኖር፣

ቀ. የሱፐርቪዥንና የቱቶሪያል ሥራ ባግባቡ ሲካሄድ፡፡

ከፍ ሲል በ"Living stone" የተገለፁት የማስተማር ልምምድ ሥኬታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንዲመለከቱት እያንዳንዱ የማስተማር ልምምድ ደረጃ የራሱ

ዓላማ አለው:: ዕጩ መምህራኑ በየደረጃዎቹ ምን ምን ተግባራትን መፈፀም እንዳለባቸው የሚያመላክቱ መመሪያዎች፣ ቅጾች . . . ያስፈልጋሉ:: ደረጃዎቹ ርስበርሳቸው የተደጋገፉና ወደበለጠ ዕድገት የሚያመሩ ሊሆኑ ይገባል:: ይህ ዕድገት (ለውጥ) በተግባር ሊታይ የሚችለው ደግሞ አሰልጣኝ ኮሌጆችና አጋር ትምህርት ቤቶች እየተደጋገፉና እየተመካከሩ ተባብረው ሲሰሩ ነው::

## 2.10 የቀደምት ሥራዎች ቅኝት

በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚካሄደውን የመምህራን አሠለጣጠን መርሀ ግብር በተመለከተ በርካት ያሉ ጥናቶች ተካሂደዋል:: ጥናቶቹ በየግኝቶቻቸው የሚጠቁሙት የመምህራን ሥልጠናው በርካታ ችግሮች ያሉበት መሆኑን ነው:: ችግሮቹ በመምህራን ምልመላ፣ በንድፈሀሳብና ተግባር ተጣጥሞ፣ በስ·ፐርቪዥንን አተገባበር፣ በምግበ መረጃ አሠጣጥ፣ በማሥተማር ልምምድ ዙሪያ የተከሠቱ ናቸው:: በነዚህ ችግሮች ሳቢያም በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ተፈላጊው ብቃት ላይ የደረሱ መምህራንን ማፍራት ገና ያልተደረሠበት ግብ መሆኑን ጥናቶቹ ያመላክታሉ::

በዚህ ርዕስ ለመዳሠሥ የተሞከረው በተለይ ስ·ፐርቪዥንን፣ ምግበ መረጃንና የማስተማር ልምምድን አስመልክቶ ከተካሄዱ ጥናቶች ውስጥ የተወሠኑትን ነው:: ሥለሆነም አጥኚዎቹን፣ የጥናታቸውን ርዕስ፣ ዓላማ፣ አጠናን ዘዴና ግኝት ባጭሩ ለማመላከት ይሞከራል፣

ኀሰም እሸቱ (1988) "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ድኅሬ የማሥተማር ልምምድ ውይይት የስ·ፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል:: የጥናታቸው አቢይ ዓላማ በትምህርት ክፍሉ የሚስተዋለውን የማስተማር ልምምድና የስ·ፐርቪዥንን አተገባበር መመርመር ነው:: ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጧቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የዕጩ መምህራንን ማስታዎሻ፣ የክሌት ቅጅ፣ የፅሁፍ መጠይቅ፣ የመገምገሚያ ቅፅ ናቸው::

የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን በመጨረሻ የደረሱበት ውጤት ስ·ፐርቫይዘሮቹ በቂ ሥልጠና የሌላቸው፣ ኮሌጁ ለማስተማር ልምምድ ተገቢ ትኩረት አለማድረጉ፣ የማስተማር ልምምዱ በቂ ቅድመ ዝግጅት ያልተደረገበትና ስ·ፐርቫይዘሮቹም ሆኑ የተማሪ አስተማሪዎቹ በዓላማው ላይ ግልፅነት የሌላቸው . . . እንደሆነ አመላክተዋል::

ሌላው የማስተማር ልምምድን በተመለከተ "የፕራክቲክም፣ የማስተማር ልምምድና የስ·ፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሠርተፊኬት መርሀ ግብር" በሚል ርዕስ ጥናት ያካሄደው ተሠጠ አሰፋ (1997) ነው:: ተሰጠ ለጥናቱ መረጃ ማሰባሠቢያ የተጠቀመው የዕጩ መምህራንን ማስታዎሻ፣ የፅሁፍ መጠይቅ፣ ተከታታይ ምልከታንና የመገምገሚያ ቅፅን ነው:: በጥናቱ ውጤትም በተጠቀሰው ኮሌጅ

ያሉት የፕራክቲከም ችግሮች የቅድመ ፕራክቲከም ውይይት አለመኖር፣ የኮሌጅ መምህራንም ሆኑ የአጋር ትምህርት ቤት መምህራን ሥለ ፕራክቲከም ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆን፣ ኮሌጁ የማስተማር ልምምዱን በግባቡ አለመከታተሉ፣ ሱፐርቪዥኑ ገምገማና ምዘና ተኮር መሆኑ የምገበ መረጃ መሠተጋብሩ ባመዛኙ ደካማ ጎንን በማጉላት ላይ ማነጣጠሩ፣ ሠልጣኞች ለሥልጠናው ብቁ አለመሆናቸው . . . እንደሆነ አመላክቷል።

ሂሩት አምሀ (1998) በበኩሏ "በፕራክቲከም ሶስት የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በደቡብ ኢትዮጵያ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 የመምህራን ሥልጠና መርሀ ግብር" በሚል ርዕስ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ዋና ተዋናይ የሆኑ አካላት (ሱፐርቫይዘሮች፣ ዕጩ መምህራንና የአጋር ት/ቤት መምህራን) ያላቸውን ሚና ፈትሻለች። በመረጃ ማሠባሰቢያነትም ቀደም ሲል አቶ ዓለም የተጠቀመባቸውንና በተጨማሪ ቪዲዮ ካሜራ ተጠቅማለች።

በጥናቷ በደረሰችበት ውጤትም ሱፐርቫይዘሮቹ በቂ ሥልጠና የሌላቸው፣ ባመዛኙ መሪዊ ሱፐርቪዥንን የሚጠቀሙና በዚህም የተማሪ አስተማሪዎች ራሥን በራስ የመገምገል ዕድል እንዳጡ፣ የክፍል ምልከታው ግምገማ ተኮር እንዳሆነና ባመዛኙ ደካማ ጎን ላይ ያተኮረና ምክር ሰጋሽ መሆኑን፣ እንዲሁም አሠልጣኝ ኮሌጁና አጋር ት/ቤቶች በትንሾት እንደማይሠሩ . . . አመላክታለች።

በሀሮማር ዩኒቨርሲቲ በሳል ድርሰት ኮርስ (Elam 101) የሚያስተምሩ መምህራንን የምገበ መረጃ አሠጣጥ ለመፈተሽ ጥናት ያካሄደችው ደግሞ ትዕግሥት ታረቀኝ (1998) ነች። የትዕግሥት ጥናት ዓላማ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው ድርሰት የሚሠጡት ምገበ መረጃ በምን ላይ እንዳተኮረና የትኛውን ሥልት እንደተከተለ ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም መምህራኑና ተማሪዎቹ ሥለ ምገበ መረጃው ያላቸውን አተያይ መፈተሽ ነው። ለመረጃ መሰብሠቢያነት የተጠቀመችው የታረሙ ድርሠቶችን፣ ቃለ መጠይቅ፣ የተማሪዎችን አስተያየት ነው። የጥናቱ ውጤት እንደጠቆመው የመምህራኑ ምገበ መረጃ ትኩረት በቅርፅ ላይ፣ የተማሪዎቹ ደግሞ በይዘት ላይ በመሆኑ አልተጣጣመም። ምገበ መረጃው አሉታዊ አስተያየቶች ያመዝኑበታል። የምገበ መረጃው ዓይነትም ትዕዛዛዊ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ኮሌጅ መምህር የሆኑት ዓለማየሁ ተክለማርያም (1997) ደግሞ "የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ" በሚል ርዕስ አንድ የሴሚናር ወረቀት አቅርበዋል። የጽሁፋቸው ዓላማ በትምህርት ቤት ተሞክሮና በማሥተማር ልምመድ ዙሪያ ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች፣ የተለያዩ ምንጮች መሠረት በማድረግ መተንተን ነው። በመረጃ ምንጭነት የተጠቀሙባቸው:- ጥናታዊ ፅሁፎች፣ የምክክር ስብሰባዎች፣ የመምህራን ትምህርት ተቋማት ጉብኝትና ውይይት እንዲሁም

የግል ተሞክሮአቸውን ነው:: በዚህም መሠረት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ዓላማን፣ በአሁኑ ወቅት ያሉትን አበይት ችግሮችና ድክመቶች ከአዲሱ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ገዕታና ጠቀሜታ አኳያ ፈትሸው የማስተማር ልምምድን በተመለከተ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውና ዛሬም ሲሠራበት ያለው አመለካከት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና አፈፃፀም በርካታ ችግሮች ያሉበት ጥራት የለሽ መሆኑን ጠቁመዋል:: ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ በማለትም በተለይ ከአዲሱ የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር በፊት ያለው ያሠለጣጠን ሂደት ያሉበትን በርካታ ችግሮች ዘርዝረዋል፣ ለተግባራዊ ልምምድ የሚሠጠው ጊዜ አናሳ መሆኑ፣ ልምምዱ መምህራን ካቀበሉ ህብረተሰብ ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን መስተጋብር የዘነጋ መሆኑ፣ ከወላጅ ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የህፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ከመቅረፁ አንፃር ጎደሎነት የሚታይበት መሆኑ፣ የማስተማር ልምምዱ ገምገማና ምዘና ላይ ማተኩሩ . . . በጥቅሉ የማሥተማር ልምምዱ በተለምዶ የታቀደውን ለማሟላት ያህል እንጂ የሥልጠናው አቢይ አካል ተደርጎ አለመወሰዱን አመላክተዋል:: ከነዚህ ችግሮች ለመላቀቅም አዲስ የትቤተማል አቅጣጫ መቀረፁንና ያሉትን ፋይዳዎች በዝርዝር አስረድተዋል::

መሀመድ ጀማል (1999) ደግሞ "በኦሮሚያ ክልላዊ መሥተዳድር የሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሃ ግብር የፕራክቲከም ኮርስ አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ "TESSO (2003)" ለ10+3 የመምህራን ሥልጠና መርሃ ግብር ያስቀመጠውን ሀገር አቀፍ መመሪያ መሠረት በማድረግ በኮሌጁ ያለውን የፕራክቲከም አተገባበር ለመፈተሽ ሞክሯል:: የጥናቱ አቢይ ዓላማ የፕራክቲከም ተግበራው ተሳታፊ የሆኑ አካላት (የኮሌጅ መምህራን፣ የትምህርት ቤት መምህራን፣ የተማሪ አስተማሪዎች፣ የኮሌጅና የተባባሪ ትምህርት ቤቶች) "ፕራክቲከም አራት" የተሠኘውን ኮርስ እንዴት እንደተገበሩትና በሂደቱ ያጋጠሙ ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ ማመላከት ነው:: ለጥናቱ የተጠቀመባቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎችም የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የገምገማ ቅፅ ናቸው::

የመሀመድ ጥናት ውጤት ኮሌጁ ከተባባሪ ትምህርት ቤቶች ጋር ቅንጅት ፈጥሮ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ባለማድረጉ የፕራክቲከሙ መርሀ ግብር የተመሠቃቀለ፣ የኮሌጁ መምህራን ለስፐርቪዥን አሉታዊ አመለካከት ያላቸው፣ ዕጩ መምህራኑም በክትትልና እገዛ እጦት አሥፈላጊውን ሙያዊ ክህሎት ያልቀሠሙበት፣ የአጋር ትምህርት ቤት መምህራን አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከፍተኛ ድጋፍ ቢያደርጉም ሥለስፐርቪዥን በቂ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆናቸው የድጋፋቸው ብቃት እና አሥተማማኝነት አጠያያቂ እንደሆነ . . . ያመላክታል::

ከላይ በጥቂቱ የቀረቡት ጥናቶች የደረሱባቸው ውጤቶች ባመዛኙ መመሣሰል ይታይባቸዋል:: ሁሉም የማሥተማር ልምምዱ፣ የስፐርቪዥን አተገባበሩና ምግበ መረጃ አሠጣጡ በተገቢው ሁኔታ አለመካሄዱን ጠቁመዋል::

እነዚህ ጥናቶች በሚያተኩሩበት ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር ርቱዕና ኢርቱዕ ተዛምዶ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ጥናት የተለየ አሠለጣጠን (ገባ-ወጣ-ገባ) በሚተገበርበት ክልል መካሄዱ፣ የጥናቱ ተተኳሪ ኮሌጅ ከተመሠረተ ገና አራተኛ ዓመቱ መሆኑና ብዙም ተሞክሮ ያላዳበረ መሆኑ፣ በስትርክቸርኑም ሆነ በምገበ መረጃ አሰጣጡ ላይ ፍተሻ ያልተካሄደበት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

### 3.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ድኅረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮችን ምግበ መረጃ አሠጣጥ መፈተሽ ነው፡፡ የሚፈትሽውም በተለይ በ1999 ዓ.ም. ሁለተኛው ወሠነ ትምህርት ለዲፕሎማ (10+3) ተማሪዎች የሚሠጠውን «ፕራክቲከም II» የተሠኘ ኮርስ መሠረት አድርጎ ነው፡፡ የዚህ ኮርስ ተሣታፊ የሆኑ የመደበኛውና የማታው መርሃ ግብር የቋንቋ ተማሪዎች ቢኖሩም ይህ ጥናት ተተኳሪ ያደረጋቸው በመደበኛው መርሀ ግብር የሚማሩትን ዕጩ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮቻቸውን ነው፡፡

ከኮሌጁ የፕራክቲከም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው በ1999 ዓ.ም በመደበኛው መርሃ ግብር 235 የቋንቋ ዕጩ መምህራን በ3 ዞኖች በ28 ወረዳዎች እና በ72 ት/ቤቶች ተመድበው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ዕጩ መምህራኑ በአበይትነት የሚሠለጥኑባቸው የትምህርት ዓይነቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የአማርኛ ቋንቋ እና የሥነ ዜጋ ትምህርት ሲሆኑ በፕራክቲከም ቆይታቸው በእነዚህ የትምህርት ዓይነቶች የማስተማር ልምምድ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዕጩ መምህራኑ ለማስተማር ልምምድ የተመደቡባቸው ቦታዎች እጅግ የተበታተኑና የተራራቁ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኮሌጁ መምህራን የሱፐርቪዥን ተግባር የሚያካሂዱት በተመሳሳይ ሳምንትና ቀናት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሁሉንም ዕጩ መምህራን ተተኳሪ ማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ 71(30%) የሚሆኑት በምቾት ናሙና አመራረጥ ተመርጠው በመረጃ ሠጭነት የጥናቱ ተተኳሪዎች ሆነዋል፡፡ ሱፐርቫይዘሮችን በተመለከተ ደግሞ ጥናቱ በድኅረ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምምድ የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሰጡ 21 መምህራንን በመረጃ ሰጭነት አካትቷል፡፡

## 3.2 የመረጃ አሠባሠብ ዘዴ

ይህን ጥናት ለማካሄድ አራት ዓይነት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፤ እነርሱም፦ የዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻዎች፣ መቅረፀ ድምጽ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና የኮሌጁ የፕራክቲከም የግምገማ ቅጽ ናቸው፡፡ በእነዚህ የመረጃ ማግኛ መሳሪያዎች አማካይነት የመረጃ አሠባሠቡ ክንውን እንዴት እንደተካሄደ ቀጥለን እንመለከታለን፤

### 3.2.1 መቅረፀ ድምጽ

ሱፐርቫይዘር እና ዕጩ መምህር በድኅረ የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉትን የምገባ መረጃ መሥተጋብር በመቅረፀ ድምፅ መቅረፅ የዚህ ጥናት መረጃ ማግኛ መንገድ ነው፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ በተሠኘው ንዑስ ርዕስ ላይ እንደተመለከትነው ዕጩ መምህራኑ የተመደቡባቸው አጋር ት/ቤቶች በጣም የተራራቁ፤ የሱፐርቪዥኑ መርሃ ግብርም በተመሳሳይ ቀን የሚካሄድ በመሆኑ እያንዳንዱ ዕጩ መምህር ከሱፐርቫይዘሩ ጋር የሚያደርገውን ድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ለመቅረጽ እጅግ አሥቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም የምቹት ናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም በወቅቱ ከተካሄዱ የአማርኛ ቋንቋ ድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይቶች ውስጥ የዘጠኝ ሱፐርቫይዘሮችና የሃያ አንድ ዕጩ መምህራን ምገባ መረጃ መስተጋብር ተቀርፆአል፡፡

### 3.2.2 የዕጩ መምህራን ማስታወሻ

የዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻ በመረጃ ምንጭነት የተመረጠበት አቢይ ዓላማ የሥልጠናው ተሳታፊ ከሆኑት አካላት በምገባ መረጃ አሠጣጥና በሌሎች ተያያዥነት ካላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ዕውናዊ ገጠመኞችንና የማስተማር ልምምድ ወሉዎችን ገጽታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን ማግኘት ሥለሚያስችል ነው፡፡

በዚህ መሠረት የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት ዕጩ መምህራን በታቀደ ናሙና አመራረጥ 71 ያህሉ ተመርጠው በፈቃደኝነት በማስተማር ልምምድ እና በሱፐርቪዥን አተገባበር ዙሪያ ማስታዎሻ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ ከቀደምት ሥራዎች (ዓለም 1988፤ ተሠጠ 1997፤ ሂሩት 1998) ተሞክሮ በመነሳት ማስታዎሻ ሲይዙ ትኩረት ሊያደርጉባቸው ሥለሚገቡ ጉዳዮች በዝርዝር የሚያሥረዳ፤ "በማስተማር ልምምድ ወቅት የማስታዎሻ አያያዝ መመሪያ" የሚል ጽሁፍ ተዘጋጅቶ በነፍስ ወከፍ

እንዲደርሳቸው ተደርጓል። ግልጽ ባልሆኑላቸው ጉዳዮች ላይም በጥናቱ አዘጋጅ፣ እንዲሁም አጥኚው መድረስ ባልቻለባቸው በራቁ ት/ቤቶች በዓላማውና አሠራሩ ላይ ገንዛቤ በጨበጡና በተወከሉ የኮሌጁ መምህራን አማካይነት ማብራሪያ እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚህ መሠረትም ዕጩ መምህራኑ የዓፉትን ማስታዎሻ በወቅቱ እንዲያስረክቡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በአጠቃላይ 120 ያህል ማስታዎሻዎች ተሠብስበዋል።

### 3.2.3 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ በሌሎች የመረጃ ማሠባሠቢያ መንገዶች ያልተደረሰባቸውን መረጃዎች ለማሟላት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል በሚል ዕምነት የተመረጠ ነው።

መጠይቁ በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ላይ ተመሥርቶ ከተዘጋጀ በኋላ ዕጩ መምህራኑና ሱፐርቫይዘሮቻቸው ለየብቻ እንዲሞሉት የተደረገ ሲሆን፣ በትንተና ወቅት ገን በተመሣሣሪና ተደጋጋፊ መልኩ ተቀናጅቶ የቀረበ ነው። በዚህ መሠረትም የማስተማር ልምምዱ ሂደት ተሳታፊ እና የዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት 235 ዕጩ መምህራን መካከል ሰላሳ በመቶ የሚሆኑት የታቀደ የናሙና አመራረጥን መሠረት በማድረግ በየተመደቡበት ት/ቤት ባላቸው ብዛት መሠረት ተመርጠው እንዲሞሉ ተደርጓል። ሱፐርቫይዘሮችን በተመለከተም በድኅረ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምምድ ወቅት ምገበ መረጃ የሰጡ 21 መምህራን መጠይቅ ሞልተዋል። ለመጠይቁ ሥርጭትና ስብሰባ የሱፐርቫይዘሮችና የአጋር ት/ቤት መምህራን በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ አስተዋጽዖ የጎላ ነው። በመሆኑም የተበተኑት 71 (ሰባ አንድ) የጽሁፍ መጠይቆች በሙሉ ተሠብስበዋል።

የጽሁፍ መጠይቁ ዝግና ክፍት ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን፣ በዝግ የአጠያየቅ መንገድ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቁጥር የተወከሉ አምስት አማራጮች ቀርበዋል። እነርሱም፡ 5 = በጣም እስማማለሁ 4 = እስማማለሁ፣ 3= ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 2 = አልስማማም፣ 1 = በፍፁም አልስማማም የሚሉ ናቸው።

### 3.2.4 የገምገማ ቅጽ

ኮሌጁ በማስተማር ልምምድ ወቅት የዕጩ መምህራኑን ሙያዊ ብቃት ለመገምገም የሚጠቀምበት ቅጽ የዚህ ጥናት የመረጃ ማግኛ መሣሪያ ነው።

ቅፁ በሠንጠረዥ መልክ የተዘጋጀ ሲሆን ሦስት አበይት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል የዕጩ መምህሩን ሥም፣ ምድብ ቦታ (ት/ቤት)፣ ግምገማ የተካሄደበትን ዕለትና ክፍለ ጊዜ፣ የግምገማውን ማካሄጃ ወሠነ ትምህርትና ፕራክቲክም የሚያመለክት አጠቃላይ መረጃ ሰጭ ነው። ሁለተኛው ክፍል በሁለት ንዑሳን ክፍሎች የተፈረጀ ሲሆን የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል የትምህርት ዕቅዱን ዓላማ ግልጽነትና ተተግባሪነት፣ ዓላማን ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባሮች ሥለመካተታቸው፣ በትግበራው ላይ የተማሪዎች ተሳትፎ ጎልቶ እንዲታይ ተገቢ የጊዜ ድልድል ሥለመካሄዱ፣ ተግባራቱ በዕቅዱ መሠረት ስለመጠናቀቃቸው የሚገመገምበት ነው። ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ደግሞ በክፍል ውስጥ ማስተማርን በመተግበሩ ሂደት ዕጩ መምህሩ በሚያስተምረው ትምህርት ላይ ያለው በቂ ዕውቀት፣ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀሙ፣ የተለያዩ ተግባራትን ማሠራቱ፣ ተማሪዎችን ማሳተፉና ማበረታታቱ፣ ተገቢ ሚዲያ እና ምሳሌ መጠቀሙ፣ የምዘና ሥልቱ የሚገመግምበት ነው። በሦስተኛው የግምገማ ቅፁ ክፍል ዕጩ መምህሩ ከት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ስላለው ግንኙነት፣ የት/ቤቱን ደንብና ሥርዓት ስለማክበሩ፣ በተለያዩ ኮሚቴዎችና ክበባት ስለሚያደርገው ተግትሮ ሥለ ዶክመንት አያያዙና የመምህርነትን ሥነምግባር ስለመላበሱ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችሉ መስፈርቶች ተቀምጠዋል።

ይህ ጥናት በተለይ የሚያተኩረው በድኅረ የማስተማር ልምምድ ምግበ መረጃ አሰጣጥ ላይ በመሆኑ ከዚሁ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው የግምገማ ቅፁ ሁለተኛ ክፍል ላይ ሱፐርቫይዘሮች (ገምጋሚዎች) ሥለ ዕጩ መምህራኑ ሙያዊ ብቃት የሠጧቸውን አስተያየቶችና የግምገማ ውጤቶች ደጋፊ መረጃዎች አድርጎ ወስዷል።

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ክፍ ሲል በተመለከትናቸው የመረጃ ማሠባሠቢያ መሣሪያዎች የተጠናቀሩት መረጃዎች የተተነተኑት አሀዛዊና አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴዎችን በመጠቀም ነው። በዚሁ መሠረት ከዕሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች አሀዛዊ የአተናተን ዘዴን መሠረት በማድረግ በቁጥር 5 እና 4 የተወከሉት አዎንታዊ መልሦች አንድ ላይ እየተሠሉ ሲደመሩ፣ በቁጥር 2 እና 1 የተወከሉት አሉታዊ መልሦችም እንዲሁ አንድ ላይ እየተሠሉ ተደምረው ተቀምጠዋል። በቁጥር 3 የተወከለው ግን ከየትኞቹም

ሳይቀላቀል ለብቻው እየተሠላ ተደምሮ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ከየምላሾቹ የተገኙ የድምር ውጤቶችም ወደ መቶኛ እየተለወጡ ተተንትነዋል፡፡

ከመቅረፀ ድምፅ፣ ከማስታዎሻና ከግምገማ ቅፅ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ ዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በአራቱም የመረጃ ማግኛ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች የተቀመጡት እርስ በርሥ ተመሣካካሪ በሚሆኑበት መንገድ ተሰናስለው /ተቀናጅተው/ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተና

### 4.1 የጥናቱ ተተኳሪዎች ዳራ

#### 4.1.1 ዕጩ መምህራን

በዚህ ጥናት በመረጃ ሰጭነት ተተኳሪ የሆኑት ሰባ አንድ ዕጩ መምህራን በፅሑፍ መጠይቅ ላይ ባሠፈሩት መሠረት የፆታ፣ የዕድሜና የቅድመ ኮሌጅ ሥልጠና የማስተማር ልምዳቸው የሚከተለውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ 1፡ የተተኳሪ ዕጩ መምህራን ዳራ፣

| ፆታ | | ዕድሜ | በቅድመ ኮሌጅ ስልጠና የማስተማር ልምድ |
|---|---|---|---|
| ሴት | 50 | 16 - 21 | - |
| ወንድ | 21 | 16 - 27 | - |

በሠንጠረዥ 1 ከሠፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት ዕጩ መምህራን ውሥጥ 50 (70.4%) ሴቶች ሲሆኑ 21 (29.6%) ደግሞ ወንዶች ናቸው። ከዕድሜ አንፃር ደግሞ ከ16-27 ዓመት ባለው ክልል ውስጥ ሲሆኑ፣ ሁሉም በኮሌጁ የ10+3 መርሀ ግብር ከመሠልጠናቸው በፊት የማስተማር ልምድ የላቸውም።

በኮሌጁ የሠርቲፍኬትም ሆነ የዲፕሎማ መርሀ ግብር እንዲሠለጥኑ ሠፊ ዕድል የሚሠጠው ለሴቶች ነው። በዚህ መሠረት በ1998 ዓ.ም. በቋንቋ ትምህርት ክፍል በዲፕሎማው መርሀ ግብር ገብተው ከሚሠለጥኑ 235 ዕጩ መምህራን ውሥጥ 171 (72.7%) ሴቶች ናቸው። ከፍ ሲል የተመለከትነው የተተኳሪ ሴት ዕጩ መምህራን ቁጥር ልቆ የታየውም በዚሁ ምክንያት ነው።

#### 4.1.2 የተተኳሪ ሱፐርቫይዘሮች ዳራ

በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ 87 መምህራን አሉ። ከእነዚህ መምህራን መካከል 60ዎቹ በ1999 ዓ.ም. በፕራክቲከም II መርሀ ግብር ዕጩ መምህራኑ ወደየተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች በመሄድ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ሠጥተዋል። ከእነዚህ ውስጥ በወቅቱ በአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ልምምድ ያካሄዱ ለነበሩት ዕጩ መምህራን የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሠጡ 21 ሱፐርቫይዘሮች ለቀረበላቸው የፅሁፍ መጠይቅ በሠጡት

መልስ መሠረት የዕድሜ፣ የፆታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥልጠና መስክና ያገልግሎት ዘመን ሁኔታ የሚከተለውን ይመስላል፤

ሠንጠረዥ 2፡- የተተኳሪ ሱፐርቫይዘሮች ዳራዊ መግለጫ

| ሱፐር ቫይዘር | ዕድሜ | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የሥልጠና መሥክ | አገልግሎት በኮሌጅ | ከኮሌጅ ወጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 51 | ወ | የመጀመሪያ ድግሪ | ሒሳብ | 3 | 21 |
| 2 | 27 | ወ | " | ፊዚክስ | 3 | - |
| 3 | 25 | ወ | " | ባዮሎጂ | 3 | - |
| 4 | 37 | ወ | " | ፔዳጎጂ | 2 | 13 |
| 5 | 39 | ወ | ሁለተኛ ዲግሪ | ካሪኩለም | 4 | 12 |
| 6 | 27 | ወ | የመጀመሪያ ዲግሪ | ጂኦግራፊ | 3 | - |
| 7 | 47 | ወ | " | አማርኛ | 2 | 24 |
| 8 | 30 | ሴ | " | አማርኛ | 3 | 3 |
| 9 | 25 | ወ | " | ታሪክ | 3 | - |
| 10 | 45 | ወ | " | ባዮሎጂ | 2 | 18 |
| 11 | 30 | ሴ | " | እንግሊዝኛ | 1 | 5 |
| 12 | 49 | ወ | " | እንግሊዝኛ | 2 | 28 |
| 13 | 48 | ወ | ሁለተኛ ዲግሪ | እንግሊዝኛን የማስተማርሥነ ዘዴ | 2 | 24 |
| 14 | 42 | ወ | የመጀመሪያ ዲግሪ | እንግሊዝኛ | 3 | 16 |
| 15 | 32 | ወ | " | ሳይኮሎጂ | 2 | 8 |
| 16 | 30 | ወ | " | አማርኛ | 3 | 5 |
| 17 | 47 | ወ | " | እንግሊዝኛ | 2 | 23 |
| 18 | 30 | ወ | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ የማስተማርሥነ ዘዴ | 5 | 4 |
| 19 | 29 | ወ | የመጀመሪያ ዲግሪ | ታሪክ | 3 | 6 |
| 20 | 32 | ወ | " | የሥነ-ጽሁፍ ማጉልመሻ | 3 | 7 |
| 21 | 48 | ወ | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛየማስተማር ሥነ ዘዴ | 2 | 22 |

ሠንጠረዥ ሁለት እንደሚያመለክተው ከሃያ አንዱ ሱፐርቫይዘሮች አሥራ ዘጠኙ ወንዶች፣ የቀሩት ሁለቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው።የዕድሜ ክልላቸውም ከ25-51 ዓመት ነው:: የትምህርት ደረጃቸውን በተመለከተ አራቱ ሁለተኛ ዲግሪ ሲኖራቸው ቀሪዎቹ /17/ የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ናቸው። ኮሌጁ ከተመሠረተ ገና አራተኛ ልደቱን ማስቆጠሩ ስለሆነ የሱፐርቫይዘሮቹ የአሠልጣኝነት ዘመንም ከ2-4 ዓመት ብቻ ነው:: በ1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግን ከ3-28 ዓመት አገልግሎት አላቸው። በአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉ ዕጩ መምህራንን ለመርዳትና ለመገምገም ከተመደቡትና የዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት ሱፐርቫይዘሮች በአማርኛ ቋንቋ የሠለጠኑት አምስት ብቻ ናቸው:: ቀሪዎች /16ቱ/ የእንግሊዝኛ

ቋንቋ እና የሌሎች የማህበራዊ ሳይንሥና የተፈጥሮ ሣይንስ የትምህርት መስኮች ምሩቃን ናቸው፡፡ ሱፐርቫይዘሮቹ የማስተማር ልምምድንና ሱፐርቪዥርንን በተመለከተ የወሠዱት ሥልጠና ወይም ወርክሾፕ እንዳለ ለማረጋገጥ የፅሁፍ መጠይቅ ቀረቦላቸው ማናቸውም ምንም ዓይነት ሥልጠና እንዳልወሠዱ ገልፀዋል፡፡ በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ሥር እንደተብራራው ሱፐርቪዥርን የማስተማር ልምምድን ሂደት በመከታተል ተጨባጭ መረጃዎችን አሠባሥቦ ለተሻለ ሥራና ውጤት የሚያንሳሳ ምግበ መረጃ መስጠትን የሚጠይቅ ሙያ ነው፡፡ ይህንን ሙያ ለትምህርት ዓላማ ግብ መምቻ መሣሪያነት መጠቀም የሚቻለው ደግሞ ሥለዓላማውና አተገባበሩ በቂ ግንዛቤ ያለው ባለሙያ ሲኖር ነው፡፡ ስለሆነም ሱፐርቫይዘሮቹ ተግባራቸውን በአግባቡ ማከናወን እንዲችሉ ሥልጠናው ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

አዲሡ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ10+3 ለሚሠጥ ስልጠና ያስፈልጋል ብሎ ካሥቀመጠው የትምህርት ደረጃ አንፃር ሲታይ ሱፐርቫይዘሮቹ በተገቢው ብቃት ላይ ናቸው ለማለት አያሥደፍርም፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ሁሉም መምህራን በከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም እንዲሠለጥኑና በየዓመቱም ከየትምህርት መሥኩ መምህራን እየተመረጡ የከፍተኛ ትምህርት /ሁለተኛ ዲግሪ/ እንዲከታተሉ እየተደረገ መሆኑን ከኮሌጁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በማስከተል ደግሞ ሱፐርቫይዘሮቹ ሥለዘመናዊ ቋንቋን የማስተማር ሥነ ዘዴ ያላቸውን ግንዛቤ እንመለከታለን፤

ሠንጠረዥ 3፡ ሱፐርቫይዘሮች ሥለ ዘመናዊ ቋንቋን የማስተማር ሥነዘዴ ያላቸው ግንዛቤ

<table>
<tr><th rowspan="2">ተ.ቁ</th><th rowspan="2">ጥያቄ</th><th colspan="6">የመላሾች ብዛት</th></tr>
<tr><th>5</th><th>4</th><th>3</th><th>2</th><th>1</th><th>ያልሞሉ</th></tr>
<tr><td>12</td><td>ሥለ ዘመናዊ ቋንቋን የማስተማር ሥነዘዴ ያለኝ ግንዛቤ ለሱፐርቪዥርን ሥራዬ በቂ ነው፡፡</td><td colspan="2">6</td><td>3</td><td colspan="2">10</td><td>2</td></tr>
</table>

የዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑ ሃያ አንድ ሱፐርቫይዘሮች ስድስቱ አዎንታዊ መልስ ሲሠጡ፤ አሥሩ አሉታዊ፣ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሶስቱ ደግሞ ቁርጠኛ መልስ ለመስጠት አልቻሉም፡፡ ቀሪዎቹ ሁለቱ ግን ምላሽ አልሠጡም፡፡ መረጃው ብዙዎቹ ሱፐርቫይዘሮች አሉታዊ መልስ መሥጠታቸውን ያሣያል፡፡ ስለዘመናዊ ቋንቋን የማስተማር ሥነ ዘዴ በቂ ግንዛቤ የሌለው ሠው ቋንቋን የማስተማር ሂደት በትክክል ገምግሞ ተገቢውን ምግበ መረጃ ይሠጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ስለሆነም ይህንን ክፍተት የመሙላትና የማስተካከሉ ተግባር በእጅጉ ሊታሠብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል ሱፐርቫይዘሮቹ ለዕጩ መምህራኑ ተገቢ የሱፐርቪዥርን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ብቃት እንዲያገኙ ሥልጠና እንደሚያስፈልጋቸው በፅሁፍ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ የሠጡት፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- የሱፐርቫይዘሮች የተጨማሪ ሥልጠና ፍላጎት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5/4 | 3 | 2/1 | ያልሞሉ |
| 9 | የዕጩ መምህራኑን የማስተማር ልምምድ ለመከታተል የሚያስችል ዘዴና ብቃት ለማግኘት የሱፐርቪዥን ሥልጠና መሠጠት አለበት፡፡ | 19 | 2 | - | |

የሱፐርቪዥን ሥልጠናን አስፈላጊነት በተመለከተ አሥራ ዘጠኙ ሱፐርቫይዘሮች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሁለቱ ግን በአስፈላጊነቱ ላይ ቁርጠኛ መልሥ የላቸውም፡፡ በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተመለከትነው ሱፐርቪዥን የተለያዩ አቀራረቦችና መርሆዎች ያሉት፣ የማስተዋል፣ የቴክኒክና የመግባባት ክህሎትን የሚጠይቅና ማስተማርን የመማር ንሽ የሚፈጥር ምገበ መረጃ መሥጠትን የሚሻ የሥልጠና አካል ነው፡፡ ሥለሆነም ሱፐቫይዘር ሆኖ የዕጩ መምህራኑን የማስተማር ልምምድ እየተከታተለ ተገቢውን ዕገዛ እንዲያደርግ የተመደበ መምህር በሱፐርቪዥን ምንነትና አተገባበር ላይ በቂ ግንዛቤ እና ችሎታ ያለው ሲሆን ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ዕጩ መምህራኑ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ማስተማርን የመማር እና የመተግበር ብቃት እንዲኖራቸው የሚያግዝ ተገቢ ምገበ መረጃ ያገኛሉ ብሎ መገመት እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

## 4.2. የማስተማር ልምምዱና የዕጩ መምህራኑ ግንዛቤ

Azeb(1997,48) እንደገለፁት የማስተማር ልምምድ ምልከታ እና ማስተማር የተሠኙ ሁለት አበይት ክፍሎች አሉት፡፡ እነዚህን ክፍሎች በሚገባ ለመተግበር ዕጩ መምህራኑ ስለማስተማር ልምምዱ ዓላማና ተግባር ግልፅ ግንዛቤ ሊጨብጡ ይገባል፡፡ ይህን በተመለከተ ዕጩ መምህራኑ በፅሁፍ መጠይቅ ለቀረቡላቸው ሁለት ጥያቄዎች የሠጧቸውን መልሶች እንመልከት፤

ሠንጠረዥ 5፡- ዕጩ መምህራኑ ሥለማስተማር ልምምዱ ያላቸው ግንዛቤ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5/4 | 3 | 2/1 | ያልሞሉ |
| 1 | ሥለ ማስተማር ልምምድ ዓላማና ተግባር በቂ ግንዛቤ አለኝ፡፡ | 63<br>88.7% | 5<br>5% | 3<br>4.2% | |
| 11 | የማስተማር ልምምዱ ቀዳሚ ክፍል የሆነውን ምልከታ ሳካሂድ በምን በምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለብኝ በቂ ግንዛቤ አለኝ | 52<br>73.2% | 10<br>14.1% | 9<br>12.7% | |

ተናግሬ በትምህርቱ ሂደትም የዕለታዊ ዕቅዱን እንድሠጣቸው ጠይቀውኝ ተነጋግረን ነው መምህሩ የገቡት።

አስረጅ 2፦ ለፕራክቲከም ከመውጣታችንና የማስተማር ልምምድ ከማካሄዳችን በፊት የኮሌጁ ምክትል ዲንና የፕራክቲከሙ አስተባባሪ ሠፊ ገለፃ በማድረግና የተለያዩ ማሳሰቢያዎችን በመስጠት አወያይተውናል። በውይይቱም በተለይ የት/ቤቱን ደንብና ሥርዓት ማክበር እንደሚገባንና ጥሩ ሥነ ምግባር ማሣየት እንደሚጠበቅብን ምክር ለግሰውናል። ይህ ካልሆነ ግን ከሥልጠናው እስከመሠናበት የሚያደርስ እርምጃ ሊወሠድ እንደሚችል አሥጠንቅቀውናል።

የቀረቡት አስረጆዎች እንደሚጠቁሙት ዕጩ መምህራኑ ሱፐርቫይዘሮቻቸው በምልከታው ጊዜ ሥለምን እንደሚያስተምሩ እንዲነግሯቸውና ዕለታዊ የትምህርት ዝግጅታቸውን /ዕቅዳቸውን/ እንዲያሣዩአቸው ያቀረቡላቸውን ጥያቄ፣ እንዲሁም የፕራክቲከሙን መርሀ ግብር በተመለከተ በኮሌጁ የተደረገላቸውን ገለፃ እንደ ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት ቆጥረውታል። የቅድመ ማስተማር ልምምድ ምልከታ ውይይት ዓላማና መገለጫ ግን ይህ አልነበረም። በምዕራፍ ሁለት በቀረበው የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ላይ እንደተገለፀው ዓላማው ዕጩ መምህራኑ፣ ሱፐርቪዥኑን የሚካሄደው የእነሡን የማስተማር ሂደት በመከታተልና በመመርመር ወደ ተሻለ ብቃት የሚያመሩበትን መንገድ የሚያመለክቱ ምግበ መረጃዎችን ለመስጠት መሆኑን ተረድተው ሥነ ልቡናዊ ዝግጅት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ ዕጩ መምህራኑ ስለቅድመ የማስተማር ልምምድ ምልከታ በቂ ግንዛቤ የላቸውም ለማለት ያስደፍራል። ከፍ ሲል በሠንጠረዥ ሰባት ለቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ መልስ የሠጡ ዕጩ መምህራን ቁጥር ብልጫ ሊያሣይ የቻለበት ምክንያትም ዕጩ መምህራኑ ስለ ቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት ያላቸው የግንዛቤ ዕጥረት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህ ግምት ግን ሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን የቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት የማካሄድ ባህልን ገና በወጉ እንዳላዳበሩ ያመለክተናል እንጂ ሙሉ በሙሉ ውይይቱ አልተካሄደም ወደሚል ማደማደሚያ አያሥኬደንም። ለዚህም የሚከተሉትን አሥረጅዎች ከዕጩ መምህራኑ ማስታወሻዎች መጥቀስ ይቻላል።

አሥረጅ 1. ከሱፐርቫይዘራችን ጋር የክፍል ውስጥ ምልከታ ከመካሄዱ በፊት ውይይት አካሂደን ነበር። በውይይቱም ሱፐርቫይዘሩ፣ "እንዳትፈሩ፣ እንዳትጨነቁ የምልከታው ዓላማ እናንተን ለመጣል ሣይሆን በምን

ደረጃ እንዳላችሁ ለማወቅ ነው" በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ እነጋገረውናል።

አሥረጅ 2. ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት አድርገን ነበር። የተወያየነውም በትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ላይ ነበር። ይህም አሥቀድሜ ጥንቃቄ እንዳደርግና ማስተካከል ያለብኝን እንዳውቅ ከፍተኛ ጥቅም ሠጥቶኛል።

የመጀመሪያው አሥረጅ ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት በሱፐርቪዥን ዓላማ ላይ ሊኖር የሚችለውን ብዥታ ከማስወገድና በራስ የመተማመን ሥሜትን ከማጎልበት አንጻር ለዕጩ መምህራኑ እንደጠቀማቸው ያመለክታል። አሥረጅ ሁለት ደግሞ ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት መካሄዱ በትምህርት ዝግጅትና አቀራረብ ላይ ትኩረት ሊሠጧቸው ስለሚገቡ ጉዳዮች በቅድሚያ ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ የጠቀማቸው መሆኑን ያመለክታል።

በአጠቃላይ ሲታይ የቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት በክፉል እንጂ በተሟላ መልኩ እንዳልተተገበረ የቀረቡት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቅድመ የማስተማር ልምምድ ሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን በሱፐርቪዥኑ ዓላማ ላይ የጋራ ግንዛቤና ስምምነት እንዲይዙና ዕጩ መምህራኑም ውጥረት (ጭንቀት) እንዳይሰማቸው የማድረግ ጠቀሜታ አለው። ሥለሆነም ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ከዚህ በማስከተል ደግሞ በማስተማር ልምምዱ ሂደት ያለውን የሱፐርቪዥን ትግበራ እንመልከት።

### 4.3.2 የሱፐርቪዥን ትግበራ

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንደተገለፀው ከቅድመ ማስተማር ልምምድ ውይይት ቀጥሎ ያለው ሱፐርቪዥናዊ ተግባር በክፍል ውስጥ የማስተማር ሂደት ምልከታ ነው። የዚህ ምልከታ አቢይ ዓላማም የዕጩ መምህራኑን የማስተማር ልምምድ ሂደት በመከታተል ሊሻሻሉ ወይም ሊጠናከሩ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ተጨባጭ መረጃዎችን መሠብሠብ ነው። ይህ አላማ ትኩረት ተሰጥቶት በተግባር መተርጎም ያለበት ሥለመሆኑ ሱፐርቪይዘሮቹ ያላቸውን አመለካከት እንዲገልፁ ቀርቦላቸው ለነበረው ጥያቄ የሠጡትን መልስ ቀጥለን እንመልከት።

ሠንጠረዥ 8፦ የሱፐርቪዥን አተገባበር አቅጣጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5/4 | 3 | 2/1 | ያልሞሉ |
| 15 | በትብብት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ የዕጩ መምህራኑ ብቃት የቅድሚያ ትኩረት አግኝቶ ሊገመገምና ሊመዘን ይገባል። | 21 | - | - | - |

መረጃው እንደሚያሣየው የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ሱፐርቫይዘሮች በሙሉ በማስተማር ልምምዱ ሂደት የዕጩ መምህራኑ የማስተማር ብቃት ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት ሊገመገምና ሊመዘን ይገባዋል ባዮች ናቸው።

መረጃው ሱፐርቪዥኑ የቅድሚያ ትኩረቱ ግምገማና ምዘና መሆኑን ያሣያል። ይህ ደግሞ ከሱፐርቪዥኑ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተገቢነት ያለው ሆኖ አይገኝም። በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ውስጥ እንደተገለፀው ሱፐርቪዥን፤ ዕጩ መምህራኑ የትምህርት ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎችን ተግባራዊ የማድረግ ብቃት እንዲኖራቸው እገዛ የሚያገኙበት የሥልጠና አካል ነው። በመረጃው ላይ እንደታየው የሱፐርቪዥኑ ቅድሚያ ትኩረት ግምገማ ከሆነ ግን ሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን ግልፅ ውይይት እንዳያካሂዱ እንቅፋት ይፈጥራል። ዕጩ መምህራኑ ዘና ብለው ሀሳባቸውን እንዳይገልፁና ጭንቀት እንዲሠማቸው ሊያደርግ ይችላል። ሥለሆነም በሱፐርቪዥን ተጠቃሚ ለመሆን የአተገባበሩ አቅጣጫ ሊስተካከል ይገባል። ከዚህ በማስከተል ደግሞ ዕጩ መምህራኑ የሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚያገኙት የማስተማር ልምምድ በሚያካሂዱበት የትምህርት ዓይነት ከሠለጠነ ባለሙያ እንደሆነ ለማረጋገጥ ቀርቦላቸው ለነበረው ጥያቄ የሠጡትን ምላሽ እንመለከታለን፤

ሠንጠረዥ 9፦ ዕጩ መምህራኑ በሙያው የሠለጠነ ሱፐርቫይዘር ማግኘት ሥለመቻላቸው።

| ተ ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5/4 | 3 | 2/1 | ያልሞሉ |
| 29 | ሱፐርቫይዘሬ የማስተማር ልምምድ በማደርግበት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሠለጠነ ነው። | 25<br>35.2% | 10<br>14% | 36<br>50.7% | |

በሠንጠረዥ ዘጠኝ ላይ የሠፈረው መረጃ እንደሚያመለክተው 36 (50.7%) ዕጩ መምህራን የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉበት የትምህርት ዓይነት የሠለጠነ ሱፐርቫይዘር አልተመደባቸውም። ይህን ዕድል ያገኙት 25 (35%) ብቻ ናቸው። 10 (14%) ግን ቁርጠኛ መልሥ አልሠጡም።

በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ላይ እንደተብራራው የማስተማር ልምምድ ዓላማ ዕጩ መምህራኑ በኮሌጁ ቆይታቸው የቀሠሙትን ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀት በተግባር የመተርጐም ብቃት እንዲያገኙ ማሥቻል ነው። ይህ ዓላማ ግብ መቺ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የማስተማር ልምምዱን ሂደት እየተከታተለና ሊሻሻሉ ወይም ሊጠናከሩ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ተጨባጭ መረጃዎችን እያሠባሠበ ገንቢ የሆኑ ምግበ መረጃዎችን የመሥጠት ብቃት ያለው ሱፐርቫይዘር ሲኖር መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ከፍ ሲል የቀረበው መረጃ የሚያሣየው ግን የዚህን ተቃራኒ

ነው። ስለሆም በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለፀው በኮሌጁ ያሉ ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዕጩ መምህራኑ ከተመደቡባቸው ሰባ ሁለት ትምህርት ቤቶች አንፃር ሲታዩ ያለው የቁጥር አለመመጣጠን አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ሱፐርቫይዘሮች ከሥራቸው ውጭ የሱፐርቪዥን አገልግሎት እንዲሠጡ መደረጉ በተለይ በምገበ መረጃ አሠጣጡ ላይ ችግር ያስከተለ መሆኑን በመቅረፀ ድምፅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ያመለክታሉ፤

አሥረጅ 1.

ሱፐርቫይዘር፦ እኔ እንደማውቀው "Language" ትምህርት ላይ pre-reading, while reading, post reading Questions አሉ። በተለይ የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና "understanding" እንደጨምርና በምን በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ መጀመሪያ ጥያቄዎቹ ቢቀርቡላቸው ጥሩ ነው። ለወደፊቱም ይህ ቢደረግ ጥሩ ነው።

ዕጩ መምህር፦ ግንዛቤያቸውን ለማወቅ ነው መጨረሻ ላይ ጥያቄዎችን ያቀረብኩት። በምን በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ግን በየቡድኑ እየተዘዋወርኩ ነግሬአቸዋለሁ።

(ሱፐርቫይዘር 2 ውይይት 1)

አሥረጅ 2፦

ሱፐርቫይዘር… ትምህርቱ በመርጃ መሣሪያ ተደግፎ ቢቀርብ መርጃ መሣሪያ አላየሁም።

ዕጩ መምህር… በመርጃ መሣሪያ አማርኛን እ .. እ…

ነባር መምህር /ማሕቶ ንብታ/፦ ይህ ርዕስ መርጃ መሣሪያ ብዙም አያሥፈልገውም..

ሱፐርቫይዘር፦ ግን እኮ የሙያ ሠዎች የሚሉት ነገር አለ የ"Ps" ሰዎች ማለት ነው። ያለ መርጃ መሣሪያ የሚሠጥ ትምህርት የለም። ለምሣሌ አሁን አንቺ ምንድን ነው ያልሻቸው ያንቀፅ ማሠሪያ ነው? ምንድንነው ያልሻቸው? እነዚያ … ነው…ናቸው… የማሠሪያ አንቀፅ ማደማደሚያዎች ያልሻቸውን በወረቀት ላይ ቻርት ሠርተሽ ብታቀርቢያቸው ኖሮ መርጃ መሣሪያ መሆን ይችሉ ነበር። እኔ የማስበው እንደዚያ ነው፤ የቋንቋ ሠው ደግሞ በተሻለ መንገድ ሊገልፀው ይችላል። እኔ ከአንቺ የተሻለ ነገር ኖሮኝ አይደለም።

(ሱፐርቫይዘር 7 ውይይት 1)

በአስረጅ አንድ ላይ ሱፐቫይዘሩ ድኅረ ንባብ ጥያቄዎች ጭምር በቅድመ ንባብ ጊዜ መቅረብ እንዳለባቸው አስተያየት አቅርቧል። ለወደፊቱም ይህን ማድረግ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ሰጥቷል። በዕጩ መምህሯ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ላይ እንደሠፈረውና በመቅረፀ ድምፁ ከተቀረጸው የመምህሯ አስተያየት መረዳት እንደሚቻለው ደግሞ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የቀረበና ጥልቅ የንባብ ዘዴን የሚጠይቅ ነው። ሥለሆነም ድህረ ንባብ ጥያቄዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ መቅረብ የለባቸውም። ከዚህም ምግበ መረጃው በትክክል እንዳልተሠጠ እንረዳለን።

በአሥረጅ ሁለት የእጩ መምህሯ ምላሽ አሠጣጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መግሪያ የሚያሥፈልገው መሆኑን በጥረጣሬ የማየት አዝማሚያ ያሣያል። ዕጩ መምህሯ አ...አ... በማለት ያቋረጠችውንና አማካሪ መምህርቷ ካፏ ነጥቃ ምላሽ የሠጠችበትን ጥያቄ እንድትጨርሠው የዚህ ጥናት አቅራቢ በጠየቃት ጊዜ፣ "አማርኛ ሥለሆነ በቀላሉ ይገባቸዋል ብዬ ነው" የሚል መልስ መሥጠቷ በመርጃ መሣሪያ አሥፈላጊነትና አጠቃቀም ላይ ያላትን ግንዛቤ አጠያያቂ ያደርገዋል።

ከሱሌኛ በተገኘው መረጃ መሠረት ሱፐርቫይዘሩ የቋንቋ መምህር አለመሆኑ ተረጋግጧል። በሙያው የሠለጠነና ልምዱ ያለው ባለመሆኑም ከሠጠው አስተያየት ማሠሪያ አንቀፅ ለተሠኘው አገላለፅ እንግዳ መሆኑንና አስተካክሉ መጥራት እንዳዳገተው መረዳት ይቻላል። ለዚህም "ምንድነው ያልሻቸው እነዚያ ነው... ናቸው... የሚባሉትን?... የማሠሪያ አንቀፅ ማደማደሚያዎች ያልሻቸው ... የቋንቋው ሠው በተሻለ መንገድ ሊገልፀው ይችላል..." የተሠኙት አነጋገሮች በአሥረጅነት ሊጠቀሡ ይችላሉ። ይህም አሥተያየቱ በተገቢ ሁኔታ እንዳልተሠጠ፣ ከመረጃ እጦት የተነሣ በራሥ ያለመተማመን ችግር እንደተከሠተና ግልፅ የሆነ አሥኀኝ ነገር እንዳልተጠቆመ ያሣያል።

ዕጩ መምህራን የማስተማር ልምምድ በሚያካሂዱበት የትምህርት ዓይነት የሰለጠነ ሱፐርቫይዘር ስላልተመደበላቸው የገጠማቸውን ችግር በማስታዎሻዎቻቸው ላይ እንደሚከተለው ገልፀውታል፤

ሀ. የተመደቡልን መምህር የቋንቋ ሰው ባለመሆናቸው በመጽሐፉ ሥላጋጠሙኝ አንዳንድ ችግሮች ለማንሳትና መፍትሔ ለማግኘት አልቻልኩም።

ለ. ለወደፊቱ መምህራኑ በሰለጠኑበት ትምህርት ብቻ ቢገመገሙ ይሻላል። አለበለዚያ በውጤት አሰጣጡም ላይ ችግር ማስከተሉ አይቀርም።

በአጠቃላይ ከመረጃዎቹ መረዳት እንደሚቻለው ባልሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ሱፐርቫይዘር ሆነው የሚመደቡ መምህራን ተገቢና ትክክል የሆነ ምገበ መረጃ መስጠት ያዳግታቸዋል። ይህ ደግሞ የዕጩ መምህራኑን ሙያዊ ብቃት ከማሳደግ አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው አጠያያቂ አይደለም። ሥለሆነም ሱፐርቪዥኑ የሥልጠናውን ዓላማ የሚያሳካ እንዲኖረው በትምህርቱ በዋናነት ወይም በንዑስነት በሰለጠኑና ተገቢውን የሱፐርቪዥን ሥልጠና በወሰዱ ሰዎች መካሄድ ያለበት መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ከዚህ በማስከተል ደግሞ ዕጩ መምህራኑ የማስተማር ልምምድ ሲያካሂዱ ሱፐርቫይዘሮቻቸው በዕቅድና በፕሮግራም ይከታተሉአቸው እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 10፦ የሱፐርቫይዘሮች ክትትል

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልሞሉ |
| 24 | ሱፐርቫይዘሬ የማስተማር ልምምድ ሳካሂድ በዕቅድና በፕሮግራም ይከታተለኝ ነበር። | 10<br>14% | | 23<br>32.3% | 38<br>53.5% | | |

በሠንጠረዥ የሠፈረው መረጃ እንደሚያሣየው የማስተማር ልምምድ ሲያካሂዱ ሱፐር ቫይዘራቸው በዕቅድና በፕሮግራም ይከታተላቸው እንደነበር አዎንታዊ መልሥ የሰጡ ዕጩ መምህራን 10(14%) ብቻ ናቸው። 38(53.5%) ዕጩ መምህራን አሉታዊ መልሥ የሠጡ ናቸው። 23(32.3%) ግን ወሥነው መግለፅ አልቻሉም።

ከዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻዎች ላይ የተገኘው መረጃም ከፍ ሲል በሰንጠረዡ ላይ የታየውን የሚያጠናክር ነው።

አሥረጀዎች፦ 1. አሠልጣኝ መምህሬ ከክፍል ገብቶ የተከታተለኝና የገመገመኝ አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

2. ድክመትና ጥንካሬያችንን እየተከታተሉ የሚረዳን ሰው የለም ሱፐርቫይዘሮች በየሰሚስተሩ መጨረሻ የሚመጡት ውጤት ሞልተው ለመሄድ ነው። አንዳንድ አስተያየት ቢሠጡም ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ነው። ዓመቱ ካለቀ በኋላ መቼ ልናሻሽለው ነው።

3. ሱፐርቫይዘሩ እኛ ዘንድ መምጣቱን እንኳ የሠማነው የት/ቤቱ ነባር መምህራን መጥቷልና ተዘጋጁ ብለው ነግረውን ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እንመጣለን ያሉበትን ቀን ትተው ባልታሠበ ጊዜ የሚመጡ እሉ።

ከፍ ሲል ከዕሉፍ መጠይቅና ከዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሱፐርቪዥንን ተከታታይነት ባለው መልኩ አይሠጥም። ከዚህም በተጨማሪ ሱፐርቪዥንን የሚካሄድበት ጊዜ ዕጩ መምህራኑ የሚሠጧቸውን ምግበ መረጃዎች በተግባር ለመፈተሽ የሚያመቻቸው አይደለም። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሥለ ዕጩ መምህራኑ የማስተማር ብቃት ተጨባጭ መረጃዎችን ማግኘትና የሥልጠናው ዓላማ ምን ያህል እንደተሳካ ማረጋገጥ አጅግ አሥቸጋሪ ነው።

ስለ ዕጩ መምህራኑ የማስተማር ብቃት የተሟላ መረጃ ለማግኘት ተከታታይነት ያለው ሱፐርቪዥንን ከማካሄድ በተጨማሪ ሱፐርባይዘሮች የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲያደርጉ ሙሉ የክፍለ ጊዜ ቆይታ ሊኖራቸው ይገባል። ይህን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የጥናቱ ተተኳሪዎች የሠጡትን ምላሽ የሱፐርባይዘሮቹን በማስቀደም ቀጥለን እንመልከት።

ሠንጠረዥ 11፡- ሱፐርባይዘሮች ሙሉ የክፍል ውስጥ ምልከታ ስለማካሄዳቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | ያልሞሉ |
| 14 | የማስተማር ልምምዱን ለመከታተል በሱፐርቫይዘርነት ሥሠማራ ክፍለ ጊዜውን በሙሉ እክፍል ውስጥ እቆያለሁ። | 13 | | - | 8 | | - |

በሠንጠረዥ አሥራ አንድ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው አሥራ ሶስት ሱፐርቫይዘሮች ሙሉውን ክፍለ ጊዜ በመቆየት የማስተማር ልምምዱን ሲከታተሉ፣ 8(ስምንቱ) ግን ሙሉ ምልከታ አያደርጉም። የዚህን መረጃ ትክክለኛነት የበለጠ ለማረጋገጥ ለእጩ መምህራኑም በተመሣሣይ መልኩ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሠጥተዋል።

ሠንጠረዥ 12፡- ሱፐርባይዘሮች ሙሉ የክፍል ውስጥ ምልከታ ስለማካሄዳቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5/4 | 3 | 2/1 | ያልሞሉ |
| 14 | ሱፐርቫይዘሩ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ተግባር ለመመልከት ክፍለ ጊዜውን በሙሉ ይቆያል። | 38<br>54% | 7<br>10% | 26<br>37% | - |

በሠንጠረዥ አሥራ ሁለት የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው 38(54%) ዕጩ መምህራን ሱፐርቫይዘሮቻቸው ሙሉውን ክፍለ ጊዜ እክፍል በመቆየት ምልከታ እንደሚያካሂዱ ሲገልፁ፣ 26(37%) እጩ መምህራን ደግሞ ሱፐርቫይዘሮቻቸው ክፍለ ጊዜውን በሙሉ ቆይተው ምልከታ እንደማያካሂዱ ገልፀዋል። የቀሩት 7(10%)ግን ቁርጠኛ መልሥ መስጠት አልቻሉም።

በሠንጠረዥ 11 እና 12 ላይ የሚታየው የአሉታ  መላሾች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም። ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ለማጣራት የዚህ ጥናት አቅራቢ ከኮሌጁ የፕራክቲከም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት መረጃ አፈላልጐ ነበር። በዚህም መሠረት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በፕራክቲከም II አንዳንድ ሱፐርቫይዘሮች ከ20-25 የሚደርሡ ዕጩ መምህራንን እንዲገመግሙ ተመድበዋል። አንዳንዶች ደግሞ በተለያዩ ወረዳዎች የተደለደሉ ዕጩ መምህራንን በአንድ ሳምንት የኮሌጁ የሱፐርቪዥን መርሀ ግብር ውስጥ እንዲገመግሙ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያትም ዕጩ መምህራን የተመደቡባቸውን 72 ያህል ት/ቤቶች ለማዳረሥ የሚያሥችል በቂ የአሠልጣኞች ሀይል ባለመኖሩ እንደሆነም የፕራክቲከሙ አስተባባሪዎች ገልፀዋል። ይህ ዓይነቱ አሠራር የማስተማር ልምምዱን ለመከታተል ክፍለ ጊዜውን በሙሉ በክፍል ውስጥ ባለመቆየት አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

በተጣማጅ ዕሁፎች ትንት ውስጥ በተለይ ቋንቋን የማስተማር ልምምድ ሂደት የሚያተኩርባቸው አራት አበይት ተግባሮች እንዳሉ ተገልጿል። ዕጩ መምህራን እነዚህን ተግባሮች ባግባቡ መወጣት ሥለመቻላቸው ተጨባጭ መረጃዎችን መሠብሠብና ገንቢ ምግበ መረጃ መስጠት የሚቻለው የመማር ማስተማሩን ሂደት ከጅማሮው እስከፍፃሜው በመከታተል ነው። ዘግይቶ በመግባት ወይም አቋርጦ በመውጣት የተሟላ መረጃ ማግኘት አይቻልም። የተሟላ መረጃ በሌለበት የሚሠጥ ምግበ መረጃ ደግሞ ከትክክለኛነቱ ተገቢነቱ ይልቅ ግምታዊነቱ ጎልቶ የሚታይ ይሆናል።

ከፍ ሲል የተገለፀውን በኮሌጁ መምህራን ዘንድ የሚታይ የሱፐርቪዥን አሠጣጥ ዕጥረት ለማሟላት ያስችላል ተብሎ የታቀደው ሌላው አማራጭ የአጋር ት/ቤቶች ነባር መምህራን ክትትልና ዕገዛ ነው። ይህን በተመለከተ ለዕጩ መምህራን ቀርቦ ከነበረው የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ደግሞ ቀጥለን እንመልከት።

ሠንጠረዥ 13፡- የአጋር ትቤት ነባር መምህራን ዕገዛ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5/4 | 3 | 2/1 | ያልሞሉ |
| 6 | ነባር መምህራን የማስተማር ልምምድ በሚደረግበት ክፍል እየተገኙ ሂደቱን በመከታተል ከፍተኛ ዕገዛ አድርገውልኛል። | 35<br>49.% | 11<br>15% | 25<br>35.2% | -<br>- |

ሠንጠረዥ 13 እንደሚያሳየው 35 (49.3%) ዕጩ መምህራን ከነባር መምህራን ከፍተኛ የሙያ እገዛ እንዳገኙ ሲገልፁ፤ 25(35.2%) ደግሞ ሙያዊ ዕገዛ እንዳልተደረገላቸው ገልፀዋል። 11(15.5%) ግን ቁርጠኛ መልሥ የላቸውም።

የማስተማር ልምምዱን ግብ መቺ ከማድረግ አኳያ ሲታይ በሠንጠረዥ 13 ለቀረበው ጥያቄ የሚጠበቀው የጐላ አዎንታዊ ምላሽ ነው። ሆኖም የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው አዎንታዊ መላሾች 49% ብቻ መሆናቸውን ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ዕገዛው በቂ እንዳልነበር ነው። በዕጩ መምህራኑ ማስታወሻዎች ላይ የአጋር ት/ቤቶች መምህራንን ክትትልና ዕገዛ በሚመለከት የተሠጡ አንድ መቶ ያህል አስተያየቶችን በመፈተሸና ድግሞሽን በማስላት የተገኘ ውጤትም ከነባር መምህራን ሊያገኙት የሚገባው ሙያዊና ተሞክሮአዊ ድጋፍ አጥጋቢ እንዳልነበር እንደሚከተለው ያሣያል፤

ሠንጠረዥ 14፡- ነባር መምህራን ስለሚያደርጉት ክትትልና ዕገዛ

| የማስታዎሻው ትኩረት ነጥብ | በዕጩ መምህራኑ ምላሽ ላይ የታየ የድግግሞሽ ብዛት |
|---|---|
| • ነባር መምህራን ያደረጉልኝ ክትትልና ዕገዛ ከፍተኛ ነበር | 21 |
| • ነባር መምህራን የሚያደርጉልኝ ክትትልና ዕገዛ እምብዛም ነው። | 56 |
| • ነባር መምህራን ምንም ዓይነት ክትትልና እገዛ አያደርጉልኝም | 23 |

ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው 79 የሚሆኑት አስተያየቶች ዕጩ መምህራኑ ከነባር መምህራን እገዛ እንዳላገኙ ወይም የተደረገላቸው ድጋፍ አጥጋቢ እንዳልነበር የሚያመላክቱ ናቸው። የድጋፉን በቂነት ያንፀባረቁት 21 አስተያየቶች ብቻ ናቸው።

በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሃ ግብር ውስጥ የአጋር ትምህርት ቤት ነባር መምህራን ትልቁና ወሳኝ ድርሻ አላቸው። ዕጩ መምህራኑ ከትምህርት ቤት አውድ ጠቃሚ ተሞክሮዎችን እንዲቀስሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ልምዳቸውን

እያቋደሱ በማስተማር ልምምዱ ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት ከነባር መምህራኑ ይጠበቃል። ሥለሆነም ያለነባር መምህራን ክትትልና ዕገዛ የማስተማር ልምምዱ ዓላማ ግቡን ሊመታ እንደማይችል ግንዛቤ ሊወሠድበትና ክትትሉና እገዛው ሊጠናከር የሚችልበት መንገድ ሊመቻች ይገባል።

በምዕራፍ ሁለት በቀረበው የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ውስጥ እንደተገለፀው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ግብ መቷ እንዲሆን ከሚያሥችሉ ጉዳዮች አንዱ ኮሌጁና አጋር ት/ቤቱ በግንባር እየተገናኙ ሲመካከሩ ነው። ይህ ዓይነቱ ምክክር ይደረግ እንደሆን ለማረጋገጥ ለስፐርቫይዘሮቹ በዕሑፍ መጠይቅ አማካይነት ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። የሠጡትን ምላሽ ቀጥለን እንመልከት።

ሠንጠረዥ 15፡- **የኮሌጁ አሠልጣኝ መምህራንና የአጋር ትምህርት ቤቶች ነባር መምህራን ስለመመካከራቸው**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 19 | የኮሌጁና የአጋር ት/ቤቶች መምህራን ሥለ ማስተማር ልምምዱና ስፐርቪዥን አተገባበሩ ፊት ለፊት እየተገናኙ ይወያያሉ። | 6 | 3 | 12 | - |

ስድስት ስፐርቫይዘሮች አዎንታዊ መልስ ሲሠጡ፣ አሥራ ሁለት ስፐርቫይዘሮች ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ሶስት ግን ቁርጠኛ መልስ አላስቀመጡም። የዚህ ጥናት አቅራቢ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምዱን መርሀ ግብር በበላይነት ከሚመሩት አስተባባሪዎች ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ያገኘው መረጃም የኮሌጁና የአጋር ት/ቤቶች ግንኙነት ባብዛኛው ደብዳቤያዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ከዚህ በማስከተል ደግሞ በድኅረ የማስተማር ልምምድ የሚካሄደውን የምገበ መረጃ መሥተጋብር እንመለከታለን።

### 4.3.3 የምገበ መረጃ አቀራረብ

ከማስተማር ልምምዱ የክፍል ውስጥ ምልከታ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ስፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን የሚያካሂዱት የምገበ መረጃ ልውውጥ /መስተጋብር/ ነው። የምገበ መረጃ አቢይ ዓላማም ዕጩ መምህራኑ ቀጣይ ተግባሮቻቸውን በተሻለ ብቃት መወጣት የሚችሉባቸውን አማራጮች ማሥገኘት ነው። በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ውስጥ ለማብራራት እንደተሞከረው በምገበ መረጃ ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው አቀራረቡ ከተፅዕኖ ፣ ከትዕዛዝ፣ ከምክር ልኮ፣ ከስሜታዊነት፣ ከግምታዊነት፣ ከጥቅላዊነት... የፀዳና ራሥን በራሥ የመገምገም ነፃነት የሚሠጥ ሆኖ ሲቀርብ ነው። የዚህ ጥናት ተተኳሪ አካላት ያካሄዱት የምገበ መረጃ

ለውውጥ ክፍ ሲል በተጠቀሰው አግባብ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ለሱፐርቫይዘሮቹና ዕጩ መምህራኑ ቀርበውላቸው ነበር። በቅድሚያ የውይይቱ መንፈስ ምን መልክ እንደነበረው ሱፐርቫይዘሮቹ የሠጡትን ምላሽ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 16፦ የውይይቱ መንፈስ ምን ይመስል እንደነበር

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 17 | በድኅረ ምልከታ ውይይት ጊዜ ዕጩ መምህራኑ ዘና ብለው ሃሳባቸውን እንዲገልፁ አበረታታቸዋለሁ። | 16 | 3 | 2 | - |

ሠንጠረዥ 16 እንደሚያሳየው ዕጩ መምህራኑ ዘና ብለው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በማበረታታት ረገድ አሥራ ስድስቱ ሱፐርቫይዘሮች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ ሁለቱ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፣ ሦስቱ ግን ቁርጠኛ መልስ የላቸውም። የዚህን መረጃ ተአማኒነት ለማረጋገጥ ለእጩ መምሕራኑ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

ሠንጠረዥ 17፦ የውይይቱ መንፈስ በዕጩ መምህራኑ ሲታይ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 \| 4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 3 | በምገባ መረጃ መስተጋብር ጊዜ የሱፐርቫይዘር አቀራረብ ዘና ብዬ ሃሳቤን እንድገልጽ አድርጎኛል። | 39<br>54.9% | 16<br>22.5% | 16<br>22.5% | |

በሰንጠረዡ እንደሚታየው በድህረ ምልከታ ጊዜ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር ያካሄዱትን ውይይት ዘና የሚያደርግ መንፈስ ነበረው፣ በማለት አዎንታዊ መልስ የሰጡ ዕጩ መምህራን 39(54.9%) ሲሆኑ 16(22.5%) ዘና የማለት ስሜት እንዳልፈጠረባቸው ገልፀዋል። ቀሪዎቹ 16(22.5%) ግን ቁርጠኛ መልስ የላቸውም።

በመረጃው መሠረት በድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ጊዜ ዘና ብለው ሃሳባቸውን እንደልብ መግለፅ የቻሉ እጩ መምህራን 39(54.9%) ብቻ መሆናቸው በሁለቱ ተስተጋባሪዎች (ሱፐርቫይዘርና ዕጩ መምህር) መካከል ሊኖር የሚገባው መቀራረብ የተጠናከረ አለመሆኑ ይጠቁማል። ይህ ደግሞ በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ውስጥ ከተዘረዘሩት ሱፐርቫይዘራዊ ክህሎቶች አንዱ የሆነውን ከሰዎች ጋር የመግባባት ክሂል ሱፐርቫይዘሮች በሚገባ እንዳልተካኑትና በአግባቡ እንዳልተጠቀሙበት የሚያመላክት ነው። ይህ ክህሎት Kinard (1988) እና Griffiths (1956) እንደገለፁት የሰዎችን ባህሪ በመረዳት ለሚከናወነው ተግባር

ተግባራና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያደርግ ብቃትን ይጠይቃል። ይህን ማድረግ የተሳነው ስትራቴጂ በምገባ መረጃ አማካይነት በዕጩ መምህራኑ ዘንድ ማስተማርን የመማር ንሸን በመፍጠር ሙያዊ ብቃታቸው እንዲሻሻል የሚያደርገው እገዛ ፍሬአማ ይሆናል ብሎ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው።

በምገባ መረጃ ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው ስትራቴጂዎቹ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ግልፅ ሲሆንና የዕጩ መምህራን ስብዕና ባለመንካት ጥንቃቄ ሲያደርጉ ነው። ይህንኑ የተመለከተ ጥያቄ ለስትራቴጂዎች ቀርቦላቸው የሰጡትን ምላሽ ቀጥሎ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 18፡ የስትራቴጂዎች የቋንቋ አጠቃቀም

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 \| 4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 22 | ከእጩ መምህራኑ ጋር ስንወያይ በግልፅ ቋንቋ እጠቀማለሁ። | 18 | 4 | 3 | - |
| 26 | በድኅረ ምልከታ ውይይት ጊዜ የእጩ መምህራኑን ስብዕና ባለመንካት ከፍተኛ ጥንቃቄ አደርጋለሁ። | 19 | 2 | - | - |

ግልፅ ቋንቋን በተመለከተ አሥራ ስምንቱ ስትራቴጂዎች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ ሦስቱ ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። አራቱ ግን ቁጥርጠኛ መልስ የላቸውም። የዕጩ መምህራኑን ስብዕና ባለመንካት የሚደረገን ጥንቃቄ በተመለከተ አሥራ ዘጠኙ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል።

በጥቅሉ ሲታይ ስትራቴጂዎቹ በድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ጊዜ ግልፅ ቋንቋ መጠቀማቸውንና የዕጩ መምህራኑን ስብዕና ባለመንካት ጥንቃቄ ማድረጋቸውን የሚያመለክት መረጃ ሰጥተዋል። ይህ እንደ ጥሩ ጎን የሚታይ ቢሆንም ቀደም ሲል በቀረቡት መረጃዎች ላይ እንደታየው ምገባ መረጃው ትዕዛዝና መመሪያ በመስጠት ላይ ያተኮረ በመሆኑ እጩ መምህራኑ አማራጮችን ከመጠቀም ይልቅ ስትራቴጂዎቻቸው የመረጡላቸውን መንገድ ብቻ እንዲከተሉ የሚያደርግ ተፅዕኖ ነበረው ለማለት ያስደፍራል። በመቅረፀ ድምፅ የተቀዳው የምገባ መረጃ መስተጋብር ላይ እንደሚታየውም የስትራቴጂዎቹ የቋንቋ አጠቃቀም ዕጩ መምህራኑ ያሏቸውን ተግባራቸውን እያሰላሰሉ እንዲቀጩና አንድን ቀጥተኛ መንገድ ብቻ እንዲከተሉ የሚያደርግ ተፅዕኖ ያለበት ነበር ማለት ይቻላል። ከዚህ በማስከተል ለአስረጅ ያህል ጥቂቶቹን አሉር አሉር እንመልከት፤

... የውድን ሥራ ሥትሠጭ ሰዓት አልወሠንሽላቸውም ብታደርጊላቸው ኖሮ የጊዜ አጠቃቀምን ይለምዱ ነበር።

. . .የግጥምን አነባበብ ሥርዓት ለማለማመድ የዝምታ ንባብን እንዲጠቀሙ ማድረግ አልነበረብሽም።

. . . የተሳሳተ መልሥ ሲሠጡ ዕርምት መስጠት ነበረብሽ።

. . . ይህንን ድክመትሽ አድርገሽ ውሰጀው . . . አጋጣሚ ነው የሚለው አይሠራም።

. . . ሌሰንፕላንሽ ላይ ለደንቡ ያህል ሰዓት አሥቀምጠሻል እንጂ አልተጠቀምሽበትም።

. ዓላማ አፃፃፍሽ ከዝርዝር ዓላማ አፃፃፍ አንፃር ሲታይ ተገቢ አልነበረም።

ከፍ ሲል ለአብነት ያህል የቀረቡት ምገበ መረጃዎች በየውይይቱ ላይ ተደጋግመው ይደመጣሉ። በዚህ መንገድ የሚገለፁ ምገበ መረጃዎች ዓለም (1988) የውድምርድ (1989)ን ሥራ በመጥቀስ እንደገለፁት ዕጩ መምህራኑ የፈፀሟቸው ስህተቶች ከብደው እና በዝተው እንዲታዩአቸው እና ወደፊት መሠራት ካለበት ይልቅ ያለፈውን በማሰላሰል ላይ እንዲያተኩሩና የተለየ አማራጭ መንገዶችንም እንዳያዩ ሊያደርግ የሚችል ነው።

ምገበ መረጃ ግብ መቺ እንዲሆን ከሚያስችሉ ሁኔታዎች አንዱ በምልከታ በተደረሠባቸው ተጨባጭ መረጃዎች ላይ ተመሥርቶ መቅረቡ ነው። ይህንኑ የተመለከተ ጥያቄ ለስፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራኑ ቀርቦላቸው የሠጡት ምላሽ እንደሚከተለው ነው፤

ሠንጠረዥ 19፡ ምገበ መረጃው በምልከታ ውጤቶች ላይ ስለመመሥረቱ ሱፐርቫይዘሮች የሠጡት ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 21 | በእኔና በእጩ መምህራኑ የሚደረገው ምገበ መረጃ ልውውጥ በምልከታ በተደረሠባቸው ነገሮች ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው። | 17 | 2 | 2 | - |

በሠንጠረዡ የሠፈረው መረጃ እንደሚያመለክተው አሥራ ሰባቱ ሱፐርቫይዘሮች ከዕጩ መምህሮች ጋር ያካሄዱት የምገበ መረጃ ልውውጥ ከማሥተማሩ ልምምድ ምልከታ በተገኙ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው ሲሉ፤ ሁለቱ ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ምላሽ ሠጥተዋል። ሁለቱ ግን ወሰነው መመለስ ተሥኗቸዋል። የዚህን መረጃ ተአማኒነት ለማረጋገጥ ለዕጩ መምህራኑም ተመሣሣይ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ደግሞ የሚከተለው ነው፤

ሠንጠረዥ 20፡- ምግበ መረጃው በምልከታ ውጤቶች ላይ የመመሥረቱ ሁኔታ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 10 | ' ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ያካሄድኩት የምግበ መረጃ ልውውጥ በምልከታ በተደረሠባቸው ተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡ | 38<br>53.5% | 17<br>23.9% | 16<br>22.5% | - |

ሠንጠረዥ ሃያ እንደሚያሣየው 38(53.5%) ዕጩ መምህራን አዎንታዊ መልስ ሲሠጡ፣ 16(22.5%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል 17(23.9%) ግን ቁርጠኛ መልስ የላቸውም፡፡

በሠንጠረዥ 19 እና 20 በሠፈሩት መረጃዎች ምግበ መረጃው በምልከታ በተደረሰባቸው ነገሮች ላይ ተመሥርቶ መቅረቡን የሚያመለክቱ አዎንታዊ መልሶች ጎልተው ይታያሉ፡፡ ሆኖም ሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራኑ የሠጡት አዎንታዊ መልስ ንፅፅራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ የዕጩ መምህራኑ አንስ ይታያል፡፡ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ፍንጭ አመላካች የሆኑ መረጃዎች በዕጩ መምህራኑ ማስታወሻዎች ላይ ይታያሉ፡፡

አሥረጅዎች፡-

1 በውይይቱ ጊዜ ሱፐርቫይዘሩ የነገረኝ በማስተምርበት ጊዜ የታዘበውን መሠረት አድርጉ ነው፡፡ ግን አንዳንዱ አስተያየቱ ከማስተማሩ ሁኔታ የወጣ ነው፡፡ ለምሣሌ "ተማሪዎች በነፍስ ወከፍ መጽሐፍ እንዲይዙ አላደረግሽም፡፡ ትምህርት ቤቱ መስጠት አለመስጠቱን ማረጋገጥ አለብሽ" ብሎኛል የኔ ሥራ ማስተማር እንጂ መፅሐፍ ማስገባት ወይም መግዛት ሥላልሆነ ይህ አስተያየት ከመማር ማስተማሩ ጋር አይገናኝም፡፡

2 ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ከማስተማር ልምምዱ በኋላ የረባ ውይይት አላካሄድንም፡፡ አትፍሪ፣ ሠው እኮ የሚባላ አውሬ አይደለም፡፡ ለወደፊቱ ድፍረት እንድታገኚ ሃሣብሽን በሠው ፊት በመግለፅ ተለማመጂ ነበር ያለኝ፡፡

በአሥረጅ አንድ ላይ ሱፐርቫዘሩ የሠጠው አስተያየት ተማሪዎች መጽሐፍ እንዲይዙ ማድረግ ወይም ያልያዙበትን ምክንያት ማረጋገጥ ይገባል የሚል ሲሆን፣ ዕጩ መምህሯ ግን ይህ አስተያየት የመማር ማስተማሩን ሂደት መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ሲሠጥ እንደማይገባ

ገልጸለች። በአሥረጅ ሁለት ላይ ደግሞ የስተርሻይዘሩን አስተያየት በምልከታ ውጤቶች ላይ መመሥረት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ ምገበ መረጃ አለመሠጠቱ ተገልጿል።

በሁለቱ አስረጅዎች ላይ የቀረቡት አስተያየቶች ምገበ መረጃው ምልከታን መሠረት አላደረገም ወደሚል ማደማደሚያ አይወስዱንም። ሆኖም በዕጩ መምህራኑ ግንዛቤ መሠረት ስተርሻይዘሮቻቸው የተሠጣቸው ምገበ መረጃ ከመማር ማስተማሩ ተግባር ጋር ግንኙነት የሌለውና ያልተሟላ ነው። ይህ አይነቱ አመለካከት ደግሞ ከፍ ሲል ለቀረበው የዕጩ መምህራኑ አዎንታዊ ምላሽ አለመጉላት እንደምክንያት ሊቆጠር ይችላል።

ጎለም /1988:27/ እንደገለፁት በምልከታ በተገኘ ጥሬ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚቀርብ ምገበ መረጃ ውይይቱን አዎንታዊ ገፅታ ሊያላብሥና ተፈላጊውን ውጤት ሊያሥገኝ ይችላል። ከዚህ አንፃር በሠንጠረዥ 19 እና 20 የተመለከትነው መረጃ ምገበ መረጃው የሚሠጥበት አግባብ ምልከታን መሠረት አድርጎ መሆኑ ጉላ ብሎ ቢታይም የአሉታዊያን መላሾች መኖር እንደ ቀላል ችግር ተደርጐ መወሰድ ስለሌለበት የበለጠ ትኩረት ሊሠጠው ይገባል።

በስተርሻይዘሮች የሚሠጠው ምገበ መረጃ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የምልከታ ውጤቶችን መሠረት ከማድረግ በተጨማሪ በሥልጠና ወቅት ከሚሠጠው ንድፈ ሃሣባዊ ትምህርት ጋር ሊጣጣም ይገባል። ይህንን በተመለከተ ለዕጩ መምህራኑ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፦

ሠንጠረዥ 21፡ ምገበ መረጃው ቋንቋን ከማስተማር ሥነ ዘዴ ጋር ያለው ተጣጥሞ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 16 | ' በውይይት ጊዜ ስተርሻይዘሬ የሚሠጠኝ ምገበ መረጃ ቋንቋን ሥለማስተማር ሥነ ዘዴ ከተማርኩት ጋር የተጣጣመ ነው። | 38<br>53.5% | 18<br>25.4% | 15<br>21.1% | - |

በሠንጠረዥ ሃያ አንድ ለቀረበው ጥያቄ 38(53.5%) ዕጩ መምህራን አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ 15(21.1%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። 18(25.4%) ግን እርግጠኛ መሆን ተቸግረዋል።

በስተርሻይዘሮቹ የሚሠጠው ምገበ መረጃ ዕጩ መምህራኑ ከቀሠሙት ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀት ጋር የሚጣጣም እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ አዎንታዊ መልስ የሠጡት ዕጩ መምህራን 53.5% ያህል ብቻ መሆኑ በምገበ መረጃውና በትምህርቱ መካከል ያለው ክፍተት ሠፊ መሆኑን ይጠቁማል።

በሠንጠረዡ ከቀረበው መረጃ በተጨማሪ በዕጩ መምህራኑ ማስታዎሻ ላይም ተመዝግበው ይዘት ያላቸው አንዳንድ መረጃዎች ተጠቀመዋል።

አሥረጅዎች፡-

1. በኮሌጁ ውስጥ ሥንማር ንባብ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት አሥተምረውናል። እነዚህ ደረጃዎችም የተለያየ ዓላማ አላቸው፡፡ ሱፐርቫይዘሩ ግን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ብቻ ሣይሆን ድኅረ ንባብ ጥያቄዎችን ጭምር ከማሥነበቤ በፊት ለተማሪዎቼ ማሣወቅ እንዳለብኝ ነው አሥተያየት የሠጡኝ። ያቀረቡት ምክንያት ተማሪዎቹ በምን ላይ እንደሚያተኩሩ በቅድሚያ ግንዛቤ እንዲያገኑ ያደርጋል የሚል ነው።
2. እኛ የተማርነው ሚዲያ / የትምህርት መርጃ መሣሪያ/ ግልፅ ያልሆኑ ነገሮችን በተጨባጭ ነገር እያቀረቡ ማብራሪያ ነው፡፡ ሱፐርቫይዘሩ ግን አመማሪያ መጽሐፉ ያሉትን አንዳንድ ቃላት በሠንጠረዥ ብታቀርቢው በማለት የሠጠኝ አስተያየት ሊዋጥልኝ አልቻለም፡፡

በመቅረፀ ድምፅ ከተቀዳው የምገበ መረጃ ልውውጥ ላይም የሚከተለውን አሥረጅ አናገኛለን፤

3. ሱፐርቫይዘር …ያለፈው ክፍለ ትምህርት ርዕስ ምን እንደነበር ተማሪዎችን ጠይቀሻቸዋል፡፡ ይህንን ግን አንቺው ራሥሽ አሥታውሠሽ መናገር ነበረብሽ፡፡

ዕጩ መምህር፡፡ አይ… ጠፍቶኝ ሣይሆን እነሡ እዲናገሩትና ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ለማድረግ ብዬ ነው እንጂ መናገር ይቻላል፡፡

(ሱፐርቫይዘር 4 ውይይት 2)

በአሥረጅ አንድ እና ሁለት ሱፐርቫይዘሮች ስለንባብ ደረጃዎችና ስለ መርጃ መሣሪያ የሠጧቸው አስተያየቶች ተገቢና ትክክለኛ አልነበሩም። ምክንያቱም አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ማንበብን ተከትለው እንጂ ቀድመው አይመጡም። የትምህርቱ መርጃ መሣሪያም አቅርቤአለሁ ለማለት ብቻ መቻል የለበትም። በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር መሥተጋብር ገለፆ፡ የትምህርቱን ዓላማ ሥኬታማ ከማድረግ አንፃር ፋይዳ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ እንደተባለውም በመጽሐፉ ያለውን በወረቀት ወይም ቻርት ገልብጦ ድጋሚ እንዲመለከቱት የማድረጉ ፋይዳ አልበያዩ ነው።

በአሥረጅ ሶሥት ላይ በሱፐርቫይዘሩ የቀረበው አስተያየት ተገቢ መሥሎ አይታይም፡፡ በዘመናዊ የማስተማር ሥነ ዘዴ የመምህሩ ተግባር ተማሪው በራሡ ጥረት ሊማር የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት ነው። ተማሪው ባለፈው የተማረውን ሳይዘነጋ ዛሬ

ከሚማረው ጋር ማቆራኘቱና አዲስ ነገር እያገኘ መሄድ ይጠበቅበታል። ከዚህ ዕውነታ አንፃር ሲታይ ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ተማሪዎች አስታውሠው እንዲናገሩ ማድረግ ተገቢ እንጅ ስህተት አይሆንም።

በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው የማስተማር ልምምድ ዓላማ ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀትን በተግባር የመተርጎም ብቃትን ማስገኘት ነው። ይህ ዕውን እንዲሆን ዕጩ መምህራን በኮሌጃቸው የቀሠሙትን ዕውቀት በማስተማር ልምምዳቸው እንዲተገብሩት የሚያስችል ምግበ መረጃ ሊያገኙ ይገባል። ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በምግበ መረጃውና በንድፈ ሃሣብ መካከል ክፍተት ከተፈጠረ ግን ዕጩ መምህራንን ግራ ሊያጋባና በሱፐርቫይዘሮቻቸው ላይ ያላቸው አመኔታም አሉታዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላልና ትኩረት ሊሠጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ከዚህ በማስከተል ደግሞ በምግበ መረጃው መሥተጋብር የጥናቱ ተሳታፊዎች ሚናና የሱፐርቪዥን አቀራረብ ምን ይመሥል እንደነበር እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 22፦ ዕጩ መምህራን በምግበ መረጃ መሥተጋብር ያላቸው ሚና

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 15 | በምግበ መረጃ መስተጋብር / ውይይት/ ጊዜ ሱፐርቫይዘሬ ተናጋሪ እኔ አድማጭ ነበርን | 35<br>49.2% | 8<br>11.2% | 28<br>38.1% | - |
| 20 | ሱፐርቫይዘሬ የራሴን ሥራ ራሴ እንድገመግም ያደርጋል | 13<br>18.3% | 10<br>14% | 48<br>67.6% | |

ሠንጠረዥ 22 በድኅረ ማስተማር ልምምድ በነበረው የምግበ መረጃ መስተጋብር የዕጩ መምህራን ሚና ምን እንደነበር የሚያመለክቱ መረጃዎችን ይዟል። በዚህ መሠረት በተራ ቁጥር 15 ለቀረበው ጥያቄ ከዕጩ መምህራን የተገኘው ምላሽ 35(49.2%) አዎንታዊ ሲሆን፣ 28(38.1%) ደግሞ አሉታዊ ነው። 8(11.2%) ግን ቁርጠኛ መልስ የላቸውም። በተራ ቁጥር 20 ዕጩ መምህራን ራሥን በራስ የመገምገም ዕድል ማግኘታቸውን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ የሠጡ 13(18.3%) ብቻ ናቸው። 48(67.6%) ዕጩ መምህራን በምግበ መረጃ መስተጋብር ውስጥ እጅግ ተፈላጊ የሆነውን ራስ በራስ የመገምገም ዕድል ማጣታቸውን ገልፀዋል።

ዕጩ መምህራን በማስታወሻቸው ላይም በምግበ መረጃ መሥተጋብሩ ተገቢ እና ጉልህ ሚና እንደማይጫወቱ ... ሁሉም ... 

ሀ. በድኅረ ምልከታ ውይይት ሱፐርቫይዘሩ ያሉትን ሃሳብ ዝም ብሎ መቀበል ወይም ማዳመጥ ነው።

ለ. ውይይቱ እኔንኝ አዋቂ አንተ ምን ታውቃለህ አፍህን ዝጋና ዝም ብለህ አዳምጠኝ ዓይነት ድባብ ነበረው።

ሐ. ምንም እንኳ ደካማ ጎን ከተባሉት ውሥጥ አሳማኝ የሆኑ ቢኖሩትም ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ ዓይነት ነበር የታየው። የተባሉትን እየተቀበሉ ጭንቅላትን እንደፒንዱለም ማወዛወዝ ነበር። ሀሳብ መሥጠት አልነበረም።

መ. በእርግጥ ባልመሠለን ነገር ላይ የተቃውሞ ሀሳብ እናቀርባለን። ግን ተቃውሞው ግልፅና ትክክለኛ ቢሆንም ሱፐርቫይዘሮች ጆሮ አይሰጡትም። እንዴ ካሉት ነገር ወደ ኋላ መመለሥ ሥለማይፈልጉ መረታትን አይሹም።

ሠ. በድኅረ ምልከታ ውይይት ጊዜ ሱፐርቫይዘሬ የሚለኝን ዝም ብሎ በማዳመጥ መጨረሻ ላይ ያልገባኝን እጠይቅ ነበር። ደግሞ ሌላ እንዲመክረኝ እጠይቃለሁ።

በመቅረፀ ድምፅ በተቀዳው የምገበ መረጃ መስተጋብር ውስጥ በጉልህ እንደታየውም የእጩ መምህራኑ ተሳትፎ እጅግ የተገደበና ውሡን ነው። አንዳንድ ዕጩ መምህራን አልፎ አልፎ ይሁንታን ወይም አለመስማማትን ሲያንፀባርቁ ከመደመጣቸው በስተቀር እጅግ ብዙውን ጊዜ የሚፈጀው የሱፐርቫይዘሮች ንግግር ነው። በሠንጠረዥ 22 ተራ ቁጥር 15 ላይ የአሉታዊ መላሾች ቁጥር 38% መድረሱ ምናልባትም ይህችን ውሡን ተሳትፎ እንደበቂ ከመቁጠር የተነሳ ሳይሆን አይቀርም ብሎ መገመት ይቻላል።

ከፍ ሲል በቀረቡት መረጃዎች ላይ እንደታየው የዕጩ መምህራኑ ሚና በአድማጭነት እና ተቀባይነት ላይ ያተኮረ መሆኑ የሱፐርቫይዘሮች ፍርድ ወይም ግላዊ ዳኝነት የጎላ እንደነበረ የሚጠቁም ነው። ይህንኑ የተመለከተ ጥያቄ ለዕጩ መምህራኑ ቀርቦላቸው የሠጡትን ምላሽ ቀጥለን እንመልከት፤

ሠንጠረዥ 23፦ ውይይቱና የሱፐርቫይዘሮች ዳኝነት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 25 | በድኅረ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ባካሄድኩት ውይይት ላይ የሱፐርቫይዘሬ ግላዊ ዳኝነት የጎላ ተሠሚነት ነበረው። | 44<br>61.9% | 15<br>21% | 12<br>16.9% | - |

ሠንጠረዥ እንደሚያሣየው 44(61.9%) ሰልጣኝ መምህራን አዎንታዊ መልሥ ሲሠጡ፣ 12 (16.9%) ሰልጣኝ መምህራን ደግሞ አሉታዊ መልሥ ሰጥተዋል፡፡ የቀሩት 15(21%) ግን ቁርጥ ያለ መልስ የላቸውም፡፡

በተጨማሪ ለሁሮች ቅኝት ወስጥ እንደተገለፀው የምገበ መረጃን ትክክለኛነት ሠጭውም ሆነ ተቀባዩ ሊያረጋግጡት የሚችሉት ካልሆነ የትኛውንም ወገን ሳይጠቅም ሊባክን ይችላል፡፡ ሥለሆነም ሱፐርቫይዘሮች ይህንን ተገንዝበው ወይይቱን ሚዛናዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 24፦ ሱፐርቫይዘሮች በምገበ መረጃ መስተጋብሩ ያላቸው ሚና

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 16 | በደጋፊ ምልከታውይይት ሰልጣኝ መምህራኑ የራሳቸውን ሥራ እንዲገመግሙ አደርጋለሁ፡፡ | 10 | 3 | 8 | - |
| 18 | በምገበ መረጃ ልውውጥ ጊዜ ለሰልጣኝ መምህራኑ መመሪያና ትዕዛዝ በመሥጠት በተግባር እንዲያውሉት አደርጋለሁ፡፡ | 19 | 2 | - | - |

በሠንጠረዥ 24 ተራ ቁጥር 16 ላይ እንደሚታየው አሥሩ ሱፐርቫይዘሮች ለሰልጣኝ መምህራኑ ራሥን በራሥ የመገምገም ዕድል እንደሚሠጡ ሲገልፁ፤ ሥምንቱ ደግሞ ይህንን ዕድል ለሰልጣኝ መምህራን እንዳልሠጡ ገልፀዋል፡፡ ሶስቱ ግን ቁርጥ ያለ መልስ የላቸውም፡፡ በተራ ቁጥር 18 ላይ ደግሞ አሥራ ዘጠኝ ሱፐርቫይዘሮች በምገበ መረጃ መሥተጋብር ጊዜ ለሰልጣኝ መምህራኑ መመሪያና ትዕዛዝ የመስጠት ሚና እንደነበራቸው ገልፀዋል፡፡ ለዚህ ጥያቄ አሉታዊ መልሥ የሰጠ ሱፐርቫይዘር የለም፡፡ ሱፐርቫይዘሮቹ በምገበ መረጃ መሥተጋብሩ የነበራቸውን ሚና በፅሁፍ መጠይቁ ላይ፤ 'በምገበ መረጃ ልውውጡ ጊዜ የእርስዎ ሚና ምን እንደነበር ይገለፁ' ለሚለው ክፍት ጥያቄ በሠጡት ምላሽ እንደሚከተለው ዘርዝረውታል፤

ሀ በማስተማሩ ሂደት የተገደሉ ነገሮችንና መስተካከል ያለባቸውን ማጉላት፤

ለ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በማንሳት በሰፊዉ አቀራረብ ድክመታቸውን እንዲያሻሽሉና ጠንካራ ጎናቸውን እንዲያጎለብቱ መምከር፤

ሐ በመጨረሻ ማስተማሩ ሂደት የተሳሳቱን እርምት ወይም ማስተካከያ መስጠት፤

መ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሃሳብ መስጠትና ችግራቸውን በማጤን መፍትሔ መስጠት፤

ሠ. በመጀመሪያ ከእነሱ የመነጨ ሃሳብ በመቀበል በዚያ ላይ ተንተርሦ ውሳኔ መስጠት፤

እነዚህ መልሶች ስትርቫይዘሮቹ በምገባ መረጃ መሥተጋብር ጊዜ የሚያደርጉትን ወይም ማድረግ የሚፈልጉትን የሚያመላክቱ ናቸው። በቀረቡት መረጃዎች ውስጥ መጠቆም፣ መምከር፣ መፍትሔ መስጠት፣ ውሳኔ መስጠት . . . የተሠኙት አገላለፆች በምገባ መረጃ መስተጋብሩ የስትርቫይዘሮች ሚና ምን እንደነበር ያመላክታሉ።

ከፍ ሲል የቀረቡት በተለያዩ የመረጃ ማሠባሠቢያ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ተመሣጣኝ ይዘት ይታይባቸዋል። ሁለቱም ተተኳሪዎች የሠጧቸው ምላሾች እንደሚጠቀሙት የምገባ መረጃ መሥተጋብሩ የስትርቫይዘሮች ሚና ገዢ የሚታይበት ነው። ስትርቫይዘሮች መመሪያና ትዕዛዝ ይሠጣሉ፤ ምክር ይለግሳሉ፤ የሠጡትን መመሪያና ትዕዛዝ ዕጩ መምህራን እንዲተገብሩት ያደርጋሉ። የዕጩ መምህራን ተሳትፎ በማዳመጥና የሚሠጣቸውን ትዕዛዝ መመሪያና ምክር በመቀበል ላይ የተወሠነ ነው። የዕጩ መምህራን ማስተማርን በመተግበር በቆዩበት ላይ ሲገጥመው ግምገማ እያካሄዱ መፍትሔዎችን የማስቀመጥ ሚና እጅግ አናሳ ነው። ስትርቫይዘሮቹ በሚሰጧቸው አስተያየቶች ላይ ማድረግ አለብህ/ሽ/፤ ልታሻሽይ/ል/ ይገባል፤ አስተካክል/ይ/፤ ለወደፊቱ ይኸንን... መቼ አለብህ/ሽ/ ተገቢ አልነበረም ወዘተ የተሠኙ ምክርና ትዕዛዝ አዘል አገላለጾችን በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ። ዕጩ መምህራን ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ አስተያየቶች የሚሠጧቸው ምላሾች ደግሞ በብዛትና በተደጋጋሚ እንደሚደመጠው፤ "እሺ... እሺ... አሥተካክላለሁ፤ አደርጋለሁ.. የሚሉ ናቸው። ዕጩ መምህራን ሚናቸው ውሡንና የሚሠጣቸውን ትዕዛዝና መመሪያ በደምሳሰው ተቀባዮች እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምክንያት ስትርቪዥን ከምዘና ያውም አሥራ ሁለት የትምህርት ክፍለ ጊዜ (Credit hour) ካለው ኮርስ ጋር መያያዙ እንደሆነ በብዙዎቹ ማስታወሻ ላይ በተደጋጋሚ ይታያል። ይህም ከላይ ለተገለፀው ዕጩ መምህራን ሚናቸውን ባግባቡ አለመወጣት ዋነው የሥጋት ምንጭ ነው ለማለት ያሥደፍራል።

ከፍ ሲል የታየው የስትርቫይዘሮችና የዕጩ መምህራን የምገባ መረጃ ላይ መሥተጋብራዊ ሚና በተጠማጅ ዕሁፎች ቅኝት ውሥጥ ከተጠቆሙት ዘጠኝ ያህል የስትርቪዥን አቀራረቦች አንዱ ሲታይ ስትርቪዥኑ መሪኔ /ትዕዛዛዊ/ እንደነበር ያመላክታሉ። ይህ ዓይነቱ ስትርቪዥን ደግሞ ዓለም(1988፡18) እንደገለፁት በስትርቪይዘሮችና ዕጩ መምህራን መካከል ሊኖር የሚገባውን መልካም ግንኙነት የሚያጠብ፤ ዕጩ መምህራን የራሣቸውን ዕውቀትና ችሎታ እንዲያዳብሩ የሚገድብና በራሥ የመተማመን መንፈስ ከማጐልበት ይልቅ የበታችነት ስሜት እንዲያሠርፅ ሊያደርግ የሚችል ነው።

በመረጃዎቹ ላይ እንደሚታየው ስፐርቫይዘሮች ምክር ልገሳን እንደ ጥሩ የምግበ መረጃ አቀራረብ ይቆጥሩታል። ይህ ዓይነቱ አመለካከት በዕጩ መምህራኑም ዘንድ እንዳለ በፅሁፍ መጠይቅ ላይ፣ 'ስለማስተማር ልምምዱና ስለስፐርቪዥኑ አተገባበር ያላችሁን አጠቃላይ አስተያየት ገለፁ' ለሚለው ጥያቄ የሠጧቸው ምላሾች እንደሚከተለው ይጠቁማሉ፤

ሀ እንዳንዶቹ ስፐርቪይዘሮች ደካማ ጎኖችን ከገለፁ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚገባን በግልፅ ሳይነግሩንና የረባ ምክር ሳይሠጡን ይሄዳሉ። ሆኖም በዚህ በኩል ሁሉም ተወቃሽ አይደሉም። ተማሪዎችን እንዴት መያዝ እንዳለብን፣ ምን ዓይነት መረጃ መማሪያ ልንጠቀም እንደሚገባ፣ የትኛውን የማስተማር ዘዴ መከተል እንደሚኖርብን፣ ሌሰንፕላን ላይ መሥፈር ያለባቸው ምን ምን እንደሆኑ ... በመንገር ማስተካከል እንዳለብን የሚመክሩን አሉ። ይህ መቀጠል አለበት።

ለ ከስፐርቫይዘሮች ጠንካራ ጎን የሆነው ባህርይ ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ ምክሮችን መስጠትና መፍትሔዎችን መግለፅ ነው።

እነዚህ ለአስረጂነት ያህል ቀረቡ እንጂ ተመሣሣይ ይዘት ያላቸው በርካታ አስተያየቶች በፅሁፍ መጠይቁ እና በማስታወሻዎች ላይ ይታያሉ።

ከተጠቀሱት ጽሁፎች ከተገኘ ግንዛቤ አንፃር ሲታይ ግን ምግበ መረጃ ምክር ለጋሽ እንዲሆን አይጠበቅም። የምግበ መረጃው አቀራረብ ምክር ልገሳ ከሆነ ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን አማራጭ የመጠቀም ዕድላቸው እንዲጠብና አንድን አቅጣጫ ብቻ እንዲከተሉ ሊያደርግ ይችላል። ስለሆነም ምግበ መረጃው ዕጩ መምህራኑ ትዕዛዝና ምክርን ብቻ ጠባቂዎች እንዳይሆኑ እና የራሳቸውን አማራጮች በመጠቀም በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያዳብሩ የማድረጉ ተግባር ትኩረት ሊሠጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ከዚህ በማስከተል ምግበ መረጃው በምን በምን ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሰጠ እንመለከታለን።

### 4.3.4 የምግበ መረጃ መስተጋብሩ ትኩረት

በመቅረፀ ድምፅ የተቀዳው መረጃ እንደሚያመለክተው ስፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራኑ በድኅረ የማስተማር ልምምድ የሚያካሂዱት የምግበ መረጃ መስተጋብር ያተኮረባቸው ነጥቦች ከድግግሞሽ ብዛትና ከተሠጣቸው የጊዜ ሽፋን አንፃር ሲታዩ ያላቸው ቅደም ተከተል የሚከተለው ነው፤

1. ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም
2. የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴ ተማሪ ተኮር ስለመሆኑ
3. የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም

4. የተግባሮች ቅደም ተከተላዊ አቀራረብ
5. የተማሪዎች/በተለይ የሴቶች/ ተሳትፎ
6. የጥቁር ሠሌዳ አጠቃቀም
7. የድምፅ ሁኔታ
8. የቋንቋ አጠቃቀም

እነዚህ ነጥቦች በምዕራፍ ሦስት ላይ የተገለፀውን የግምገማ ቅፅ ሁለተኛ ክፍል መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው። የግምገማ ቅፁ ለትምህርት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም 16% ለክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ትግበራ ደግሞ 42% እንዲይዝ የተዘጋጀ ነው። ሱፐርቫይዘሮቹ የመማር ማስተማሩን ልምምድ ሲከታተሉ ቅፁን እየተከተሉ ነጥብ ይሠጣሉ (ይሞላሉ)። በግምገማ ቅፁ ሦስተኛ ክፍል ላይ የሰፈሩትን ነጥቦች በተመለከተ ግን መረጃ የሚያገኙት በኮሌጁ ደረጃ ከተቋቋሙ የትምህርት ቤት ተመክሮና የማስተማር ልምምድ ከሚቴዎች እና ከተባባሪ መምህራን መሆኑን የዚህ ጥናት አቅራቢ ከአንዳንድ ሱፐርቫይዘሮች ጋር ባካሄደው ቃለ መጠይቅ ማረጋገጥ ችሏል።

ሱፐርቫይዘሮች ተመሳሳይ የሱፐርቪዥን መከታተያና መገምገሚያ ቅፅ መከተላቸው የሱፐርቪዥኑን አተገባበር ወጥ በማድረግ በኩል አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። ሆኖም ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሱፐርቪዥኑ ግምገማና ምዘና ተኮር በመሆኑ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ነጥቦች በተመለከተ የሚሠጡ ምገባ መረጃዎች በዕጩ መምህራኑ ዘንድ ማስተማርን የመማር ንሸ የመፍጠር ሃይል ይኖራቸዋል ለማለት አያስደፍርም።

ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የግምገማ ቅፅ መሠረት በማድረግ ሱፐርቫይዘሮች የሚሠጡት ምገባ መረጃ በይበልጥ ያተኮረው በዕጩ መምህራኑ ጠንካራ ጎን ላይ ነው ወይስ በደካማ ጎኖቻቸው ላይ የሚለውን መፈተሽ አንዱ የዚህ ጥናት ዓላማ ነው። በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ጊዜ እንደተገለፀው ምገባ መረጃ የተሻለ ውጤት ማምጣት ላይ ያነጣጠረ፣ የመሥራት ፍላጎትን የሚያነሣሣ ወሩህ ተስፋን አመልካች ሊሆን ይገባል። ይህ ዕውን ሊሆን የሚችለው ደግሞ ምገባ መረጃው የዕጩ መምህራኑን አዎንታዊ ጎኖች በማጉላት ድክመቶቻቸውን ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ብቃቱ እንዳላቸው በማመልከት ላይ ያተኮረ ሲሆን ነው። ይህንን በተመለከተ ለዕጩ መምህራኑ ጥያቄ ቀርቦላቸው ቀጥሎ ያለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 25- የምገባ መረጃው ትኩረት።

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 19 | የሱፐርቫይዘሩ ምገባ መረጃ ለደካማ ጎኔ የሚሰጠው ትኩረት ከሚሰጠው በላይ ነው። | 32<br>45% | 11<br>15.4% | 28<br>39.4% | - |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው 32 (45%) መላሾች በድኅረ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ያገኙት ምግበ መረጃ በደካማ ጐናቸው ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት እንዳደረገ ገልፀዋል። 28(39.4%) መላሾች ደግሞ ምግበ መረጃው ለደካማ ጐኖች የበለጠ ትኩረት እንደሰጠቱን ገልፀዋል። 11(15.4%) ግን ምግበ መረጃው በየትኛው ላይ ይበልጥ እንዳተኮረ ማስታወስ ወይም መወሰን ተሥኗቸዋል።

በዕጩ መምህራኑ ማስታወሻ ላይ የምግበ መረጃን ትኩረት በተመለከተ ከሠፈሩ አስተያየቶችም አብዛኞቹ (60% ያህሉ) በደካማ ጐን ላይ ይበልጥ ያነጣጠረ መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው።

አሥረጅ፦

1. አብዛኛው ትኩረቱ በደካማ ጐኖች ላይ ነበር።
2. ስለጠንካራም ሥለ ደካማ ጐኖችም አስተያየት ተሰጥቷል፤ ነገር ግን ሥለደካማ ጐን የተሰጠው ያመዝናል።

የዚህ ዓይነት ይዘት ያላቸው አስተያየቶች በየማስታወሻዎቹ ላይ በተደጋጋሚ ይታያሉ። በሙትረፀ ድምፅ በተቀዳው ውይይት ላይ እንደሚታየውም ብዙዎቹ ምግበ መረጃዎች ጠንካራና ደካማ ጐኖችን የጠቆሙ ቢሆኑም ድግግሞሹ ሲታይ ውይይታቸው ከተቀዳው ዘጠኝ ሱፐርቫይዘሮች ውስጥ በተለይ ሰባቱ በደካማ ጐን ላይ የበለጠ ትኩረት እንደሠጡ መረዳት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ በአንዳንዶቹ ዘንድ ድክመቶች የቀረቡት ገና ከውይይቱ መነሻ ላይ ነው። ለአሥረጅ ያህል አለፍ አለፍ እንመልከት፤

ሀ. እንግዲህ ቅድም ባስተማርሽው መሠረት በታዩ አንዳንድ ችግሮችና ጥንካሬዎች ዙሪያ ነው የምንነጋገረው። እና መጀመሪያ ላይ አንቺ ያስቀመጥሽው ዓላማ የንግድን ምንነት ያብራራሉ የሚልና ሌሎች ተመጋጋቢ ዓላማዎች አስቀምጠሻል። እንደነዚህ ያሉ ዓላማዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ስላልሆኑ ወደፊት ብታስተካክይ ጥሩ ነው።

(ሱፐርቫይዘር 4 ውይይት 2)

ለ. ከሌሰንፕላንሽ እንጀምርና ዓላማው ላይ ይረዳሉ ያልሽው ከዝርዝር ዓላማ አጻጻፍ አንፃር ሲታይ ተገቢ አልነበረም። አጠቃላይ ነው። "SMART" መሆን አለበት እየተባላችሁ ተምራችሁ የለም እንዴ!

(ሱፐርቫይዘር 9 ውይይት 1)

ሐ. እሺ ድንበሬ... በማስተማሩ ሂደት የተመለከትኳቸውን አስተያየቶች እንደሚከተለው አቀርብልሻለሁ። በምሠጣቸው አስተያየቶች ላይ የራስሽን አሥተያየት ማቅረብ ይፈቀድልሻል።... በቅድሚያ ሌሰንፕላንሽን ሥንመለከት ዝርዝር ዓላማዎች አሉ። ከነዚህ ዝርዝር ዓላማዎች መካከል የመጀመሪያው" ከልዩ ልዩ ምንጭ መረጃ መሠብሠብን ይገነዘባሉ" ይላል። ይህ ዓላማ የሚለካ አይደለም። ጥቅል ነው።...

(ሱፐርቫይዘር 5 ውይይት 1)

Growers and Walters (1983) እንደገለፁት ሱፐርቫይዘሮች የሚሠጡት ምግበ መረጃ የዕጩ መምህራኑን የመማተኛ መብት የሚጋፋና ደካማ ጎኖቻቸውን ሁሉ በነቂስ በመዘርዘር የሚያስጨንቃቸው እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል።

በድኅረ የማስተማር ልምምድ በሚካሄደው የምግበ መረጃ መሥተጋብር የሚነሡ ጉዳዮች ለሁለቱም ተሥተጋባሪዎች ፍንትው ብለው ሊታዩ ይገባል። ይህ ዕውን እንዲሆንም በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ሥር እንደተገለፀው ምግበ መረጃው በተቻለ መጠን ዝርዝርና ውሡን እንጅ አጠቃላይ ይዘት ያለው መሆን የለበትም።

ከላይ ሲል የተገለፀውን ግንዛቤ መሠረት በማድረግ በጥናቱ የቀረቡ ምግበ መረጃዎች ሲፈተሹ በመጠኑ ዝርዝራዊነትና ውሡንነት የተንፀባረቀባቸው ሆነው ተገኝተዋል። ለአሥረጅነት ያህል የሚከተሉትን ከመቅረፀ ድምፅ የተገኙ መረጃዎች መጥቀስ ይቻላል።

ሱፐርቫይዘር፦ እንዳንድ ቃላትን ሥትፅፊ የፊደላትን ቅርፅ የጠበቁ ቢሆኑ፤ ፊደላትንና ቃላትን በጽሁፍሽ ውስጥ ባትዘሊ። ለምሣሌ ማስረጃ ሊጠቅሥልሽ እችላለሁ። "ውሀ እና ሕይወት ግንኙት አላቸው" ብለሽ ሥትፅፊ "ውሃ ሕይወት ግንኝነት አላቸው" አልሽ። "እና" የሚለው ተረፈ። ግንኙነት የሚለውን ቃል ሥትፅፊም "ኙ" "ኘ" ሆኖ ነው የቀረበችው ቅጥል አልነበራትም።... ውሃ ባለበት ብለሽ ስትፅፊም "ዓባት" ነበር ያልሽው። እንደ አማርኛ ቋንቋ መምህርነትሽ ትኩረት ማድረግ አለብሽ።

(ሱፐርቫይዘር 7 ውይይት 1)

ሱፐርቫይዘር፦ ... ሚዲያ መጠቀምሽ ጥሩ ነው። ነገር ግን ሚዲያው የሥነ ቃልን ትርጉም ወይም ዘርፎችን የሚዘረዝር ቻርት ብቻ መሆን አልነበረበትም። ከዚህ ይልቅ ሥንቃሉ ራሡ ክፍል ውስጥ

የሚመጣበት ሁኔታ መፈጠር ነበረበት፡፡ ለምሳሌ የሠርግ ዘፈን አለ፡፡ ተረት አለ፡፡ ዕንቆቅልሽ አለ.... እንደነዚህ ያሉትን በቴፕ በመቅዳት ብታሰማን። ወይም ተማሪዎች እንዲከወኑት ብታደርጊ ኖሮ ሥነ ቃሉን ከነአደራረጉና ድባቡ ማለትም ስሜቱ ማግኘት ቻልሽ ማለት ነበር፡፡

(ሉፕርቫይዘር 6 ውይይት 2)

እነዚህ ለአስረጅነት የቀረቡ ምገበ መረጃዎች የዕጩ መምህራኑ ድክመት የት ላይ እንደነበረ ጠቅሰው የሚጠቁሙ እና አብነት በማቅረብ ግልፅ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ሱፐርቫይዘሮች ከፍ ሲል በተጠቀሰው ዓይነት የዕጩ መምህራኑን ድክመት ያመላከቱ ቢሆኑም አንዳንዶች ግን ይህን መንገድ አለመከተላቸውን የሚጠቁሙ መረጃዎች በዕጩ መምህራኑ ማስታወሻዎች ላይ እንደሚከተለው ሠፍረው ይገኛሉ፤

አስረጆዎች፦

ሀ ከምልከታ በኋላ የተወሠነ ነገር ተናግሮ ነበር። ይህም በእኛ በእጩ መምህራን ላይ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉብን ሰብስቦ ተናግሯል፡፡ ነገር ግን እነዚያን ችግሮች እንዴት ማስተካከል እንደምንችል አልጠቆመንም፡፡ ለምሳሌ፤ ከእናንተ መሀል ሊያስተምር ሁለት ተማሪዎች ተጣልተው ለያይታችሁ ካስቀመጣችኋቸው በኋላ እርምጃ አልወሠዳችሁም ብሏል፡፡ እርምጃው ምን መሆን እንዳለበት ሥነጠይቅ የተሠጠን ምላሽ አማራጭህን ነዋ! በማለት ምንም አማራጭ ሳይጠቁመን ሄዷል፡፡

ለ ዝም ብሎ ደካማ ጎኖቻችንን የአጠቃላዩ በአንድ ላይ ነግሮን መሄድ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደካማ ጎን ለአንተ ወይም ለአንቺ ነውና አሻሽል/ይ/ ብሎ ሥላልተናገረ የገባን ነገር የለም፡፡

ሐ ሱፐርቫይዘሩ በየክፍሉ ለ15 እና 20 ደቂቃ ያህል እየገባ ከመገመገ በኋላ በስረፍት ሞላውን በአንድ ላይ ሰብስቦን ብዙ ጠንካራ ጎኖችን ነው የተመለከተኩት፡፡ መጠነኛና ጥቃቅን ሥህተቶች ናቸው በአንዳንዶቻችሁ ላይ የታዩት፡፡ የብላክቦርድ አጠቃቀም፣ ሌሰንፕላን አወጣጥ ላይ የአላማና የተግባር አሠፋፈር... ናቸው እንደ ድክመት የያዝኳቸው በተረፈ ጥሩ ነው በርቱ.. በማለት ተቻኩሎ ጥሎን ሄደ፡፡

እንደነዚህ ያሉ ምገበ መረጃዎች ተፈላጊውን መልዕክት በግልፅ አያስተላልፉም። በመሆኑም ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን ድርጊት መለስ ብለው እንዲቃኙ ሊያደርጉ አይችሉም። ምገበ መረጃው ዕጩ መምህራኑ ደካማና ጥንካሬያቸውን የሚያዩበትና ለተሻለ ብቃት የሚዘጋጁበት እንዲሆን ዝርዝር እና ውሑን ሆኖ ከመቅረብ በተጨማሪ በቂ የጊዜ ትኩረት የተቸረው ሊሆንም ይገባል። ይህንን በተመለከተ ለዕጩ መምህራኑ የቀረበውን ጥያቄና የተገኘውን ምላሽ ቀጥለን እንመልከት።

ሠንጠረዥ 26፡- ለድጋፈ የማስተማር ልምምድ ውይይት የተሠጠው ጊዜ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 18 | በድጋፈ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በቂ የውይይት ጊዜ አልነበረንም። | 21<br>29.5% | 14<br>19.7% | 36<br>50.7% | - |

ሠንጠረዥ ሃያ ስድስት እንደሚያሣየው በድጋፈ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር ያደረጉት ውይይት በቂ ጊዜ እንደተሠጠው የገለፁት 36(50.7%) ሲሆኑ 21(29.5%) በቂ ጊዜ እንዳልተሰጠ እንዳልተወያዩ ገልፀዋል። 14(19.7%) ግን የውይይቱ ጊዜ በቂ መሆን አለመሆኑን በእርግጠኝነት መግለፅ አልቻሉም።

በድጋፈ የማስተማር ልምምድ በቂ የውይይት ጊዜ እንደነበራቸው የጠቆሙ ዕጩ መምህራን 50.7% ያህል ብቻ መሆናቸው ምገበ መረጃው በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት እንደማያስደፍር ያመለክታል። ለዚህ እጥረቱ አንዱ ምክንያት ቀደም ሲል የተገለፀው የሱፐርቫይዘሮችና የዕጩ መምህራኑ ቁጥር አለመመጣጠን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህ ጉዳይ ሱፐርቫይዘሮች ስለ ማስተማር ልምምዱና ሱፐርቪዥን አተገባበሩ ያላቸውን አስተያየት እንዲገልፁ በቀረበላቸው የዕሑፍ መጠይቅ ላይ እንደሚከተለው ተጠናክሮ ይገኛል።

ሀ በአንድ ግምገት ጊዜ ውስጥ ከሃያ አምስት በላይ ዕጩ መምህራንን መገምገምና አስተያየት መስጠት እጅግ አስቸጋሪ ነው። በዚህ ላይ የዕጩ መምህሮች ክፍለ ጊዜ መደራረብና አለመመቻቸት ሌላው ችግር ነው።

ለ በሁለት ወረዳዎች እና በአራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችን ለመገምገም ከወዲያ ወዲህ ስል ነበር የቆየሁት። በትራንስፖርት ችግርና ፍለጋ የሚባክነው ጊዜም ቀላል አልነበረም።

በዚህ ምክንያት ከእያንዳንዱ ዕጩ መምህር ጋር ሠፋ ያለ ውይይት ለማድረግ ችግሮች ነበሩ።

ድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት በቂ ጊዜ እንዳያገኝ ምክንያቱ ከላይ የተገለፀው የሱፐርቫይዘሮች እና የዕጩ መምህራን ቁጥር አለመጣጣምና የመርሀ ግብሩ አለመመቸት ብቻ እንዳልነበረ የሚጠቁሙ ሌሎች ምክንያቶችን ጭምር አንዳንድ ዕጩ መምህራን በማስታወሻቸው ላይ አስፍረዋል።

አስረጆዎች፦

ሀ. ጊዜ የለኝም ብሎ ተመልሶ ለመሄድና አገሩ ለማደር ስለሚፈልግ ዝም ብሎ የአጠቃላዩን በአንድ ላይ ነግሮን ብቻ ነበር የሄደው።

ለ. ሱፐርቫይዘሩ ሀገሩን ሊወደው ካለመቻሉ የተነሣ መጥቶ የተወሠነ ተግሬ ዝምግም ተመልሶ ደብረ ማርቆስ ሄዶ ስለሚያድር ብዙም ጊዜ ሰጥቶ ስላልተወያየን በተሠጠን አስተያየት ደካማ ጐን ላይ መነጋገር አልቻልንም።

አምረጆዎች፦ በሱፐርቫይዘሮች ዘንድ ለሱፐርቪዥኑ ተግባር በተለይም ለምገበ መረጃው ተገቢ ትኩረት ያለመስጠት ሁኔታም እንዳለ ይጠቁማል።

በተጥግዶ ፅሁፎች ቅኝት ውስጥ እንደተገለፀው ምገበ መረጃ ዕጩ መምህራኑ ስህተቶቻቸውን ለማረምና ወደተሻለ ብቃት ለመሸጋገር የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚያገኙበት፣ ሱፐርቫይዘሮችም የሥልጠናው ዓላማ ምን ያህል እንደተሳካ የሚረዱበት ቁልፍ የሥልጠና አካል ነው። ስለሆነም የቅድሚያ ትኩረት አግኝቶ ሊተገበር ይገባል።

## 4.4 የጥናቱ ተተኳሪዎች ምገበ መረጃን፣ ሱፐርቪዥንንና፣ የማስተማር ልምምድን በተመለከተ ያላቸው አስተያየት

Reed and Bergeman (1995) እና Livingstone (2001) እንዳሥረዱት የማስተማር ልምምድና ሱፐርቪዥን ግብ መቺ ሊሆን የሚችለው በመርሀ ግብሩ ተዋናይ የሆኑ አካላት በአስፈላጊነቱና አተገባበሩ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ሲያሠርፁ ነው። ይህን ሃሣብ መሠረት በማድረግ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ ዕጩ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ምገበ መረጃን፣ ሱፐርቪዥንና በጥቅሉም የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ ያላቸውን አስተያየት ለመቃኘት ተሞክሯል።

### 4.4.1 የዕጩ መምህራን አስተያየት

#### 4.4.1.1 ዕጩ መምህራን ስለ ምገበ መረጃው ፋይዳ ያላቸው አስተያየት፡፡

በድጋሬ የማስተማር ልምምድ ዕጩ መምህራን ከሱፐርቫይዘሮቻቸው ጋር የሚያካሂዱት የምገበ መረጃ መስተጋብር ሥህተቶቻቸውን ለማረምና ወደተሻለ ብቃት ለመሸጋገር የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚያገኙበት ነው፡

ቀጥሎ የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ዕጩ መምህራኑ በምገበ መረጃ መስተጋብሩ ተጠቃሚ ሥለመሆን አለመሆናቸው መረጃ ለማግኘት ሲባል የቀረቡ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 27፦ የምገበ መረጃው ፋይዳ በዕጩ መምህራን አተያይ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | ያልሞሉ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5|4 | 3 | 2|1 | |
| 23 | ከሱፐርቫይዘሬ የማገኘው ምገበ መረጃ የማስተማር ብቃቴን እንዳሻሽል ያደረገልኝ እጅግ አጋዥ ነው፡፡ | 22<br>30.9% | 11<br>15.4% | 38<br>53.5% | - |
| 28 | ከሱፐርቫይዘሬ በተሠጠኝ ምገበ መረጃ ተደስቻለሁ፡፡ | 34<br>47.8% | 13<br>18.3% | 24<br>33.8% | |

በሠንጠረዥ 27 ተራ ቁጥር 23 ለቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ መላሾች 22(30.9%) ሲሆኑ፣ አሉታዊ መላሾች ደግሞ 38(53.5%) ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 11(15.4%) ቁርጠኛ መልስ የላቸውም፡፡ በተራ ቁጥር 28 ዕጩ መምህራኑ ከሱፐርቫይዘሮቻቸው በሚሠጣቸው ምገበ መረጃ መርካት አለመርካታቸውን ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 34(47.8%) ያህሉ ተደስቻለሁ ሲሉ 24(33.8%) ደግሞ አለመደሠታቸውን ገልፀዋል፡፡ 13(18.3%) ስሜታቸውን ወሥነው መግለፅ አልቻሉም፡፡

በሠንጠረዥ 27 ላይ የሠፈረው መረጃ ቀደም ሲል በሠንጠረዥ 24 እና 25 ላይ የተተነተኑትን ሚናና የምገበ መረጃውን ትኩረት በተመለከተ ከቀረበው ጋር ሲነፃፀር በመጠኑም ቢሆን ያለመጣጣም ሁኔታ ይታይበታል፡፡ ቀደም ሲል የቀረቡት መረጃዎች ተተንተነው በምገበ መረጃ መስተጋብሩ ዕኩል ወይም ተመጣጣኝ ተሣትፎ እንዳልነበራቸውና የምገበ መረጃው መስተጋብር በአብዛኛው በደካማ ጐን ላይ ያተኮረ እንደነበር አመላክተዋል፡፡ ይህ ጎደሎነቱ ሁኔታ ደግሞ ተነሣሽነትን ከመፍጠርና ብቃትን ከማሻሻል አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ሥር በቀረቡ ንድፈ ሃሣባዊ መረጃዎች ማረጋገጫ የሠጠበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በሠንጠረዥ 27 ላይ ምገበ መረጃው ብቃታቸውን ለማሻሻል እንዳላገዛቸውና በዚህም እርካታ እንደተሠማቸው የገለፁ ዕጩ መምህራን ቁጥር



UNIVERSITY
LIBRARY

እጅግ አናሳ እንደሚሆን ሲጠበቅ ብዙም አንሶ አልተገኘም። ለዚህ ምክንያቱ ቀደም ሲል እንደታየው ዕጩ መምህራን ምክር ልክነን እንደ በጉ ነገር መቁጠራቸውና የምግበ መረጃው አቀራረብ ዓመቺን ዝርዝር /ውሁን/ በመሆኑ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

### 4.4.1.2 ዕጩ መምህራን ሥለ ሱፐርቫይዘሮቻቸው ያላቸው ግምትና አስተያየት፣

በተጣማሪ ዕሁፎች ቅኝት ላይ እንደተገለፀው የሱፐርቫይዘሮች አቢይ ተግባር ዕጩ መምህራን በማስተማር ሙያቸው ወደተሻለ ብቃት እንዲረማመዱ ማገዝ ነው። ይህንን መሠረት ያደረገ መነሻ በማድረግ ለዕጩ መምህራን ሶስት ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የሠጡአቸውን ምላሾች ቀጥለን ተራ በተራ እንመለከት፣

ሠንጠረዥ 28፦ ዕጩ መምህራን ስለ ሱፐርቫይዘሮቻቸው ያላቸው ግምት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 4 | ሱፐርቫይዘሬ ለሱፐርቪዥን ተግባር በቂ ችሎታ አለው። | 31<br>43.6% | 17<br>23.9% | 2<br>30.9% | - |

ሠንጠረዥ ፳ እንደሚያሳየው ሱፐርቫይዘራቸው ሱፐርቫይዘራዊ ብቃት እንዳለው የገለፁ ዕጩ መምህራን 31(43.6%) ሲሆኑ፣ ብቃት የለውም የሚል ምላሽ የሰጡ ደግሞ 23(30.9%) ናቸው። 17(23.9%) ግን ቁርጠኛ መልሥ የላቸውም።

ሠንጠረዥ 29፦ ዕጩ መምህራን ስለሱፐርቫይዘራቸው ለእነሱ ድጋፍ ሰጭና አበረታች ሥለመሆኑ ያላቸው አስተያየት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 12 | ሱፐርቫይዘሬ የማስተማር ልምምድ ወደ ሚካሄድበት የሚመጣው እኔን ለማበረታታና ለመደገፍ ነው። | 29<br>40.8% | 20<br>28.1% | 22<br>30.9% | |

ሱፐርቫይዘራቸው ደጋፊያቸውና አበረታቻቸው ሥለመሆኑ አዎንታዊ መልስ የሰጡ 29(40.8%) ናቸው። 22(30.9%) ደግሞ ሱፐርቫይዘራቸው የማስተማር ልምምድ ወደሚያካሂዱበት የሚመጣው እነሱን ለመደገፍና ለማበረታታት ነው ብለው አያምኑም። የቀሩት 20(28.1%) ግን ወስነው መመለስ አልቻሉም።

ሠንጠረዥ 30፦ ዕጩ መምህራኑ ስትርቫይዘራቸው ሥለ እነሱ ያለውን አመለካከት በተመለከተ ያላቸው ግምት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5፤4 | 3 | 2፤1 | ያልሞሉ |
| 26 | ስትርቫይዘሩ ለኔ ያለው ግምት ዝቅተኛ ነው | 28<br>39.4% | 11<br>15.5% | 32<br>45.1% | |

በሠንጠረዡ ላይ በቀረበው መረጃ መሠረት 28(39.4%) ዕጩ መምህራን ስትርቫይዘራቸው ለእነሱ ዝቅተኛ ግምት አለው ብለው ይገምታሉ ወይም ያስባሉ። 32(45.1%) ደግሞ ስትርቫይዘራቸው ዝቅተኛ ግምት ይሠጡናል የሚል ዕምነት ወይም ግምት የላቸውም 11(15.5%) ግን ቁርጠኛ መልሥ መስጠት አልቻሉም።

ከዛ ሌላ በሠንጠረዥ 28 እና 29 እና 30 የቀረቡት መረጃዎች በስትርቫይዘሮችና በዕጩ መምህራኑ መካከል ሊኖር የሚገባው መልካም ግንኙነት በጥሩ ደረጃ ላይ አለመገኘቱን ያጠቁማሉ።

በስትርቫይዘሮችና በዕጩ መምህራኑ መካከል መልካም ግንኙነት ካልሠፈነ ምግበ መረጃው ማስተማርን የመማር ጉጉት ከመፍጠርና ብቃትን ከማጎልበት አንፃር የረባ ሚና ይጫወታል ተብሎ አይታሰብም።

በዛ ያሉ ዕጩ መምህራን ስትርቫይዘሮቻቸው ለጉብኝት ሲመጡና በክፍል ውስጥ የማስተማር ተግባራቸውን ሲከታተሉ የደስታና የመረጋጋት መንፈስ እንደማይሠማቸው በማስታወሻዎቻቸው ላይ ገልፀዋል። ለአሥረጅ ያህል ቀጥሎ ያሉትን እንመልከት፤

ሀ ስትርቫይዘራችን ሲመጡ በጣም እፈራለሁ። ምክንያቱም ውጤት ነዋ! ያውም ባለ አሥራ ሁለት ክሬዲት።

ለ ከፍርሃቱና ከመደናገጤ የተነሣ በሌስንፕላኔ ላይ ያሠፈርኩትን መጠበቅና መጨረስ አልቻልኩም።

ሐ ስትርቫይዘራችን ለክፍል ምልከታ ሲመጡ የሚሠማኝ ስሜት ብዙ ጊዜ ድንጋጤና መረበሽ ነው። ምክንያቱም የእነሡ መምጣት ከውጤት ጋር ስለሚያያዝ ነው። በእሡ ፊት ስናገር ብሣሣትስ፣ ይታዘበኛል፣ ሠነፍ ነው ይለኛል፣ ማርኬን ይቀንሥብኛል፣ ተማሪዎች ይጠቋቆሙብኛል፣ ይሥቁብኛል፣ ይንቁኛል የሚለው ፕጥብ በደንብ የምናውቀውን ጥምር እንዳናቀርብ ያደርገናል።

መ የማስተማር ዘዴዬ ድር ገለፃ ነበር ስትርቫይዘሩ ሲመጣ ግን ወደ ቡድን ሥራ ተቀየረ።

የቀረቡት መረጃዎች የሱፐርቫይዘሮች ለጉብኝት መምጣትና ምልከታ ማካሄድ በዕጩ መምህራን ዘንድ መደናገጥንና መረበሽን እንደፈጠርና የተሻለ ውጤት አገኛለሁ በሚል አስተሳሰብ የማስተማር ዘዴያቸውን እስከመቀየር እንደደረሡ ያመላክታሉ። በዚህ ዓይነት በራስ አለመተማመንንና መደናገጥን የሚገልፁ ማስታወሻዎች 55% ያህል ይሆናሉ። ለዚህ ምክንያቱ ሱፐርቪዥኑን ከምዘና ጋር መያያዙ እና ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዕጩ መምህራኑ፣ ሱፐርቫይዘር የእነሡ ደጋፊና አበረታች ሥለመሆኑ ያላቸው እመኔታ ዝቅተኛ መሆን ነው ለማለት ያሥደፍራል።

### 4.4.1.3 ዕጩ መምህራን ሥለሥርዓተ ትምህርቱ ያላቸው አስተያየት፤

መምህራንን ለማሠልጠን የሚዘጋጅ ሥርዓተ ትምህርት ሠልጣኞች ማስተማርን ሊማሩ በሚችሉበት አግባብ መቀረፅ እንዳለበት በምዕራፍ ሁለት ላይ የሠፈረው ንድፈ ሃሣባዊ መረጃ ያሥገነዝባል። ይህን በተመለከተ ለዕጩ መምህራን ጥያቄ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሠጥተዋል፡

ሠንጠረዥ 31፦ ዕጩ መምህራን ሥለሥርዓተ ትምህርቱ ያላቸው አስተያየት፤

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5\|4 | 3 | 2\|1 | ያልሞሉ |
| 1 | ሥርዓተ ትምህርቱ ማስተማርን እንድማር በሚችልበት አግባብ የተቀረፀ ነው | 40<br>56.3% | 15<br>21.1% | 16<br>23.8% | - |

ሠንጠረዥ 31 ላይ በሠፈረው መረጃ መሠረት 40 (56.3%) ዕጩ መምህራን ሥርዓተ ትምህርቱ ጥንቃቄ ተቀርጿል የሚል አመለካከት አላቸው። 16(23.8%) ደግሞ ሥርዓተ ትምህርቱ ጥንቃቄ አልተቀረፀም ባዮች ናቸው። 15(21.1%) ግን ሥለሥርዓተ ትምህርቱ አግባብነት ቁርጠኛ ምላሽ የላቸውም።

በሥርዓተ ትምህርቱ አግባብነት ላይ አዎንታዊ አመለካከት ያሠረፁ ዕጩ መምህራን 56.3% ያህል ብቻ እንደሆኑ ከፍ ሲል የቀረበው ሠንጠረዥ ያሣያል ለዚህ ምክንያቱ በተለይ ከትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል የሚያመላክቱ አንዳንድ መረጃዎች በዕጩ መምህራን የክፍት ጥያቄ መልሶችና ማስታዎሻዎች ላይ ይገኛሉ። አንዳንዶቹን ለማሥረጃ ያህል ቀጥለን እንመልከት፤

ሀ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ የሚሠጥበት ጊዜ በጣም በዝቷል። በሁለት ወይም ሶስት ወር ቢያልቅ ይሻላል፡፡

ለ. እንደኔ ከሆነ መቅረት ያለበት ነው የመምህርነትን ሥራ እንዳንወደው ያደረገ ነው።

ሐ. የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምዱ ሁለተኛ ዓመትን ከጨረሱን በኋላ ቢሆን።

መ. የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ ባይኖር። ምክንያቱም የአጋር ት/ቤት መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎቹ ለኛ በጐ አመለካከት የላቸውም።

ሠ. የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ኮሌጁ በቅርበት እንዲከታተለው ምድባችን ባቅራቢያው ቢሆን

ረ. የኮሌጁ መምህራን ሱፐርቪዥን ለማድረግና ለመገምገም በዓመት አንድና ሁለት ጊዜ ብቻ ከሚመጡ በተከታታይ በየሴሚስተሩ ሶስት ጊዜ እንኳ መጥተው ምገባ መረጃ ቢሠጡ።

ሰልጣኝ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እና የሱፐርቪዥን አተገባበርን በተመለከተ ለክፍት ጥያቄ በሠጧቸው መልሶችና በማስታወሻዎቻቸው ባሠፈሯቸው አስተያየቶች ላይ በጣም ጉልቶ የሚታየው "መርሀ ግብሩ የሚካሄድበት ጊዜ አንድ ዓመት ሙሉ መሆን የለበትም፤ ማጠር አለበት" የሚለው ነው። ብዙዎቹ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምድ ንድፈ ሃሳብን ከተግባር ጋር ለማገናኘትና ልምድ ለመቅሠም ጠቀሜታ እንዳለው ቢያምኑም ፕሮግራሙ ከሁለት እና ሶስት ወራት በላይ መፍጀት የለበትም የሚል አመለካከት አላቸው። በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ከአሠልጣኝ መምህሮቻቸው ጋር ለሱፐርቪዥን ተግባር የሚያገኙት ለአንድ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ መሆኑ ደግሞ ሌላው ቅሬታቸው ነው።

## 4.4.2 የሱፐርቫይዘሮች አስተያየት

### 4.4.2.1 የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አፈፃፀም መመሪያና ሰልጣኝ መምህራን የተመደቡባቸውን የአጋር ትምህርት ቤቶች በተመለከተ

አንድ መርሃ ግብር ግብ መቺ የሚሆነው ግልፅና ተተግባሪ መመሪያ ሲኖረው ነው። ይህን የተመለከተ ጥያቄ ለሱፐርቫይዘሮቹ ቀርቦላቸው የሰጡትን ምላሽ ቀጥለን እንመልከት፤

ሠንጠረዥ 32፦ ሱፐርቫይዘሮች የት/ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መመሪያ ግልፅና ተተግባሪ ሥለመሆኑ ያላቸው አሥተያየት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 4 | 3 | 2 1 | ያልሞሉ |
| 8 | የኮሌጁ የት/ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አፈፃፀም መመሪያ ግልፅና ተተግባሪ ነው። | 7 | 6 | 8 | - |

ሠንጠረዥ እንደሚያሣየው የአፈፃፀም መመሪያው ግልፅና ሲተገበር የሚችል ነው በማለት አዎንታዊ መልስ የሰጡ ሱፐርቫይዘሮች ሰባት ሲሆኑ፣ ስምንቱ ደግሞ ግልፅና ተተግባሪ አይደለም የሚል መልሥ ሰጥተዋል። ስድስቱ ግን ቁርጥ ያለ መልስ አልሰጡም። በአፈፃፀም መመሪያው ላይ በርከት ያሉ ሱፐርቫይዘሮች አሉታዊ ምላሽ መስጠታቸው መርሃ ግብሩን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር አሳሳቢ የሆነ ችግር መኖሩን ያመላክታል።

ሱፐርቫይዘሮቹ የመመሪያውን ተተግባሪነት በተመለከተ አሉታዊ ምላሽ እንዲሠጡ ምክንያት የሆኗቸው ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ከእዚህ በማስከተል በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የሠጧቸው መልሦች ይጠቁማሉ።

ሠንጠረዥ 33፦ የማስተማር ልምምድንና ሱፐርቪዥንን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎች ሥለመኖራቸው።

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 4 | 3 | 2 1 | ያልሞሉ |
| 5 | ልዩ መምህራኑ የተመደቡባቸው አጋር ት/ቤቶች ከኮሌጁ የራቁና የተበታተኑ ሥለሆኑ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ለመስጠት አያመቹም። | 17 | 2 | 2 | - |
| 6 | በአጋር ትምህርት ቤቶች የት/ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድን መርሃ ግብር ለመተግበር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች አሉ። | 4 | 4 | 11 | 2 |

በሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 5 ላይ ልዑ መምህራኑ የተመደቡባቸው አጋር ት/ቤቶች ከኮሌጁ የራቁና የተበታተኑ በመሆናቸው ለሱርቪዥን አገልግሎት አሠጣጥ አላመቺ መሆናቸውን አሥራ ሰባት ሱፐርቫይዘሮች ገልፀዋል። ከዚህም በተጨማሪ በተራ ቁጥር 6 ላይ እንደሚታየው በአጋር ት/ቤቶች የት/ቤት ተሞክሮንና ማስተማር ልምምድን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች አሉ የሚል ግምት ያላቸው ሱፐርቫይዘሮች አራት ብቻ ናቸው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

በምዕራፍ ሦስት ላይ እንደተገለፀው ዕጩ መምህራን በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች በሚገኙ ትቤቶች መመደባቸው በአንድ በኩል ሲታይ በየትምህርት ቤቶቹ አላሥራላጊ የሰው ኃይል ክምችትና መጨናነቅ እንዳይከሠት ሊያደርግ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ከፍ ሲል በቀረቡት መረጃዎች ላይ እንደታየው ኮሌጁ የቅርብ ክትትልና የሱፐርቪዥን ድጋፍ እንዳያደርግ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም በሥልጠናው መርሀ ግብር ላይ የሚሳተፉ አካላት የሀብትን አግባብነት ጥቅምና ጉዳት እንዲገነዘቡና ሱፐርቪዥኑ ባግባቡ እንዲሠጥ የማድረጉ ሥራ ትኩረት ሊሠጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

#### 4.4.2.2 ሱፐርቫይዘሮች ሥለ ትቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምዱ ያላቸው ግምትና አስተያየት

በዛ ያሉ (85% ያህሉ) የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ የሥልጠናው አካል ሆኖ መቀጠል እንዳለበት ያምናሉ። ሆኖም በአፈፃፀሙ ላይ የጉሉ ችግሮች ሥላሉበት ተፈላጊውን ውጤት ማምጣት እንዳልቻለና በዚሁ ከቀጠለም አሉታዊ ገፅታው ሊያመዝን እንደሚችል ሥጋት አላቸው። ይህን በተመለከተ የሚከተሉትን አስተያየቶች ሠንዝረዋል።

ሀ የትቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ ጥሩ መምህር ለመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ማንም አይክድም። ነገር ግን በአፈፃፀም ደረጃ የአጋር ትቤቶች ሥርጭት የተበታተነ መሆኑ፣ የአጋር ትቤቶች መምህራን ለፕሮግራሙ ትኩረት ባለመሥጠታቸው የውጤት ግሽበት መታየቱ፣ የመደበኛውን የማስተማር ሂደት ማጓጎሉ፣ ዕጩ መምህራኑ አልባሌ ቦታ ለመዋል መጋለጣቸው፣ ምግብ መረጃው ባግባቡ አለመሠጠቱ ዋና ዋና የአፈፃፀም ችግሮች ናቸው።

ለ የትቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ መኖሩ ጥሩ ነበር፣ ነገር ግን ጊዜው ለአንድ ዓመት ያህል የተራዘመ መሆኑ በጣም መሠላቸትን በሁሉም ዘንድ አምጥቷል።

ሐ የአጋር ትቤት መምህራን ከፍያ የለንም / የጥቅማ ጥቅም ተካፋዮች አይደለንም/ የሚል ቅሬታ ሥላላቸው ለፕሮግራሙ ቀና አመለካከት የላቸውም። በዚህ የተነሣም ለሁሉም ተማሪ ተመሣሣይ የሆነ የጋሽበ ውጤት ይሠጣሉ።

መ ፕሮግራሙ በደመነፍስ የሚመራና የጊዜ መግደያ እየሆነ ነው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ሠ. ዕጩ መምህራን በየአካባቢያቸው ሥለሚመደቡ ከትምህርቱ ይልቅ ለሌሎች ጉዳዮች ቅድሚያ ይሠጣሉ። የዘመድ አዝማድ ሥራ እንዲሠራ ምክንያትም ሆኗል።

ረ. የማስተማር ልምምዱ አንድ ዓመት ሙሉ ከሚሆንና በ2ኛ ዓመት ላይ ከሚሆን ሶስተኛ ዓመት መጀመሪያ ሰሚስተር ላይ ብቻ ቢሆን ይሻላል።

ሰ. የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ እጅግ የበዛ ጊዜ እና የበዛ "ክሬዲት ሀወር" መሠጠቱ ትክክል አይደለም። ለአንድ ኮርስ አሥራ ሁለት ክሬዲት መሥጠት ያውም ባግባቡ ክትትል ለማይደረግበት ነገር ተገቢ አይደለም።

ከላይ ሲል የቀረቡት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ስፐርቫይዘሮች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በዓላማ ደረጃ ጥሩ ቢሆንም ሲፈፀም ግን በርካታ ችግሮች አሉበት የሚል ግምትና አስተያየት አላቸው። ቀደም ሲል በዕጩ መምህራን አስተያየት ላይ እንደተመለከትነው ፕሮግራሙ ለአንድ ዓመት ያህል መሆኑን ስፐርቫይዘሮቹም የወደዱት አይመስልም። ብዙዎቹ (90%) የሚሆኑት መቀነሥ አለበት፤ ቢበዛ ለአንድ ሴሚስተር ብቻ ሊሆን ይገባል፤ ወቅቱም በሁለተኛ ዓመት ላይ ከሚሆን ይልቅ በሶስተኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ ቢሆን ይሻላል፤ የሚል አስተያየት አላቸው። ሶስተኛ ዓመት ላይ እንዲሆን የፈለጉት ዕጩ መምህራኑ በቂ ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀት ጨብጠው ለመሄድ ይችላሉ ከሚል ሐሳብ እንዲሆነም ገልፀዋል።

### 4.4.2.3 ስፐርቫይዘሮች ስፐርቪዥኑና ምገበ መረጃው ስላስገኘው ፋይዳ ያላቸው አስተያየት

በተለያዩ ፅሁፎች ላይ እንደተገለፀው የስፐርቪዥን ዓላማ ዕጩ መምህራኑ በኮሌጅ ቆይታቸው የቀሠሙትን ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀቶች በዕውናዊው የመማር ማስተማር አውድ ላይ መተግበር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ወይም ማመቻቸት ነው። የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ ስፐርቫይዘሮች ያከናወኑት የስፐርቪዥን ተግባር ስላስገኘው ጠቀሜታ እንደዲገልፁ ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ክፍት ጥያቄ ላይ ያሠፈሯቸው አስተያየቶች በአብዛኛው አሉታዊ ናቸው።

አስረጅዎች፦

ሀ. ስፐርቪዥኑ በቂውን ጊዜ የይድረስ ይድረስ በመሆኑ ጥሩ ውጤት ያመጣል የሚል ዕምነት የለኝም።

ለ. በጠባብ ጊዜ ውስጥ በርካታ ተማሪዎች እንዲገመገሙ መደረጉ በምግበ መረጃ አማካይነት ተማሪዎች ድክመት ጥንካሬያቸውን እንዲለዩና እንዲያሻሽሉ የማድረጉ ሥራ ባግባቡ አልተከናወነም፡፡ ለወደፊቱ ሥራ ያለ ጊዜ ተሠጥቶት ተከታታይ ሆኖ ቢሠጥ ይሻላል፡፡

ሐ. በአመት ለአንድና ሁለት ጊዜ ብቻ ጉብኝቶ ለተማሪዎቹ ሙያ መሻሻል የሚረዳ ምግበ መረጃ እሠጣለሁ ማለት ከንቱ ነው፡፡

መ. ሱፐርቪዥን ድጋፍና ዕርማት ለመስጠት ሳይሆን ያው እንደፈተና ውጤት ለመስጠት የሚካሄድ በመሆኑ ተማሪዎች ትኩረታቸው ለውጤታቸው እንጂ ለምግበ መረጃው አይደለም፡፡

ሠ. ሱፐርቫይዘሮች በጋራ የወሰድነው ሥልጠና ባለመኖሩ ምግበ መረጃ የምንሠጠው እንደየግንዛቤያችን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በውጤት አሠጣጥ ላይ ጭምር ችግር እያስከተለ ነው፡፡

ረ. የሱፐርቫይዘሮች ትኩረት በሥነ ዘዴ (Methodology) ላይ ብቻ መሆኑና ከዲፓርትሜንቱ ውጭ ባሉ መምህራን እንዲሠጥ መደረጉ ተፈላጊውን አጥጋቢ ውጤት ያስገኛል ብዬ አልጠብቅም፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚጠቁሙት ሱፐርቪዥን በዓላማው መሠረት ባግባቡ እንዳልተካሄደና ተፈላጊውን ውጤት ማምጣት እንዳልቻለ ነው፡፡ እነዚህ አስተያየቶች ቀደም ሲል ዕጩ መምህራኑ ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ከሠጧቸው አስተያየቶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ ሁለቱም ወገኖች (ሱፐርቫይዘርና ዕጩ መምህር) የሱፐርቪዥን አተገባበር ሂደትና በዚህ ሂደት ውስጥ ያለው የምግበ መረጃ መስተጋብር የሥልጠናውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ጠቀሜታ ከማስገኘት አንፃር ውስንነቶች እንዳሉበት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በመምህራን ሥልጠና መርሃ ግብር ውስጥ ሱፐርቫይዘሮችና ዕጩ መምህራን ዋነኞቹ ተዋንያን ናቸው፡፡ ያለ እነሱ ንቁ ተሳትፎ ሥልጠናው ግቡን ይመታል ተብሎ አይታሠብም፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል የጠቀሷቸው አስተያየቶች ተገቢ ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በክፍል አራት ይህን ጥናት ለማካሄድ የተሠበሠቡ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ የተተኳሪዎቹን ዳራ፣ በማስተማር ልምምዱ ሂደት የነበረውን የሱፐርቪዥን ሂደትና ትግበራ እንዲሁም ተተኳሪዎች ስለማስተማር ልምምዱና ሱፐርቪዥኑ ያላቸውን ግምትና አስተያየት ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ በማስከተል ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ ወደሚቀርብበት የመጨረሻ ምዕራፍ እናመራለን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣብ

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አቢይ ትኩረት በአማራ ክልላዊ መስተዳድር በሚገኘው በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በ10+3 መርሀ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድጎረ የማስተማር ልምምድ የሚካሄደውን የምገባ መረጃ መስተጋብር መፈተሽ ነው። ፍተሻው የተካሄደው ደግሞ በዋናነት የሚከተሉትን አራት ዓላማዎች መሠረት አድርጎ ነው።

ሀ ምገባ መረጃዎቹ በምልከታ በተደረሠባቸው ነገሮች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለመሆናቸውን መለየት፣

ለ በምገባ መረጃ አቀራረብ ሂደት ላይ የስፐርቫይዘሮችን የቋንቋ አጠቃቀም መመርመር፣

ሐ በምገባ መረጃ መስተጋብሩ የስፐርቫይዘሮችንና የዕጩ መምህራንን ሚና ሚዛናዊነት መመርመር፣

መ የስፐርቫይዘሮቹ ምገባ መረጃ በተለይ የሚያተኩርበትን ጉዳይና የሚቀርብበትን ሥልት ለይቶ መጠቆም፣

ሠ እጩ መምህራኑ ለምገባ መረጃው ያላቸውን አስተያየት መፈተሽ፣

እነዚህን አበይት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በመቅረፀ ድምፅ፣ በጽሁፍ መጠይቅ፣ በእጩ መምህራን ማስታወሻ፣ እንዲሁም ኮሌጁ በሚጠቀምበት የግምገማ ቅፅ አማካይነት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል። እነዚህ መረጃዎች በይዘታቸው መሠረት በየፈርጁ እየተቀመጡ እና እየተመሳከሩ ከተጣማጅ ፅሁፎች ትንተና በተገኘ ንድፈ ሃሣባዊ ግንዛቤ መሠረት ትንተናና ግምገማ ተካሂዶባቸዋል። በዚህም መሠረት ከሚከተለው ማጠቃለያ ላይ መድረስ ተችሏል።

1 ስፐርቫይዘሮች ሥለ ስፐርቪዥን አተገባበርና ምገባ መረጃ አቀራረብ ሥልጠና ያልወሰዱ ናቸው። ስፐርቪዥን የተለያዩ አቀራረቦችና መርሆዎች አሉት። የአቀራረቦቹንና የመርሆችን ምንነትና ፋይዳ በሚገባ ተረድቶ ለተፈላጊው ዓላማ ለማዋልም ሙያው የሚጠይቃቸው ክህሎቶች አሉ። ሥለሆነም ስፐርቫይዘር ሆኖ ለዕጩ መምህራን ዕገዛ የሚያደርግ ግለሰብ ሥለ ስፐርቪዥን ዓላማ፣ አቀራረብ፣ መርህ እና ሙያው ሥለሚጠይቀው ክህሎት ግንዛቤ ያገኘ ዘንድ የሥልጠና አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም። በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የማስተማር ልምምዱ ግብ መቺ እንዲሆን ለእጩ መምህራን ዕገዛ የሚያደርጉ ስፐርቫይዘሮች ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ዓይነት

ሥልጠና አልወሰዱም። በመሆኑም የሱፐርቪዥን አተገባበርና የምግበ መረጃ አሠጣጡ ከልማዳዊው መንገድ የተላቀቀ አልሆነም።

2. ሱፐርቫይዘሮች ከሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ውጭ ለሱፐርቪዥን ተመድበው ታይተዋል፡፡ የማስተማር ልምምድ ዕጩ መምህራኑ በኮሌጅ የቀሠሙትን ንድፈ ሃሳባዊ ዕውቀት በዕውነተኛው የመማር ማስተማር አውድ የሚተገብሩበት የሥልጠና አካል ነው። ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀቱ በተግባር መተርጎም አለመተርጎሙን ማረጋገጥ የሚችለው ደግሞ በዚያ ትምህርት የሠለጠነው ባለሙያ ነው። በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ግን ይህ አልተደረገም። ሱፐርቫይዘሮቹ በዋናነት ወይም በንዑስነት ባልሠለጠኑበት የትምህርት መስክ የማስተማር ልምምድ ለሚያደርጉ ዕጩ መምህራን ሱፐርቫይዘር ሆነው ይመደባሉ። ይህ ደግሞ ከትምህርቱ ዓይነት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ባላቸው ነጥቦች ላይ የሚሠጠውን ምግበ መረጃ ተገቢነትና አጥጋቢነት አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድርበት ችሏል።

3. የምግበ መረጃው ልውውጥ በመመሪያ አሰጣጥና በምክር ልገሳ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ ሱፐርቫይዘሮች ለእጩ መምህሮች መመሪያ መሥጠትንና ምክር ለግሶ እንደ ጥሩ የምግበ መረጃ አቀራረብ ቆጥረውታል። ዕጩ መምህራኑም በተለይ ምክር ለግሶ የጥሩ ሱፐርቫይዘር ተግባር ነው የሚል አመለካከት አላቸው። ይህም ዕጩ መምህራኑ የራሳቸውን አማራጮች ከመጠቀም ይልቅ በሱፐርቫይዘሮቻቸው የሚነገረውን ተቀብለው መተርጎም ላይ ብቻ እንዲያተኩሩና አንድን አቅጣጫ ብቻ እንዲከተሉ ምክንያት ሆኗል።

4. በምግበ መረጃ አቀራረብ ጊዜ የሱፐርቫይዘሮች የቋንቋ አጠቃቀም ዕጩ መምህራኑን ለተሻለ ሥራ የማነቃቃት ኃይሉ አናሳ ነው፡፡ ምግበ መረጃ ለዕጩ መምህራኑ ማስተማርን የመማር ጎዳ ሊፈጥር በሚችልበት መልኩ ሊቀርብ ይገባል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የሱፐርቫይዘሮቹ የቋንቋ አጠቃቀም የዕጩ መምህራኑን ችግር የመፍታትና ወደተሻለ ሥራ የመረማመድ ብቃት እንዳላቸው የሚያመለክት እንጂ በሥራቸው ፀፀትና ቁጭት ተሰምቷቸው እንዲወሠወሱ የሚያደርግ መሆን የለበትም። የዚህ ጥናት የመረጃ ትንተና እንደሚያሣየው ሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ሲሠጡ የሚጠቀሙበት ቋንቋ፡- ማድረግ አልነበረብህም/ሽም፣ ብታደርገው፣/ነው/ ኖሮ፣ልትገልጭላቸው/ ልትገልፅላቸው/ ይገባ ነበር፣ ማሥራር ነበረብህ/ሽ፣ እንደሡ አይደለም፣ ጥሩ መንገድ አልነበረም… ወዘተ. የሚሉ አገላለፆች በብዛትና በተደጋጋሚ ይታይበታል። እንዲህ ዓይነቱ የቋንቋ አጠቃቀም ዕጩ መምህራኑ ሥህተቶቻቸው ገዝፈው እንዲታዩአቸውና ፀፀት ወይም ቁጭት

እንዲሠማቸው ከማድረጉም በላይ ከስህተት መውጫው መንገድ አንድ ብቻ እንደሆነ አድርገው እንዲያምኑ ሊያደርግ የሚችል ነው።

5. የምግበ መረጃ መስተጋብሩ ስትርቫይዘር ተኮር ባህርይ ጉልቶ ታይቶበታል፡- በምግበ መረጃ መስተጋብር እጅግ ተፈላጊውና ውጤታማው አቀራረብ ዕጩ መምህራኑ የራሣቸውን ተግባር የሚገመግሙበትን መንገድ ማመቻቸት ነው። ምግበ መረጃው ከአንድ ወገን ብቻ የሚፈሥ መሆን የለበትም። የመረጃ ትንተናው ውጤት እንደሚያሣዬው ግን የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ ስትርቫይዘሮች አቀራረብ ባመዛኙ መራሒ (ትዕዛዛዊ) ስትርቪዥንን ነው። በመሆኑም የስትርቫይዘሮቹ ግላዊ ዳኝነት ጉልቶ ይታያል። ዕጩ መምህራኑ የራሣቸውን ተግባር በራሣቸው እይታ የሚገመግሙበትንና አማራጮችን የሚያገኙበትን እድል እንዲያጡም ምክንያት ሆኗል።

6. ስትርቪዥኑ ግምገማና ምዘና ተኮር ነው፡- የስትርቪዥን ዓላማ ዕጩ መምህራኑ ማስተማርን መማር እንዲችሉ ማገዝ ነው። በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የስትርቫይዘሮች ዋና ትኩረት ኮሌጁ ባዘጋጀው የመገምገሚያ ቅፅ መሠረት ዕጩ መምህራኑን በመገምገም ውጤት ማሥፈር ነው። ስትርቪዥኑ ለግምገማና ምዘና ቅድሚያ ትኩረት እንዲሠጥ መደረጉ ዕጩ መምህራኑ ስትርቫይዘሮቻቸው የእነሡ ፈላጊዎችና አበረታቾች መሆናቸውን በአሉታዊ መልክ እንዲመለከቱት ምክንያት ሆኗል፡ በዚህ ምክንያትም ስትርቫይዘሮቻቸው የክፍል ምልከታ ሲያካሂዱ ብዙዎቹ እጩ መምህራን ይደናገጣሉ፤ ይረበሻሉ። በድኅረ የማስተማር ልምምድ በሚኖረው የምግበ መረጃ መስተጋብርም በራሣቸው ተማምነው የመሠላቸውን ሃሣብ ከመሠንዘር ይልቅ የመሸቆጥቆጥና ፈራ ተባ የማለት ባህርይ ያሣያሉ።

7. ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት በተገቢው መንገድ አልተካሄደም፡- በስትርቪዥን አተገባበር ሂደት ውሥጥ የመጀመሪያው ሥራ ቅድመ የማስተማር ልምምድ ውይይት ማካሄድ ነው። ይህ ዓይነቱ ውይይት ዕጩ መምህራኑ በስትርቪዥኑ ዓላማና የትኩረት ነጥቦች ዙሪያ ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በሥነልቦና ዝግጁ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። የዚህ ጥናት የመረጃዎች ትንተና እንደሚያሣየው ግን ቅድመ የማስተማር ልምምድ ተገቢ ትኩረት አግኝቶ ባግባቡ አልተካሄደም። ይህም ዕጩ መምህራኑ የስትርቪዥን ዓላማና ተግባር ግምገማና ምዘና ማካሄድ ብቻ ነው የሚል ግንዛቤ እንዲይዙ ምክንያት ሆኗል።

8. ለዕጩ መምህራኑ ከአጋር ትምህርት ቤት ነባር መምህራን የሚደረግላቸው ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ አናሳ ነው፡- የአጋር ትምህርት ቤቶች ነባር መምህራን በትምህርት ቤት የተግባር ማስተማር ልምምድ ጊዜ የዕጩ መምህራኑን የዕለት ከዕለት ዕንቅስቃሴ

መስታተልና አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ በሚችሉበት መቼት ውስጥ ናቸው ሥለሆነም ሙያዊ ድጋፍ ከማድረግና ተሞክሮን ከማጋራት አንፃር የጐላ ሚና ይኖራቸዋል። የጥናቱ መረጃዎች ትንተና እንደሚያሣየው ግን ነባር መምህራን ለዕጩ መምህራኑ የሚጠበቀውን ያህል እገዛ አላደረጉላቸውም። በዕጩ መምህራንና በነባር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነትና ተደጋግፎ የላላ ነው።

9. ኮሌጁ ለሱፐርቫዥን ተግባር የሠጠው ትኩረት በቂ ሆኖ አልተገኘም፡- በትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ውስጥ ሱፐርቪዥን ቁልፍ ጉዳይ ነው። ሱፐርቪዥን ውጤታማ የሚሆነው ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ሲተገበር ነው። በደብር ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሱፐርቫይዘሮች ለሱፐርቪዥን ተግባር የሚሠማሩት በሴሚስተሩ መጨረሻ ላይ ትምህርቱ በሚጠቃለልበት ወቅት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ዕጩ መምህራኑ በተለይ በድኅረ የማስተማር ልምምድ ወይይት ላይ በሚሠጡ ምገባ መረጃዎች አማካይነት ሥራቸውን መለስ ብለው ለመቃኘትና አሻሽለው ለማቅረብ የሚያበቃ ጊዜ እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል።

በአጠቃላይ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሀ ግብር ያለው የፓራክቲከም ሁለት ኮርስ ትግበራ ባግባቡ እንዳይካሄድ ከፍ ሲል የተጠቀሱት ችግሮች መሠናክል ሆነውበታል። በእነዚህ ችግሮች ምክንያትም መርሀ ግብሩ በሱፐርቫይዘሮቹም ሆነ በእጩ መምህራኑ ዘንድ ተወዳጅነቱ እየቀነሠና አሠልቺ እየሆነ መጥቷል።

## 5.2 የመፍትሔ ሃሣብ

ከፍ ሲል በማጠቃለያው ላይ ለማሣየት እንደተሞከረው በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ እና በዚህ ሂደት ውስጥ ያለው የሱፐርቪዥን አተገባበር ችግሮች ታይተውበታል። እነዚህ ችግሮች ሥር ሠደው የሥልጠናው መርሀ ግብር ግቡን እንዳይመታ ከወዲሁ አፋጣኝ መፍትሔ ሊሠጠው እንደሚገባ ይህ ጥናት ያመላክታል። በዚህ መሠረት በጥናቱ የተተነተኑትን መረጃዎች መነሻ በማድረግ በአሁኑ ጊዜ በሥልጠናው ሂደት ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ከዚህ በታች ያሉት የመፍትሔ ሃሣቦች ተጠቁመዋል፤

1. በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሂደት ውስጥ ሱፐርቪዥን ወሣኝ ጉዳይ ነው። ያለሱፐርቪዥን የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ ዓላማ ግቡን ይመታል ተብሎ አይጠበቅም። ሥለሆነም ይህንን ቁልፍና ወሣኝ ተግባር ለሚያከናውኑ ሱፐርቫይዘሮች ለሥራው ዓላማና አተገባበር ሥልጠና የሚያገኙበት መንገድ ቢመቻች፤

2. ዕጩ መምህራን በኮሌጅ ቆይታቸው የቀሠሙትን ንድፈ ሃሣባዊ ዕውቀት ተገቢውን ሥነ ዘዴ ተጠቅመው በተግባር መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥና ትክክለኛ መረጃዎችን ማሠባሠብ የሚችለው የማስተማር ልምምዱ በሚካሄድበት የትምህርት ዓይነት የሠለጠነ ሱፐርቫይዘር ነው። ስለሆነም የሱፐርቫይዘሮች ምደባ ይህንን ታሣቢ ባደረገ መልኩ በዋናነትና በንዑስነት በሠለጠኑበት የትምህርት መስክ የሱፐርቪዥን አገልግሎት እንዲሠጡ ቢደረግ፣

3. የምገባ መረጃ ዕጩ መምህራን ደካማና ጥንካሬያቸውን የሚያዩበትና የተሻለና የበለጠ ለመሥራት የሚነሣሡበት ቁልፍ የሱፐርቪዥን አካል ነው። ይህ እውን የሚሆነው በምግበ መረጃ መስተጋብሩ ዕጩ መምህራን በንቃት ሲሳተፉ፣ የራሳቸውን ተግባር ራሣቸው መገምገምና አማራጮችን መጠቀም ሲችሉ ነው፤ ሥለሆነም ሱፐርቫይዘሮች በድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ወቅት የራሣቸው ሃሣብ ብቻ ተሠሚነት እና ተቀባይነት እንዲኖረው በእጩ መምህራን ላይ ጫና ላለመፍጠር ጥንቃቄ ቢያደርጉ፣

4. ሱፐርቫይዘሮች በርካታ እጩ መምህራንን በአጭር ጊዜ /አንድ ሳምንት/ ውስጥ እንዲከታተሉና እንዲገመግሙ መደረጉ የሱፐርቪዥኑን ሥራ የይድረስ ይድረስ እንዲሆንና ምገባ መረጃው በአግባቡ እንዳይሰጥ አድርጎታል። ስለሆነም የኮሌጁ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ ማስተባበሪያ ችግሩን አጢኖ ሱፐርቪዥን የሚካሄድበትን ጊዜ ቢያሠፋና በቂ ሱፐርቫይዘሮችን ቢመድብ፣

5. በጥናቱ እንደታየው በኮሌጁ ሱፐርቪዥን በቂ ጊዜ ተሰጥቶት እየተተገበረ አይደለም። ለዚህም አገልግሎቱን ከመስጠት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተጓዳኝ ችግሮች(ለምሳሌ የአበል ትላፍ፣ የጊዜ እጥረት . . .) በምክንያትነት ሊጠቀሡ ይችላሉ። ስለሆነም በሱፐርቪዥን አተገባበር በምግበ መረጃ አሠጣጡ ላይ የሚታየውን ጉድለት ለማሟላትና ለማጠናከር ዕጩ መምህራን ባልደረባዊ ሱፐርቪዥን (Colleague supervision) የሚያካሂዱበትን ሁኔታ ኮሌጁ ቢያመቻች፣

6. በጥናቱ ውስጥ እንደታየው ሱፐርቪዥኑ ለግምገማና ምዘና የቅድሚያ ትኩረት በመስጠቱ ዕጩ መምህራን ሱፐርቫይዘሮቻቸውን ደጋፊዎቻቸውና አበረታቾቻቸው አድርገው እንዳይመለከቷቸው ምክንያት ሆኗል። ይህ የሱፐርቪዥን ዓላማና ተግባር አይደለምና የቅድሚያ ትኩረቱ በምግበ መረጃ መሥተጋብሩ ላይ ቢሆን፣

7. ሱፐርቫይዘሮቹም ሆኑ እጩ መምህራን "የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምዱ ፕሮግራም አንድ ዓመት ሙሉ መቆየት የለበትም። የአሠለጣጠን ሥርዓቱም ገባ-ወጣ ገባ (In-out-In) ከሚሆን ይልቅ ገባ-ገባ-ወጣ (In-In-out) ቢሆን ይሻላል" የሚል አቋም አላቸው። ሥለሆነም የክልሉ ትምህርት ቢሮና በሥሩ የሚገኙ ኮሌጆች በሥራ ላይ

የሚሰጠውን የአሠራሩን ሥርዓት መለስ ብለው ቢቃኙና አማራጮችን ጭምር ከግምት ውስጥ በማስገባት የጋራ ግንዛቤ ቢጨብጡ።

8. በሁሉም ሆነ በአጋር ት/ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ አስተባባሪ ኮሚቴዎች መቋቋማቸው በጣም ጥሩ እና ተገቢ ነው፤ ሆኖም ለመርሀ ግብሩ ዓላማ መሳካት አዎንታዊ ሚና መጫወት ካልቻሉ መቋቋማቸው ብቻውን ግብ ሊሆን አይችልም። የጥናቱ የመረጃዎች ትንተና ዕጩ መምህራኑ ከአጋር ት/ቤቶች ነባር መምህራን የሚያገኙት ድጋፍ አጥጋቢ አለመሆኑን አሳይቷል። ይህ ችግር ቸል ሊባል የሚገባው ስላልሆነ ኮሌጁ ከአጋር ት/ቤቶች ጋር በመነጋገር እየተገናኘ በችግሩ ዙሪያ ውይይት ቢያካሂዱበትና የጋራ አቋም የተያዘበት መፍትሔ ቢሠጥ።

9. የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ብቁ መምህራንን ከማፍራት አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው አጠያያቂ አይደለም። ዓላማው ግብ መቼ የሚሆነው ግን በመርሀ ግብሩ የሚሳተፉ የተለያዩ አካላት ትኩረት ሰጥተው በትጋት ሲንቀሳቀሱ ነው። ይህንን በተመለከተ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ "የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አፈፃፀም መመሪያና የኮርስ አደረጃጀት" የሚል መመሪያ በጐንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አማካይነት እንዲዘጋጅ በማድረግ የሥልጠናው መርሀ ግብር ተሳታፊ የሆኑ አካላትን የሥራ ድርሻና ሀላፊነት በዝርዝር አሥፍሯል። ይህ በጥሩ ጐኑ የሚጠቀስ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ በተግባር መገለፁ ነውና እያንዳንዱ አካል የተጣለበትን ኃላፊነት በተገቢ ሁኔት ሥለመወጣቱ የጋራ ግምገማ እየተካሄደ ቢረጋገጥና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ቢኖር።

## ሙዳዩ ቃላት

| | |
|---|---|
| መምህር መር | Teacher centered |
| መስተጋብር | Interaction |
| መቼት | Setting |
| ምገባ መረጃ | Feedback |
| ሱፐርቫይዘሮች | Teacher Educators |
| ተለዋዋጮች | Variables |
| ነባር መምህራን | Cooperative teachers |
| ገሽ | Motivation |
| አጋር ትምህርት ቤት | Cooperative school |
| ዕጩ መምህራን | Candidate teachers |

## ዋቢ ፅሁፎች


ሂሩት አምሃ (1998) "በፕራክቲከም ሂደት፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር፣ በደቡብ ኢትዮጵያ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 የመምህራን ሥልጠና መርሀ ግብር" ለአማርኛ ማስተማር ኤም ኤ ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ት/ቤት (ያልታተመ)::

መሀመድ ጀማል (1999) "በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳደር በሮቤ መምህራን ኮሌጅ በ10+3 የዲፕሎማ መርሀ ግብር የፕራክቲከም ኮርስ አተገባበር ፍተሻ" ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድኅረምረቃ ት/ቤት (ያልታተመ)::

ሥንታየሁ ጫንያለው (1995) "ከክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ የሚሠሩ መመዘኛዎች ምርጫና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ" መጽሔተ ትምህርት:: ቅፅ 7፣ ቁጥር 5፣ ገፅ 30-50::

ተክለሃይማኖት ኃይለሥላሴ (1992) "የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርት አዲስ አቅጣጫ" መጽሔተ ትምህርት:: ቅፅ 4፣ ቁጥር 10፣ ገጽ1-14::

ተሠማ አሰፋ (1997) "የፕራክቲከም፣ የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሠርተፊኬት (10+1) መርሀ ግብር::" የአርትስ ማስተርስ ድግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)::

ትዕግሥት ታረቀኝ (1998) "በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የበላል ድርሰት መምህራን ምጋቢ ምላሽ ትኩረት ፍተሻ" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ. ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

ትምህርት ሚኒስቴር (1994) የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ::

(1996) "ተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ (CPD) ፕሮግራም" (ቦታው ያልተጠቀሰ፣ ያልታተመ)::

ንጋቱ ተክለማርያም (1997) "የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ" ሥርዓተ ትምህርት መጽሔት:: ቅፅ 2፣ ቁጥር ገጽ 26-31::

ንጉሤ አሰፋ (1988) "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ትንተና" ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት (ያልታተመ)::

ደረጀ ገበሬ (1997) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል የማሥተማር ልምምድ መርሃ ግብር አተገባበር ከተማሪ አስተማሪዎች /ተለማማጆች/ እና ገምጋሚዎች አመለካከት አንፃር" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)::

ሃገራር መምህራን ትምህርት ክፍል (1997) የ10+3 "ፕሮግራም ለሚሠለጥኑ ዕጩ መምህራን የተዘጋጀ የት/ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የአፈፃፀም መመሪያና የኮርስ አደረጃጀት::" (እንደገና ለ1998 ዓ.ም እንዲያገለግል ሆኖ የተሻሻለ፤ ያልታተመ)::

ፈንታ ሞገስና የሴፍ አንተነህ (1997) መሠረታዊ የሥራ አመራር መርሆዎችና የትምህርት ሥራ አመራር:: በአማራ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ፤ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ሥልጠና የተዘጋጀ ሞጁል፤ አማራ ክልላዊ መንግሥት ት/ቢሮ፤ ባህርዳር::

Alebachew Mekonnen (1996) "Pre-servcie and Inservice Teacher Education and Training" Educations Journal Vol. 2 No. 2, PP 42-63.

Allwright D. (1988) Observation in the Language Classroom. New York: Longoman Inc.

Anberber Mengesha (1975) "The Application of Supervision in Ethiopian Schools" Addis Ababa: Addis Ababa University. Unpublished.

Armstrong O. (1991) A Hand Book of Human Resource Management. London: Kogan Page, Ltd.

Aseb Desta (1971) "A Handbook for Elementary School Student Teaching" Addis Ababa. Faculty of Education: AAU. Unpublished.

Calderhead, J (1987) "The quality of Reflection in Student Teachers' Professional learning" European Journal of Teacher Education. Vol. 10, No. 3, PP 269-273.

Classroom Observation: http://gli/berkelay. edu/faculty/observation doc.

Clifford M. (1981) Practicing Educational Psychology: Boston: Haughton Miffin Company.

Cogan M. (1973) Clinical Supervision. Boston: Houghton-Miffilin.

Cohen, R. and Manion, L. (1983) A Guide to Teaching Practice. London: Routledge.

Daniel Tefera et al (2002) "Introduction to Educational Psychology" Distance Education Material for In-Service Trainees: Continuing and Distance Education Division. Unpublished.

Day, C. (1993) "Reflection: A Necessary but not Sufficient Condition for professional Development" British Educational Journal. Vol. No. 19, PP 83-93.

Dececco, J. (1968) The Psychology of Learning and Instruction Educational Psychology. New Jersey: Printice- Hall Inc.

Dennis Thiessen and Ardacole (eds) (1993) "Reporting Teacher Education in Canada Policy Making in Practice" Journal of Education Policy. Vol. 8, No. 3, PP 205-225.

Dove L. (1986) Teachers and Teachers Education in Developing Countries. London: Croom Helm.

Eraut, M. (1994) Developing Professional Knowledge and Conference. London: Falmer Press.

ESAURP (1987) University Capacity in Eastern and Southern Africa Countries. Daresalaam: Heinemar Educational Books Inc.

Evertson (1985) "Training Teachers in Classroom Management An Experimental Study in Secondary Classroom" Journal of Educational Research. Vol. 79 No. 1.

Eye G. and Leonore A. Netzer (1965) Supervision of Instruction. New York: Harper and Row, Inc.

Fish, D. (1989). Learning Through Practice in Initial Teacher Training. London: Kogan Page.

Fletcher, S. (2000) A Handbook on Mentoring. London: The Falmer Press.

Freedman et al. (1980) Improving Teacher Education Resource and Recommendations. New York: Longman Inc.

Freire, P. (1993) Pedagogy of the Oppressed. Newyork: The Continuum Publishing Company.

Gage N. M. (1970) The Conditions of Learning. New York: Holt, Rinehart and Winston.

Girmay Berhe (2005) "Instructional Supervision: methodology for Quality Teaching and Learning" Paper presented for Training Workshop for School Managers, Education Supervisors Organized by Yeka Sub-city Administration Educational Development in Cooperation with Plan Ethiopian, Addis Ababa, December 2005. Unpublished.

Goble, N. M. and Porter, J. F. (1977) The Changing Role of the Teacher International prospectives. Paris: NFER Publishing Co. Ltd.

Goldhammer et al (1980) Critical Supervision: Special Methods for the Supervision of Teachers. (2nd ed) New York: Holt, Rienehart and Winston.

Gorton Richard A. et.al (1988) Encyclopedia of School Administration and Supervision. New York: Oryx Press.

Griffiths D. (1956) Human Relations in School Administration New York: harper and Row Publishers.

Griffiths F. (1979) Administrative Theory in Education. Michigan: Pendell Publishing Company.

Grower, R. and Walters, S. (1983) Teaching Practice Handbook: A Reference Book for EFL Teachers in Training. Oxford: Heinemann International.

Gwynn, J. (1984) Theory and Practice of Supervision. New York: Dodd, Mead and Company.

Hailom B. (1997) "The Use of Classroom Data for Self Applicaisal in the EFL. Practicum: A strategy of Observation, Reflection and Action" Ethiopian Journal of Education. Vol. XVII. No. 1 PP 1-29.

Hammer Bernard (1972) "Grade Expectations, Differential Teacher Comments, and Students Performance" Journal of Educational Psychology.

Harris, B.M. (1963) Supervision Behavior in Education. New York: Prentice Hall, Inc.

Haymmon T. and Reymond L. (1977) Concepts of Practices of Mangement (2nd ed.). Cincinnati: South Western Publishing Co.

Husen T. and Postlethwaite T. (eds) (1994) The International Encyclopedia of Education. 2nd ed Vol. 10 Oxford: Pergamon.

ICDR (1999) Teacher Education Handbook. Addis Ababa MOE.

Ivancevich, J.M and William G. Glueck (1989) Foundation of Personnel. USA: Richard D. Irwin Inc.

Jacobs H. et al. (1981) Testing ESL Composition: A Practical Approach. Rowley, Massachusetts, New buny House Publshers.

Kenezavich, S. (1969) Administration of Public Education (2nd ed). New York: Harper and Row Publishers.

Kinard, J. (1988) Management. Massachusetts. D. H. Health and Company.

Leavit Howard, (1991) "World wide Issues and Problems in Teacher Educaton" Journal of Teacher Education. Vol. 42; No.5, PP. 322-331.

Lema Setegne and Taffesse Asfaw (1997) "Pre Training Practice Classroom Observation in the Cooperative Schools, Principles, Practice and Results" In Proceedings of the 1st Workshop on Teaching Practice: Addis Ababa KCTE. Unpublished.

Lewin. K. M. and Stuart, J. S (2003) "Research in Teacher Education: New Perspectives on Practice, Performane and Policy" MUSTER Synthesis Report. Susex: Department for International Development (DFID) Educational papers.

Livingstone G. (2001) "The Practicum in Teacher Education: its nature and the nature of Teachers" A paper Presented at the Workshop Organized for TTI Instructors: Addis Ababa. Unpublished.

Markos Tadesse (2000) "Effects of Instructor Evaluative Comments Up on Students' Subsequent Performance with Particular Reference to Freshman Studnets in Makalle Busines College" Educational Journal. Vol. 4, No. 10, PP 92-110.

Mbamba, Mauno A. (1992) Book of Reading in Educational Management. Harrare, UNESCO.

Milton, Ohmer (1978) On College Teaching. California, Jossey Boss Ins.

MOE (1991) "A National Guidelines for Teacher Educators." Addis Ababa.

(2002) "National Framework for Teachers Education System Overhaul" Addis Ababa. Unpublished.

(2003) "Teacher Education System Overhavl (TESO) Hand Book" Addis Ababa. Unpublished.

(2004) "Higher Deploma Programme for Teacher Educators, Module" Addis Ababa. (Unpublished).

Murrey Harvey R. et al (1999) A Cross Cultural Comparison of Student Concerns in the Teaching Practicum. International Educational Journal, School of Education Flinders University of South Africa.

Okumbe, J. A (1998) Educational Management: Theory and Practice. Nairobi: Nairobi University.

Owen, Steven V. et.al. (1978) Educational Psychology. Boston: Little Bowen and Company.

Pagr, Ellis B. (1964) Teacher Comments and Student performance: Reading in Educational Psychology. New York: Harcourt, Brance World, Inc.

Pajak Edward (1989) The Central Office Supervisor of Curriculum and Instruction: Setting the Stage for Success. Boston: Allyn and Bacon. Inc.

Peer Review of Teaching Project: http://www.unl/edu/peerrev/. TEESO 2003.

Perrot E. (1982) Effective Teaching A Practical Guide to Unproving your Teaching. New York: Longman.

Piaget, J. (1973) To Understand is to Invent. New York: Viking Press.

Reed, A.J.B. And Bergeman, V. E. (1995) In the Classroom: An Introduction to Education. (2nd ed.) London: The Dehkin Publishing Groups, Inc.

Richards, J. and Nunan, D. (eds) (1990) Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Ruth Wajnryb (1992) Classroom Observation Tasks. A Resource Book for Language Teachers and Trainers: Cambridge: Cambridge University press.

Schon, D. (1983) The Reflective Practioner, Basic Books. New York: McMillan.

Seyyadain, M. S. (1985) "Personal Characteristics and Job Satisfaction: Indian-Nigerian Comparison." International Journal of Psychology, Vol. 20 PP. 143-153.

Sexason, S. B. et al. (1986) The Preparation of Teachers Unstudied Problems in Education. Cambridge: Bookline Books: Inc.

Smith, B. Othanel (1970) Teachers for the Real World. Washington: The American Asociation of College for Teacher Education.

Spears H. (1955) Improving the Supervision of Instruction. New York. Prentice-Hall Inc.

Srivastava, R. C and Bose, K. (1978) Theory and Practice of Teacher Education in India. New Delhi: Chugh Publications.

Stern, J. (1995) Learning to Teach: A Guide for School Based Initial and In-Service Training. London: David Fulton Publishers.

Stones, E. and Morries, S. (1972) Teaching practice: Problems and Perspectives: A Reappraisal of the Practical Proffessional Element in Teacher Preparation. London: Methuen.

Tabachnick, R. R and Zechner, K. M. (1991) "The Impact of the Student Teaching Experience on the Development of Teacher Prospectives" Journal of Teacher Education. Vol. 35, No. 6. PP 28-36.

Tekeste Negash (1990) The Crisis of Ethiopian Education: Some Implications for Nation-Building. Sweden: Department of Education-UPPSala University.

Teshome Wagaw (1979) Education in Ethiopias Prospect and Retraspect. Michigan: Michigan University Press.

Teshome Yizengaw (2004) "The Status and Challenges of Ethiopian Higher Education system and its contribution to development" The Ethiopian Journal of Higher Education. Vol. 1 No. 1. PP. 1-20.

Tirussew Teffera (2006) "An Introductory Note on the Educational Note on the Educational System and Teacher Education" Paper Presented at 1st Meeting of National Coordinators for Training Initiative for Sub-Saharan Africa 7-9 March, 2006, BREDA, Dakar Senegal Higher Education.

Wallace, M (1991) Training foreign Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

World Bank (1994). Higher Education Development for Ethiopia Pursuing the Vision. Washington D.C: World Bank.

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አባሪ

# አባሪ አንድ

## በማስተማር ልምምድ ወቅት የዕጩ መምህራን የማስታወሻ አያያዝ መምሪያ

ይህ መምሪያ ቋንቋን በማስተማር ልምምድ በሱፐርቫይዘሮችና በዕጩ መምህራን የሚደረገውን የምልከታ መረጃ መሥተጋብር ለመፈተሽ የሚያስችሉ ማስታወሻዎች እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሲባል የተዘጋጀ ነው። ፍተሻው /ጥናቱ/ ግብመች ሊሆን የሚችለው ትክክለኛና አሥተማማኝ መረጃዎች ሲገኙ ነው። ከዚህ አንፃር በትምህርት ቤት ተግባርና የማስተማር ልምምድ (Practicum) መርሀ ግብር ቋንቋን የማስተማር ልምምድ ሥታካሂዱ ሥለአያችኋቸው እና ሥለገጠሟችሁ የተለያዩ ሁኔታዎች እንዲሁም ሥለተሠማችሁ ስሜት ቀጥሎ በቀረቡት መመሪያዎች መሠረት ማስታወሻ በመያዝ ትብብር እንድታደርጉልኝ አጥኚው በአክብሮት ይጠይቃል።

### 1. አጠቃላይ መግለጫ

1.1 ማሥታወሻው ላይ ሥም መፃፍ አያሥፈልግም።

1.2 መረጃዎቹ ሁሉ በሚስጥር ሥለሚያዙ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አያሳድሩም።

1.3 ማስታወሻው በተቻለ መጠን በግልፅ ቋንቋ የተፃፈና ለንባብ የማያስቸግር ሊሆን ይገባል።

1.4 የማሥተማር ልምምዱን ሂደት በየሳምንቱ ሳይዘነጉ መፃፍ አሥፈላጊ ነው።

1.5 ከሱፐርቫይዘሩ የክፍል ውስጥ ጉብኝት በኋላ የማስተማሩን ሂደት ወዲያውኑ በማሥታወሻ ላይ መግለፅ (ማሥፈር) ተገቢ ነው።

1.6 የያዛችሁትን ማሥታወሻ በየሳምንቱ መጨረሻ ለሚመለከተው ተወካይ አካል ማሥረከብ ይገባል።

1.7 ማሥታወሻ ለመያዝ በዚህ መመሪያ ከተጠቀሱት የትኩረት ነጥቦች በተጨማሪ መነሳት ያለበት ጉዳይ ካለ ማሥፈር ይቻላል።

### 2. አበይት የትኩረት ነጥቦች

የማስታወሻችሁ ይዘት በተቻለ መጠን ቀጥሎ ባሉት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ቢሆን ይመረጣል፤

2.1 የክፍል መምህራችሁ ሥለሚያደርጉላችሁ ድጋፍ

2.2 የአጋር ት/ቤት መምህራን ሥለሚያደርጉላችሁ እገዛና ክትትል

2.3 ሱፐርቫይዘሮቻችሁ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለማድረግ ሲመጡ የሚሠማችሁ ሥሜት (በመምጣታቸው ደሥታ፣ ድንጋጤ፣ መረበሽ ወዘተ.)

2.4 የምታስተምሯቸው ተማሪዎች ባህርይ ምን እንደሚመሥል

2.5 በክፍል ውስጥ ሱፐርቫይዘሩ ባሉበት ሥታስምሩ፣

2.5.1 ምን ስሜት ተሠማችሁ?

2.5.2 የማስተማር ብቃታችሁ ከወትሮው ቀነሠ? ጨመረ? ተለዩ? . . .

2.5.3 በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዳችሁ ላይ ያሠፈራችኋቸውን ተግባሮች አጠናቀቃችሁ? ወይስ አላጠናቀቃችሁም? ካላጠናቀቃችሁ ለምን?

2.5.4 የሚያስተማር ሥነዘዴያችሁ ከወትሮው የተለዩ ነበር? ወይስ ያው ነበር?

2.5.5 ከተማሪዎቻችሁ ጋር የነበራችሁ ግንኙነትስ ከወትሮው ተለዩ?

2.6 ሱፐርቫይዘሩ ለምልከታ ወደክፍል ከመግባታቸው በፊት ውይይት አድርጋችሁ ነበር? ካደረጋችሁ የውይይቱ ትኩረትምን ምን ላይ ነበር?

2.7 በድኅረ ምልከታ (ምልከታው ካበቃ በኋላ) ከሱፐርቫይዘራችሁ ጋር ያደረጋችሁት ውይይት ምን ምን ላይ ያተኮረ ነበር?

2.8 በድኅረ ምልከታ ውይይት የሱፐርቫይዘሩ ትኩረት በጠንካራ ጎኖቻችሁ ወይስ በደካማ ጎኖቻችሁ ላይ ነበር?

2.9 ሱፐርቫይዘሩ ሥለሰጥዋችሁ ድክመታችሁ የነገሯችሁን በሙሉ ትቀበሏቸዋላችሁ ወይስ የማትቀበሏቸውም አሉ? ካሉ ምሣሌ እየጠቀሳችሁ አስረዱ።

2.10 በሙያችሁ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ በተማራችሁትና አሁን ሱፐርቫይዘራችሁ በሚነግሯችሁ መካከል የማይጣጣም ነገር አለ? ካለ ግለፁት።

2.11 በድኅረ ምልከታ ውይይት የናንተ ተሣትፎ ምን ነበር? (ሱፐርቫይዘራችሁ) ያሏችሁን አምሮ መቀበል፣ ዝም ብሎ ማዳመጥ ወይም የመሠላችሁን ሀሳብ በተቃውሞ ወይም በድጋፍ መልክ የማቅረብ ነፃነት አላችሁ?

2.12 ከሱፐርቫይዘራችሁ ጋር ሥትወያዩ በሁለታችሁ መካከል ያለው ግንኙነት ምን መልክ ነበረው /የመግባባት መንፈስ፣ የበላይና የበታች መንፈስ፣ ያልኩህን ተቀበል ዓይነት መንፈስ . . . ወዘተ./

2.13 የሱፐርቫይዘሩ አቀራረብ ምን መልክ አለው? /ምክር መስጠት አማራጭ ማቅረብ፣ ይህን ፈፅሞ ብሎ ማዘዝ ወዘተ./

2.14 በድኅረ ምልከታ ከሱፐርቫይዘራችሁ ጋር የምታደርጉት ውይይት ጠቀሜታው ምን ያህል እንደሆነ ግለፁ።

2.15 በክፍል ቃላይ ስክ ያመጠበ ሰሌዳው ያገኙሁን አስተያየት ምን ይመስላል? ግለፁ።

# አባሪ ሁለት

## የዕጩ መምህራት ማስታዎሻ ናሙናዊ ጥንቅር

### 2.1 የሱፐርቫይዘሮችን ድጋፍ በተመለከተ

- የኮሌጅ መምህራን ፕራክቲከም በምንወጣበት ጊዜ የሚያደርጉት ድጋፍ በጣም ዝቅተኛ ነበር። ምክንያቱም እነሱ የሚመጡልን ቱቶሪያል፣ ግምገማ፣ ፈተና ለመስጠት ብቻ ነው። ከኢንፎርሜሽን የራቁ በመሆናቸው ለችግራችን ፈጥኖ ደራሾች አይደሉም።

- ከኮሌጅ መምህራን የረባ ድጋፍ አግኝተናል ማለት አይቻልም። ምክንያቱም እኛ የነበርነው ከኮሌጁ በብዙ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሥለበነበር ነው። በቱቶሪያል ጊዜም ቢሆን የተደረገልን ድጋፍ እጅግ በጣም ውሱን ነው።

- በፕራክቲከም ወቅት መምህሮቻችንም ሆኑ ኮሌጁ ረስተውን ነበር ማለት ይቻላል።

- የኮሌጁ መምህራን ተግባራቸው የተለያየ ነው። የተወሠኑት ጥሩ ዕውቀት እንድንጨብጥና መልካም ውጤት እንድናመጣ ከፍተኛ እገዛ ሲያደርጉ ጭራሽ ደንታ ቢስ የሆኑ መደበኛ የሥራ ጊዜያቸውን በፍሬ ቢስ ወሬ በመሸፈን የረባ ምክር እንኳ ሳይለግሱ ይሄዳሉ።

- የኮሌጁ መምህራን የሚያደርጉትልን ድጋፍ ወደ መጥፎ ሥራ እንዳንገባ ምክር በመስጠትና ምጃዩል በየወቅቱ እንዲደርሰን ማድረግ ነው።

- የኮሌጁ መምህራን የሚያደርጉትልን ድጋፍ እዚህ ግባ የማይባል ነው። ምክንያቱም ካለው የጊዜ ማነስ አንፃር ለእኛ ምንም ያህል እገዛ ሳያደርጉ ተጣድፈው መመለሥ ነው።

- ቱቶሪያል በመስጠት፣ ከምልከታ በኋላ ምክር በመስጠት፣ እንዴት ማስተማር እንዳለብን ምክርና አስተያየት ሰጥተውናል፣ ሆኖም ሊያስመሠግን የሚችል ድጋፍ አላደረጉትልንም።

- ለልምምድ በወጣንበት ትምህርት ቤት እያለን የኮሌጁ መምህራን ድጋፍ አድርገውልናል ማለት አይችልም። በዓመቱ ወይም ስሚስተሩ መጨረሻ ቢመጡም ለገጠሙን አንዳንድ የት/ቤት አስተዳደር ሁኔታና የማስተማር ተግባር ችግሮች መፍትሔ ሰጥተዋል ማለት አይቻልም።

- ድጋፋቸው የአጋር ት/ቤት መምህራን የመደበኛ መምህሩን ያህል ክፍለ ጊዜ እንዳያሸክሙን በማድረግና አበል በወቅቱ እንድናገኝ ከማሳሰብ የዘለለ አልነበረም።

- አድርገውልኛል የምለው ድጋፍ የለም። እንዲያውም በአለባበስና በውበት ዝቅ ያለውን ለማነጋገር አይፈልጉም።

- በማስተማር ልምምዱ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን ተማሪዎችን እንዴት በመምራት እንዳለብን ይነግሩናል።

## 2.2 የአጋር ት/ቤት መምህራንን ክትትልና ዕገዛ በተመለከተ

- የአጋር ት/ቤቶች መምህራን የሚያደርጉልን እገዛና ክትትል ብዙም አይደለም እኛም እንደነሱ ብዙ ክፍለ ጊዜ እንድንይዝ ይፈልጋሉ። አንዳንዶቹም በእኛ ላይ የመጠራጠርና የፍርሀት ስሜት አላቸው። ስለሆነም እገዛና ክትትሉ እዚህ ግባ አይባልም።

- የአጋር ት/ቤት መምህራን እገዛም ሆነ ክትትል ለማድረግ ብዙም ፈቃደኛ አይደሉም።ምክንያቱም ብዙዎቹ የመሠላቸት ሁኔታ ይታይባቸዋል።

- በሌሰንፕላን አወጣጥ ላይ ግምገማ በማድረግ እገዛ አድርገውልናል። በማስተማር ሂደት የገጠመንን ችግር በተመለከተም ጥያቄና ምክር ከጠየቅናቸው ይተባበራሉ።

- የአጋር ት/ቤት መምህራን የጐላ አስተዋጽኦ አያደርጉልንም፤ እንዲያውም በጣም የሥራ ጫና ያበዙብን ነበር።

- የአጋር ት/ቤት መምህራን ድጋፍ ይህን ያህል ጐልቶ የሚታይ አይደለም። በእርግጥ የተሻሉ አሉ። ለምሳሌ ሌሰንፕላን እንዴት ማዘጋጀት እንዳለብን፤ ወደ ክላስ ከመግባታችን በፊት ስለምናስተምረው ትምህርት ዝግጅት ማድረግ እንዳለብን፤ ስለተማሪዎች አያያዝ ወዘተ. ምክር ሲያደርጉልን ብዙዎቹ መምህራን ግን ለምልከታ ወደ ክፍላቸው እንድንገባ ፈቃደኞች አልነበሩም። በሰበብ አስባቡ እንድንርቃቸው ይፈልጉ ነበር። ማጋነን ባይሆንብኝ በሞራላችን ላይ ይረማመዱብን ነበር።

- የአጋር ትቤት መምህሩን የሚያደርጉልን ክትትልና ድጋፍ ክፍለ ጊዜውን መንገር፣ የተማሪውን ፀጥታ ማስከበር፣ እንዴት ማስተማር እንዳለብን መምከር የፈተና አወጣጥን ማሳየትና የመረጃ መሳሪያ መስጠት ነው።

- በማስተማር ሂደቱ ማድረግ የሚገባንን በመምከር፣ ስለ ጥናታዊ ጽሁፍ አዘገጃጀት በማሳየት በተለይ በሌሰን ፕላን ዝግጅት ላይ ማስተካከያ ያደርጉልናል

- እንዴት ማስተማር እንዳለብኝና ከተማሪዎች ጋር እንዴት መቀራረብ እንዳለብኝ ከመከሩኝ በኋላ እንደመደበኛ መምህር በመቁጠር ተማሪዎቻቸውንና ክፍላቸውን አስረከቡኝ። ከዚያ በኋላ የእሳቸውን ድጋፍ አላገኘሁም።

- የትምህርትቤቱን የውስጥ አሠራር በማሳወቅ በኩል እገዛ አድርገውልናል

- የአጋር ት/ቤት መምህሩን ዋነኛ ትኩረታቸው ክፍለ ጊዜያቸውን እንድንሸፍንላቸው እንጂ እኛን ማገዝ አልነበረም። በበኩሌ ከማስተማር ልምምዱ ምን አገኘሁ? ተብዬ ብጠየቅ የተብራራ መልስ አላገኝም። ምክንያቱም የአጋር ት/ቤት መምህሩን እገዛ ስላላደረጉልኝ።

- አንዳንዶቹ ያበረታቱናል። አንዳንዶቹ ደግሞ ገምጋሚዎቻቸው መስለን ነው የምንታያቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የማናናቅ ስሜት ይታይባቸዋል።

- የአጋር ት/ቤት መምህሩን በመጠኑ የጠየቅናቸውን ለመመለስ ይሞክራሉ። ማለትም ከኮሌጅ መምህሩን ጋር ሲነፃፀሩ ይሻላሉ ለማለት ነው እንጂ ብዙዎቹ እንደ ዱር አውሬ ነው የሚመለከቱን።

## 2.3 ስቱፐርቫይዘራቸው ምልከታ ለማካሄድ /ለግምገማ/ በሚመጣበት ጊዜ ስለሚሠማቸው ስሜት

- ስቱፐርቫይዘሬ ለምልከታ ሲመጣ ለጊዜው የመደናገጥና የመረበሽ ስሜት ተሰምቶኝ ነበር። እያደር ግን ተረጋጋሁ።

- ስቱፐርቫይዘሬ ሲመጡ መረበሽ ታይቶብኝ ነበር። ምክንያቱም በአንድ እና ሁለት ቀን ቆይታ ብዙ ነገሮችን አሟልተን እንድናስረክብ ወይም እንድናሳይ ስለሚጠይቁ ያንን ሁሉ እንዴት አሟላለሁ ብዬ እጨነቃለሁ። ከዚያ በላይ የሱፐርቫይዘሮቹን ባህሪ ስለማናውቅ እንፈራለን።

- ሱፐርቫይዘራችን ለክፍል ምልከታ ሲመጡ የሚሰማኝ ስሜት ድንጋጤና መረበሽ ነው። ምክንያቱም የነሱን መምጣት ከውጤት (ምዘና) ጋር ስለምናያይዘው ነው።

- ስትርቫይዘሬ ለምልከታ ሲመጣ ብቻ ሳይሆን መምጫው ቀን መቃረቡን ሳስብ ጀምሮ እጅግ እፈራለሁ። ብዙ እሰጋለሁ። ምክንያቱም ከፍተኛ ክሬዲት ያለውን ኮርስ ውጤት ወሳኙ እሱ ስለሆነ ነው። በዚህ ኮርስ ደህና ውጤት የሰኮረ ተማሪ መሞቻም የለው። ዝቅተኛ ውጤት ያመጣ ደግሞ መነሻም የለው።
- ስትርቫይዘሬ መጣ ሲባል የማደርገው ሁሉ ይጠፋኛል። በቃ ቅጥ አምባሩ ጥፍትፍት ነው የሚለኝ።

- ስትርቫይዘሬ ሲመጣ ደስታ የሰማኛል። ምክንያቱም የማስተማር ተግባሬን ተመልክቶ ስለጠንካሬና ደካማ ጎኔ ጠቃሚ ምክር የሰጠኛል ብዬ ስለማስብ ነው።
- ስትርቫይዘሬ ለምልከታ ሲመጣ የመጨነቅም ሆነ የመረበሽ ስሜት አይሰማኝም።
- ሁሌን ሁሉ ጊዜ አዘጋጅቼ ሥለምገባ የስትርቫይዘሬ መምጣት አያስፈራኝም። እውነቱን ለመናገር ከሱ ይልቅ ሌላ ዕውቀት የሌለውና መገምገም የማይችል ሰው እከፍሌ ቢመጣ ይጨነቀኛል። ስትርቫይዘሬ ግን ብሳሳት እንኳ ሠው ከስህተት እንደማይድን ተረድቶ ያርመኛል እንጂ አያዳጅለኝም

## 2.4 ስትርቫይዘሬቸው በተገኘበት ሲያስተምሩ ስለተሠማቸው ስሜት

- ስትርቫይዘሬ ባለበት ሳስተምር እሳሳት ይሆን? ተማሪዎች ጥያቄ ያበዙብኝ ይሆን? የሚል ስጋት ያድርብኛል። በዕለቱ የሚገባ ተዘጋጅቼ ነበር። ዕለታዊ ዕቅዴን አጠናቅቄአለሁ። የማስተማር ስን ዘዴዬን ግን ቀይሬአለሁ። ተማሪዎች የሚወዱት ገለፃን ቢሆንም የዚያን ዕለት ግን ተማሪዎች ባይወዱትም የግድ ተማሪ ተኮር ለማድረግ ስል የቡድን ሥራን ተጠቅሜበታለሁ።

- ስትርቫይዘሬ ባለበት ሳስተምር ደስ ብሎኛል። በሚገባ ተዘጋጅቼ ስለ ነበር የማስተማር ብቃቴ ከወትሮው ጨምሮ ነበር። ዕለታዊ ዕቅዴን ከሞላ ጎደል አጠናቅቄአለሁ። የማስተማር ስን ዘዴዬ ከወትሮው በተለየ መልኩ ተማሪ ተኮር ነበር።

- በክፍል መምህሬ በተገኙበት ሳስተምር በሙሉ ስሜት ነበር። ምክንያቱም በዚያች ዕለት ያለ የሌለ ዕውቀትና ችሎታዬን ተጠቅሜ ውጤቴን ለማሳመር ስል ስለምዘጋጅ አልተረበሸኩም። የማስተማር ስን ዘዴዬም ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ ተማሪ ተኮርንቱ ይጕላ ነበር።

- ከወትሮው የተለየ ስሜት አልተሰማኝም። ስትርቫይዘሬን ልክ እንደተማሪዎቼ ለማየት ራሴን አሳምኜው ነበርና አልተጨነቅኩም።
- ከፍተኛ ፍርሀት ተሰምቶኝ ነበር። በጭንቅላቴ የሚታየኝ ውጤቴ በመሆኑ እያንዳንዷ ቃሌ ስህተት መሳላ ትታየኝ ነበር። በመሆኑም ሌሰንኘላኔ ሌላ የማስተምረው ሌላ ሆኖብኝ ተቸገሬ ነበር።
- በጣም ተጨንቄ ነበር። ወትሮ ከምጠቀምበት ለየት ባለ ሁኔታ አስተምራለሁ ብዬ ብዙም አልተሳካልኝም። ተግባሮቼ ሳይጠናቀቁ ተደወለ።
- ሱፐርቫይዘሬ ባለበት ሳስተምር ፍርሀትና ጭንቀት ይወረኛል። አቀርቅሮ ሲጽፍ ሳየው ግን በሙሉ የምሰራው ሁሉ ስህተት መስሎ ተሰምቶኝ ነበር። ሌሰን ኘላን ላይ ያሰፈርኩትን ያጠናቀቅሁት ገና 15 ደቂቃ ቀርቶ ነው። እንደገና የቡድን ስራ በማሰራት ቀሪውን ጊዜ ሸፈንኩ።
- የማስተማር ብቃቴ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ጨምሮ ነበር። ባጋጣሚ የምወደው ርዕስ ግጥም ስለነበር ትምህርቴ እኔም የግጥም ፍቅር ስላለኝ ሱፐርቫይዘሬ በዚህ አጋጣሚ ስለመጣልኝ ደስታ ተሰምቶኝ ነበር።
- የተሠማኝ ስሜት የመጨነቅ አይሉት የመጠንቀቅ የማስተማር ብቃቴ ከወትሮው ተጋሎ ነበር። በዕለቱ የትምህርት ዕቅዱ ላይ ያሰፈርኩት ተጠናቋል። ግን ከመደናገጤ የተነሳ በእየተግባሩ ላይ ብዙ ስላልሄድኩበት ሰዓት ተርፎብኝ ነበር።
- መጀመሪያ ፍርሀት ወሮኝ ነበር እያደር ግን ለቀቀኝ። እግዜር ይስጣቸውና ተማሪዎችም ችግሬን አውቀውልኛል መሠለኝ በደንብ ስለሚሳተፉ ተበረታታሁ። ዋናው ግምገማ ደግሞ ተማሪን ማሳተፍ ስለሆነ ድፍረት አገኘሁ።

## 2.5 የተማሪዎችን ባህርይ በተመለከተ

- ተማሪዎቹ እነሱም የሚገመገሙ መስሏቸውም እንደሆን እንጃ ጨዋነታቸውና ተሳትፎአቸው ከወትሮው ጨምሮ ነበር።
- አንዳንድ ጉረምሶና የተሠማቸው ተማሪዎች በዕለቱ ሊፈታተኑኝ ፈልገው ነበር። ከበድ ከበድ ያሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ጉድ ሊያደርጉኝ ሲሉ እስቲ በቅድሚያ ተወያዩበት በማለት እነሱ እየተወያዩ እያሉ ሱፐርቫይዘሩ ሞባይሉ ጮሆበት ወጣ። ሸክም የተነሣልኝ ያህል ቀለለኝ።

- አንዳንድ ተማሪዎች የግትርነት ባህርይ ስለሚያሳዩ ብዙ ማብራሪያና ምሳሌ ለመስጠት ተገድጄ ነበር። ብዙዎቹ ግን ህፃናትም በመሆናቸው ለመሳተፍ በጣም ይጥራሉ።

- ከሌቶች ይልቅ ወንዶቹ ናቸው በስፋት የሚሳተፉት ስተርቫይዘሩ ደግሞ ብዙ ጊዜ ሌቶችን ማሳተፍ አለባችሁ ስለሚሉ ብጉተጉታቸውም አልሆነልኝም ነበር።

- ለመደበኛ መምህሩ የሚሰጡትን ክብር ያህል ለኔ አይሰጡም። አንዳንዶች ያለመደበኛ መምህሩ የማይዳኙና ስነ ስርዓት የማያከብሩ አሉ።

- ተማሪዎቹ ጉብዝና ጥሩ አስተማሪ ነው የሚሉት በገለፃ የሚያስተምራቸውን ነው። የቡድን ሥራ ሲሷቸው አይወዱም ጊዜ ማሳለፊያና የሰነፍ አስተማሪ ስራ መስሎ ነው የሚታያቸው። ቢሆንም በዕለቱ በገለፃ ማስተማር በራስ ውጤት ላይ መፍረድ ስለሆነ አላደረኩትም።

- አንዳንዶቹ ደስ የሚያሰኝ ባሕሪ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ በጣም የሚያስጠላ ባሕሪ ነበራቸው።

## 2.6 ቅድመ ምልከታ ውይይትን በተመለከተ

- ምልከታ ከመካሄዱ በፊት ከስፐርቫይዘሬ ጋር ውይይት አድርገን ነበር። እንዳትፈሩ፣ እንዳትጨነቁ የምዘናው ዓላማ እናንተን ለመጣል ሳይሆን ያላችሁበትን ደረጃ ለማሳወቅ ነው ብለውናል።

- ስፐርቫይዘሩ እክፍል ከመግባቱ በፊት አወያይቶናል። ነጥቦቹም ገብቼ እንዴት እንደምታስተምር እመለከትሀለሁ። አትፍራ፣ ተማሪዎችን ተቆጣጠር፣ ረዳሾችን ትጣ፣ ጥያቄ ተቀበል፣ ሌት ተማሪዎችን አሳትፍ፣ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ድጋፍ አድርግላቸው .... የሚሉ ነበሩ።

- ውይይት አድርገናል። እሳቸው ወደ ክፍል ሲገቡ ምን እንደማስተምር ጠየቁኝና ነገሯቸው። ዕለታዊ ዕቅዴን መያዜን እንዳልረሳ ነገሩኝና አንድ ኮፒ እንደሚፈልጉ ነግረውኝ ሰጠኋቸው ከዚህ በኋላ ነበር ወደ ክፍል የገቡት።

- ከምልከታው በፊት የተወያየነው ነገር የለም። ለምናልባቱ ክፍል የሚገቡበትን ክፍለ ጊዜ ማንሳውቅ ውይይት ከተባለ እንጂ።

- ከምልከታው በፊት ውይይት አናደርግም፡፡ እመጣለሁ ካለ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ብቻ ነው፡፡ አንዳንዴማ እኮ ምንም ሳይነግሩን ይመጡና የምንይዝ የምንጨብጠውን ያሳጡናል፡፡

- ውይይት አላደረግንም፡፡ እንዲያውም መምጣቱን የሰማነው ከ/ትቤቱ መምህራን ነው፡፡ ከዚያ ከአንድ ቀን በኋላ ተራ በተራ እክፍል እየገባ ገምግሞ ተመልሶ ሄደ
- መጀመሪያ ደህንነታችንን ጠየቁን፤ ከዚያም የመጡበትን ዓላማ ካስረዱን በኋላ የማስተማር ልምምዳችንን እንደሚመለከቱና በዚህም መፍራትና መጨነቅ እንደሌለብን ነገሩን፡፡

## 2.7 በድኅረ ምልከታ የተካሄደውን የምገበ መረጃ ትኩረት በተመለከተ

- ባወየነው ትኩረቱ ስለሌሰን ኘላን አወጣጥ፤ ስለ ዓላማ አፃፃፍ፤ ስለ መርጃ መሳሪያና ስለ ሌት ተግባሮች ተሳትፎ ነበር፡፡

- በማስተማር ልምምዱ ወቅት የታዩትን ጠንካራ ጎኖች ቀጥሉባቸው ሲሉን ደካ ጎኖችን ደግሞ እየዘረዘሩ በማሳየት እንድናሻሽል ይመክሩናል፡፡

- የሱፐርቫይዘሬ አስተያየት ጠንካራ ጎኔንም የጠቀመ ቢሆንም በጣም ብዙውን ጊዜ ግን ደካማ ጎኔን በሚመለከት ነው የነገረኝ፡፡ ወደፊትም ማሻሻል እንዳለብኝ ምክር ለግሶኛል፡፡

- በተናጠል አልተወያየንም፡፡ ግን በጥቅሉ ንግግር ሲያደርጉ ምንም እንኳ ብዙዎቻችሁን ከዚህ አንፃር በክፍል ተገኝቼ ባላያችሁም እዚህ ያሉ ነባር መምህራን እናንተ በዲሲኘሊን የታነፃችሁና ጥሩ አስተማሪዎች እንደሆናችሁ ነግረውኛል በማለት ተናግረው ሄደዋል፡፡

- በድኅረ ምልከታ ውይይት የሱፐርቫይዘሩ ትኩረት በደካማ ጎኔ ላይ ነበር፡፡ ይኸውም ይህን ይህን ነገር ሁለተኛ መድገም የለብሽም፡፡ በዚህ በዚህ መንገድ አስተካክለሽ ነው መቀበል ያለብሽ በማለት እንዳሻሽል ጠበቅ ያለ መመሪያና ምክር ለግሠውኛል፡፡ እኔም የተሰጠኝን መመሪያና ምክር በመቀበል ደካማ ጎኖቼን ለማሻሻል መጣር ይኖርብኛል፡፡

- ውይይቱ ግልጽ የሆነ መልዕክትና ትኩረት አልነበረውም። እዚህም እዚያም መርገጥ ነው። ከቁም ነገሩ ይልቅ ቀልዱ ይበዛል። እሳቸውን አድናቂ ተማሪ ያለ ይመስል ከእናንተ መሀል እኔን የሚተካኝ እንደሚኖር አልጠራጠርም ይላሉ።
- የት/ቤቱን ደንብና ሥርዓት አክብሩ፤ ወገኖቻችሁን በቅንነት አገልግሉ የሚል ዲስኩር አሰምተውን ነበር የተለያየ ነው።
- በኔ አስተያየት 70 ፐርሰንት የሚሆነው በደካማ ጎን ላይ ያተኮረ ገለፃ ነበር።

## 2.8 ሱፐርቫይዘሬቸው የሚሰጣቸውን ምግበ መረጃ መቀበል አለ መቀበላቸውን በተመለከተ

- ሱፐርቫይዘሬ በጥንካሬም ይሁን በድክመት የነገሩኝን እቀበለዋለሁ። ምክንያቱም የሱፐርቫይዘሮቻችንን አስተያየት ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ ከኛ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ነው።
- በድጋፍ ምልከታ ጊዜ ሱፐርቫይዘሬ የነገረኝን ሁሉ በሙሉ ተቀብያለሁ። ምክንያቱም ለኔ የሚጠቅመውን ነገር እንደመከረኝ ያለጥርጥር ስለተረዳሁ ነው።
- የሆነ ያልሆነውን መናገርና መጻፋቸውም የበዛ ይመስለኛል። እክፍል ውስጥ የቆየው ለ15 እና 20 ደቂቃ በመሆኑ አስተያየቱ ለውጤቱ እንደሚረዳኝ ባምንበትም እውነቱን ለመናገር ግን አልጣመኝም። እንዲያውም ትዝብት ነው ያደረብኝ።
- ሱፐርቫይዘሬ የሚሉትን ለመቀበል በጣም ተቸግሬ ነበር። አንደበቴ እሺ ይላል ሀሳቤ ደግሞ አልተቀበለውም። ለምሳሌ ንግድን የተመለከተ ንባብ አስነብቤ ተማሪዎቼ ሊያብራሩና እኔም ስገልጽ ሶሻል ሳይንስ አደረከው ብለውኛል ግን አልፈረድባቸውም እሳቸው የሒሳብ እንጂ የቋንቋ መምህር አይደሉም።
- ሱፐርቫይዘሬ በጠንካራም ይሁን በድክመት ካስቀመጣቸው ውስጥ የማልቀበላቸው ብዙ አሉ። ምክንያቱም ይህ "Personal" የሆነ ስራ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ በጥንካሬ ተማሪ አሳታፊ መሆኔን ጠንካራ ጎኔ ነው ብሎ ቢነግረኝም ውስጤ አልተቀበለውም። ብዙ ይቀረዋል ብዬ አስባለሁ።

በደካማ ጉንም ተማሪዎችን በስማቸው አትጠራም፣ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ቀን አልጻፍክም፣ አላስመርክም የሚለውን አልቀበለውም::

- በበኩሌ አልቀበለውም:: ምክንያቱም እኔን የገመገመኝ መምህር ደካማ ጐኔን ሲነግረኝ ሁለት ተማሪዎች ድንጋይ ላይ ተቀምጠዋል፣ ወንበር አሰርተሽ መስጠት ነበረብሽ ብሎኛል እኔ ለት/ቤቱ አስተዳደር አመልክቻለሁ መፍትሔ ግን አልተሰጠም:: በራሴ ወጭ ደግሞ ወንበር ላሰራ አልችልም:: የመጣሁት ለልምምድ እንጂ ወንበር ለማሰራት አይደለም ብዬ በጣም ተናደድኩ:: በዚህም የሚሰጠኝ አስተያየት ሁሉ አስጠላኝ፣ ምንም የተቀበልኩት የለም::
- በ40 ደቂቃ ውስጥ 86 ተማሪዎችን እንዳሳትፍ አዞኛል:: እሱ በኮሌጅ ውስጥ 40 ተማሪ ይዞ እንኳ ሁሉን ማሳተፍ አልቻለም:: አንዳንዱ ትዕዛዙና መመሪያው ሊፈጸም የማይችል በመሆኑ አልተቀበልኩትም:: በእርግጥ የተቀበልኩትም አለ:: የሰዓት አጠቃቀምን የጥቁር ሰሌዳን በተመለከተ የሰጠኝ አስተያየት ተገቢ ነበር::

## 2.9 በድጎረ የመማር ማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘራቸው ጋር ያካሄዱትን የምገባ መረጃ መስተጋብር ጠቀሜታ በተመለከተ

- በበኩሌ ጥሩ ምክር ያገኘሁበትና ለወደፊቱም ምን ምን መስራት እንዳለብኝ ግልጽ መመሪያ የተሰጠኝ ስለሆነ ተደስቼበታለሁ::
- መምህሩ የቋንቋ መምህር ባለመሆናቸው ጥሩ ምግበ መረጃ አገኘሁ ማለት አልችልም:: የሚናገሩትን ሁሉ እየተጠራጠሩ ስለሚናገሩ እኔም ትክክል ብዬ መቀበል አልቻልኩም::
- ነኀ ነኀ ተደርጐ በጥድፊያ የተካሄደ ስለሆነ የተፈለገውን ያህል እና እንደምጠብቀው አልሆነም::
- ምግበ መረጃው ለማ ለማ እንደሆን ሳይለይ ጠቅላላውን ተማሪ አንድ ላይ በመሰብሰብ የተሰጠ በመሆኑ የተመቸ ነገር አላገኘሁበትም::
- ደካማ ጐኖቼ ምን ምን እንደነበሩ በመጠኑ አይቼበታለሁ::

## 2.10 በምግብ መረጃ መስተጋብሩ ጊዜ የነበራቸውን ተሳትፎ በተመለከተ

- አንዳንድ ጥያቄዎችን እያነሳሁ ማብራሪያ ከመጠየቅ በስተቀር ሌላ ተሳትፎ አልነበረኝም።
- ቢቃወምም ቢደግፍም ሱፐርቫይዘሬ ግን ከቁም ነገር አይቆጥረውም
- በማመንና በማሳመን ላይ የተመሠረተ ውይይት እካሄዳለሁ:: ሁለታችንም ማስረጃችንን እያቀረብን እኔ ማስረጃ ካለኝ በ "Negative" መልክ የያዘውን አስተካክሎ ይሞላልኛል።
- ሱፐርቫይዘሬ ምክር ሲሠጠኝ እኔም እሺ እሺ እያልኩ ምክሩን እንደምቀበል የማረጋገጫ ቃል እሰጥ ነበር።
- ያልተቀበልኩትን ነገር ለመግለጽ ብሞክርም ማንም አልሰሠማኝም፣ በመሆኑም ምንም ነፃነት የለኝም ነበር።
- ተሳትፎዬ ሱፐርቫይዘሩ የሚለኝን በንቃት ማዳመጥ ነበር:: መጨረሻ ላይ ምን አስተያየት አለሽ ሲለኝ ብቻ ጥቂት ቃላትን ተናግሬአለሁ::
- ምን ምን እንዳደረኩ ዘረዘርኩለትና ሱፐርቫይዘሬ ጥሩ ነው በማለት የራሱን አስተያየት ቀጠለ።
- ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ስወያይ ሀሳቤን በነጻነት የመግለጽ መብት ነበረኝ::

## 2.11. አጠቃላይ ስለ ሱፐርቫዥኑና ምግብ መረጃው የሰጡት አስተያየት

- ምግብ መረጃ ወደፊት የበለጠ እንድንሰራ፣ ደካማ ጎኖቻችንንም ለማስተካከል የጐላ አስተዋጽኦ አለው። ግን ባግባቡ ስለማይካሄድ ምናልባትም ጊዜ ከተረፈ (ከተገኘ) እንጂ ምግብ መረጃ ሊሰጠም ላይሰጥም ስለሚችል የታሰበበት አይመስለኝም።

- ምግብ መረጃው ለወደፊት ስራዬ ጠቃሚ ነገር የማገኝበት ነው ብዬ ስለማምን ወደፊት ሰፋ ያለ ጊዜ ቢሰጠውና ቢከናወን ይጠቅማል ብዬ አስባለሁ::

- በኛ ኮሌጅ እንኳ ሱፐርቪዥን የሚባለው ነገር እንዳለ አይቆጠርም:: በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ ያውም ከሁለቱ አንዱ ወይም ሁለቱም ሳይካሄድበት ይቀራል ይህ እኛን ጐድቶናል።

- እኔ የምለው ግን መምህራን ለቱቶሪያል ሲመጡ እግረ መንገዳቸውን የማስተማር ልምምዳችንንም ቢመለከቱና ምግብ መረጃ ቢሰጡን እመኛለሁ::

ምክንያቱም ምገብ መረጃ ከሌለና ውጤት ሞልቶ መሮጥ ከሆነ ከነድክመታችን ልንዘልቅ ነው ማለት ነው።

- ምገብ መረጃውና ሱፐርቪዥኑ እንደአንድ ተግባር ቢቆጠር።
- መምህራኖቹ በየትምህርት ዓይነታቸው ቢገመገሙ ይሻላል ብዬ አስባለሁ አለበለዚያ ውጤቱም ሆነ ምገብ መረጃው ትክክል አይሆንም።
- ገና ተማሪዎች እንጂ ተመርቀን መምህር አልሆንም። ስለዚህ እንደተማሪነታችን የኮሌጁ መምህሮቻችን ሳይረሱን እየተከታተሉ ድክመት ጥንካሬያችንን ካላሳዩን ከኮሌጅ አባር ክትትልና ድጋፍ መንሳት ትክክል ያልሆነ ተግባር ስለሆነ ሱፐርቪዥኑንና ምገብ መረጃ በጣም ስለሚጠቅመን ለኮሌጁ ለማስገንዘብ እፈልጋለሁ።

- ምገብ መረጃ እንደኔ እምነት የታዩ ድክመቶችን በሚቀጥለው ጊዜ ላለመድገም ይረዳል። ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ አጠናክሮ ደካማ ጎኖችን አስወግዶ ባዶ እግራቸውን እሾህና ጠጠር እየወጋቸው ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው ለሚመጡ ተማሪዎች አጥጋቢ ትምህርት እንድንሰጥ ይረዳናልና ይታሰብበት ብዬ መልዕክቴን ለሚመለከተው ሁሉ በዚህ አጋጣሚ አስተላልፋለሁ።

## አባሪ ሦስት

## የሱፐርቫይዘሮችና የዕጩ መምህራን ምግበ መረጃ መስተጋብር ቅጅ ናሙና

### ሱፐርቫይዘር 1

### ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር፡ ከጀመጀመሪያው ጀምረን ሳየው ከክፍል ውስጥ ገብተህ በርመዝጋትህ የተማሪዎችህን «አቴንሽን» ለመግብ ይረዳል፡፡ ብላክቦርድ ማጽዳትህ ርዕሰ መፃፍህ፡ ... በሙሉ ቅድመ ዝግጅቶች በመሆናቸው በጥሩ ጐን የሚታዩ ናቸው፡፡ ወደ ሊስን ፕላንህ ሥመጣ ሊስን ፕላንህ ጥሩ ሆነው ሁለት ሦስት ተግባራትን ነጣጥለው አያሳዩም፡፡ ለምሣሌ ውይይት ማድረግ እንዳለባቸው፡ ንባብ እንደሚያቀርቡ ወይም እንደሚያነቡ ... እነዚህ በጥቅሉ የቀረቡ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ዕጥረት ይታያል፡፡

ሌላው ርዕሱን እንደፃፍክ 'Just" በቀጥታ ወደ ንባብ እንዲገቡ ነው ያደረከው፡፡ ግን ከዚያ በፊት የሽግግር፡ ልጆችን የማዘጋጀ ነገር ወይም የክለሳ ነገር አንዳንድ ሆሄዎችን ብታቀርብ ጥሩ ነበር፡፡ በቀጥታ ይህንን አንብቡና እነዚህን ተግባሮች ሥሩ ነው ያልካቸው፡፡ በሉ የዕለቱ ርዕስ ይኸ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን እነዚህን ሞክሩ በማለት የማዘጋጃ ነገሮች አላቀረብክም፡፡ እነዚህ ነገሮች መለመድ አለባቸው ነው፡፡ ተግባር አንድ እና ሁለት ውይይትና የንባብ ጊዜ ሥላልተከፋፈሉ «ቢቃ አቁሙ» «ሥትላቸው» «ቅይ ጋሺ » አልጨረስንም ብለው ነበር። ይህ ምንድ ነው 5 ደቂቃ ለቡድን ሥራ፣ 5 ደቂቃ ሊጋራ ውይይት፣ የቀረችውን 5 ደቂቃ ወይም 10 ደቂቃ ደግሞ ለንባብ ብትል ኖር ቆንጆ ይሆን ነበር።

ሌላው ጠቅለል ትንህ ግሩፕን ሱፐርቫይዝ አድርገሀል። ይህ ቆንጆ ነው ማንቀቃትህም ጥሩ ነው። ነገር ግን ቡድን ላይ ነው ያተኮርከው የግለሠቦችን ተግትሮ ጥምር ማካተት ነበረብህ። የግለሰቦችን ተሣትፎ ያማከለ መሆን ነበረበት።

ሌላው መልኚዎቼ ሥትወያዩ ያተኮርከው ዕውቀቱ ላይ ነው። አንተ አማርኛን ነው የምታሥተምረው። ቋንቋን ነው የምታሥተምረው ሥለዚህ አሁን ለምሣሌ ንግድ ምንድ ነው? እዚህ ላይ ብዙ እንዲያብራሩ አይደለም የሚፈለገው እንደኔ እምነት። ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፣ ነገር ግን እዚያ ምንድ ነው ልጆቹ ከሚያውቁት ነገር ተነሥተው እንዲወያዩ ነው።

አንዳንድ ነገሮችን እንዲገምቱ ነው። ወደ ንባብ ውስጥ እንዲገቡ ከምንባቡም ከዚያ ባሡብት መልክ እንዲለትሙ ነው፣ እንዲያዛምዱ ነው። እና ባብዛኛው ክህሎታቸው ላይ ያተኮረ ውይይት ብታቀርብ ቆንጆ ነበር ብዬ እገምታለሁ ለምሳሌ በንባቡ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች፣ በማንበባቸው ማወቃቸው፣ ያወቁትን መናገራቸው፣ መከራከራቸው፣.... ላይ ትኩረት ብታደርግ ቆንጆ ነው።

ሌላው ምግሌዎቹ ላይ የተሠጡ ምሳሌዎች ናቸው ንግድን አሥመልክቶ አንዳንድ አባባሎች ተያያዥ ነገሮች ተጠቅሠዋል። አንተም አንሥታህላቸዋል። ነገር ግን በአካባቢ ነገሮች ላይ ያተኮሩትና የተመሠረቱ ቢሆኑ ጥሩ ነው።

ሌላው ከንባብ ውስጥ ቁልፍ ቁልፍ የሆኑና ሊያወየዩ ይችላሉ ያልካቸውላን በፀሳ ከቦርድ ላይ ጽፈህላቸዋል። ይህ ቆንጆ ነው። እነዚህንና የመሣሠሉት የተወሠኑት ጥሩ ጥሩ ናቸው። የተወሠኑት ደግሞ ሊሸሻሉ ይገባቸዋል ብዬ አስባለሁ። በአጠቃላይ ክፍሉን የመቆጣጠር፣ የመከታተል የማሳተፍ ጉዳይ ጥሩ ነው ብዬ እገምታለሁ። ነገር ግን ምንድነው ንባብ ላይ የለሆሳስ ብለሀቸዋል። ማለትም ቀስ ብለው ለየግላቸው እንዲያነቡ አድርገሀል፣ በዚያ በኋላ ደግሞ ተራ በተራ እየተነሱ ጮክ ብለው እንዲያነቡ አድርገሀል። ይህ ምንድነው ጠቀሜታው ብለህ ታምናለህ ?

ዕጩ መምህር፡- ማለትም የንባብ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉና እንዲያዳብሩ ነው። መጀመሪያ ቀስ ብለው በለሆሳስ አንብበውታል። ከዚያ ደግሞ ጮክ ብለው በማንበብ የንባብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና እንዲለማመዱ ነው።

ሱፐርቫይዘር፡- ጥሩ ለሌላው ሠው በንባብ ማሠማት?

ዕጩ መምህር፡- አዎ

ሱፐርቫይዘር፡- ግን ጊዜ ሊሻማብህ ይችላል የሚል ግምት ስላለኝ ነው። እንደነዚህ ያሉ ነገሮች "Actually" በሌለን ኖትህ ላይ የተቀመጡ አልነበሩም። ክህሎቱን በንባብ ደረጃ ለማዳበር በሌለን ኖትህ ላይ ያሥቀመጥካቸው ነጥቦች የሉም። ነገር ግን ያልተቀመጡ ከሆን ጊዜ ሊሻማብህ ይችላል። አንድን ተግባር በሁለት በሦስት መልኩ ማቅረቡ ንባብ ክህሎት ላይ ያተኮረ ካልሆነ፣ ጊዜ ሊሻማብህ ይችላል ነው። በተረፈ ይኸው ነው። ጥሩ ነው በርታ ነው።

ዕጩ መምህር፡- እሺ

## ሱፐርቫይዘር 2

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር፡- እሺ አምኅስ የማስተማር ሥነ ዘዴው በጣም ቆንጆ ነው እንዲሁ በአቃላይ መልኩ ሲታይ ግን እንዲያው አጠቃላይ የሆኑ አስተያየቶችን ለመስጠት መጀመሪያ ከጠንካራ ጐኖቹ ከዚያም ስለ ደካማ ጐኖቹ ከዚያም ገንቢ አስተያየቶች ወደ መስጠት እንሄዳለን።

ጠንካራ ጐን ብዬ ከያዝኩልሽ ውስጥ አንደኛው የብላክቦርድ አጠቃቀም እሡ ጥሩ ነው። ማበረታቻ ቃላትን በመጠቀም ተማሪዎችን ማነቃቃትም ጥሩ ነው። ከሌላ ማኅኬድ ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን ተጠቅመሻል። በተለይ የቡድን ሥራ አጠቃቀም ጥሩ ነው። የቡድን ሥራ፣ ገለፃ፣ ጥያቄና መልስ ተጠቅመሻል ጥሩ ነው። ሌላ የግንዛቤ ጥያቄዎች "Reading passage" ካነበቡ በኋላ ያላቸውን "understanding" ለመገምገም የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በቦርድ ላይ ጽፈሽላቸዋል ያም ጥሩ ነው። በራስ የመተማመን መንፈስም ጥሩ ነው። እንግዳም ሆነ ምናምን ቢመጣ ያለመረበሽ ሁኔታ አለ ይህ ጥሩ ነው። ተገቢ የሆኑ ሚዲያዎችን ተጠቅመሻል። ይህም እንዳየሁት ተማሪዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጐላቸዋል። ተገቢ የሆኑ የንምኅምኅና የምዘና ዘዴዎች ተማሪዎችን በቡድን ማሠራት፣ ጥያቄዎችን እየጠየቅሽ እንዲመልሡ ማድረግ እንዲሁም ማብራሪያ በመስጠት ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለመረዳት ጥረት አድርገሻል። ተማሪዎች ከሚሠጡሽ ምላሽ በመነሳት "already" የተነደፉ ዓላማዎችን ተማሪዎች ጥሩ Understand ያደረጓቸው መሆኑ ይታወቃል።

ደካማ ጐኑ ወደፊት መስተካከል አለባቸው ብዬ የያዝኳቸው ነገሮች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

አንደኛው ሁሉንም ተማሪዎች ዕኩል አለማሣተፍ፣ ጐበዝ ተማሪዎች ላይ ብቻ የማተኮር ሁኔታ ይስተዋላል።

ሌሊሳ መምህር፡- እ… ምን መሠለህ … አብዛኛውን ተማሪዎች ተሣታፊዎች ናቸው እንዲያውም ከቁተረያል በኋላ ነው ይህንን «ክለሳ» የያዝኩት ጐበዙንና ሠነፉን ብዙም አላለየኋቸውም። የዚህ የከተማ ልጆች ከመሆናቸው አንፃር በጣም «ፋስት» ናቸው። ምንም ነገር የመረጥኩት የለም — ከተማሪዎች መሀል ከየግሩፕ ነው ሥጠይቅ የነበረው — ሴት ወንድ እያልኩ።

ሱፐርቫይዘር፡- ምን መሠለሽ ሁሉም ተማሪዎች እጅ ላያወጡ ይችላሉ። በአይናፋርነትም የተነሣ ወይም በተለያየ ምክንያት ላይሣተፉ ይችላሉ። ካለማወቅም ዝም ሊሉ ይችላሉ።

ስለዚህ ጉብዝ፣ መካከለኛ፣ ሰነፍ... ሁሉም ቢሳተፉ የተሻለ ነው ከሚል አኳያ ነውና እንደ አስተያየት ብትይዢው ጥሩ ነው።

ሌላው የማስተማር ቅደም ተከተል ላይ ነው። ለምሳሌ ምንባብን በቡድን ነው የሠጠሻቸው። ከዚህ ይልቅ ምንባቡን በግላቸው አንብበው በኋላ በቡድን እየተወያዩ ቢሠሩ ወይም ደግሞ አንድ ሠው ሁለት ሰው እንዲያነበው ቢደረግ አይሻልም?

ዕጩ መምህር፦ ይህን ያደረኩት 1ኛ ደቂቃው ትንሽ ነው። ወጥተው እስከሚያነቡ ድረስ ደቂቃው ያልቅብኛል። 20 ደቂቃ ስለሆነ 2ኛው ደግሞ ከግሩፕ ሁለት መጽሐፍ አለ። ከ3 ተማሪዎች ጋር በአንድ ላይ እያደርኩ አንደኛዋ እያነበበች በሀግቡ ዙሪያ እንዲወያዩ ነው ያደረኩት።

ሱፐርቫይዘር፦ ሌላው የቡድን ሥራ ሥትሠጭ ሰዓቱን አልወሠንሽላቸውም።

ዕጩ መምህር፦ ፊሊ ነኝ የያዝኩላቸው።

ሱፐርቫይዘር፦ ግን ለእነሡ Inform ቢታደርጊላቸው የጊዜ አጠቃቀምን እንዲለምዱ ማለት ነው። ለምሣሌ ውይይት የምታደርጉት ለዚህን ያህል ደቂቃ ነው ብትያቸው፣ ለልጆቹ awareness መፍጠር ሊሆን ይችላል ሌላ በየቡድኑ አንድ Lead የሚያደርግና አንድ ሀሳብ የሚያሠባስብና የሚጽፍ ብትመድቢ ጥሩ ነበር።

ሌላው በቡድን ሥራ ጊዜ ተዟውሮ ክትትል አለማድረግ አልፎ አልፎ ይታይ ነበር። በቡድን ሥራ እየተዘዋወሩ መመልከት ተጨማሪ ማብራሪያ በሚፈለግበት ጊዜ አስፈላጊውን ዕገዛ ማድረግ ተገቢ ነበር።

ሌላው ጥያቄዎች በተለይ passage Reading Understanding ጥያቄዎችን ጽፈሽላቸዋል ወይትቦርድ ላይ ያጥሩ ነው። ነገር ግን በቋንቋ ላይ እንደምንረዳው ግን መጀመሪያ እነዚያን ጥያቄዎች ተማሪዎች ቢያውቋቸው ኖሮ በምን በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ግንዛቤ ሊወስዱ ይችሉ ነበር። በዚህም በይበልጥ ሥለ «ፓሴጁ» ጉጉት ሊያድርባቸውና የማንበብ ፍላጐት ሊጨምር ይችላል። የትኩረት አቅጣጫቸውንም ሊቀይሱ ይችላሉ። ግን በስተመጨረሻ ነው ጥያቄዎችን ያቀረብሽላቸው እና የፃፍሽላቸው።

ዕጩ መምህር፦ ግንዛቤያቸውን ለማወቅ ነው መጨረሻ ላይ ጥያቄዎችን ያቀረብኩት ግን በምን በምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው በየቡድኑ ዞሬ ነግሬአቸዋለሁ።

ሱፐርቫይዘር፦ እንደዚያ ከሆነ "ok" ግን እንደማውቀው "Language" ትምህርት ላይ Pre reading, while reading, post reading Question አለ ። በተለይ የተማሪዎች የማንበብ ፍላጐትና "understanding" እንዲጨምርና በምን በምን ላይ ማተኮር

እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ መጀመሪያ ጥያቄዎቹ ቢቀርቡላቸው ጥሩ ነበር ነው። ለወደፊቱ ይህ ቢደረግ ጥሩ ነው።

ሌላው ለሚቀጥለው የቤት ሥራ ሰጥተሻቸዋል። ጥሩ ነው። እንደአጠቃላይ ያየሁት የማስተማር ዘዴ ጥሩ ነው። ለወደፊቱ ተጠናክሮ ይቀጥል። ይኸው ነው እንግዲህ… መጨረሻ ላይ አንቺ ለትሠጭው የምትፈልጊው አስተያየ ካለ?

ዕጩ መምህር፦ በተረፈ ጠንካራና ደካማ ጐን ሥለተነገረ በጣም ጥሩ ነው። ያው እንግዲህ እናስተካክላለን።

## ሱፐርቫይዘር 3

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር ፦ የምሠጥሽ አስተያየት ከጠንካራ ጐንሽ ነው የምጀምረው በኋላ ደግሞ መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች አሳይሻለሁ። ጠንካራ ብዬ የያዝኳቸው፦ የባለፈውን ትምህርት በመከለስ መጀመርሽ፣ ተግባሮችሽም በጣም ጥሩ ናቸው። የጥቁር ሠሌዳ አጠቃቀምሽም ጥሩ ነው ብዙ ባትጠቀሚበትም የእጅ ጽሁፍሽም ጥሩ ነው። በተለይ ደግሞ ተማሪዎችሽ በጣም በመነቃቃት ነው የሚሣተፉልሽ። ምናልባት የተለያዩ ተግባራትን ሥለምታሠሪያቸው ሊሆን ይችላል። ተማሪዎችን በሥም እየጠራሽ ማሣተፍሽ በጣም ጥሩ ነው። የምትሠጫቸው ምሣሌዎች ከተማሪዎች ውጫዊ ህይወት “partical Example” ከምንለው ጋር የሚመሣሠሉ በመሆናቸው በጣም ጥሩ ናቸው። በዕለታዊ ዕቅድ ላይ መስፈር የሚገባቸው ተግባሮች ናቸው በዕቅዱ የሠፈሩት የየቡድኖቹን ጠንካራና ደካማ ጐን ነግረሻቸዋል። ድምጽሽም ይሰማል። እነዚህ ናቸው ከሞላ ጐደል ጠንካራ ጐን ብዬ የያዝኳቸው።

መሻሻል ይገባዋል ብዬ የያዝኩት ካልገባኝ ታሥተካክይኛለሽ 1ኛው በዕቅድሽ ላይ ያስቀመጥሽውን ነው በክፍል ውስጥ መተግበር ያለብኝ በዕቅድሽ ላይ 30 ደቂቃ ተማሪዎች የቡድን ሥራ ሠርተው ያገቡበርቃሉ ብለሻል ግን ተማሪዎች 15 ደቂቃ እንኳ አልፈጀባቸውም። ሌላው አንቺነሽ ብዙውን ጊዜ የፈጀሽው አስተያየት በመስጠት ፣ በመከለስ፣ ግምገማ በመሰጠት፣ ነገር ግን በዕቅድሽ ላይ ለአንቺ ተግባር ያሠፈርሽው 3 ደቂቃ ብቻ ነው። የፈጀሽው ግን 15 በላይ ነበር። ከዕቅዱ ጋር «ማች» አላደረግሽም any way ተማሪ ተኮር ነበር ግን አንቺ ብዙውን ደቂቃ ፈጅተሻል ነው ሌላው ባህሉ ትንሽ ተቀይሯል እያልሽ አስተያየት ስጥተሻል ግን ሥነ ቃል ከትውልድ ወደ ትዉልድ ሲሸጋገር ለውጥ ማምጣቱ አይቀርም። በዚህ ዘመን የቀረበው በሌላ ዘመን ሲከናወን የተወሰነ ለውጥ ማምጣቱ አይቀርም። ለውጡም ብዙውን ጊዜ በግጥሙ ላይ ሊሆን



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ይችላል ታዲያ ሥነ ቃል ከዘመን ዘመን ለውጥ ካሣዩ በባህል ላይ ለውጥ አይታይም ወይ?

ዕጩ መምህር፡- ለውጥ ይታያል፣ ግን ቅድም ከተማሪዎች ጋር አስተያየት ሥንሠጣጥ ሠምተሽ እንደሆን ባህላችንን ሥናሳድግ መጥፎዎችን እየጣልን፣ ጥሩዎችን እየያዝን ነው የምንሄደው። ተማሪዎች የገና ጨዋታ ሲጨዋወቱ እስተውለሽ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ በልምድ ሥድብ ዓይነት ነገር ይጨምሩበታል። እንደገና ማንቅርቅርያ ሠርቆ.. ይላሉ። ይህ ደግሞ ከባህላችን ያስወጣናል። አስተማሪ ያልሆነና ጥሩ ያልሆነ ነገር ይናገራሉ። ልብ አላልሽው ይሆናል እንጂ ከባህሉ አትውጡ አልኳቸው እንጂ ግጥሙም ባህሉም ሊለወጥ ይችላል አንቺ እንዳልሽው።

ሱፐርቫይዘር፡- ቆንጆ እንደዚያ ከሆን አስተያየቱ በዚያ መልኩ ይስተካከላል ሌላ ደካማ ጐን አልያዝኩም። በጣም ቆንጆ ነው በዚሁ ቀጥይ በርቺ። ፖርትፎሊዮሽን አይቻለሁ። ያቀረብሽው ጥሩ ነው። ሆኖም ግን ቱቶሪያል አልተሠጠም ይላል ት/ቤቱ ግን አንቺ ሰጥቻለሁ ብለሽ አሥፈርሜኛለሁ። ይህ እንዴት ነው በእርግጥ ሠጥተሻል ወይ?

ዕጩ መምህር፡- ቱቶሪያል ሳይሆን ለሴት ተማሪዎች አንዳንድ ነገሮች ለምሣሌ ሥለ ሞዴስ አጠቃቀም ትምህርት ሠጥቻለሁ። መደበኛ ክበቤ በጐ አድራጐት ነው ከዚያ ወጣ ብዬ ለሴት ተማሪዎች ክበብ አንዳንድ ትምህርቶችን ሠጥቻለሁ።

ሱፐርቫይዘር፡- ቱቶሪያል በት/ቤቱ አይሠጥም ማለት ነው? ምንድ ነው ችግሩ?

ዕጩ መምህር፡- ቱቶሪያል ይሠጣል። ግን በዚህ ትምህርት ላይ አልተሠጠም። ቱቶሪያል እየተሠጠ ነው። ለምሣሌ ሠሞኑን በህዝብ ቆጠራ ምክንያት እኛ እዚህ ቱቶሪያል ላይ ነን።

ሱፐርቫይዘር፡- አንቺ ቱቶሪያል አልሠጠሽም ማለት ነው?

ዕጩ መምህር፡- ቱቶሪያል አይደለም... ያ... ለልጃገረዶች ክበብ የተሠጠ ትምህርት ነው

ሱፐርቫይዘር፡- እሺ ጨርሻለሁ

ዕጩ መምህር፡- አመሠግናለሁ።

## ሱፐርቫይዘር 4

## ውይይት 2

ሱፐርቫይዘር፡- እሺ ድንበሬ 6ኛ ሀ አማርኛ ስታስተምሪ በተለይም «ከልዩ ልዩ ምንጭ መረጃ መሠብሰብ» የሚል ርዕስ ሥታሥተምሪ ተመልክቻለሁ። በማሥተማሩ ሂደት የተመለከትኳቸውን አሥተያየቶች እንደሚከተለው አቀርብልሻለሁ። በምሰጣቸው አስተያየቶች ላይ የራስሽን አስተያየት ምን እንደሆን ማቅረብ ይፈቀድልሻል።

ሌሰን ኘላንሽን ስንመለከት ዝርዝር ዓላማዎች አሉ፡፡ ከነዚህ ዝርዝር ዓላማዎች መካከል የመጀመሪያው «ከልዩ ልዩ ምንጮች መረጃ መሠብሠብን ይገነዘባሉ» ይላል፡፡ ይህ ዓላማ የሚለካ አይደለም፡፡ ጥቅል ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማ እንዲሆን "SMART" መሆን አለበት፡፡ ሌላው ዓላማ ግን ጥሩ ነው፡፡

ዕጩ መምህር፦ እሺ

ሱፐርቫይዘር፦ ተግባራትን ስንመለከት በጊዜ ተሸንሽነው የቀረቡ ናቸው፡፡ ተግባር አንድ 10 ደቂቃ ተግባር ሁለት 15 ደቂቃ፣ ምዘና 10 ደቂቃ መደምደሚያ 3 ደቂቃ… እያልሽ አቅርበሻቸዋል፡፡ ይህ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን የመምህሩን ሚና ነው የገለጽሽው የተማሪውን ሚና አልገለጽሽም፡፡ እንዲህ ማድረግ፣ እንዲህ እንዲሠሩ ማደራጀት ወዘተ. ነው ያልሽው ተማሪዎች ይወያያሉ፣ ይመልሳሉ፣ ወዘተ. ማለት ነበረብሽ፣፣

ዕጩ መምህር፦ ተማሪዎች ይወያያሉ፣ ይደራጃሉ፣ … ማለት ነበረብሽ ነው?

ሱፐርቫይዘር፦ አዎ፣ … የመምህሩን ሚና ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችም ምን ምን እንደሚሠሩ ተግባራቸውን ማመላከት ነበረብሽ፡፡

ዕጩ መምህር፦ እሺ…

ሱፐርቫይዘር፦ አዎ ለምሳሌ እንዲሠሡ ማድረግ ሳይሆን ይሠጣሉ፣ ያደርጋሉ ወዘተ ብይ

ዕጩ መምህር፦ እኔ እኮ በመጽሐፉ የሚሠሩትን እንግራለሁ እንጂ አድራጊዎቹ እኮ እነሡ ናቸው፡፡ እኔ ሥሩ ካልኳቸው ካልነገርኳቸው እንዴት ይሠሩታል??

ሱፐርቫይዘር፦ ንገሪያቸው፣ ግን ሥትነግሪያቸው እነሡ ደግሞ ማድረጋቸው መገለጽ ነበረበት

ዕጩ መምህር፦ እሺ…

ሱፐርቫይዘር፦ ሌላው ክለሳ ስታቀርቢ በጣም አሥረዝመሽዋል፡፡ ማብራሪያ፣ ምሣሌ እያልሽ ብቻ 18 ፈጀተሽበታል፡፡ ልክ አዲስ ትምህርት አድርገሽ ነው ያቀረብሽው፡፡ ይኽ መሥተካከል አለበት የግድ ፡፡ ቢያንስ ከ5 ደቂቃ ባይበልጥ ጥሩ ነው፡፡

- ተማሪዎችን የማግተፉ ሁኔታ በጣም ጥሩ ነው
- በሚዲያነት በሌሰን ኘላንሽ ላይ የሠፈረው የእከሡም ሀውልት ነው፣ ነገር ግን በተግባር ያዋልሽው የሣልበዓን ሀንፃ ነው፣ ለምን?

ዕጩ መምህር፦ በአጋጣሚ የአክሡምን ሀውልት አሥቀድመው ሥላዩት አሁን ደግሞ የሣልበዓን ቢያዩት ይሻላል ብዬ ነው፡፡

ሱፐርቫይዘር፦ አይ… እንደሡ ከሆነ በሌሰንኘላንሽም ላይ መቀየርሽን መግለጽ ነበረብሽ፡፡ በሌሰንኘላኑ የሠፈረውና በተግባር ያዋልሽው ሚዲያ ተለያይቷል፡፡ ይህ መሆን አልነበረበትም፡፡

ዕጩ መምህር፦ እሺ

ሱፐርቫይዘር፦ ሌላው ችግርሽ ደግሞ ምንድ ነው? … በመስኮት አካባቢ ተማሪዎች ተደርድረው ነበር። ያን ጊዜ ተከሉ! … ትይ ነበር። ይህን ማለት ግን አልነበረብሽም። ቢመለከቱ ምን ቸገረሽ ዞር በሉ ማለት ከውጭ ያለው የዩኒት ሲደሩ ወይም የዘበኛው ሥራ ነበር። አንቺ ግን የእነሡን ሥራ ወስደሽ ዞርበሉ! ከዚህ ሂዱ በማለት አላሥፈላጊ የሆን ጊዜ አጥፍተሻል። ያንቺ ተግባር ማሥተማር ብቻ ነው። ቢደረደሩ ምን ቸገረሽ እሥካልረበሹ ድረስ

ዕጩ መምህር፦ አይ እየረበሹ እኮ ነው ጋሼ!

ሱፐርቫይዘር፦ አልረበሹም… አልረበሹም። ዝም ብለው ተደርድረው ነበር የሚመለከቱት እርግጥ የተማሪዎችን "attention" ሊሠርቅ ይቻላል። ቢሆንም ይህ የዩኒት አስተባባሪ ሥራ ሥለሆነ እነሡን በሚመለከት ዞር በሉ እያልሽ ጊዜ ማጥፋት የለብሽም።

ዕጩ መምህር፦ አይ የኔንም "attention" ሥለ ሠረቁኝ እኮ ነው

ሱፐርቫይዘር፦ ለምን አትተያቸውም። ያንቺ ትኩረት ለምን ወደነሡ እንዲሆን ትፈቅጃለሽ ?

ዕጩ መምህር፦ ለመተው ያሥቸግራል። ተማሪዎቼም ወደዚያ ሲሳቡ ይችላሉ ብዬ ሥለ ሠጋሁ ነው።

ሱፐርቫይዘር፦ አይ እንደዚያ በማድረግሽ እኮ ጊዜሽን እየገደልሽ ነው። ያንን ማድረግ ያንቺ ሥራ እስካልሆን ድረስ በማስተማር ሥራሽ ላይ ብቻ ማተኮር ነበረብሽ ነው የኔ ምክር።

ዕጩ መምህር፦ እሺ

ሱፐርቫይዘር፦ በቀረበው ፎቶ ግራፍ ከፎቶ ተገቢ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ ምክረሻል ጥሩ ነው። ግን ለተወሠኑ ተማሪዎች ብቻ ነው ያሥየሻቸው ሁሉም ማየት ነበረባቸው።

ዕጩ መምህር፦ ከጊዜ አንፃር ነው። መጨረሻ ላሳያቸው ነግሬአቸው ነበር።

ሱፐርቫይዘር፦ በአብዛኛው ትምህርቱ ገለፃ ነበር። ብዙውን ጊዜ አንቺ ፊጅተሻል የሚፈለገው ግን ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ለማድግ ነበር። በእርግጥ የጊዜ ዕጥረት ሥለሚያጥመኝ እንደምትይ ይገባኛል። ጊዜን ባግባቡ የመጠቀም ልምድ ማዳበር ያሥፈልጋል።

በተረፈ እነዚህን የተሠጡሽን አሥተያየቶች ካሥተካከልሽ ለወደፊቱ ጥሩ መምህር እንደምትሆኚ ተሥፋ አለኝ።

ዕጩ መምህር፦ እሺ

<u>ሱፐርቫይዘር 5</u>

<u>ውይይት 1</u>

ሱፐርቫይዘር፦ ታምራለች እንግዲህ 7ኛ ሀ ለ 40 ደቂቃ ያህል በቆየባቸው ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያያዝኳቸውን ጠንካራና ደካማ ጐኖች እነግርሽና በዚያ ዙሪያ ያለሽን አሥተያየት ትገልጭልኛለሽ።

ዕጩ መምህር፦ እሺ

ሱፐርቫይዘር፦ በመጀመሪያ ከዓላማ አቀራረጽ ሥንነሳ ዓላማዎችሽ ግልጽ ሆነው ተቀርፀዋል። የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያመላክት መልክ ተቀርፀዋል። ብዬ አስባለሁ ከዚያ ቀጥሎ የሚመጣው የመማር ማስተማሩን ተግባሮች ሥናይ ተግባሮቹን መምህር ተኮር ሆነው ነው ያገኘኋቸው። የተማሪዎችን እንቅስቃሴ ወይም የሥራ ድርሻ የሚያመላክት ነገር አላቀረብሽም። ትምህርቱ ደግሞ ተማሪ ተኮር ነው። ተግባራዊ ከንውኑን ስመለከተው ተማሪ ተኮር ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በሌሰንፕላንሽ ላይ ግን ተማሪ ተኮር አድርገሽ አላስቀመጥሽውም… ቡድኖችን እየተዘዋወርሽ እንዲሣተፉ፣ እንዲሠሩ ማድረግሽ በጣም ጥሩ ነው። በዚሁ ልትቀጥይ ይገባል። ቡድኖች የደረሡባቸውን ግንዛቤዎች በተወካዮቻቸው አማካይነት እንዲያቀርቡ ማድረግ ለሌላውም እንዲያካፍሉ ማድረግሽ ጥሩ ነው። እንዲህ እንዲህ ያለው ጥረት ይበረታታል።… ከቡድን ሥራዎች አቀራረብ አንፃር ያለውን ሥመለከት ሰባት ቡድን አደራጅተሻል። ከነዚህ ውስጥ ስድስቱ በወንድ ተማሪዎች ነው የቀረቡት አንድሴት ብቻ ናት አቅራቢ የሆነችው በዚህም የወንድና የሴት ተማሪዎችን ተሣትፎ የተመጣጠነ ለማድረግ አልሞከርሽም። እ… ጥቁር ሠሌዳ አጠቃቀምሽ ግን ጥሩ ነው። በተረፈ ከተማሪዎች ጋር በምታደርጊው ውይይት ተማሪዎችን ለማበረታታት የምታደርጊው ጥረት ጥሩ ነው። የሚሠጡትን አስተያየት ለመቀበል ያደረግሽው ጥረት ጥሩ ነው። ለምግሌ ማቴሪያል የሚለውን ቃል ለምን በአማርኛ አንተካውም! የሚል አስተያየት ሲቀርብ የሠጠሽው ምላሽ ተገቢ ነው ብዬ አስባለሁ።… በተረፈ ደግሞ በጣም ጠንካራ ጐን ሆኖ ያገኘሁት ሴት ተማሪዎችን ለማሣተፍ ያደረግሽው ጥረት ነው። በተደጋጋሚ እስቲ ሴት ተማሪዎች ተሣተፉ ትያለሽ፣ እንዲሞክሩ ትገፋፊያለሽ፣ በመጠኑ ጥሩ ውጤትም አይቻለሁ። ሆኖም ግን አብዛኞቹ ሴት ተማሪዎች እንዳሰብሽው ሊሣተፉልሽ አልቻሉም። ያንቺ ጥረት ግን ጥሩ ነው። ሊቀጥልና ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው። የተማሪዎችሽ የክፍል ተሣትፎአቸውም በጣም ሞቅ ያለ ነው። ብዙ ተማሪዎች ጠይቆ ለመረዳት ከፍተኛ ፍላጐት ያላቸው ናቸው። ብዙዎቹ ደግሞ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት

ሞክሬዋለ። ሞቅ ያለ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ነበር። በዚሁ ልትቀጥይ ይገባል። ትምህርቱን በአጠቃላይ በተዘጋጀ ዕቅድ መሠረት ለማቅረብ ጥረት አድርገሻል። … እንግዲህ በኔ በኩል የያዝኳቸው እነዚህ ናቸው እነዚህን በተመለከተ የምትሠጭው አስተያየት ካለ መሠንዘር ትችያለሽ።

ዕጩ መምህር፡- ችግሮችን ማለትህ ነው?

ሱፐርቫይዘር፡- አዎ፣ አሁን በሠጠሁሽ አስተያየት ላይ ያንቺ አስተያየት ምንድ ነው? የምትቀበያቸውና የማትቀበያቸው አስተያየት ካሉ፣

ዕጩ መምህር፡- ተግባሮችን ባብዛኛው መምህር ተኮር ነው ያደረግሽው ያልከው ግን ያው በቡድን እንዲሠሩ አድርጌአለሁ። በአብዛኛው ደግሞ እኔ ማጠቃለያ መስጠት ሥላለብኝ ነው። እነሱን ብቻ እያሠራሁ እኔ ቁጭ ብል እነሱ ደግሞ ትችት ይሠጣሉ። እኛው ብቻ የምንሠራ ከሆነ መግቢያ ካልተሠጠን ደግሞ ማጠቃለያ ካልተሠጠን መምህር ምን ያደርግልናል የሚሉ ናቸው ባብዛኛው በዚህ ት/ቤት ያሉት ሥለዚህ እኔ ወደ እነሡም ሳላበዛ እኔም ሳልጫን ያቀረብኩ ነበር የመሠለኝ እንጂ እዚህ ላይ ባብዛኛው ገለፃ አደረግሽው ያልከው ላይ ነው አስተያየት ያለኝ። ዝም ብል እንደ ችሎታ ማነሥ የመቁጠር ነገር አለ። አታሥተምሪንም፣ ግልጽ አልሆንልንም.. እንዲህ እንዲህ ያለ ነገር ነው ባብዛኛው እዚህ ት/ቤት ያለው። እነሱን ብቻ ዝም ብዬ ማዳመጥ ሥለሌለብኝ ነው ወደ ገለጻውም እየገባሁ ያስተማርኩት

ሱፐርቫይዘር፡- አዎባሌ እነሱን ብቻ ተናጋሪ አድርገሽ አንቺ ተቀመጭ አይደለም። መምህሩ አመቻች ነው " Facilitator" ነው የሚባለው። አቅጣጫ ማሣየት ማገዝ፣ መደገፍ ነው የመምህሩ ተግባር ብዙውን ሊሠሩት የሚገባቸው ተማሪዎች ናቸው። ከዚህ አንፃ ነው አስተያየት የሰጠሁሽ። ለምሣሌ እዚህ ላይ ብትመለከች፡-

- ተማሪዎች ማመልከቻ እንዴት እንደሚጽፉ መናገር
- ተማሪዎች ቡድን እንዲመሠረቱና የቡድን ተጠሪ እንዲመርጡ ማድረግ
- የሚጠየቁባቸውን ነጥቦች ጥቁር ሠሌዳ ላይ መጻፍ
- የተሠጡሩ ወገኖችን ለመጠየቅ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎችን ለመጠየቅ በማመልከቻ ጽፈው እንዲያነቡ ማድረግ እንጂ እንዲህ እንዲህ ያደርጋሉ አላልሽም።

ዕጩ መምህር፡- አሀ ! ያደርጋሉ… ያደርጋሉ አላልሽም ነው። እኔ በእርግጥ በዚህ አባባል ውስጥም እነሱ እንደሚፈጽሙ ነበር የማስበው ግን የቃላት አገላለጽ ትክክል አይደለም ስለተባለው ወደፊት ለማስተካከል ጥረት አደርጋለሁ።

ሱፐርቫይዘር፡- እሺ መልካም ነው ሌላስ የምትይው ይኖራል

ዕጩ መምህር፡- ሌላ ያው ባብዛኛው ሴቶች እንዳልኩት ሲሣተፉልኝ አልቻሉም፡፡ እነሡ ላይ ዕጥረት አለ፡፡ ብጉተጉትም የማፈር ሁኔታም ከታችም ይዘውት የመጡት ሁኔታና ልምድ ሊያግተቶቸው አልቻለም፡፡

ሱፐርቫይዘር፡- መጉትጉት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የተለያዩ ተግባሮችንና ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሣተፉ ማድረግ አለብሽ እንጂ ብጉተጉት… ብጉተጉት ሲሣተፉልኝ አልቻሉም ብለሽ ሙተው የለብሽም፡፡ ጥረት ማድረግ ይኖርብሻል አለበለዚያ የማስተማር ጥረትሽን እንደ አቅጣጫ ብቻ ነው የሚያደርግብሽ

ዕጩ መምህር፡- እሺ

## ሱፐርቫይዘር 6

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር፡- እሺ አሥቴር 8ኛ B ነው የተገመገምሽው አይደል?

ዕጩ መምህር፡- አዎ

ሱፐርቫይዘር፡-ርዕሱ ምን ነበር? ሥነ ጽሁፍ የሚልና በሥነ ጽሁፍ ውስጥ ደግሞ የሰነቃል፡፡

ዕጩ መምህር፡- አዎ

ሱፐርቫይዘር፡- እና የተጠቀምሽው የመማር ማስተማር ዘዴ ጥሩ ነው፡፡ አስተያየቴን የምጀምረው ከትምህርት ዕቅድሽ ላይ ነው፡፡ እና መማር ማስተማር ዕቅድሽ ላይ ያስቀመጥሽው ዓላማ እሡላይ /ሌሰንኘላኑ/ አስከምጨዋለሁ አስተያየቴን … ዓላማዎች በሦስት ይከፈላሉ፡፡ ከሦስቱ አንዱ ደግሞ አዕምሮታዊ ነው፡፡ አዕምሮታዊ ራሱ ደግሞ 6 ደረጃዎች አሉት፡፡ ስድስት በክብደት ደረጃ ነው የሚቀመጡት፡፡ ያንቺ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡ በመሆናቸው ተማሪዎችን ወደ ተግባር እንዳይሄዱ እንዳይመራመሩ የሚያግዱ ዓላማዎችን ብቻ ነው የሠፈርሽው፡፡ እዚህ ላይ አሁን ለግሌ ሥነ ቃል ያሠባስባሉ ብታይው ኖሮ ወደ ተግባር ሄዱ ማለት ነው፡፡ የሥነ ቃልን ንድፈ ሀሳብ ካዩ በኋላ ተረት ይሰበስባሉ፣ ዕንቆቅልሽ ይሠበስባሉ … ወይም ደግሞ የተሠበሠቡ ሥነ ቃሎችን ይተቻሉ፣ ይነመግግሉ በማለት ወደተግባር ማስገባት ይቻል ነበር፡፡

ዕጩ መምህር፡- እህ … እሺ

ሱፐርቫይዘር፡- የመማር ማስተማር ቅደም ተከተሉ ላይም ጥቅል ነው ያደረግሽው የተማሪው ሙያ ምንድነው? የመምህር ሚና ምንድን ነው የሚለው ተለይቶ ተማሪው ይህን ይህን ያሠራል፣ መምህሩ ደግሞ ይህን ይህን .. ያግዛል ተብሎ መለየት ነበረበት፡፡

ተግባሩም ደግሞ በቡድን ይወያያሉ ነው የሚለው በምን ላይ ነው የሚወያዩት መገለፅ ነበረበት።

ዕጩ መምህር፦ እ... እንትን ... ሥነ ቃል ምንድነው ? በሚለው ላይ ይወያያሉ

ሱፐርቫይዘር፦ አዎ እሡ ላይ ሊስንኙላት ላይ ተጽፏል ወይ?

ዕጩ መምህር፦ እዚህ ላይ አልተገለፀም

ሱፐርቫይዘር፦ መፃፍ ነበረበት። የቡድን ውይይት ያደርጋሉ ብቻ ነው የሚለው

ዕጩ መምህር፦ የሥነ ቃልን ዓይነት ይዘረዝራሉ፣ የተዘረዘሩት ደግሞ ያብራራሉ፣ ያብራሩትን ያቀርባሉ ብዬ ነው።

ሱፐርቫይዘር፦ ሌስንኙላት ይህን ይላል ወይ?

ዕጩ መምር፦ አይ ሌሡንኙላት ይህን ሁሉ አይልም

ሱፐርቫይዘር፦ እሱን ነው እየነገርኩሽ ያለሁት የሚሠሩ ተግባራት ሁሉ ሌስን ኘላኑ ላይ መሥፈር ነበረባቸው።

ዕጩ መምህር፦ እህ... አሁን ስለ ሌስን ኘላኑ ነው አስተያየት የሚሠጠው

ሱፐርቫይዘር፦ አዎ ሌስን ኘላንሽን በተመለከተ ነው አስተያየት እየሠጠሁሽ ያለሁት

ሱፐርቫይዘር፦ ወደ ሌሎቹ ስንሄድ ደግሞ ጥቁር ሠሌዳ አጠቃቀም ላይ መስተካከል ያለባቸው ነገሮች ያሉ ይመስለኛል። ጥቁር ሠሌዳውን በርዕሱ ብቻ ሞልተሽዋል አይደል?

እጩ መምህር፦ አዎ፣ እሚፃፍ ነገር ባለመኖሩ፣ በውይይት ብቻ የሚያልቁ በመሆናቸው ርዕሱን እስተዋውቄ የዕለቱን ትምህርት ከገለፅኩ በኋላ ወደ ቡድን ውይይት ስለሚገቡና የሚፃፍ ነገር ባለመኖሩ ነው ጥቁር ሠሌዳውን ያልተጠቀምኩበት

ሱፐርቫይዘር፦ ግን አሁን በቡድን ውይይት ላይ የሚነሱ ነጥቦች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃ ፉ የሚገባቸው ይኖራሉ።

ዕጩ መምህር፦ ምሳሌዎቹ ደግሞ በአዘጋጀሁት ሚዲያ ( የትምህርት መረጃ መሣሪያ) አማካይነት ስለቀረቡ ጥቁር ሠሌዳ ላይ ብዙም የሚፃፍ ነገር የለም በዚህ የተነሳ ነው።

ሱፐርቫይዘር፦ አዎ ፡ ግን መስተካከል ይኖርበታል። ጥቁር ሠሌዳው ጥቅም ላይ መዋል ይገባዋል።

ዕጩ መምህር፦ እሺ

ሱፐርቫይዘር፦ ሌላው በቡድን እየተዘዋወርሽ አበረታተሻል። ተማሪዎች በንቃት ተሣትፈዋል። ይህ ሁሉ ጥሩ ነው።

ሱፐርቫይዘር፦ ርዕሥሽን ሥነ ጽሁፍ ብለሽ ቀጥታ ወደ ሥነ ቃል ነው የገባሽው።

ዕጩ መምህር፦ እንዲህ ነው ያልኩት፣ ሥነ ቃል በሁለት ይከፈላሉ።

ሱፐርቫይዘር፡- አይ አይደለም ርዕሱን ሥነ ጽሁፍ ነው ያልሽው የዕለቱን ርዕስ

ዕጩመምህር፡- ሥነ ጽሁፍ አልኩና በሥነጽሁፍ ዉስጥ ሁለት ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም ሥነ ግጥም እና ሥነ ቃል። በዛሬው ትምህርት የምናየው ሥነ ቃል ነው ነበር ያልኩት።

ሱፐርቫይዘር፡- አይ አይደለም፤ በሥነ ጽሁፍ ውስጥ ያሉት ብዙ ነገሮች ናቸው፡፡

ዕጩ መምህር፡- ብዙ ነገሮች አሉ።

ሱፐርቫይዘር፡- ልቦለድ አለ። ረጅም ልቦለድ አጭር ልቦለድ ወዘተ በሥነ ጽሁፍና በሥነ ቃል መካከል ያለውን ልዩነት ካሣየሽ በኋላ ወደ ሌላው ብትሄጂ ጥሩ ነበር፡፡

ዕጩ መምህር፡- እሺ

ሱፐርቫይዘር፡- ሌላው ሚዲያ (የትምህርት መረጃ መሣሪያ) መጠቀምሽ ጥሩ ነው፡፡ ሚዲያው ግን መሆን ያለበት የሥነ ቃል ትርጉምን የሚያሳዩ ወይም የሥነ ቃል ዘርፎችን የሚያሣዩ ቻርት ብቻ መሆን አልነበረበትም። ከዚያ በላይ መሆን ነበረበት ሥነ ቃሉ ራሱ ክፍል ውስጥ የሚመጣበት ሁኔታ መፈጠር ነበረበት ከሬዲዮ ተቀርጾ ሊመጣ ይቻላል ለምሣሌ ዘፈን አለ ተረት አለ...

ዕጩ መምህር፡- አዎ ዘፈን አለ ምሣሌዊ አነጋገር አለ። ለምሣሌ ከመጠምጠም መማር ይቅደም የሚለው በቃሌ አቅርቤላቸዋለሁ።

ሱፐርቫይዘር፡- አዎ ብለሽላቸዋል። ግን ከዚያም በላይ መሄድ ነበረበት፡፡

ዕጩ መምህር፡- እሺ

ሱፐርቫይዘር፡- ሌላው ያየሁት ችግር የቡድን ሥራ ሁሉም እንዲያቀርቡ ነው ያደረግሽው የቀረበው ነገር ደግሞ አንድ ዓይነት ነገር ነው። ይህ አይነቱ አካሄድ ጊዜ ፈጅ በመሆኑ ከዚህ ይልቅ አንድ ወይም ሁለት ቡድን ካቀረበ በኋላ እስቲ ደግሞ ሌሎች ለየት ያለ ነገር ያላችሁ ብትያቸው የቀረውን ጊዜ ለውይይት ብታውይው የተሻለ ነበር። ካልሆነ ግን ተማሪዎችን የሚያሠለችና ጊዜም ያላግባብ መፍጀት ይሆናል፡፡

ዕጩ መምህር፡- አንድ ወይም ሁለት ብቻ ሲያቀርብ እስከ ዛሬ ብዙ ተማሪዎች ምንድ ነው እዚያ ጋር የሚሠራው? ለምን እኛስ አናቀርብም ስለሚሉ ነው፡፡

ሱፐርቫይዘር፡- አይ ዛሬ ያላቀረበው ቡድን በሌላ ጊዜ ደግሞ ተራው ደርሶት እንዲያቀርብ ማድረግ ትችያለሽ ።

ዕጩ መምህር፡- እንዲዚያ ማድረግ ይቻላል

ሱፐርቫይዘር፡- እሺ እንግዲህ እ...እ..

ዕጩ መምህር፡- እሺ አመሠግናለሁ በጣም

ሱፐርቫይዘር፡- እኔም አመሠግናለሁ።

## ሱፐርቫይዘር 7

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር፦ መጀመሪያ ከጠንካራ ጎኑ ልጀምርና ትምህርቱ ከባለፈው መጀመሩ ቆንጆ ነገር ነው። ወደፊትም መበረታታት ያለበት ነው። ተማሪዎችን በቡድን ውይይት ጊዜ ለማገዝ ያደረግሽው ጥረትም ጥሩ ነው። የመማር ማስተማር ዕቅዱ በከፊልም ቢሆን የዕለቱን ትምህርት በሚያመላክት መልኩ መዘጋጀቱም ጥሩ ነገር ነው። ትምህርቱን ተማሪ ተኮር አድርገሽ ማቅረብሽም ጥሩ ነው። አሥረጅ ምሳሌዎችን ብላክቦርድ ላይ መጻፍሽም ጥሩ ነው። ተማሪዎችን በሥማቸው እየጠራሽ ማሣተፍሽ፣ ሴት ተማሪዎችን ማበረታታትሽም መቀጠል ያለበት ጥሩ ነገር ነው።

ሥለ ዕለቱ ትምህርት ያደረግሽው ዝግጅትም ለደረጃው በቂ ነው ብዬ አስባለሁ ቆንጆ ነው። ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱት ለማረጋገጥ ያደረግሽው ጥረትም እንዲሁ ሊበረታታ የሚገባው ነው ። ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ዕድል መስጠትሽና በስተመጨረሻም የቤት ሥራ መስጠትሽ ቆንጆ ነው ይበረታታል። እነዚህ ጠንካራ ጎኖች ብዬ የያዝኳቸው ናቸው።

ሌሎች ወደፊት ሊሻሻሉ ይገባሉ ብዬ የያዝኳቸው ደግሞ ሚከተሉት ናቸው፡- ዑማም ትልቅ ችግር ሆኖ የታየው ቅድም በmentor እንደተነገረሽ የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀም ላይ ነው። መጀመሪያ ጥቁር ሰሌዳውን በደንብ አላጠፋሽውም። በኋላ ላይ ደግሞ አንዴ በጻፍሽው ላይ መስመር የለም። በጻፍሽው ላይ ደርበሽ ትጽፊያለሽ የእጅ ጽሁፍሽም ሰሌዳ ላይ የሚታየው መሻሻል የሚገባው ነው ወደ ኋላ ላይ ይህን በተመለከተ Coment የማደረገው ይኖረኛል።

ሌላ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሰሌዳ ላይ ቢጻፍ ጥያቄ ጠይቀሻቸዋል አይደል እንዴ ለውይይት የሚሆን ነገር?እነዚያን በቃል ነው የገለጽሽላቸው። እንዲህ ሲሆን ተማሪዎቹ ምን ያህሉን ጥያቄ ሊይዙና ወደ ውይይት ይገባሉ ብለሽ ታስቢያለሽ? ከዚህ አንጻር የመወያያ ጥያቄዎችንም ሠሌዳ ላይ ብትጽፊላቸው የተሻለ ነበር።

ሌላው ክፍሉ ሲካሄድ ተማሪዎች ቢሳተፉበት መልካም ነበር። ይበልጥ ተማሪ ተኮር ለማድረግ ተማሪዎች ቢሳተፉበት ይመረጣል። የመወያያ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ከመቅረባቸውም በፊትም ተማሪዎቹ መንደርደሪያ ሀሳቦች ቢሰጧቸው። መግቢያ ቢኖረው ማለትም Theme የሚባል ዋና ነገር አለና ቢሰጣቸው በዚያ ተመርተው የመወያየት ጥያቄዎችን ይሞክሩልሽ ነበር።

የመማር ማስተማር ዓላማ ውጤት፣ ድርጊት ከዚህ በተጨማሪ መስፈርትና ሁኔታ የሚባሉ ሦስት Components አሉት። አንቺ ግን እዚህ ያቀረብሽው ውጤትና ድርጊትን ብቻ ነው። ስለዚህ መሥፈርትና ሁኔታ የሚሉት ቢታከሉ እንዲሁም የማስተማር መማሩ ዓላማ ለተማሪዎች ቢገለጹላቸው ዓላማዎች ተማሪዎች ወዴት እንደሚሄዱ የሚያመላክቷቸው አቅጣጫዎች ናቸውና ይህን ማድረግ ነበረብሽ። ሌላ ለቡድን ውይይት የሚያስፈልገው ጊዜ ለተማሪዎች ቢገለጹላቸው ጨርሰናል፣ አልጨረስንም፣ ጨርሳችኋል፣ አልጨረሳችሁም... ከምትባባሉ ይህን ያህል ጊዜ አላችሁ ብለሽ ወስነሽ ብትሠጫቸው።

ሰልጣኝ መምህር፦ ለተቻለሁ

ሱፐርቫይዘር፦ ድምጽሽ ለሁሉ ተሠሚ አይደለም። በተለይ ወደ ኋላ አካባቢ የተቀመጡ ተማሪዎች ለማዳመጥ ይቸገራሉ። እኔ ራሴ ለመስማት እቸገር ነበር። ሌላው አንዳንድ ቃላትን ስትጽፊ ፊደላትን ትክክለኛ ቅርፃቸውን የጠበቁ ቢሆኑ፣ ፊደላትንም ባትበዪ፣ ለምሳሌ ማስረጃ ልጠቅሥልሽ እችላለሁ። ውሀ እና ህይወት ግንኙነት አላቸው ብለሽ ተናገርሽና ሥትጽፊ ውሀ ህይወት ግንኙነት አላቸው አልሽ "እና" የሚለው ተረሣ። ግንኙነት የሚለውን ቃል ስትጽፊም "ኙ" "ኘ" ሆና ነው የቀረበችው ፡ ቅጥል አልነበራትም። እንደ አማርኛ ቋንቋ መምህርነትሽ ትኩረት ማድረግ ነበረብሽ ውሀ ባለበት ሁሉ... ብለሽ ስትጽፊ "ባለበት" የሚለውን "ባላባት" ብለሽ ነው የጻፍሽው።

ሌላው ሠሌዳ ላይ የሚጻፉ ጠቃሚ ነገሮችን ተማሪዎች አደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ብታደርጊ ምሳሌዎች ናቸው ከተማሪዎች ቢመጡም አንቺ አስተካክለሽባቸው እንዲገለብጧቸው ብታደርጊ፣

ትምህርቱን ደግሞ ተጨባጭ ለማድረግ ብትሞክሪ አበበ፣ አስቴር ረጃጅም ናቸው ከምትይ ይልቅ ክፍል ውስጥ ረጅምም አጭርም ተማሪዎች ይኖራሉና እነሱን አስወጥተሽ እያሣየሽ ትምህርቱን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ማቅረብ ትችይ ነበር።

መደበኛ ቃላትን ለመጠቀም ብትሞክሪ ጥሩ ነው። እዚህ ላይ እርግጠኛ አይደለሁም ሁለቱቹም እና ሁለቱም ከሚሉት ትክክለኛ የሆነው የቱ ነው?

ሰልጣኝ መምህር፦ ሁለቱም

ሱፐርቫይዘር፦ ሥትጽፊ ግን ሁለቱቹም ነበር ያልሽው።

ሌላው ተማሪዎች የሚሠጡት መልስ ትክክል መሆን አለመሆኑ ቢገለፀላቸው ለምሳሌ እኔ ለራሴ ያልገባኝ ነገር ነበር። አበበ ጉብዝ ነው አልማዝ ጉብዝ ነች ። ስለዚህ ሁለቱም ጎበዝ ናቸው ብሎ የመለሰ ተማሪ ነበር።

ዕጩ መምህር፦ በጉብዝና ዕኩል ናቸው ነው ያለው፡፡

ሱፐርቫይዘር፦ አይ በጉብዝና አላለም። ዕኩል ናቸው ነው ያለው፡፡ ትክክል ነውም ስህተት ነውም አልተባለም። ዝም ብሎ ብቻ ጥሩ ነው ተብሎ ታልፏል፡፡ ማበረታታቱ ቆንጆ ነው፣ ግን ትክክል መሆን አለመሆኑ ካልተገለፀለት ነገ ፈተና ላይ በሚሠጠው መልስ ችግር ሊከሠት ይችላልና ለይተሽ ትክክል መሆን አለመሆኑን ብትነግሪው ጥሩ ነበር።

ሌላው ደግሞ ትምህርቱ በመርጃ መሣሪያ ተደግፎ ቢቀርብ መርጃ መሣሪያ አላየሁም።

ዕጩ መምህር፦ በመርጃ መሣሪያ አማርኛ እ... እ...

ነባር መምህር፦ ( ጣልቃ በመግባት)፦ ይህ ርዕስ መረጃ መሣሪያ ብዙም አይጋብዝም፡፡ የዚህ ርዕስ ዋናው ትኩረት መደምደሚያ ሀሳቦችን መሥጠት የሚል ነውና መረጃ መሣሪያ ብዙም አያስፈልገውም። ወደፊት አሁን Next week ማወዳደርና ማነፃፀር የሚል ርዕስ አለ። ያን ጊዜ አጭርና ረጅም ተማሪዎችን አቅርባ ማደማደሚያ እንዲሠጡ ልታደርግ ትችላለች።

ሱፐርቫይዘር፦ ግን የሙያ ሠዎች የሚሉት ነገር አለ። የ "ps" ሠዎች ማለት ነው፡፡ ያለ መረጃ መሣሪያ የሚሠጥ ትምህርት የለም። ለምሣሌ አሁን አንቺ ምንድነው ያልሻቸው ማሠሪያ አንቀጽ ነው? ምንድነው ያልሻቸው? እነዚያ ነው ናቸው... የማሠሪያ አንቀጽ ማደማደሚያዎች ያልሻቸውን በወረቀት ላይ ቻርት ሠርተሽ ብታቀርቢያቸው እነዚያ ምን መሆን ይቻላሉ? ..... መርጃ መሣሪያ መሆን ይቻላሉ፡፡ እኔ እንደዚያ ነው የማምንውና የማስበው። የቋንቋው ሠው ደግሞ በተሻለ መንገድ ሊገልፀው ይችላል። እኔ ከአንቺ የተሻለ ነገ ኖሮኝ አይደለም፡፡

አጥኚ ( ) ፦ እሺ.....

ሱፐርቫይዘር፦ መማር ማስተማሩ በዕቅዱ መሠረት ቢከናወን ለምሳሌ ወጥተው ያቀርባሉ ብለሻል በሌሰን ኘላንሽ ላይ ግን ወጥተው አላቀረቡም፡፡

ዕጩ መምህር፦ ተነስተው ያቀርባሉ

ሱፐርቫይዘር፦ እሱ እንደሱ ነበሩ መባል ያለበት። እዚያች ሌሰን ኘላን ላይ በሰፈረው መሠረት መፈፀም ይኖርበታል። በእርግጥ ይህ ይህንን ያህል የጐላ ስህተት ተደርጐ ባይወሠድም። ግልጽ ማጤቃለያ ቢሠጣቸው፡፡ በእርግጥ ደወሉ ያደናገረሽ ይመስለኛል። ... እነዚህን ብታሥተካክይ ለወደፊቱ ጥሩ መመህር እንደምትሆኚ ተስፋ አደርጋለሁ።

ዕጩ መምህር፦ እሺ አመሠግናለሁ።

## ሱፐርቫይዘር 8

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር፦ እሺ መቅደስ በ7ኛ ለ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ግጥምን በተመለከተ ሥርዓተ ትምህርቱን ያከተተችሽ። በምልከታ ሂደት ውስጥ የተመለከትኳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች አቀርብልሻለሁ።

ስለዚህ መጀመሪያ ከዓላማው ነው የምጀምረው። ዓላማዎችሽ በግልጽ ዝርዝር በሆነ መልኩ ተቀምጠዋል። ከየት ተነሥተሽ የት መድረስ እንዳለብሽ የሚያመለክቱ ናቸው ብዬ አስባለሁ።

ተግባራቱ ጋር ስመጣ በጊዜ ተከፋፍለው ተቀምጠዋል። ነገር ግን የሚታየው ጉደሉ ምንድነው? የአንቺ ተግባር ብቻ ነው የሚያመላክተው ተማሪዎች እንዲህ ያደርጋሉ፣ እንዲህ ይሰራሉ... የሚል የተማሪውን ተግባር አመላካች ነገር አላሠፈርሽም። ይህ ደግሞ ሌሰን ፕላኑን ብቻ ለሚያየው ሰው መምህር ተኮር ትምህርት የምታሥተምሪ ነው የሚያስመስለው። ትምህርቱ ደግሞ መሆን ያለበት ተማሪ ተኮር ነው። ስለዚህ ሌሰንፕላኑ ላይ መስፈር ያለበት በትምህርቱ የምትከናወነውን ተግባር ነው መሆን ያለበት በዚያ መንገድ እንዲስተካከል ያስፈልጋል።

ያለፈውን ትምህርት ተማሪዎች እንዲከልሱ ማድረግሽ በጣም ጥሩ ነው። አንቺም ከምትከልሺው ይልቅ እነሱ ምን እንደተማሩ አስታወሰው እንዲከልሱ ማድረግሽ በጣም ቆንጆ ነው። የብላክቦርድ አጠቃቀምሽም ጥሩ ነው።

ተማሪዎችሽን የማሳተፍ ሁኔታ በጣም ጥሩ ነው፤ እንዲያውም ሞቅ ያለነው ብዬ ነው የያዝኩት።ተማሪዎች በቡድን እንዲያነቡ ማድረጉ በምን እንደሆነ አላውቅም መማሪያ መጻሕፍት አጥረዋል። ተማሪዎች በነፍስ ወከፍ መጽሐፍ ይዘው አላየሁም። ለቋንቋ መምህር ደግሞ ዋናው መማሪያ መማሪያ መጽሐፉ ነው። አለበለዚያ ቋንቋን ማስተማር ያስቸግራል እና ያ ባለመሆኑ ወይም በሌላ ምክንያት ሊሆን ይችላል በቡድን እንዲያነቡ አድርገሻል። ዓላማው ደግሞ ያነበቡ ሥርዓቱን እንዲለምዱ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ጮክ ብለው እንዲያነቡ ወይም በየግል እንዲያነቡ ነው ማድረግ ያለብሽ በቡድን ማስነበቡ ፋይዳ የለውም።

እየተዘዋወርሽ ለማበረታታት ያደረግሽው ነገር ጥሩ ነው። ግጥሙን አንቺ ከምታነቢው እነሱ ቢያነቡ ነው የሚመረጠው። አንቺ ናሙና ካሳየሻቸው በኋላ እነሱ እንዲያነቡት ይጠበቃል። አንቺ ብቻ የምታነቢው ከሆነ ግን እንደ ቲዎሪ

ነው የሚመስሉት። ስለዚህ ወደፊት ይህችን እንድታስተካክይ ነው… በቀየሁባቸው ያገኘሻቸውም እነዚህን ነው የራስሽን አስተያየት ደግሞ ራስሽ መስጠት ትችያለሽ።

ዕጩ መምህር፡- ግጥሙ ላይ ያልኩው የጊዜ ማጠር ነው እንጂ ሳስነብባቸው ነበር

ሱፐርቫይዘር፡- የጊዜውን ማጠር ራስሽ አስተካክለሽ ጥቃቅን ነገሮችን በማስገድ ወደ ዋናው ነገር አትኩረሽ መቅረብ የሚገባውን ነገር በወቅቱ ማቅረብ ነበረብሽ ካለሽ ሥራ ጋር።

ዕጩ መምህር፡- ሌላው ደግሞ አንተ እንዳልከው ግጥም አልነበረም በግሩፕ የሰጠኋቸው መነሻ ሀሳብ ነው በቡድን እንዲያነቡ ያደረኩት። ስድንባብ ነው ለመነሻ ያህል ያቀረብኩት።

ሱፐርቫይዘር፡- በቡድን ማስነበቡ ምን ፋይዳ አለው። እንዲወያዩበት ብታደርጊ ኖሮ ይሻል ነበር። ምክንያቱም ምንድነው መጽሐፉ አነስተኛ ነው ብየሻለሁ በቡድን ሲያነቡ የሚያነቡትንና የማያነቡትን መለየት አትችይም። ለምን ቢባል አያነቡትም ስለዚህ ይህንን በዚህ መንገድ አስተካክይው።

ዕጩ መምህር፡- እሺ አስተካክላለሁ።

## ሱፐርቫይዘር 9

## ውይይት 1

ሱፐርቫይዘር፡ እሺ ክፍለ መምህርነትን እንዴት አገኘሽው?

ዕጩ መምህር፡- ጥሩ ነው

ሱፐርቫይዘር ፡- ከሌሰንፕላንሽ እንጀምርና አላማው ላይ ይረዳሉ ያልሽው ከዝርዝር ዓለማ አጻጻፍ አንፃር ሊታይ ተገቢ አልነበረም አጠቃላይ ነው። SMART መሆን አለበት አተተባበኛቸው ተምረሻቸው የለም እንዴ?

ዕጩ መምህር፡-አዎ ግን አንብቦ መረዳት ሥለሆነ ዋነው ትምህርት ያንን ለማመልከት ብዬ ነው።

ሱፐርቫይዘር፡- ቢሆንም ከክፍሎች ውስጥ እየጠቀስሽ ይናገራሉ፣ ወይም ይጽፋሉ፣ ወይም ያዳምጣሉ፣ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣ ወዘተ ማለት ነበረብሽ። አለበለዚያ ይረዳሉ የሚለው ለመመዘን ያስቸግራል መረዳታቸው በምን ይገለጻል ነው ዋናው ጥያቄ።

ዕጩ መምህር፡- እሺ

ሱፐርቫይዘር፡- ተግባሮቹ ጥሩ ናቸው በዝርዝር አቅርበሻቸዋል ነገር ግን ችግር ያለው ለተግባሮቹ የመደብሽው ሰዓት ነው። ሌሰንፕላን ላይ ለደንቡ ያህል አስቀምጠሽዋል እንጂ አልተጠቀምሽበትም። ለምሳሌ ለንባብ 10 ደቂቃ ለቡድን ሥራ 10 ደቂቃ

ለመያያት 10 ደቂቃ ለማጠቃለያ 10 ደቂቃ ብለሻል። በመሀል ላይ ያሉ ሌሎች አምራሳዊ ተግባሮች ለምሳሌ መግቢያ ክለሳ የመሳሰሉት ጊዜ አልተመደበላቸውም ግን 10 ደቂቃ ያህል ፈጅተሽባቸዋል ስታስተምሪ በዚህ ላይ ሌሰን ለሰገኘላገሽ ላይ አምር አስር ደቂቃ የመደብሽላቸው አንዱ 15 ሌላው 20 ሌላው 5 ደቂቃ ሲፈጅ ነው ያምተዋልኩት አስቀድመሽ በደንብ አስብሽ እንደ የተግባሮቹ ጥልቀትና ሥፋት ገምተሽ መመደብ ነበረብሽ ሌላው ተማሪዎች የቡድን ሥራዎች ተራ በተራ እንዲያነቡ ማድረግሽ ጥሩ ነው። ተግባራቸውን በተመለከተ ግን ደጋግመሽ የምትጠሪያቸው የተወሰኑ ልጆች ብቻ ነበሩ። ሌሎቹም እንዲሳተፉ ማበረታታት ነበረብሽ ይህንን ብታስተካክይ ጥሩ ይመስለኛል ምክንያቱም የተወሰኑ ተማሪዎችን ንቃ ማሳተፍ ሌሎቹ እንዲደክሙና የተረሱም ሊመስላቸው ይችላል።

ሌላው በጣም ማሻሻል ያለብሽ የጥቁር ሰሌዳ አጠቃቀምሽን ነው ። እዚህም እዚያም ትፅፊ ነበር። የእጅ ጽሁፍሽ ለእኔም አስቸግሮ ነበር ተማሪዎችም ሲቸገሩ ተመልክቻለሁ።

ሰልጣኝ መምህር፡- በጥቁር ሰሌዳ ላይ የመጻፍ ልምድ ሥለሌለኝ እንጂ በወረቀት ላይ እንኳ ጥሩም ባይሆን ጽሁፌ ለንባብ አያስቸግርም።

ሱፐርቫይዘር፡- አዎ የመምህር ዋናው የድህሪት መሳሪያ ጥቁር ሰሌዳ ነውና እየተለማመድሽ አሻሽይ። ጥቁር ሰሌዳው ሲቦዝን አንዳንድ የወዳደቁ ጠመኔዎችን እየተጠቀምሽ ወይም ከመምህራን በመጠየቅ ተለማመጅ በሌሎች ወረቀት ላይ መጻፋም ጥሩ ነው ያስለምዳል።

ሰልጣኝ መምህር፡- እሺ

ሱፐርቫይዘር፡- ሌላው መልመጃዎች ስታሰሪ አንዳንድ ጊዜ የተማሟተ መልስ ሲሠጡ ዕርማት ወይም ማስተካከያ መስጠት ነበረብሽ ለምሳሌ አንቀጽ ማለት አራት ነጥብ የሚደረግበት ነው ብላ መልሳለች አንቺም አዎ ትክክል ብለሻል ግን የአራት ነጥብ መኖር አንቀጽ ሊያሳይ ሥለማይችል ቢታብራሪላቸው መልካም ነበር ። አረፍተ ነገር ላይ ሁሉ አራት ነጥብ ይገባ የለም እንዴ ?

ሰልጣኝ መምህር፡- አይ ባትማቸው የሚያውቁትን መምከራቸው ጥሩ ነው ትክክል ያልኩት።

ሱፐርቫይዘር፡-ነገሮን በትኩሙ ይባል የለ ትክክል መሥኋቸው ሳይለምዱት ቶሎ ማረም አለብሽ በተረፈ ተማሪዎች ሲመልሱ ማበረታታትሽ ጥሩ ነው ችግሩ ቅድም እንዳልኩሽ ሁሉንም አለማሳተፍሽ ነው እነዚህን ለማሻሻል ምክሬ በተረፈ ጥሩ ነው። ከዚህ በተረፈ ጥሩ ነው ፍርሀት አላየሁብሽም ዘና ብለሻል ጎርቺ።

ሰልጣኝ መምህር፡- እሺ ጋሼ አመሰግናለሁ ።
ሱፐር ቫይዘር፡- ምንም አይደል።

# አባሪ አራት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
## በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ፕራክቲከም መርሀ ግብር ቋንቋን ለማሥተማር ልምምድ ሱፐርቫይዘሮች የተዘጋጀ መጠይቅ

ውድ መምህራን፦

የዚህ መጠይቅ አቢይ አላማ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ 10+3 መርሀ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድጋፊ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮችን ምግበ መረጃ ለመተንተን የሚያስችሉ መረጃዎችን መሠብሰብ ነው።

ጥናቱ ግብ መቶ የሚሆነው ትክክለኛና አሥተማማኝ መረጃዎች ሲገኙ ነው። ሥለሆነም በመጠይቁ የሰፈሩ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ መልሶ ነው ብላችሁ የምታምኑበትን በመግለፅ እንድትተባበሩኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

የሥራ ጊዜያችሁን መሥዋዕት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ ልባዊ ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ።

- በመጠይቁ ላይ ሥምዎን መጻፍ አይኖርብዎትም።

I. አጠቃላይ መረጃ
   - 1.1 ዕድሜ
   - 1.2 ጾታ
   - 1.3 የትምህርት ደረጃ
   - 1.4 አሁን በዘርፉ ትምህርቱ የሚያስተምሩት ኮርስ
   - 1.5 በማሥተማር ሥራ ላይ ለምን ያህል ጊዜ ቆዩ
     - 1.5.1 በኮሌጅ መምህርነት
     - 1.5.2 ከኮሌጅ ለላ

II. የማስተማር ልምምድን እና ሱፐርቪዥንን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች መመለሻ፤

ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልሶ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች አሉ፤ እነርሱም 5=በጣም እስማማለሁ፤ 4=እስማማለሁ፤ 3= ለውሳኔ እቸገራለሁ 2=አልስማማም፤ 1=በፍፁም አልስማማም የሚሉ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ መልሶ ነው ብላችሁ ያመናችሁበትን በመምረጥ በሰንጠረዡ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ /X/ ምልክት በማድረግ ጠቁሙ።

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ሥለ ሱፐርቪዥን አሠጣጥ ሥልጠና ወስጃለሁ | | | | | |
| 2 | በድኅረ ምልከታ የሚካሄድ ምገባ መረጃ መስተጋብር ዕጩ መምህራኑ መመሪያዎችንና ምክሮችን የሚቀበሉበት ሊሆን ይገባል፡፡ | | | | | |
| 3 | የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማሥተማር ልምምድ ለመምህርነት ሙያ አሥፈላጊ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ | | | | | |
| 4 | በድኅረ ምልከታ በሚደረገው የምገባ መረጃ መሥተጋብር ዕጩ መምህራኑ አሥተያየቱን ለመረዳት አይቸገሩም፡፡ | | | | | |
| 5 | ዕጩ መምህራኑ ለትምህርት ቤት ተሞክሮ እና ማሥተማር ልምምድ የተመደቡባቸው አጋር ትምህርት ቤቶች ከኮሌጁ የራቁና የተበታተኑ በመሆናቸው የሱፐርቪዥን አገልግሎት ከመስጠት አንፃር ምቹ አይደሉም፡፡ | | | | | |
| 6 | በአጋር ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮ እና ማሥተማር ልምምድ መርሀ ግብርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች አሉ፡፡ | | | | | |
| 7 | የመምህራን ሥልጠናው ሥርዓተ ትምህርት ዕጩ መምህራኑ ማስተማርን ሊማሩ በሚችሉበት መንገድ የተቀረፀ ነው፡፡ | | | | | |
| 8 | የኮሌጁ የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ አፈፃፀም መመሪያ ግልፅና ተተግባሪ ነው፡፡ | | | | | |
| 9 | ዕጩ መምህራንን ለመከታተል የሚያስችል ዘዴና ብቃት ለማግኘት የሱፐርቪዥን ሥልጠና መሰጠት ይኖርበታል፡፡ | | | | | |
| 10 | ዕጩ መምህራኑ አማራጭ የማስተማር ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ አበረታታቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 11 | የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማሥተማር ልምምድ መርሀ ግብርን መሠረት በማድረግ ለሱፐርቪዥን ከመሄዴ በፊት ከዕጩ መምህራን ጋር እየተገናኘሁ በመወያየት ዕቅድ አወጣለሁ፡፡ | | | | | |
| 12 | ሥለ ዘመናዊ ቋንቋን የማሥተማር ሥነዘዴ ያለኝ ግንዛቤ ለሱፐርቪዥን ሥራዬ በቂ ነው፡፡ | | | | | |
| 13 | ለሱፐርቪዥን ዕጩ መምህራኑ ወደ ተመደቡበት በምሄድበት ጊዜ በቅድሚያ የምመጣበትን ሰዓትና ጉዳይ አሳውቃቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 14 | የማስተማር ልምምድን ለመከታተል በሱፐርቫይዘርነት ሥሠማራ ክፍለ ጊዜን በሙሉ እክፍል ውስጥ እቆያለሁ፡፡ | | | | | |
| 15 | በትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ ሂደት የዕጩ መምህራን ብቃት የቅድሚያ ትኩረት አግኝቶ ሊገመገምና ሊመዘን ይገባል፡፡ | | | | | |
| 16 | በድኅረ ምልከታ ውይይት ዕጩ መምህራኑ ራሳቸውን እንዲገመግሙ አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 17 | በድኅረ ምልከታ ውይይት ጊዜ ዕጩ መምህራኑ ዘና ብለው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 18 | በምገባ መረጃ ልውውጥ (መሥተጋብር) ለዕጩ መምህራኑ መመሪያና ትዕዛዝ በመስጠት በተግባር እንዲያውሉት አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 19 | የኮሌጅ መምህራንና የአጋር ትቤት መምህራን ሥለ ማስተማር ልምምዱና ሱፐርቪዥን አዘውትረው ፊት ለፊት እየተገናኙ ይወያያሉ፡፡ | | | | | |
| 20 | የማስተማር ልምምዱ በኮሌጁ በቂ ክትትልና ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | በእኔና በዕጩ መምህራኑ የሚካሄደው የምገበ መረጃ መስተጋብር በምልከታው በተደረሰባቸው ነገሮች ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው:: | | | | | |
| 22 | ከዕጩ መምህራኑ ጋር ሥንወያይ በግልፅ ቋንቋ እጠቀማለሁ:: | | | | | |
| 23 | በእኔና በዕጩ መምህራኑ መካከል የሚካሄደው ምግበ መረጃ አንዱ ሌላውን የማይሜን/ሚዛናዊነት ያለው/ ነው:: | | | | | |
| 24 | የክፍል ውስጥ ምልከታ ከመካሄዱ በፊት ከዕጩ መምህሩ(ሯ) ጋር ቅድመ ምልከታ ውይይት እናደርጋለን:: | | | | | |
| 25 | በድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ጊዜ የዕጩ መምህራኑን ስብእና ላለመንካት እጠነቀቃለሁ:: | | | | | |

III. **ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሶቻችሁን ባለው ክፍት ቦታ ላይ ፃፉ**

26. ሥለ ትምህርት ቤት ተሞክሮና የማሥተማር ልምምድ እንዲሁም ሥለ ሱፐርቪዥን አተገባበር የወሰዱት ሥልጠና፣ ወርክሾፕ፣ ሰማናር አለ? ከአለ የሥልጠናውን ይዘት ባጭሩ ያሥረዱ::

27. በድኅረ የማሥተማር ልምምድ ውይይት ጊዜ ከዕጩ መምህራን ጋር ሲወያዩ የእርስዎ ሚና ምን ነበር?

28. ከሌይ ካዘጋጀው ቅፅ በተጨማሪ የዕጩ መምህራንን የፍል ውስጥ የመማር ማሥተማር ክንውን መመዝገቢያ ሌላ አማራጭ አለዎት? ካለ ይግለፁት::

29. በአጠቃላይ ሥለ ትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እና ሥለ ሱፐር ቪዥን አተገባበር ያለዎትን አስተያየት ቢገልፁ::

# አባሪ አምስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የቋንቋ ትምህርት ክፍል መርሀ ግብር 2ኛ ዓመት ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

**ውድ ዕጩ መምህራን፣**

የዚህ መጠይቅ አቢይ ዓላማ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሀ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድኅረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮችን ምግበ መረጃ ተገቢነት ለመፈተሽ የሚያስችሉ መረጃዎችን መሠብሰብ ነው። ጥናቱ ግብ መቺ የማሆነው ትክክለኛና አሥተማማኝ መረጃዎች ሲገኙ ብቻ ነው። ሥለሆነም በመጠይቁ የሰፈሩ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ መልሥ ነው ብላችሁ የምታምኑበትን በመጠቆምና በመግለፅ እንድትተባበሩኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ጊዜያችሁን በመሠዋት ለምታደርጉልኝ ትብብር አስቀድሜ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

I. አጠቃላይ መረጃ

1.1 ጾታ

1.2 ዕድሜ

1.3 ወደኮሌጆ ከመግባትሽ (ህ) በፊት በመምህርነት አገልግለሻል (ሃል)?

ሀ. አዎ ለ. አላገለገልኩም

II. የማስተማር ልምምድንና ሱፐርቪዥንን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች መመሪያ፡-

ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልሥ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አምሥት አማራጮች አሉ፤ እነርሱም፡- 5=በጣም እስማማለሁ፣ 4=እስማማለሁ፣ 3=ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 2=አልሥማማም፣ 1=በፍፁም አልሥማማም የሚሉ ናቸው። ለየጥያቄው መልሥ ነው ብላችሁ ያመናችሁበትን በመምረጥ በሠንጠረዡ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ /X/ ምልክት በማድረግ ጠቁሙ።

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጭ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ሥለ ትምህርት ቤት ተሞክሮና ማሥተማር ልምምድ ዓላማ፣ ተግባር በቂ ግንዛቤ አለኝ። | | | | | |
| 2 | የትምህርት ቤት ተሞክሮና ማስተማር ልምምድ የመምህርነትን ሙያዊ ብቃት እንዳላድግ ከፍተኛ አሥተዋፅኦ አድርጓልኛል። | | | | | |
| 3 | በምግበ መረጃ መሥተጋበር ጊዜ የሱፐርቫይዘሩ አቀራረብ ዘና ብዬ ሀሳቤን እንድገልፅ ያደርገኛል። | | | | | |
| 4 | ሱፐርቫይዘሩ ለሱፐርቪዥኑ ተግባር በቂ ችሎታ አለው። | | | | | |
| 5 | በአጋር ት/ቤቱ ለሥልጠናው አሥፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችን ለማግኘት አልተቸገርኩም። | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ነባር መምህሩን በማስተምርበት ክፍል ሁል ጊዜ እየተገኙ ሙያዊ ክትትልና ዕገዛ ያደርጉልኛል:: | | | | | |
| 7 | ሥርዓተ ትምህርቱ ማሥተማርን እንድማር በምችልበት አግባብ የተቀረፀ ነው:: | | | | | |
| 8 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የምናደርገው ብቻችንን ሆነን ፀጥታ በሠፈነበት ክፍል ወይም ቦታ ነው:: | | | | | |
| 9 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር የደረኩት የምግበ መረጃ ልውውጥ በሥራዬ እንዳልተጋና ተሥፋ እንድቆርጥ የሚያደርግ ነው:: | | | | | |
| 10 | ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ያካሄድኩት የምግበ መረጃ ልውውጥ ሁሉ በምልከታ በተደረሰባቸው ተጨባጭ መረጃዎች ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው:: | | | | | |
| 11 | የማሥተማር ልምምድ ቀዳሚ ክፍል የሆነውን ምልከታ ሳካሂድ በምን በምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለብኝ በቂ ግንዛቤ አለኝ:: | | | | | |
| 12 | ሱፐርቫይዘሬ የማሥተማር ልምምድ ወደሚካሂድበት ትምህርት ቤት የሚመጣው እኔን ለመደገፍና ለማበረታታት ነው:: | | | | | |
| 13 | በማሥተማር ልምምድ ጊዜ ከሱፐርቫይዘሬ የሚሠጠኝ ሙያዊ ድጋፍ በማስተማሩ ተግባር ንቁ ተሳታፊ እንድሆን አድርጎኛል:: | | | | | |
| 14 | ሱፐርቫይዘሩ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ተግባር ለመመልከት ክፍለ ጊዜውን በሙሉ ይቆይ ነበር:: | | | | | |
| 15 | በምግበ መረጃ መስተጋብር/ውይይት/ ጊዜ ሱፐርቫይዘሩ ተናጋሪ እኔ አድማጭ ነበርን:: | | | | | |
| 16 | በውይይት ጊዜ ሱፐርቫይዘሬ የሚሰጠኝ ምግበ መረጃ ቋንቋን በማስተማር ሥነ ዘዴ ከተማርኩት ጋር የተጣጣመ ነው:: | | | | | |
| 17 | ሱፐርቫይዘሬ የክፍል ውስጥ ጉብኝት ከማድረጉ በፊት ተገናኝተን ሥለሱፐርቪዥኑ እንወያያለን:: | | | | | |
| 18 | በድኅረ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር በቂ የውይይት ጊዜ አልነበረኝም:: | | | | | |
| 19 | የሱፐር ቫይዘሬ ምግበ መረጃ በደካማ ጎኔ ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር:: | | | | | |
| 20 | ሱፐርቫይዘሬ የራሴን ሥራ ራሴ እንድገመግም ያደርጋል:: | | | | | |
| 21 | በድኅረ የማሥተማር ልምምድ ውይይት ጊዜ ሱፐርቫይዘሬ ምን ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ትዕዛዝና መመሪያ ይሰጠኛል:: | | | | | |
| 22 | በድኅረ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር የማደርገው ውይይት ቀጣይነትና ተከታታይነት ነበረው:: | | | | | |
| 23 | ከሱፐርቫይዘሬ የማገኘው ምግበ መረጃ የማስተማር ብቃትን እንዳሻሽል ያደርገልኝ ዕገዛ አናሳ ነው:: | | | | | |
| 24 | ሱፐርቫይዘሬ የማሥተማር ልምምድ ሳካሂድ በዕቅድና በፕሮግራም ይከታተለኝ ነበር:: | | | | | |
| 25 | በድኅረ የማስተማር ልምምድ ከሱፐርቫይዘሬ ጋር ባደረኩት ውይይት ላይ የሱፐርቫይዘሬ ግላዊ ዳኝነት የበለጠ ተሰሚነት ነበረው:: | | | | | |
| 26 | ሱፐርቫይዘሬ ለኔ ዝቅተኛ ግምት አለው:: | | | | | |
| 27 | ሱፐርቫይዘሬ አማራጭ የማስተማር ዘዴዎችን እንድጠቀም አበረታቶኛል:: | | | | | |
| 28 | ከሱፐርቫይዘሬ በተሰጠኝ ምግበ መረጃ ተደስቻለሁ:: | | | | | |
| 29 | ሱፐርቫይዘሬ የማስተማር ልምምድ ባካሄድኩበት የትምህርት ዓይነት የሰለጠነ ነው:: | | | | | |

III. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሶቻችሁን ከየጥያቄዎቹ ግርጌ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ጻፉ።

30. በድኅረ የማስተማር ልምምድ ውይይት ላይ የነበረውን የሱፐርቪዥንን አቀራረብ እና የምገባ መረጃ ልውውጥ በተመለከተ ሊጠናከር /ሊቀጥል/ የሚገባው ወይም መሻሻል /መለወጥ/ ያለበት ጉዳይ ካለ ግለፅ(ጭ)።

31. ሥለ ፐሬክቲከም እና ቋንቋን ሥለማስተማር መግለፅ የምትፈልገው (ገው) ሀሳብ ካለ ግለጭ (ፅ)።

32. የኢ.ጋ.ር ት/ቤት ነባር መምህሩን ሥላደረጉልህ(ሽ) ሙያዊ ዕገዛ ያለህን(ሽ) አስተያየት ግለፅ(ጭ)።

Debre Markos College of Teachers Education - Department of Professional Studies

# Evaluation Criteria for Practicum -Teaching Practice Observation

Evaluation: 50 %

School ____________________

Grade Level-Observed ____________________

Date Observed __________ Time __________

Practicum/Semester __________ Academic Year __________

Candidate Teacher ____________________

Sex ______ ID No ____________________

Department ____________________ Section ____________________

| | Evaluation Criteria and Performance Indicators | Obtained Score | | | | | Multiplied/ Weighted Score | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | | |
| 1 | **Lesson planning and classroom teaching**<br>*1.1. There is careful lesson planning: (6%)*<br>*Indicators:* Objectives are clear and achievable, the balance of teacher and students activity ensures students fully participate, appropriate use and quality of instructional resources, appropriate assessment techniques, and content based classroom activities are well stated in the lesson plan. | | | | | | | |
| | *1.2. There is frequent use of lesson plan:* (2%)<br>*Indicators:* prepares and always uses daily lesson plan, and there is a match between the content on the day's lesson plan, subject text content to be taught and the annual lesson plan. The daily lesson plan was prepared based on the annual lesson plan and subject content. | | | | | | | |



137

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | Formal observation of classroom teaching<br><br>*2.1. Classroom teaching is based on high intellectual quality and ensures that the candidate teacher has good subject knowledge and applies this effectively in the classroom. (4%)*<br>*Indicators:* Very good reflection, regular and appropriate use of a wide variety of learning experiences, teaching learning activities are explicit, systematic, varied, challenging and the content is engaging. | | | | | | | |
| | *2.2. The candidate teacher's talk is focused on learning-he/she share the purpose of lessons with students and explanations and instructions are explicit. (2%)*<br>*Indicators:* Teaching focuses on key concepts and ideas with in topics, subjects and on the relationship between and among these concepts. Monitoring is well established, teaching ensures lessons are effective and maximize learning. | | | | | | | |
| | *2.3. Learning and teaching activities are explicit, systematic, varied and challenging, and designed to move students on to the next level. (2%)*<br>*Indicators:* There is organized delivery of lesson, clear flow of ideas, and sequences of activities, clarity and good command of language, ability to use good examples, kindly reactions to students' responses. | | | | | | | |
| | *2.4. Candidate teacher demonstrates that he/she understands and uses effective methods such as active learning strategies to encourage students to actively participate in lessons and learn better. (4%)*<br>*Indicators:* Teaching is of high quality because of the very good strategies; he/she is positively committed to active learning methods and monitors students' participation lessons through regular observation and provision of activities. | | | | | | | |
| | *2.5. Candidate teacher encourage the skills and confidences of students needed for independent learning.(2%)*<br>*Indicators:* Show clear ability to help others and make involved, encourage others to speak and express their views and to reflect on and communicate about what they are learning. | | | | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **2.6. Classroom teaching link to real life situation. (2%)**<br>*Indicators:* Local and familiar examples are used there are practical experiences and provide opportunities for concrete application of learning experiences. | | | | | | | |
| | **2.7. Candidate teacher understands and accepts that students learn at different rates and vary teaching methods accordingly. (2%)**<br>*Indicators:* There is match in strategies to the need of individuals and groups. He/she uses variety of different teaching approaches, dependent on students need and compatibility, classroom context; subject being taught, and desired outcomes. | | | | | | | |
| | **2.8. Assessment techniques are used and the results are communicated. (3%)**<br>*Indicators:* Appropriate assessment techniques at different stages of instruction during and after were used. Assessment results were communicated to inform ongoing learning and there is appropriate feed back given to students | | | | | | | |
| 3 | Teacher is positive role model for their students and show respect for them so that students feel safe and confident. (3%)<br>*Indicators:* There is a good relationship and atmosphere of mutual respect. The school (classroom) is a conducive and engaging learning environment. | | | | | | | |
| 4 | There is a positive and productive relation ships between candidate teacher, teachers, and staff. (3%)<br>*Indicators:* There is collaboration with / school teachers to share experiences, willingness to accept others ideas, provides positive and constructive ideas with good interaction. The quality, openness, and congruence of relationships existing in the classroom are reflected. There are regular communication mechanisms. | | | | | | | |
| 5 | Candidate teacher commitment to improve teaching and on going professional development is evident. (2%)<br>*Indicators:* There is a need and well established system for improvement: Frequent use of library, frequent communication on academic issues with teachers, courage to update knowledge & skills, attendance on trainings and tutorials, articulate high achievement expectation to students. | | | | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | Candidate teacher know the individual students learn at different rates and meet their learning demands.(3%)<br>*Indicators:* The needs of different groups have been recognized and planned and have commitment to support. Identified groups such as students with special needs, girls, disabled, talented, slow learners, etc... have been provided positive support (guidance, make up/tutorial class, special education, follow up, etc.) | | | | | | | |
| 7 | Documentation and recording of students' academic performances, diaries, evidences, follow ups, etc.(3%)<br>*Indicators:* Data collected on school practices, students performances, self – evaluation, follow ups, attendances; clearly show that there is a very good and clear system of data collection. School regulation and information were documented. There is regular system of reporting of information about areas of strength and areas of requiring improvement in school/ classrooms. | | | | | | | |
| 8 | Candidate teachers involved in school clubs and community based programs which develop his/her understanding of wider issues. (2%)<br>*Indicators:* Participate him/her self and encourage students to take part in co-curricular activities, school clubs, and school - parent meetings, etc by taking leadership in co-curricular activities. | | | | | | | |
| 9 | There is a commitment to equality of opportunities (2%)<br>*Indicator:* Respect student's rights and provide proper support with no disparity on the basis of any special needs, gender, ethnic background, or family-economic status, etc. | | | | | | | |
| 10 | Appropriate standard of behavior, personality and professional ethics are evident in a variety of contexts. (3%)<br>*Indicators:* Candidate teacher's responsibility, self-esteem, and independence in school are supported and valued, loyal and fully obeyed to rules and regulations of the school, punctuality for school days and with work maintained, interest and satisfaction towards the profession. | | | | | | | |
| | Scales: 1(Poor) 2(Fair) 3(Good) 4( Very good) 5(Excellent) Total: | | | | | | | |
| ☛ **This evaluation score should be converted in to a score you need (50%) after it has first been corrected and multiplied out of 250.** | | | | | | | | |

School Teachers: Evaluation :________( out of 250) ________ (Out of 50%)
Name: ________________________________
Signature______________________________

College Instructors: Evaluation :______( Out of 250) ________ (Out of 50%)
Name: ________________________________
Signature______________________________

Average Score: _______ (out of 250) ________ (Out of 50%)

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና የተጠቀምኩባቸውን ምንጮችም በሙሉ የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም: በላይሁን አውላቸው

ፊርማ: ______


አድራሻ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
አዲስ አበባ


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የማስረከቢያ ጊዜ ሰኔ 1999